አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የነውር እሳቤ በሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ እምነት

በ

ሞላ ጀምበሬ

ሰኔ 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የነውር እሳቤ በሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ እምነት

ለፎክሎር የፒ. ኤች. ዲ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ሞላ ጀምበሬ

አማካሪ

ዘሪሁን አስፋው

ሰኔ 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

“የነውር እሳቤ በሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ እምነት” በሚል ርዕስ ለፎክሎር የፒ. ኤች. ዲ. ዲግሪ ማሟያ በሞላ ጀምበሬ አለምነህ በሰኔ ወር 2009 ዓ.ም የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል።

## የፈታኝ ቦርድ አባላት


አማካሪ ፡- **<u>አቶ ዘሪሁን አስፋው</u>** ፊርማ ........................................

የውጪ ፈታኝ ፡- **<u>ፕሮፌሰር ሺፈራው በቀለ</u>** ፊርማ .......................................

የውስጥ ፈታኝ ፡- **<u>ፕሮፌሰር ሀብታሙ ወንድሙ</u>** ፊርማ .......................................

# ካርታዎች


## ሀ. የአማራ ክልል ካርታ በዞን




ደቡብ ጎንደር ዞንን የሚያሳይ ቀስት

ምንጭ ፦ የአማራ ክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ቢሮ


ለ. የደቡብ ጎንደር ዞን ካርታ በወረዳ




ምንጭ ፦ የደቡብ ጎንደር ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ መምሪያ

ሊቦ ከምከም ወረዳን የሚያሳይ ቀስት

## ሐ. የሊቦ ከምከም ወረዳ ካርት በቀበሌ




ተጠኚ ቀበሌዎችን (አግድ ቅርኛ፣ ሚካኤል ደብር፣ ይፋግ፣ አዲስ ዘመን፣ ብራ አቦ እና ብርኩቴ) የሚያሳይ ቀስት

ምንጭ ፦ የደቡብ ጎንደር ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ መምሪያ

# ምስጋና

ይህ ጥናት ከዳር እንዲደርስ ጊዜያቸውን መስዋዕት አድርገው ያለምንም መሰልቸት በተደጋጋሚ በማረም ገንቢ አስተያየታቸውንና ምክራቸውን ላካፈሉኝ አስተማሪዬና አማካሪዬ ዘሪሁን አስፋው ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

በአካባቢያቸው ስገኝ በፍቅር እየተቀበሉ የምፈልገውን መረጃ ሁሉ ካለስስት የሰጡኝ በአባሪነት ስማቸውን ያያያዝኩት መረጃ ሰጪዎቼና ሌሎችም የሊቦ ከምከም ወረዳ ነዋሪዎች በሙሉ ባሰብኳቸው ቁጥር ቸርነታቸው ወሰን ያልፍብኛልና ምስጋናዬን ይውሰዱ።

ባለቤቴ ወ/ሮ ሙሉቀን ገበየሁ ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ በገጠሙኝ መሰናክሎች ሁሉ እንዳልወድቅ ከጎኔ ሳትለይ ላደረግሽልኝ ድጋፍና ላሳየሽኝ ትዕግስት ከልቤ አመሰግንሻለሁ፡፡ ልጃችን በረከት ለአንተ መስጠት የነበረብኝን ጊዜ ባለመስጠት የህፃንነት ዘመንህን ስለተሻማኩት ከልቤ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡ ወንድሜ ተመስገን የአንተን ውለታም አልዘነጋሁትም፡፡

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ዕድሉን ስለሰጠኝና የገንዘብ ድጋፍም ስላደረገልኝ፤ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን እከታተል ዘንድ ስለፈቀደልኝና ጥናቱን ለማድረግም መጠነኛ የገንዘብ ድጋፍ ስላደረገልኝ ሁለቱንም በጣም ላመሰግናቸው እወዳለሁ፡፡

ትኩረቴን በመሰብሰብና አካሄዴን በማረቅ ጥናቴን መስመር ላስያዙልኝ የደረጃ ማበልጸጊያ ፈታኞቼ ለዶ/ር አለሙ ካሳዬ እና ለዶ/ር መንግስቱ ለገሰ የከበረ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ ለጥናቱ የማጠቃለያ ተቋቁሞ ያቀረብኩትን ጽሁፌን በማንበብ በተቋቁሞ ላይ ገንቢና አስተማሪ አስተያየትና ጥያቄ ላቀረቡልኝና በመጨረሻም የመመረቂን ዜና ላበሰሩኝ ፈታኞቼ ፕሮፌሰር ሽፈራው በቀለና ፕሮፌሰር ሀብታሙ ወንድሙ የከበረ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

# አጠቃሎ

ጥናቱ በሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ አስተሳሰብ፣ እውቀትና እምነት ውስጥ ነውር የያዘውን ሰፊ ትርጉምና ገዥ ቦታ በመመርመር የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና መግለፅን ዋና አላማ አድርጎ የተካሄደ ነው፡፡ ጥናቱ አይነታዊ ገላጭ የአጠናን ዘዴን ተከትሎ የተካሄደ ሲሆን፤ የጥናቱ መረጃዎች በቤተ መዛግብትና የመረጃ መረብ ዳሰሳ፣ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት አማካይነት የተገኙ ናቸው፡፡ በጥናቱ የተሳተፉ ሰዎች የተመረጡት በዋናነት በአላማ ተኮር የናሙና ስልት ነው፡፡

ምግብ፣ ሞትና የግብርና ስራን ርዕሰ ጉዳያቸው ያደረጉ 126 ነውሮች ተሰብስበው የጥናቱ አካል የተደረጉ ሲሆን፤ ከእነዚህ መካከል በተወሰኑት ላይ ጭብጥን መሰረት ያደረገ የመረጃ ትንተና ተካሂዷል፡፡ ማህበረሰቡ ነውር ለሚላቸው የምግብ አይነቶች ለጤና ጠንቅ ስለሆኑ፤ ከሞት ጋር ለተያያዙ ድርጊቶች ድርጊቶቹ ወደ ሞት ስለሚያመሩ፤ ከስራ ጋር ለተያያዙ ድርጊቶች ድርጊቶቹ በረከትን ስለሚያሳጡ የሚሉ ጉዳዮችን ዋና መንስኤ እንደሚያደርግ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

ማህበረሰቡ ነውሮችን የሚፈጥረው የአባላቱን ባህሪና አስተሳስብ ለመግዛት፤ የልጆቹን ሰብዕና ለመቅረፅ፤ ስጋዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶቹን ለማርካት፤ በአጠቃላይም ለአኗኗሩ መርህ፣ ለግንኙነቱ ደንብና ህግ ሆነው እንደሚያገለግሉት በማሰብ ነው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ነውሮች ከጥቅም በስተቀር የጎንዮሽ ጉዳት ሊኖራቸው ይችላል የሚል እምነት የለውም፡፡ ይሁን እንጅ ነውሮቹ በጥልቀት ሲመረመሩ የየራሳቸው የሆነ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ሚና ያላቸው ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ግን ነውሮች የማህበረሰቡን ጥንተ ማንነት፣ ባህል፣ ደንብ፣ አስተሳሰብ ወዘተ. የሚያሳዩና በአጠቃላይም የማህበረሰቡ የህይወት ፍልስፍና ምን እንደሚመስል ለመረዳት የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ከዚህ በመነሳትም ነውሮችን ሁሉ ጎጅ አድርጎ ከመውሰድ ይልቅ አዎንታዊ ሚና ያላቸውን በመለየት እነሱን ማክበርና ማስፋፋት ተገቢ መሆኑን፤ አሉታዊ ሚና ያላቸውን ደግሞ በሂደት ሊቀሩ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር እንደሚያስፈልግ የሚጠቁሙ ይሁንታዎች ተሰንዝረው ጥናቱ ተቋጭቷል፡፡

# ማውጫ

ካርታዎች ....................................................................................................ሀ

ምስጋና ....................................................................................................መ

አጠቃሎ ....................................................................................................ሠ

ማውጫ ....................................................................................................ረ

ምዕራፍ አንድ ....................................................................................................1

የጥናቱ መግቢያ....................................................................................................1

1.1 የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ እና አካባቢ መመረጥ ምክንያቶች....................................................3

1.1.1 የርዕሱ መመረጥ ምክንያቶች....................................................................4

1.1.2 የጥናቱ አካባቢ መመረጥ ምክንያቶች....................................................5

1.2 የጥናቱ ዋናና ዝርዝር ዓላማዎች....................................................................7

1.3 ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ....................................................................7

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ....................................................................................8

1.5 የጥናቱ ወሰን ....................................................................................9

1.6 ሙያዊ ስነምግባርና የመስክ ገጠመኞች ....................................................10

1.6.1 ሙያዊ ስነምግባር ....................................................................10

1.6.2 የመስክ ገጠመኞች ....................................................................11

1.7 የጥናት ጽሁፉ አደረጃጀት....................................................................13

ምዕራፍ ሁለት ....................................................................................14

ክለሳ ድርሳን ....................................................................................14

2.1 ጽንሰ ሃሳባዊ ዳራ ....................................................................................14

2.1.1 የነውር ምንነትና ባህሪያት....................................................................14

2.1.2 የነውር መፈጠርና መኖር ምክንያቶች ....................................................18

2.1.3 የነውር ሚናና ምደባ ....................................................................19

2.2 ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፍ ....................................................................23

2.2.1 የማህበራዊ ግንባታ ስነ እውቀት ንድፈ ሀሳብ....................................................23

2.2.2 ስነ ፋይዳ....................................................................................26

2.3 የቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ....................................................................27

2.3.1 በኢትዮጵያ ነውር ዙሪያ የተሰሩ ቀደምት ጥናቶች......................................................27
2.3.2 በውጭ ሃገራት ነውር ላይ የተደረጉ ጥናቶች.............................................................33

ምዕራፍ ሶስት ..........................................................................................................41
የጥናቱ ስነዘዴ...........................................................................................................41
3.1 የጥናቱ አይነት ..................................................................................................41
3.2 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴና አተገባበር ....................................................................42
3.2.1 የካልዓይ መረጃዎች አሰባሰብ ዘዴና አተገባበር ..............................................42
3.2.2 የቀዳማይ መረጃዎች አሰባሰብ ዘዴና አተገባበር .............................................43
3.2.2.1 የመረጃ አሰባሰብ ሂደት..............................................................................43
3.2.2.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና አተገባበር....................................................48
3.3 የመረጃና ውጤት አተናተንና አተረጓጎም ሂደት ...................................................51
ምዕራፍ አራት .........................................................................................................54
የጥናቱ ትኩረት አካባቢ ማስተዋወቂያ.......................................................................54
4.1 የሊቦ ከምከም ወረዳ አጭር ትውውቅ ...................................................................54
4.2 የሊቦ ከምከም ወረዳ አጠቃላይ ዳራ.....................................................................55
4.2.1 የህዝብ ሁኔታ፣ ቋንቋና ሃይማኖት ....................................................................55
4.2.2 የአየር ጠባይና መልክዓምድራዊ ሁኔታ..............................................................56
4.2.3 የኢኮኖሚና መሰረተ ልማት ሁኔታ ....................................................................57
4.2.4 የዝምድና መፍጠሪያና መረዳጃ ተቋማት ............................................................58
4.2.5 የቤተሰብ ማህበራዊ ሚናና የስርዓተ ፆታ ሁኔታ..................................................61
4.2.6 ልማዳዊ እምነቶች.............................................................................................66
4.2.7 የባህል ለውጥና መሻሻል .....................................................................................73

ምዕራፍ አምስት ........................................................................................................78
የምግብ ነውሮች የመረጃ አቅርቦት፣ ትንተናና ውጤት.................................................78
5.1 የመረጃ አቅርቦትና ትንተና ..................................................................................78
5.1.1 *የምግብ አይነት ምርጫና ተያያዥ ነውሮች* እውቀት፣ ልምድና ትግበራ....................79
5.1.1.1 የጤና መታወክን የሚያስከትሉ የምግብ አይነቶች ..............................................82

5.1.1.2 የትዳር አጋር ማጣትን የሚያስከትሉ የምግብ አይነቶች ........................................87
5.1.1.3 ለድርቅና ድህነት የሚያጋልጡ የምግብ አይነቶች ..................................................90
5.1.1.4 ለተረጋጋ ህይዎት ማጣት መንስኤ የሆኑ የምግብ አይነቶች.................................92
5.1.2 የምግብ አዘገጃጀት፣ አመጋገብና ተያያዥ ነውሮች እውቀት፣ ልምድና ትግበራ......94
5.1.2.1 ንፍቀትና ድህነትን የሚያስከትሉ የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ልምዶች............96
5.1.2.2 በረከትን የሚያሳጡ የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ልምዶች...................................99
5.1.2.3 ውግዘትን የሚያስከትሉ የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ልምዶች.............................102
5.1.2.4 የጤና መታወክን የሚያስከትሉ የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ልምዶች.................105
5.2 በመረጃ ትንተናው የተገኙ የጥናቱ አበይት ውጤቶች..................................................113
ምዕራፍ ስድስት ...........................................................................................................115
የሞት ነውሮች የመረጃ አቅርቦት፣ ትንተናና ውጤት........................................................115
6.1 የመረጃ አቅርቦትና ትንተና..........................................................................................115
6.1.1 ሞትን የሚጠሩና የሙት መንፈስን የሚያስቀይሙ ድርጊቶች.......................................116
6.1.2 መካንነትን የሚያስከትሉ ሁኔታዎች .........................................................................126
6.1.3 ንፅህናን የሚያሳጡ ድርጊቶች...................................................................................129
6.1.4 ለድርቅና ድህነት የሚያጋልጡ ሁኔታዎች ..................................................................133
6.1.5 የሃዘን ስሜትን የሚያባብሱ ተግባራት .........................................................................135
6.2 በመረጃ ትንተናው የተገኙ የጥናቱ አበይት ውጤቶች..................................................139
ምዕራፍ ሰባት .............................................................................................................141
የግብርና ስራ ነውሮች የመረጃ አቅርቦት፣ ትንተናና ውጤት..............................................141
7.1 የመረጃ አቅርቦትና ትንተና ........................................................................................141
7.1.1 በረከትን የሚያሳጡ ድርጊቶች....................................................................................143
7.1.2 ፍሬ አልባነትን የሚያስከትሉ ድርጊቶች ......................................................................149
7.1.3 የድህነት መንስኤ የሚሆኑ ተግባራት............................................................................155
7.1.4 የስራ አለመስለጥን የሚያስከትሉ ተግባራት ..................................................................158
7.2 በመረጃ ትንተናው የተገኙ የጥናቱ አበይት ውጤቶች..................................................161

ምዕራፍ ስምንት ........................................................................................................163
የውጤት ትንትናና ትርጎማ...............................................................................................163
8.1 የነውር እሳቤ ...........................................................................................................163
8.2 የምግብና ተያያዥ ነውሮች እሳቤ ...............................................................................166
8.3 የሞትና ተያያዥ ነውሮች እሳቤ...................................................................................169
8.4 የስራና ተያያዥ ነውሮች እሳቤ ..................................................................................174
8.5 የነውሮች ሚና ..........................................................................................................179
ምዕራፍ ዘጠኝ ...........................................................................................................190
የጥናቱ ማጠቃለያና ይሁንታ.........................................................................................190
9.1 ማጠቃለያ...................................................................................................................190
9.2 ይሁንታ.......................................................................................................................195
የተጠቀሱ ምንጮች ......................................................................................................199
አባሪዎች ......................................................................................................................206
አባሪ አንድ - የምግብ አይነት፣ የአዘገጃጀትና የአመጋገብ ነውሮች ስብስብ …....................206
ሀ. ነውር የሆኑ የምግብ አይነቶችና ነውር የመሆናቸውን ምክንያት የሚያሳይ ሰንጠረዥ.........206
ለ. ከምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ጋር በተያያዘ ነውር የሆኑ ድርጊቶችንና
ነውር የመሆናቸውን ምክንያት የሚያሳይ ሰንጠረዥ......................................................208
አባሪ ሁለት - ከሞት ጋር የተያያዙ ነውሮች ስብስብ .........................................................211
አባሪ ሶስት - ከግብርና ስራ ጋር የተያያዙ ነውሮች ስብስብ....................................................214
አባሪ አራት - የመረጃ ሰጭዎች ግላዊ መረጃና የቀረቡ ጥያቄዎች ናሙና ..........................217
1. በቃለ መጠይቅ የተሳተፉ አባላት ግላዊ መረጃና የቀረቡ ጥያቄዎች ናሙና................217
ሀ. በቃለ መጠይቅ የተሳተፉ አባላት ግላዊ መረጃ...........................................................217
ለ. ለቃለ መጠይቅ የቀረቡ ጥያቄዎች ናሙና ..................................................................220
2. በተተኳሪ የቡዱን ውይይት የተሳተፉ አባላት ..............................................................221
ሀ. በነውር ምንነት፣ አይነትና የመከልከላቸው ምክንያቶች ዙሪያ.................................221
ለ. ለሴቶችና ህፃናት ብቻ ነውር በሆኑ ጉዳዮችና ምክንያቶቻቸው ዙሪያ..................222
ሐ. ከነውሮች ጋር በተያያዙ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ እነሱን መጣስ ሊያስከትል
በሚችለው ቅጣትና በነውሮች ሚና ዙሪያ ...............................................................223

# ምዕራፍ አንድ

## የጥናቱ መግቢያ ፦

“ባህል” በየዘመኑ የተለያዩ ፍችዎች እየተሰጡት የመጣ ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ይሁን እንጅ የተሰጡት ፍችዎች አንዱ ከሌላው ብዙም የራቀ አይደሉም፡፡ ከተሰጡት ፍችዎች መካከል ለምሳሌ ያህል የተወሰኑትን ብንመለከት Calhoun (2002:105) “ባህል” ዕውቀትን፣ እምነትን፣ ሞራልን፣ ህግን፣ ወግንና ሌሎች ሰው የህብረተሰብ አባል በመሆኑ የቀሰማቸውን ክህሎቶችና ልምዶች ጭምር የሚያጠቃልል ውሁድ ነው ይላሉ፡፡ የራስወርቅ (2004፡3) “ባህል” የአንድ ማህበረሰብ አባላት የሚረከቧቸውን የተጠራቀሙ ዕውቀቶች፣ እምነቶች፣ መመሪያዎች፣ አመለካከቶች፣ ስነምግባራት፣ ህጋጋት፣ ወጎች፣ ተለምዶዎችና ሰዎቹ የሚገለገሉባቸውን ቁስ አካላዊ ንብረቶችን ጭምር የሚያጠቃልል ሰፊ ፅንሰ ሃሳብ ነው ይለዋል፡፡

ከነዚህ ፍችዎች በመነሳት “ባህል” በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የሚፈጠር፣ የሚያድግና በየጊዜው የሚዳብርና በዚህም ምክንያት የፈጠረውን ህብረተሰብ የትናንት፣ የዛሬና የነገ ማንነት የሚያሳይ ስርዓት ነው ማለት ይቻላል፡፡

የሰው ልጅ በባህሪው ከመሰሎቹ፣ ከተፈጥሮና ከማያውቀው ዓለም (the other world) ጋር ተስማምቶ መኖርን የሚሻና ለዚህም ባህልን በመሳሪያነት የሚጠቀም ፍጡር ነው፡፡ በመሆኑም ፍላጎቴን ያሟሉልኛል፣ ከመሰሎቼ ጋር በሰላም ለመኖር ዋስትና ይሆኑኛል፣ ሌሎችን ለመቆጣጠርም ያስችሉኛል የሚላቸውን የተለያዩ ባህሎች ይፈጥራል፡፡ እየተወለደ የሚያድገው የማህበረሰቡ ክፍልም (በጋራ ተስማምቶ ባይፈጥራቸውም) ቀደምቶቹ የፈጠሯቸውን ባህሎች በሂደት እየተማራቸውና እየለመዳቸው የራሱም እውቀትና እምነት ያደርጋቸዋል፡፡

በሚፈጥራቸው ባህሎች አማካይነትም ስጋዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶቹን ለማርካት የሚያስችሉ እሴቶችን ያካትታል፤ ስርዓት አልባው ህገኛ፣ ቅርፅ የለሹ ባለቅርፅ እንዲሆንም ያደርጋል፡፡ ከማህበራዊ ልማዶች ማፈንገጥን ይከላከላል፤ የእርስበርሳዊ ግንኙነቱ ጤናማ እንዲሆን ያደርጋል፤ በጥሩ ምግባር የታነፀና ለህግ ተገዥ የሆነ ማህበረሰብን ይፈጥራል፡፡ ከሚፈጥራቸው ባህሎች መካከልም ልማዳዊ ህጎች ይጠቀሳሉ፡፡ ስለሆነም ልማዳዊ ህጎችን እየፈጠረ፤ በሂደትም ከልማዳዊ ህጎች ጎን በጎን የተለያዩ የተፃፉ ህጎችን እያወጣ በእነሱ

ሲገለገል ቆይቷል - አሁንም ይገለገላል፡፡ በሚያወጣቸው የተፃፉ ህጎች አማካይነትም ሰላሙን ለማስጠበቅ፣ መብቱን ለማስከበርና ግዴታውንም ለመወጣት ጥረት ያደርጋል፡፡

ከዚህ በላይ በመንደርደሪያነት ከቀረበው ሃሳብ የሰው ልጅ የሚተዳደረው በዋናነት በሁለት አይነት ህጎች (በልማዳዊ እና በተፃፉ ህጎች) አማካይነት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት ልማዳዊ ህጎች ላይ ነው፡፡

ልማዳዊ ህግች (Customary laws) በተፃፈ ድንጋጌ መልክ ሳይሆን በነባር- ልማድ አማካይነት ተላልፈው የመጡና አንድ የተወሰነ የማህበረሰብ ክፍል እንዲከወኑ ወይም እንዳይከናወኑ የተስማማባቸውን ባህሪያት፣ እሴቶች፣ እምነቶች፣ አመለካከቶችና ስሜቶች ወዘተ. የያዙ ናቸው (Sorcar, 2009፡2-3)፡፡ ስለሆነም ልማዳዊ ህጎች አንድ ማህበረሰብ ወደፊት እንዲሆኑለት ከሚፈልጋቸው ወይም እንዲከሰቱበት ከማይፈልጋቸው ውጤቶች በመነሳት የሚፈጥራቸው የአድርግ አታድርግ መመሪያዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ከአንድ ማህበረሰብ የአድርግ አታድርግ ልማዳዊ ህጎች መካከል ደግሞ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው “ነውር” ይጠቀሳል፡፡ ነውር አንድ ማህበረሰብ እንዲህ ባደርግ በህይወቴ ላይ ችግር ይገጥመኛል ብሎ ለሚፈራቸው ወይም ለሚያስባቸው ክስተቶች፣ አድራጎቶች፣ አሰራሮች፣ ሁነቶች፣ ድርጊቶችና አጋጣሚዎች ወዘተ. የራሱን እምነታዊ ማብራሪያ (belief expression) በማቅረብ የማህበረሰቡ አባል እነሱን ከማድረግ፣ ከመከወን ወዘተ. እንዲቆጠብ የሚያደርግበት የልማዳዊ ህግ አንድ አካል ናቸው (Muhammad et al, 2015፡ 1)፡፡ ስለዚህ ነውር የአንድ ማህበረሰብ እምነት፣ ልምድና እውቀት የሚገለፅበት፤ አንድ ማህበረሰብ ከሚፈጥራቸውና ከሚተዳደርባቸው የአድርግ አታድርግ ልማዳዊ ህጎች መካከል አታድርግን ከሚመለከቱት የሚመደብ ነው፡፡

በነውር ዙሪያ ጥናት ካካሄዱ መካከል *Kilonzo* et al (2009፡ 39 - 41) ፣ Adebileje (2012፡94) እና Selvi and Ramachandran (2012፡1) እንደሚገልፁት በተለይም የአፍሪካውያን ህይዎት ከልማዳዊ ህጎችና ተያያዥ ልማዳዊ እምነቶች በዋናነትም ከነውሮች ጋር በሰፊው የተቆራኘ ነው፡፡ እንደነዚህ ሰዎች ነውሮች አፍሪካውያን ህይወትንና እውነትን የሚረዱባቸው፤ አንድነታቸውን በማጠናከር ጤናማ የሆነ ግንኙነትን የሚፈጥሩባቸው፤ በመኖር፣ በመልመድና በመተግበር የእውቀታቸው፣ የእምነታቸውና የህይወታቸው አካል የሚያደርጓቸው የልማዳዊ ህጎች አካል ናቸው፡፡

በመሆኑም ነውሮች የእነሱ አማኝና ተቀባይ ስለሆነው የማህበረሰብ ክፍል አኗኗር፣ ፍላጎት፣ ስነ ልቡናዊ ዕውቀት፣ ፍልስፍና፤ በአጠቃላይም ስለዛ ማህበረሰብ ማንነት ሰፊ ግንዛቤ የሚሰጡ ናቸው፡፡ ስለሆነም የአንድን ህዝብ ነውሮች ማጥናት ማለት የነውሮቹ ባለቤት የሆነውን ህዝብ ማወቅ ማለት ነው፡፡ ህዝቦችን ማወቅ ደግሞ በዛ ሃገርና ህዝብ ላይ አዎንታዊ የሆነ ማህበራዊ ለውጥና ዘላቂ ልማት (Sustainable development) ለማምጣት የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡

ልማት ዘላቂነት አለው የሚባለው እንዲለማ የሚፈለገውን ማህበረሰብ ባህል መሰረት አድርጎ ድህነትን የሚቀንስ፣ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን የሚያመጣ፣ የሁሉንም መሰረታዊ ፍላጎት የሚያሟላ፣ የተረጋጋ ፖለቲካዊ ስርዓትን የሚገነባ፣ እንዲሁም የተፈጥሮ አካባቢን ከጉዳት የሚታደግ ሲሆን ነው (Takoyoh et al, (የህትመት ዘመን ያልተጠቀሰ): 5 - 6)፡፡ ይሁን እንጅ እንደሳቸው ልማትን ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ብቻ አስተሳስሮ የመመልከትና ባህልን የልማት እንቅፋት አድርጎ የማየት አስተሳሰብ ስላለ በየሃገራቱ የሚወጡ የልማት ዕቅዶች እንዲለማ የሚፈለገውን ማህበረሰብ ባህል ታሳቢ ያላደረጉ ናቸው፡፡ በመሆኑም የሚወጡ የልማት ዕቅዶች ውጤታማና ዘላቂነት ያላቸው አይደሉም፡፡ በባህል ዙሪያ ጥናት ያካሄዱት Hurreiz (2006፡100) እንደገለፁትም የአፍሪካውያን ነውሮች በተለይም አፍሪካውያን ባልሆኑ አጥኝዎች ዘንድ የልማት እንቅፋት የሆኑ ጎጅ ባህሎች ተደርገው ይታሰባሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ትኩረት ተሰጥቷቸው አልተጠኑም፡፡

በሃገራችን ያለውን እውነታ ስንመለከትም ነውሮች በአግባቡ አልተጠኑም፡፡ ባለመጠናታቸውም አሁን ያሉበት ወቅታዊ ሁኔታም አይታወቅም፡፡ ስለዚህ እነሱን በመሰብሰብ፣ በማደራጀት፣ በመተንተንና በመተርጎም ያላቸውን አካባቢያዊ እሳቤና እምነት፣ ማህበራዊ ትርጉም፣ ሚና ወዘተ. መመርመርና መገንዘብ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ ስለሆነም በደቡብ ጎንደር ዞን ውስጥ በሚገኘው ሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ ማሳያነት ይህ ጥናት ተደርጓል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ እና አካባቢ መመረጥ ምክንያቶች

ይህ ክፍል ለተጠኘው ርዕሰ ጉዳይ እና ለተጠኘው አካባቢ መመረጥ አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶች የቀረቡበት ነው፡፡

### 1.1.1 የርዕሱ መመረጥ ምክንያቶች

ይህን ርዕሰ ጉዳይ በጥናት ርዕስነት ለመምረጥ ያስቻሉ ምክንያቶች ሁለት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ለዚህ ጥናት በተመረጠው አካባቢ በአንድ ወቅት በሌላ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ጥናት ሳካሂድ የነውሮች ሚና የጎላ ሆኖ ማግኘቴ ነው፡፡ የሶስተኛ ዲግሪ ትምህርቴን ከመጀመሬ በፊት ለሌላ የምርምር ስራ ሃገር በቀል በሆነው የልጆች አስተዳደግ ዙሪያ አንድ ጥናት ጀምሬ ነበር፡፡ ጥናቱም ሰሜንና ደቡብ ጎንደርን ማእከል በማድረግ ከሰሜን ጎንደር ጎንደር ዙሪያና ደንቢያ፣ ከደቡብ ጎንደር ደግሞ ሊቦ ከምከምና ፎገራ ወረዳዎች ላይ ትኩረት ያደረገ ነበር፡፡ በዚሁ መሰረትም በተጠቀሱት ወረዳዎች ውስጥ የሰበሰብኳቸው አብዛኞቹ መረጃዎች ለልጆች "ነውር" ናቸው የሚባሉ ነገሮች የበዙበት ነበር፡፡ ይሄ ሁኔታ ብዙ ነገሮች ለልጆች ለምን ነውር ሊሆኑ ቻሉ? የሚል ጥያቄን በውስጤ ፈጠረብኝ፡፡ ይህ ሁኔታም ወደራሴ የአስተዳደግ ህይወት ተመልሼ እኔ የተቀረፅኩት፣ የተኮተኮትኩትና ያደግኩበት ማህበረሰብ አጠቃላይ ሰብዕናም የተገነባው በዚሁ እምነት ነው ማለት ነው? የሚል ሃሳብ አጫረብኝ፡፡

ይህ እሳቤ ደግሞ ነውር የሚባለው ጉዳይ በልጆች ላይ ብቻም ሳይሆን በአጠቃላዩ የማህበረሰቡ ክፍል ላይም በተለያየ ቅርፅ ሊኖር እንደሚችል እንዳስብ አደረገኝ፡፡ በመጨረሻም የሶስተኛ ዲግሪ ትምህርቴን መከታተል ስጀምርና የመመረቂያ ጽሁፍ የሚሆን ርዕስ ሳስብ ነውር ሊሰራበት የሚገባው ርዕሰ ጉዳይ እንደሆነ አመንኩ፡፡

ርዕሰ ጉዳዩ ሊጠና የሚገባው ነው ወደሚል ሃሳብ ካመራሁ በኋላ ርዕሱን እንድመርጠው ያደረገኝ ሌላኛው መሰረታዊ ምክንያት ደግሞ የሃገራችን ነውሮች የአጥኝዎችን ትኩረት ያላገኙ መሆናቸው ነው፡፡ ነውሮች (በተለይም የአፍሪካውያን ነውሮች) አፍሪካውያን ባልሆኑ አጥኝዎች ዘንድ ጎጅ ባህልና ያልተማሩ ህዝቦች ቅርስ ተደርገው ስለሚፈረጁ እንዳልተጠኑ ቀደም ሲል ጠቁሜያለሁ፡፡ Osei (2006፡ 45 -46) የአፍሪካውያን ነውሮች በጎጅ ባህልነት የተፈረጁትና የአጥኝዎችንም ትኩረት የተነፈጉት አማኞቹ ስለነውሮች ያሏቸው እምነቶችና የሚያቀርቧቸው እምነታዊ ገለፃዎች እውነተኛነታቸው በዘመናዊ ሳይንስ ሊረጋገጥ አይችልም የሚል አስተሳሰብ ስላለ ነው ይላሉ፡፡ በሌላ በኩል ግን Osei ስለ ነውሮች የሚሰጡ እምነታዊ ገለፃዎች ሁል ጊዜ በሳይንስ ሊረጋገጡ የሚችሉ አይደሉም ብሎ መፈረጅ፤ በሳይንስ አለመረጋገጣቸውንም የጎጅነታቸው መገለጫ አድርጎ መውሰድ ተገቢ

እንዳልሆነ ይገልፃሉ፡፡ እንደሳቸው አባባል በአብዛኛው ባህል ውስጥ በቤተሰቦች መካከል የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም ነውር ሲሆን፣ ይህ የሆነበት ምክንያትም በዚህ መንገድ በሚወለዱ ልጆች ላይ የጤና ችግር ያመጣል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ እንደ Osei ይህ በሳይንሱም የሚደገፍ ነው ፡፡

Sims እና Stephens (2005፡57 - 59) ደግሞ የአንድ ማህበረሰብ እምነት ሲጠና በዋናነት ሊተኮርበት የሚገባው እምነቱ በሳይንስ መረጋገጥ አለመረጋገጡ፣ እውነት መሆን አለመሆኑ፣ ወይም ደግሞ ጥሩ አልያም መጥፎ መሆን አለመሆኑ ላይ አይደለም ይላሉ፡፡ እንደእነሱ ዋናው ጉዳይ የሚጠናው ነገር ለአማኙ ምን ማለት ነው? የሚጠናው ነገር ከአማኙ ማህበራዊ ደረጃ ጋር እንዴት ይጣጣማል? አማኙ በዚህ ነገር ለምን ያምናል? አማኙ ይሄን ጉዳይ እንዴት ተማረው? ወዘተ. ለሚሉ ጥያቄዎች በቂ ምላሽ ለመስጠት መሞከር ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ስመለከተው ርዕሰ ጉዳዩ ያልተጠና ግን ደግሞ ሊጠና የሚገባው ነው፡፡
ከፍ ሲል በተጠቀሰውም ሆነ በሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶች መነሻነት የሃገራችንን ነውሮች ሰብስቦ ሰዎቹ ለምን እንዲህ አሉ? ለምን እንደዚህ ያደርጋሉ/ይሰራሉ? ምክንያቱና ውጤቱስ ምንድነው? የሚሉትን ጉዳዮች ለመመርመር፣ ሳይንሳዊ ትንታኔ ለመስጠትና ሰንዶ ለትውልድ ለማስተላለፍ ገና አልተሞከረም ማለት ይቻላል፡፡ ይሄንንም ርዕሰ ጉዳዩ ሊጠና የሚገባው ነው ወደሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ባካሄድኩት የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡

ስለሆነም ትኩረት ያላገኘን ርዕሰ ጉዳይ በማጥናት ያለውን ያለመጠናት ክፍተት በተወሰነ መጠንም ቢሆን ለመሙላትና ነውሮች ጎጅ ልማዶች ናቸው የሚለውን አገላለጽ ለመመርመር በማሰብ በዚህ ርዕስ ላይ ማጥናትን መርጫለሁ፡፡

### 1.1.2 የጥናቱ አካባቢ መመረጥ ምክንያቶች

የዚህ ጥናት ትኩረት ሊቦ ከምከም ወረዳ ላይ ነው፡፡ ይህ ወረዳ በደቡብ ጎንደር ዞን ውስጥ ይገኛል፡፡ ለዚህ ወረዳ መመረጥ አነሳሽ የሆኑት ሁለት አበይት ምክንያቶች ናቸው፡፡
አንደኛው ምክንያት በአካባቢው ተከስቶ የነበረ የፀጥታ መደፍረስ ችግር ነው፡፡ የትልመ ጥናት ተቋቁሞ ያቀረብኩት በሰሜን ጎንደር ዞን በሚገኘው ጎንደር ዙሪያ ወረዳ ላይ ለመስራት ነበር፡፡ ይሁን እንጅ ከተቋቁሞ በኋላ መረጃ ለመሰብሰብ በሄድኩበት ጊዜ በሰሜን ጎንደር ውስጥ ከሚኖረው ቅማንት ማህበረሰብ ጥያቄ ጋር በተያያዘ በአካባቢው አለመረጋጋት

ተከስቶ ስለነበር ከአማካሪዬ ጋር በመነጋገርና ትምህርት ክፍሉን በማስፈቀድ የጥናት አካባቢውን ወደ ሊቦ ከምከም ወረዳ ቀይሬአለሁ፡፡
ለወረዳው መመረጥ ምክንያት የሆነው ሌላኛው ጉዳይ ደግሞ ከወረዳው ማህበረሰብና ባህል ጋር የመተዋወቅ አጋጣሚ (የትውውቅ አጋጣሚው ቀደም ሲል በጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ላይ ተነስቷል) የነበረኝ መሆኑ ነው፡፡ ይህ እውቂያ በበኩሉ እርስበርሳቸው የሚደጋገፉ ሌሎች ሶስት ተጨማሪ አነሳሽ ምክንያቶችን ፈጥሯል፡፡

**አነሳሽ ምክንያት አንድ -** የአብክመ[1] ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ባሳተመው መጽሄፍ (2001፡16 - 17) ላይ እንደተገለፀው የአማራ ክልል ህዝቦች በጋብቻ ተሳስረውና በደም ተዋህደው ለዘመናት አብረው የኖሩ በመሆናቸው በመካከላቸው የጎላ የባህል ልዩነት አይታይም፡፡ ቀደም ሲል ለርዕሰ ጉዳዩ መመረጥ አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶችን ሳነሳ በልጆች ባህላዊ አስተዳደግ ዙሪያ በተለያዩ አካባቢዎች የሰበሰብኳቸው መረጃዎች ተቀራራቢነት ያላቸው መሆኑን መግለፄም ይሄንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ወረዳ የተመረጠበት አንደኛው ምክንያት ከሌሎች የክልሉ አካባቢዎች ጋር የጎላ የባህል ልዩነት ስለማይታይበትና ይህ ከሆነ ደግሞ ከተጠኝ ቦታ ስፋት ይልቅ አንድ ውስን አካባቢን በመምረጥ ስለነገሩ ጥልቀት ያለው መረጃ መስጠት የተሻለ ነው ከሚልና ለእኔ ቅርበት ያለውም አካባቢ ይሄኛው በመሆኑ ነው፡፡

**አነሳሽ ምክንያት ሁለት -** ስለ ባህላዊ የልጆች አስተዳደግ ባደረግኩት የመረጃ ስብሰባ ወቅት የዚህ ወረዳ ማህበረሰብ ልጆቹን በሚፈልገው መንገድ ለመቅረጽ ከሚጠቀምባቸው ባህሎቹ መካከልም በዋነኛነት ነውሮች ተጠቃሽ እንደሆኑ ተገንዝቤያለሁ፡፡ ስለሆነም ለወረዳው መመረጥ መነሻ የሆነው ሁለተኛው ምክንያት ማህበረሰቡ የሚከተለው ባህላዊ የልጅ አስተዳደግ ስርዓት ነውሮች በአካባቢው በስፋት ሊገኙ እንደሚችሉ አመላካች ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

**አነሳሽ ምክንያት ሶስት -** ቀደም ሲል በልጆች አስተዳደግ ዙሪያ በአካባቢው በካሄድኩት የጥናት ወቅትም ሆነ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ለማጥናት ከወሰንኩ በኋላ ባደረኩት የሰነድ ፍተሻ በወረዳው ነውሮች ዙሪያ የተሠራ ጥናት አላገኘሁም፡፡ ይህም አካባቢውን እንድመርጥ ምክንያት ሆኖኛል፡፡

[1] አማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፡፡

## 1.2 የጥናቱ ዋናና ዝርዝር ዓላማዎች

የጥናቱ ዋና ዓላማ የሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ በነውር ላይ ያለውን እሳቤና ነውር ለሚላቸው ጉዳዮች የሚሰጠውን መንስኤ ምክንያት በመመርመር የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና መግለፅ ነው፡፡ ጥናቱ ዋናውን ዓላማ መሰረት ያደረጉ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች አሉት፡፡

- ነውር በማህበረሰቡ እምነት፣ አስተሳሰብ፣ ዕውቀት፣ ክህሎትና ባህርይ ውስጥ የያዘውን ማህበራዊ ፍች መመርመር፤
- በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ ነውሮች የሚዘወተሩባቸውን ርዕሰ ጉዳዮችና ነውር የሆኑትን ለምን እንደሆኑ የራሳቸውን ገለፃ መሰብሰብ፡፡
- የማህበረሰቡ ነውሮች ያላቸውን (አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ) ሚና መግለፅና መተንተን፤
- በነውሮች አማካይነት የተጠኘውን ማህበረሰብ አካባቢያዊ እውቀት፣ አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና ወዘተ. መግለፅና መተንተን፤

## 1.3 ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

1. ነውር የሚለው እሳቤ በተጠኘው ማህበረሰብ እምነት፣ አስተሳሰብ፣ ዕውቀት፣ ክህሎትና ባህርይ ውስጥ  እንዴት ይገለፃል?
2. በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ ነውሮች የሚዘወተሩባቸው ርዕሰ ጉዳዮችና ነውር የሆኑባቸው መንስኤዎች ምንድን ናቸው?
3. የማህበረሰቡ ነውሮች ያላቸው ሚና ምንድነው ?
4. ነውሮች የተጠኘውን ማህበረሰብ የህይወት ፍልስፍና ለመረዳት ያስችላሉ?

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

1. በነውሮች መነሻነት የአካባቢው ማህበረሰብ ስለሚመራባቸው ደንቦች፣ ትውፊታዊ ስርዓቶች ስለቆሙባቸው ህጎች፣ ባህርያዊና ድርጊታዊ ልምዶች ስለተከለከሉባቸው ሁኔታዎች መረጃዎችን ይሰጣል፡፡

   በመሆኑም የትምህርት፣ የልማት፣ የባህል ወዘተ. ፖሊሲ አውጭዎች ፖሊሲ ከማርቀቃቸውና ከማውጣታቸው በፊት ህዝቡ ከፖሊሲው ምን እንደሚጠብቅ የሚጠቁም የፖሊሲ ግብዓት ከዚህ ጥናት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

2. ነውሮች የተፃፉ ህጎች ስራ ላይ ከማዋላቸው በፊት እንደመተዳደሪያ ህግ ሆነው ያገለግሉ የነበሩና አሁንም ቢሆን ብዙ ተከታይና አማኝ ያላቸው እንደሆኑ ጥናቱ ያሳያል፡፡

   ስለሆነም ህግና ፍትህ ማስከበርን የእለት ተዕለት ተግባራቸው ያደረጉ ተቋማት ከዚህ ጥናት ለስራዎቻቸው አጋዥ የሆኑ ግብዓቶችን ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

3. ጥናቱ የነውሮችን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ሚና በማሳየት አዎንታዊ ሚና ያላቸው የበለጠ የሚጠናከሩበትን፤ አሉታዊዎቹ ደግሞ በሂደት ሊቀሩ የሚችሉበትን ሁኔታ የሚጠቁም ነው፡፡

   በመሆኑም የዚህን ጥናት ውጤት የሚመለከቱ ወላጆች፣ መንግስትና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት የነውሮችን አሉታዊ ጎን ብቻ በመመልከት እነሱን በጅምላ ከመንቀፍ ወጥተው ስለአዎንታዊ ሚናቸውም ማሰብ እንዲጀምሩ፤ የጎንዮሽ ጉዳታቸውንም ተረድተው በተለዬ ሁኔታ በነውሮች ተጎጅ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን እንዲያግዙ የሚያስችል ግንዛቤን ሊያገኙበት ይችላሉ፡፡

4. ይህ ጥናት በጥናቱ ከታዩ ጉዳዮች በመነሳት በቀጣይ በጥልቀት መጠናትና መጣራት ስላለባቸው ባህላዊ እውቀቶች ክፍተት ይጠቁማል፡፡

   ስለሆነም የፎክሎር/የባህል፣ የታሪክ፣ የስነጽሁፍ፣ የሶሲዮሎጅ፣ የስነልቡና ወዘተ. አጥኝዎች የጥናት መነሻ የሚሆኑ የተወሰኑ ፍንጮችን ሊያገኙበት ይችላሉ፡፡

5. ጥናቱ በሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ ውስጥ ነውሮች የሚዘወተሩባቸውን ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዮችና የተወሰኑ ነውሮችን ያሳያል፡፡

   ስለሆነም ለማህበረሰቡ ባህል እንግዳ የሆኑ (ለኑሮም ሆነ ለጉብኝት ወደ አካባቢው የሚሄዱ) ሰዎች ማህበረሰቡ የተለያዩ ነውሮች እንዳሉት አስቀድመው በማወቅና

እነሱን በማክበር ከማህበረሰቡ ጋር መልካም ተግባቦትን እንዲፈጥሩ የሚያስችል የተወሰነ መረጃ ከዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

6. ጥናቱ ስለ አካባቢው ግለሰባዊ፣ ቡድናዊ እና ማህበረሰባዊ እርስ በርሳዊ ግንኙነት፣ ስለ ማህበረሰብ እውቀት፣ እምነት ወዘተ. መረጃ ይሰጣል፡፡ ስለሆነም የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ አንባቢዎች ሙያዊና አካዳሚያዊ የሆነ እውቀትን ሊያገኙበት ይችላሉ፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከተጠኝ ቦታ አኳያ በሊቦ ከምከም ወረዳ ውስጥ ባሉ 6 ቀበሌዎች ላይ ብቻ ያተኮረ ነው (ቀበሌዎቹ የተመረጡበት ምክንያትና የቀበሌዎቹ ዝርዝር በምዕራፍ ሶስት ስር ተገልጿል) ፡፡

ከተጠኝ ርዕሰ ጉዳይ አኳያ ጥናቱ በሃገረሰባዊ ልማዶች ላይ፣ ከሃገረሰባዊ ልማድ ዘሮች መካከልም ከልማዳዊ እምነቶች ውስጥ በሚመደቡት "ነውሮች" ላይ ብቻ ያተኮረ ነው ፡፡ ይሄ ሲባል ግን ጥናቱ ከነውሮች ውጭ ያሉ የፎክሎር ዘሮችን ፈፅሞ አልተመለከተም ማለት አይደለም፡፡ ነውሮች በተለያዩ የፎክሎር ዘሮች (በተለይም በስነ ቃል ዘሮች) ውስጥ የመገኘትና በእነሱ አማካይነትም የመገለፅ ባህሪ ያላቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም ተጠኚው ማህበረሰብ ነውሮችን ለመግለፅና ለማጠናከር የሚገለገልባቸው እምነት ነክ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ተረኮችና መሰል የስነ ቃል ዘሮችም የጥናቱ አካል ናቸው፡፡

አካባቢያዊ ዳራ በቀረበበት ምዕራፍ አራት ውስጥ እንደተገለጸው ተጠኚው አካባቢ የተለያዩ ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ህዝቦች የሚኖሩበት ነው፡፡ በመሆኑም በሁሉም እምነት ተከታዮች ውስጥ ያሉ ነውሮች ሊጠኑ ይገባል፡፡ ነገር ግን በወረዳው ውስጥ ከሚኖረው ጠቅላላ ህዝብ መካከል አብዛኛውን ቁጥር (98%) የያዘው የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ በመሆኑ ጥናቱ በነዚህ ላይ ብቻ አተኩሯል፡፡

የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ በሆኑት የማህበረሰቡ ክፍሎች ውስጥም ከአነጋገር፣ ከምግብ፣ ከግብርና ስራ፣ ከቦታ፣ ከአለባበስ፣ ከአካሄድ፣ ከጋብቻ፣ ከሞት፣ ከማንነት፣ ከአቅምና መሰል ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ በርካታ ነውሮች እንዳሉ በመረጃ ስብሰባ ወቅት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ከተጠቀሱት ርዕሰ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ነውሮች ሁሉ ሊጠኑ የሚገባቸው ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ በአንድ በኩል ለጥናቱ የተመደበው የጊዜና የገንዘብ ሁኔታ ሁሉንም ለማጥናት አይፈቅድም፡፡ በሌላ በኩልም ከሁሉም ርዕሰ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ነውሮችን ለማንሳት ከመሞከር ይልቅ የተወሰኑትን ወስዶ እነሱን በጥልቀት

ማየት የተሻለ ነው፡፡ ስለሆነም ጥናቱ በመረጃ ስብሰባ ወቅት ከሌሎች የተሻለ ሰፊ መረጃ በተገኘባቸውና በማህበረሰቡ ውስጥ ተዘውታሪ ሆነው በተገኙ ከምግብ፣ ሞትና የግብርና ስራ ጋር በተያያዙ ነውሮች ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

## 1.6 ሙያዊ ስነምግባርና የመስክ ገጠመኞች

ይህ ንዑስ ርዕስ በጥናቱ ተግባራዊ የተደረጉ ስነምግባራዊ ጉዳዮች እና ከጥናቱ ጋር የተያያዙ ገጠመኞች የቀረቡበት ነው፡፡

### 1.6.1 ሙያዊ ስነምግባር

ከካልዓይ ምንጮች መረጃዎች ሲሰበሰቡ ከሚፈጠሩ ስነምግባራዊ ችግሮች መካከል መረጃዎችን በተዓማኒነት አለመውሰድና ምንጭን በአግባቡ ያለመጥቀስ በዋናነት ይጠቀሳል (ያዴሳ፣ 2008፡48)፡፡ በመሆኑም ይህ አይነት ችግር በዚህ ጥናት ውስጥ እንዳይከሰት ለማድረግ ሲባል መረጃዎችና መረጃዎቹ የተገኙባቸው ምንጮች በትክክል እንዲወሰዱና እንዲሰፍሩ ተደርጓል፡፡

የአንድን ማህበረሰብ ባህል ለማጥናት ቀዳማይ መረጃዎችን የሚሰበስብ ተመራማሪ መረጃ የሚሰጡ፣ የጥናቱን አካባቢ ምቹ የሚያደርጉ ሰዎችን እገዛና ትብብር ይፈልጋል፡፡ ተፈላጊውን እገዛና ትብብር ለማግኘትና ውጤታማ የሆነ ጥናት ለማካሄድ ደግሞ አጥኚው በሚያጠናው ማህበረሰብ ዘንድ መታመንና ወግና ባህላቸውን ጠብቆ መቆየት፣ ተገቢውን ከበሬታ መስጠትና የጥናቱን ዓላማ በግልፅ ማሳወቅ ይጠበቅበታል (Belay and Abdinasir, 2015፡ 38)፡፡ በዚሁ መሰረትም በቀዳማይ መረጃዎች ስብሰባ ወቅት ለተጠኚው ማህበረሰብ እራሴንና የጥናቴን አላማ በማስተዋወቅ መረጃ በመስጠት እንዲተባበሩኝ ፈቃዳቸውን ጠይቄያለሁ፡፡ ባህላቸውን በማክበርና በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎቻቸው ላይ በመሳተፍ ቤተሰባዊ ስሜት ፈጥሬያለሁ፡፡ መረጃ ከመሰብሰቤ በፊት መረጃ ለመስጠት ፈቃዳቸውን ከሰጡኝ ሰዎች ጋር በዋናነት ያለሙሉ ፈቃዳቸው ምስላቸው በፎቶ እንደማይወጣ፣ ድምፃቸው በዲጅታል ካሜራ እንደማይቀረጽና ስማቸውም እንደማይጠቀስ፤ መረጃ እየሰጡ እያሉ ያልፈለጉት ወይም ያላስደሰታቸው ነገር ቢፈጠር በማንኛውም ሰዓት መረጃ መስጠቱን ማቋረጥ እንደሚችሉ የቃል ስምምነት ፈፅሜያለሁ፡፡

በአጠቃላይ ለጥናቱ የሚሆኑ ከካልዓይም ሆነ ቀዳማይ ምንጮች የተገኙ መረጃዎችን ከአንድ ጥናት የሚጠበቁ ስነምግባራዊ መርሆዎችን በጠበቀ መልኩ ለመሰብሰብ ጥረት

አድርጌያለሁ፡፡ ይሄን ማድረጌም ከመረጃ ሰጭዎች ጋር በቀላሉ ተግባብቼ ሰፊ መረጃ ለመሰብሰብ እንድችል፤ የመረጃ ትንተናና ትርጎማ ስራውም ከተገኙት መረጃዎች ብቻ የመነጨ እንዲሆን ለማድረግ አግዞኛል፡፡ ሆኖም የገጠሙኝ መልካም ነገሮችና አስቸጋሪ ሁኔታዎችም ነበሩ፡፡

## 1.6.2 የመስክ ገጠመኞች

ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ሙያዊ ስነምግባሮች መከተሌ ከመረጃ ሰጭዎቼ ጋር በቀላሉ መግባባትና ሰፊ መረጃን መሰብሰብ እንድችል አግዞኛል፡፡ በየደረጃው ባሉ ቢሮዎች ውስጥ የሚገኙ የስራ ሃላፊዎች፣ ባለሙያዎችና ተጠኝዎቹ የማህበረሰቡ አባላት ባህላቸው እንዲጠና ያላቸው ፍላጎት ከፍተኛ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም ትኩረታቸውን በተጠኝው ማህበረሰብ ባህል ላይ ያደረጉ መረጃዎች ባይኖሩም አካባቢውን በተወሰነ መልኩ የሚገልፁና በጽሁፍ የሰፈሩ ጥቂት ዶክመንቶችን የሚመለከታቸው አካላት አልነፈጉኝም፡፡ ወደህዝቡ ውስጥ በመግባት መረጃ ስሰበስብም የአካባቢው ማህበረሰብ የሚያውቀውን መረጃ በማቀበል፣ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ሌሎች ሰዎችን በመጠቆም፣ እንዲሁም በማንኛውም ጊዜና ቦታ ያለስጋት እንድንቀሳቀስ በማድረግ ሰፊ እገዛ አድርጎልኛል፡፡

በአጠቃላይ ተጠኝው ማህበረሰብ ያሳየኝ ቀና ትብብር የመረጃ ስብሰባ ስራዬ የተቃና እንዲሆን ጥሩ አጋጣሚን ፈጥሮልኛል፡፡ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮቻቸው ላይ በመሳተፍ ቤተሰባዊ ስሜትን ለመፍጠር ጥረት ማድረጌ መረጃ ሰጭዎቼ የሚያውቁትን መረጃ በቀናነት እንዲሰጡኝ ለማድረግ ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ ይህ ሲባል ግን ችግሮች አልገጠሙኝም ማለት አይደለም፡፡ በመረጃ ስብሰባ ወቅት የተለያዩ ችግሮችም ገጥመውኛል፡፡

በመስክ መረጃ ስብሰባ ወቅት ያጋጠመኝ አንዱና ዋነኛው ችግር ለጥናት ከመረጥኩት ርዕስ የሚመነጭ ነው፡፡ የመረጥኩት የጥናት ርዕስ በሰዎች ፊት በግልፅ የማይነገሩ ወይም ምስጢር ነገሮች የበዙበት፣ ስለ ነውሮች ለመናገር በራሳቸው ነውር የሆኑ ቃላት ያሉበት፣ አስጊና አስፈሪ ሁኔታዎች ያሉበት፣ አግላይ ታሪኮች የተካተቱበት ወዘተ. ስለሆነ የምርምር ሂደቱ (በተለይም አጀማመሩ) ፈታኝ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት በቃለ መጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ካሳተፍኳቸው ሰዎች ጋር በግልፅ ለመወያየት ተቸግሬ ነበር፡፡ ነውር የሚሏቸውን ነገሮችና ከእነሱ ጋር የተያያዙ ገጠመኞቻቸውን በዝርዝር ለማውራት ሲጨነቁ፣ የሰሙትንና ያዩትን ታሪክ እየሸፋፈኑና እያሳጠሩ ለማለፍ ሲሞክሩ ስመለከት ክስተቱ ምን

ያህል ከባድ እንደነበር ለመታዘብ ችያለሁ፡፡ የዚህን ችግር ምንጭ ስመረምር ችግሩ በዋናነት  በማህበረሰቡ ውስጥ ስለ ነውር መናገር በራሱ ከነውር የሚቆጠር ጉዳይ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ እንዲሁም እርስ በርስ ከመፈራራት፣ በጥናቴ ላይ በቂ ግንዛቤ ካለመጨበጥ፣ እገሌ ነው የነገረው/እገሊት ነች የነገረችው ታስብለኛለህ በሚል ሚስጥር ያወጣል ብሎ ከመጠራጠር፣ የተደበቁ ሚስጥሮችንና በይፋ የማይነገሩ ጉዳዮችን ማውጣት ግጭት ይቀሰቅሳል ብሎ ከመስጋት ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ለጥናቴ ትልቅ ፈተና ስለነበር በቀጥታ ወደ ጉዳዩ ከመግባቴ በፊት ከማህበረሰቡ ጋር የነበረኝን ውስን ትውውቅና የርዕሰ ጉዳይ ማስተዋወቅ ስራ በማስፋት ከማህበረሰቡ ጋር ይበልጥ መግባባት እንዳለብኝ ተረዳሁ፡፡ በዚህም በጉዳዩ ዙሪያ በይፋና በሌሎች ፊት በግልፅ መነሳት የሚችሉትን ነውሮች እንዲነግሩኝና በስፋትም እንዲያብራሩልኝ አድርጌያለሁ፡፡ በግልጽና በሌሎች ፊት ስለነሱ መናገር በራሳቸው ነውር የሆኑትንና ሌሎችን የሚያገሉ ነውሮችን በሚመለከት ደግሞ ሚስጥር ነው ያሉትን ሁሉ እንደማከብር በመግለፅና በግል እንዲነግሩኝ በማግባባት ተፈጥሮ የነበረውን ችግር ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ባልችልም መቀነስ ግን ችያለሁ፡፡

ከፍ ሲል በተጠቀሰው መልኩ ከመረጃ ሰጭዎች ጋር በፈጠርኩት መግባባት መሰረት መረጃ ስሰበስብ ደግሞ ከመረጃ ሰጭዎች የመረጃ እጥረት ጋር የተያያዘ ችግርም ገጥሞኛል፡፡ ብዙዎቹ መረጃ ሰጭዎች ነውር የሆኑ ነገሮችን ያውቃሉ - ለምን ነውር እንደሆኑ ግን በቂ መረጃ የላቸውም፡፡ ምክንያቱን ሲጠየቁ መልሳቸው ቀደምቶቻችን ይሄን ማድረግ ነውር ነው እያሉ ስላሳደጉን እኛም ለልጆቻችን ይሄንኑ እያስተላለፍን እንቀጥላለን እንጅ ነውር ስለሆኑበት ምክንያት አናውቅም - ቀደምቶቻችንም አልነገሩንም የሚል ነው፡፡ በመሆኑም የመረጃ ሰጭዎቹ የመረጃ እጥረት ከመረጃ ስብሰባውም ባሻገር በመረጃ ትንተና ስራው ላይም ትልቅ እንከን ፈጥሮብኝ ነበር፡፡ ስለሆነም በግል ቃለ መጠይቅ በቂ ምላሽ ያላገኙትን ጥያቄዎች በመለየትና የቡድን ተኮር ውይይት በማዘጋጀት የቡድኑ አባላት እየተጋገዙ ምላሽ እንዲሰጡ ለማድረግ ሞክሬያለሁ፡፡ ይህን በማድረጌም ችግሩ ሙሉ በሙሉ ተቃሏል ለማለት ባይቻልም በተወሰነ ደረጃ ግን ለመቀነስ ችያለሁ፡፡

በመስክ መረጃ ስብሰባ ወቅት ያጋጠመኝ ሌላኛው ችግር የአካባቢው የፀጥታ ሁኔታ ነው፡፡ የመጀመሪያና ሁለተኛ ዙር የመረጃ ስብሰባ ስራዬን ያለምንም የፀጥታ ችግር ለመሰብሰብ ችዬ ነበር፡፡ ሆኖም የሶስተኛ ዙር የመረጃ ስብሰባ ስራዬን አጠናቅቄ እንደተመለስኩ በአካባቢው የፀጥታ መደፍረስ ችግር ስለተከሰተ በሶስተኛው ዙር ከተሰበሰቡ መረጃዎች

መካከል ግልፅ ያልሆኑ መረጃዎችን ወደ ቦታው ተመልሼ ለማጣራት የተወሰነ ችግር አጋጥሞኛል፡፡ ሆኖም ግን አብዛኞቹን መረጃዎች ቀድሜ ስለሰበሰብኩ፤ የተወሰኑ መረጃ ሰጭዎች የስልክ አድራሻም ስለነበረኝ እየደወልኩ በመጠየቅ እና በአካባቢው ተፈጥሮ የነበረው የፀጥታ መደፍረስ ሁኔታ ሲረጋጋ ወደ ቦታው በአካል በመሄድ የመረጃ ክፍተቱን ለመሙላት ሞክሬያለሁ፡፡

## 1.7 የጥናት ጽሁፉ አደረጃጀት

የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ አደረጃጀት በዘጠኝ ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ነው፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱ መግቢያ ክፍል ሲሆን፤ በውስጡም ጥናቱን የሚያስተዋውቁ ጉዳዮች የቀረቡበት ነው፡፡ ምዕራፉ ሁለት ክለሳ ድርሳን የተካሄደበት ክፍል ሲሆን፤ በውስጡም ለስራው ደጋፊ የሆኑ ጽንሰ ሃሳቦች፣ ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፎች እና ቀደምት ተዛማጅ ጽሁፎች ቀርበውበታል፡፡ ምዕራፍ ሶስት የጥናቱ ስነ ዘዴ ክፍል ነው፡፡ በስሩም የጥናቱ አይነት፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴና አተገባበር፣ የመረጃና ውጤት አተናተንና አተረጓጎም ሂደት ቀርበዋል፡፡ ምዕራፍ አራት የጥናቱን ትኩረት አካባቢ አጭር ትውውቅ እና አጠቃላይ ዳራ የሚመለከቱ ጉዳዮች ይገኙበታል፡፡ ከአምስት እስከ ሰባት ያሉት ተከታታይ ሶስት ምዕራፎች በቅደም ተከተል ከምግብ፣ ከሞትና ከግብርና ስራ ጋር በተያያዙ ነውሮች ዙሪያ ከመስክ በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ የመረጃ ትንተናና የውጤት ማጠቃለያ የቀረቡባቸው ናቸው፡፡ ምዕራፍ ስምንት በመረጃ ትንተና ምዕራፎች ውስጥ በተገኙ የጥናቱ ውጤቶች ላይ የውጤት ትንተናና ትርጎማ የተካሄደበት ነው፡፡ የጥናቱ የመጨረሻ ክፍል የሆነው ምዕራፍ ዘጠኝ ደግሞ የጥናቱ ማጠቃለያና ይሁንታዎች የተሰነዘሩበት ነው፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጥናቱን በአጭሩ የሚያስተዋውቁ፣ የጥናቱን ሙያዊ ስነምግባር፣ የመስክ ገጠመኞችንና የጥናታዊ ጽሁፉን አደረጃጀት የሚያሳዩ ክፍሎች የቀረቡ ሲሆን፤ በሚቀጥለው ምዕራፍ ደግሞ ክለሳ ድርሳን ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳን ፦

ይህ ክፍል በሶስት ርዕሰ ጉዳዮች የተዋቀረ ነው፡፡ የመጀመሪያው ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውና ለመረጃ ትንተና ስራው ዳራ የሆኑ ጽንሰ ሃሳቦች የተቃኙበት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ጥናቱን የሚመሩ የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፎች የቀረቡበት ሲሆን፤ ሶስተኛው ደግሞ ርዕሰ ጉዳዩን በሚመለከት ከዚህ ጥናት በፊት የተካሄዱ ተዛማጅ ጽሁፎች የተዳሰሱበት ነው፡፡

## 2.1 ጽንሰ ሃሳባዊ ዳራ

በዚህ ርዕስ ስር የነውርን ምንነትና ባህሪያት፤ የመፈጠርና የመኖር ሰበብ፤ እንዲሁም ሚናና ምደባን የሚመለከቱ ርዕሰ ጉዳዮች ተብራርተዋል፡፡

### 2.1.1 የነውር ምንነትና ባህሪያት

የነውርን ምንነትና ባህሪያት በዝርዝር ከማቅረቤ በፊት ግን ጥናቱ ከፎክሎር የሚመደብ ስለሆነ ስለ ፎክሎር የተወሰኑ መንደርደሪያ ሃሳቦችን እዚህ ቦታ ላይ አቀርባለሁ፡፡ ፎክሎር የሰው ልጅ የህብረተሰብ አባል በመሆኑ (በህብረተሰብ ውስጥ በመኖሩ ምክንያት) የሚማራቸውን ወይም የሚለምዳቸውን እውቀቶች፣ ልማዳዊ እምነቶች፣ ስነጥበቦች፣ ስነምግባሮች፣ ደምቦች፣ ይሆናሎችና የመሳሰሉትን ችሎታዎችና ልምዶች ሁሉ የሚያካትትና እነሱንም የሚያጠና የማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ ነው፡፡ ነውሮች በፎክሎር ስር ይጠቃለላሉ በሚል ከተጠቀሱት ዘሮች መካከል ከልማዳዊ እምነቶች የሚመደቡ ናቸው፡፡

ልማድ የአንድ ማህበረሰባዊ ስብስብ አይነተኛ የሆነ አድራጎት ወይም ወግ ሲሆን፤ ማህበራዊ ልማድ የሚባለው ደግሞ የአንድ ማህበረሰብ የጋራ የሆኑ ልማዶች ጥቅል መጠሪያ ነው (Dorson, 1972: 3)፡፡ ማህበራዊ ልማድ ሰዎች አጥብቀው የያዟቸው እምነቶችና ልማዶች መነሻ ምንጫቸውና ትርጉማቸው ምንድነው? ሰዎች በአንድ ነገር ለምን ያምናሉ? የሚያምኑባቸው ነገሮችስ ምንድናቸው? የተወሰኑ ልማዶችንስ ለምን ይከተላሉ? የሚሉና መሰል ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚሞክር የፎክሎር ዘርፍ ነው (ፈቃደ፣ 1991፡13 - 14)፡፡ ማህበራዊ ልማድ በውስጡ የተለያዩ የፎክሎር ዘርፎችን የሚያካትት ሲሆን፤ በእሱ ስር ሊካተቱ ከሚችሉት መካከል ልማዳዊ እምነቶች ይጠቀሳሉ (Toelken, 1996:9)፡፡ ይሄ ሲባል

ግን ለአካዳሚያዊ የፎክሎር ጥናት እንዲያመች ሲባል በማህበራዊ ልማድ ዘውግ ውስጥ ይመደብ እንጅ ሁሉም የፎክሎር አይነቶች የሚከወኑበት ዋና መሰረት ከልማድና ከእምነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡

እምነት ለአንዳች ግብር ተብሎ ከሚከናወነው የሃገረሰባዊ እምነትና ልማዳዊ ድርጊት አንስቶ እስከ የልዕለ ሰብናና ልዕለ ተፈጥሮ እንዲሁም ሃይማኖታዊ እሳቤዎች ድረስ ያሉትን የሚያቅፍ ነው (Sims and Stephens, 2005:54)፡፡ ስለዚህ እምነት አምነን የምንፈጽማቸውን ድርጊቶችና ተግባራት የሚያጠቃልል ሰፊ ጽንሰ ሃሳብ ሲሆን፤ እምነት ከሚፈፀምባቸው መካከልም ልማዳዊ እምነቶች ይጠቀሳሉ፡፡

ልማዳዊ እምነቶች እራሳቸውን የቻሉ እውቀቶች ሳይሆኑ እንደአመለካከት ሂደትና የእውቀት መንገድ የሚቆጠሩ፣ ብዙ ጊዜ ተጨባጭ የሆነ ሳይንሳዊና ሃይማኖታዊ ማስረጃ የማይቀርብባቸው፣ ተቀባይነታቸውም እምነቱ ባለበትና በሚፈፀምበት አካባቢ የሆነ እምነት መራሽ ልማዶች ናቸው (Evans & Myers, 1994፡48; Motz, 1998: 340-349; Schoemaker, 1990:54)፡፡

ልማዳዊ እምነቶች (Customary beliefs) አንድ ማህበረሰብ በረጅም ዘመን የህይወት ተሞክሮው ያዳበራቸው፣ የክስተቶችን መፈጠር ከጥሩ ወይም ከመጥፎ አጋጣሚዎች ጋር በማያያዝ የራሱን ማብራሪያ የሚያቀርብባቸው ዘልማዳዊ እምነቶች ናቸው (ሰሎሞን፣ 2007፡179፤ Abelson, 1979:17; Green, 1997: 44)፡፡ ስለዚህ ልማዳዊ እምነቶች አንድ ማህበረሰብ በአንድ በኩል የጥሩ እድል ትዕምርት አድርጎ የሚቀበላቸውን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በህይወቱ ላይ መጥፎ አጋጣሚን ያስከትሉብኛል በሚል የማያከናውናቸውን ድርጊቶችና ክስተቶች የሚመለከቱ የእምነት ገፅታዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ነውሮች አንድ ማህበረሰብ አካባቢያዊ ልምዱን መሰረት አድርጎ የሚፈጥራቸው ባህላዊ ደምቦች ናቸው፡፡ በዚሁ መነሻነትም በፎክሎር ስር ሊጠቃለሉና በእሱ ስርም ሊጠኑ ከሚችሉ የፎክሎር ዘሮች መካከል ነውሮች በዋነኛነት ከልማዳዊ እምነት የሚመደቡ ናቸው፡፡

"ነውር" የሚለውን ቃል በምልዓት የሚተካ የእንግሊዝኛ አቻ ቃል ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡ ይሁን እንጅ "የተከለከለ" የሚል የአማርኛ አቻ ሊሰጠው የሚችለው "taboo" በተወሰነ መልኩም ቢሆን ይገልፀዋል፡፡ ነውር የሆነ ነገር ሁሉ የተከለከለ ነው ማለት ይቻላል -

የተከለከለ ነገር ሁሉ ነውር የሆነ ነገር ነው ማለት ግን ያስቸግራል፡፡ ስለሆነም ለነውር "taboo" የሚለው ቃል ሙሉ በሙሉ አቻው ነው ሊባል የሚችል አይደለም - የተወሰነ ልዩነት አላቸው፡፡ ሆኖም ግን ከሌሎች በተሻለ ይገልፀዋል ብዬ ስላመንኩ ለጥናቱ ሲባል በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተጽፈው የተገኙ ጽንሰ ሃሳቦች የተሰበሰቡት taboo" የሚለው ቃል ነውርን እንደሚተካው ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ነውር "taboo"ንም የሚያጠቃልል/ የሚጨምር ጽንሰ ሃሳብ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

Omobola (2013: 221-223) ነውር በትክክል መቼ እንደተፈጠረ በእርግጠኝነት ለመናገር የሚያስችል መረጃ ባይኖርም የሰው ልጅ በጋራ መኖር ከጀመረበት ዘመን አንስቶ የተፈጠረና በስራ ላይም የዋለ ሊሆን እንደሚችል ይገልፃሉ፡፡ እንደኝህ ሰው አንድ ህዝብ የሚመራባቸው መደበኛ የሆኑ ሃይማኖታዊ እና ማህበራዊ ህጎች ከመፈጠራቸው በፊት ነውሮች እንደ ህግ በመሆን አገልግለዋል፡፡ ሃይማኖታዊና ማህበራዊ ተቋማት ከተፈጠሩ በኋላም የተፈጠሩት ሃይማኖታዊ ዶግማዎችም ሆኑ የተፃፉ ማህበራዊ ህጎች በተከታዮቻቸው ዘንድ የተከበሩ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ነበራቸው - አሁንም አላቸው፡፡

ነውሮች በአብዛኛው በአንድ ውስን አካባቢ ባህል የታጠሩ ሲሆኑ፤ የተወሰኑት ግን ለምሳሌ፦ በዘመዳሞች መካከል የሚፈፀም የግብረ ስጋ ግንኙነት፣ ስርቆት፣ ሰው መግደል አይነት ድርጊቶች በአብዛኛው የአለማቀፋዊነት ባህሪ የሚታይባቸው ናቸው (Ogunyemi, 2007፡ 5; Omobola, 2013: 222)፡፡ ነውሮች ሁል ጊዜ ቋሚ ወይም እንደነበሩ ሆነው የሚቀጥሉ ሳይሆኑ ባለው ተጨባጭ ሁኔታና ባለው ጊዜያዊ ፍላጎት የመለወጥ፣ የመሻሻል እና ከእናካቴውም የመክሰም ባህሪ የሚታይባቸው ናቸው (Osei, 2006፡ 44-45)፡፡ ከዚህ በላይ ከቀረቡት ሃሳቦች በመነሳት ተፈላጊ ሆነው የተገኙ ነውሮች ባንድም ሆነ በሌላ መንገድ በአዲስ የሚከሰቱ፤ ተፈላጊ ያልሆኑት ደግሞ ቀስ በቀስ መልካቸውን የሚቀይሩ ወይም የሚጠፉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

አንዳንድ ነውሮች በባህሪያቸው የተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን ብቻ (ህፃናትን፣ ሴቶችን፣ ወንዶችን፣ የተማሩትን፣ ያልተማሩትን ወዘተ.) የሚመለከቱ ናቸው (Sorcar, 2009፡ 5)፡፡ ነውሮች በባህሪያቸው እነሱን በሚጥስ ላይ ቅጣትን የሚያስከትሉ፤ እነሱን መጣስ ሊያስከትል ስለሚችለው ችግርም ብዙ ጊዜ በሳይንስ ሊረጋገጡ የማይችሉ እምነታዊ ገለፃዎችና ምክንያቶች የሚቀርቡባቸው ናቸው (Fershtman et al, 2011:139 -143 ; Mhaka, 2014: 375)፡፡

ከባህሪያቱ በመነሳት አጥኝዎች "ነውር" ለሚለው እሳቤ ተቀራራቢነት ያለው ብያኔ ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ፡- Chemhuru and Dennis (*2010፡123*) የሚከተለውን ብያኔ ሰጥተውታል፡፡

> ነውሮች የአንድ ማህበረሰብ አባላት የተወሰኑ ድርጊቶችንና ሁነቶችን ከመፈፀም ለምሳሌ፡- አንዳንድ የምግብ አይነቶችን ከመመገብ፣ የተቀደሱና የተከበሩ ስፍራዎችን ከመርገጥና በእነሱ አካባቢ ከመንቀሳቀስ፣ በእንሰሳት ላይ ጭካኔ የተሞላበት ተግባር ከመፈፀም፣ የተፈጥሮ ሃብቶችን ቀጣይነታቸውን በሚያሳጣና በሚያወድም አኳሃን ከመጠቀም እንዲቆጠቡ በሚል የሚጣሉ የክልከላ ህጎች ናቸው፡፡[2]
>
> Taboos are avoidance rules that forbid members of the human community from performing certain actions, such as eating some kinds of food, walking on or visiting some sites that are regarded as sacred, cruelty to non human animals, and using nature`s resources in an unsustainable manner.

የነውርን ምንነት በሚመለከት Muhammad A. et al (2015:1)ም "ነውር ስምምነትን ወይም ልማድን መነሻ ያደረገ ማህበራዊ ክልከላ ወይም እገዳ ነው" ወይም "Taboo is any social prohibition or restriction that results from convention or tradition." በማለት የChemhuru እና Dennisን ሃሳብ ያጠናክራሉ፡፡

በአጠቃላይ የጽንሰ ሃሳቡን ባህሪያትና ምንነት በሚመለከት ከዚህ በላይ ከቀረቡት ሃሳቦች በመነሳት ነውሮች አንድ ማህበረሰብ ልማዱንና እምነቱን መሰረት አድርጎ እንደመጥፎ ነገር የሚቆጥራቸውንና በአባላቱም እንዲፈፀሙም የማይፈልጋቸውን ድርጊቶች፣ አድራጎቶች፣ አሰራሮችና ሁነቶች ወዘተ. በሚመለከት የሚደነግጋቸው ባህላዊ ደምቦች ናቸው፡፡ ስለዚህ የአንድ ማህበረሰብ ነውሮች ከማህበረሰቡ ልማዶችና እምነቶች ጋር ከፍተኛ የሆነ ቁርኝት ያላቸውና የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡

ነውር በአማርኛ የሚሰጠውን ፍች ስንመለከት ደግሞ ለምሳሌ፡- ኪዳነወልድ ክፍሌ (1948፡ 643) "ህፀፅ፣ ገመና" ይሉታል፡፡ ደስታ ተክለወልድ (1962፡854) "ክፉ ግብር፣ ሃጢያት" ይሉታል ፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያዘጋጀው *መዝገበ ቃላት* (1993፡ 282) ደግሞ "በህብረተሰቡ ባህልና እምነት መሰረት እንደ መጥፎ ነገር የሚታይ፣

[2] በዚህ ጥናት ውስጥ አንድ ሃሳብ በአማርኛ ቋንቋ ቀርቦ ቀጥሎ የእንግሊዝኛ አቻው በቀረበበት ቦታ ላይ ሁሉ ትርጉሙ የራሴ ነው፡፡

የሚቆጠር (ድርጊት፣ ምግባር ...)" ይለዋል፡፡ ለዚህ ቃል "የተከለከለ"፣ "የማይፈቀድ"፣ "እርም"፣ "ግዝት"[3] ፣ "ሃራም"[4] የሚሉ ቃላትም ቅርበት ያላቸው ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ ከተጠቀሱት ቃላት መካከል በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ የተለመደው "ነውር" የሚለው ቃል ነው፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ "ነውር" የሚለው አገላለጽ የተመረጠው የባህል ጥናት የተጠኝውን ማህበረሰብ  የቋንቋ አጠቃቀም መሰረት ሊያደርግ ይገባል ከሚል እሳቤ ነው፡፡ ሆኖም ከመስክ የተሰበሰቡት መረጃዎች እንዳላቸው የአገላለጽ አመችነት ሁኔታ በተለይም እርም፣ ያልተፈቀደ፣ ክልክል የሚሉ አጠቃቀሞች "ነውር" የሚለውን ቃል ሊተኩ በሚችሉበት አኳሃን በዚህ ጥናት ውስጥ ስራ ላይ ውለዋል፡፡

በዚሁ መሰረትም በዚህ ጥናት ውስጥ "ነውር" ሲባል በዋናነት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል *መዝገበ ቃላት* ላይ ተወስዶ ከፍ ሲል የቀረበውን ብያኔ ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

### 2.1.2 የነውር መፈጠርና መኖር ምክንያቶች

ሰዎች ነውሮችን የሚፈጥሩባቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሏቸው፡፡ እንደ Sorcar (2009፡ 4-7) ሰዎች ነውሮችን የሚፈጥሩት ሃገራት የሚያወጧቸውን ህጎች ለመደገፍ ወይም ለመቃወም፣ ሃይማኖቶችንና ሌሎች የእምነት ስርዓቶችን ለማጠናከር ፣ቀደምት ነውሮችን ለማስጠበቅና ይበልጥ ለማጉላት፣ በግልጽ ከሚታዩና ከማይታዩ ጉዳቶች ራስንና አካባቢን ለመጠበቅ፣ የበላይነትን ለሌሎች ለማሳየት ወይም በሌሎች ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር፣ አንዳንዴም በነውር አሳቦ ግላዊ ፍላጎትን ለማሟላት ነው፡፡ Omobola (2013: 224)ም ሰዎች ነውር የተባሉ ነገሮችን አምነው እንዲቀበሉና እንዲንከባከቡ የሚያስገድዷቸው በአማኞቹ ዘንድ ነውሮች የተለያዩ አደጋዎችን አስቀድሞ ለመከላከል ይረዳሉ፣ የግልና የአካባቢ ንጽህናን በማስጠበቅ ጤናማ ህይወትን ለመምራት ያስችላሉ የሚሉ አካባቢያዊ እምነቶች መኖራቸው ነው በማለት የSorcarን ሃሳብ ያጠናክራሉ፡፡ ይሄ ማለት ግን ነውሮች እንደየሚፈጠሩበት አካባቢና ባህል የየራሳቸው መፈጠሪያ ምክንያት ስለሚኖራቸው የመፈጠራቸው ምክንያቶች ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ብቻ ናቸው ማለት አይደለም፡፡

---

[3] "ግዝት" በኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት አካባቢ የተለመደ ቃል ነው፡፡

[4] "ሃራም" በእስልምና ሃይማኖት አካባቢ የተለመደ ቃል ነው፡፡

ቀደም ባለው ክፍል ስለባህሪያቸው ሳነሳ ነውሮች እነሱን በሚጥስ ላይ ቅጣትን የሚያስከትሉ፣ ስለመከልከላቸውም እምነታዊ ገለፃዎች የሚቀርቡባቸው እንደሆኑ ገልጫለሁ፡፡ ነውር የተባሉ ነገሮችን መጣስ ጥሰቱን በፈፀመው ግለሰብ፣ በቤተሰቡና በአጠቃላይም በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ መጥፎ አጋጣሚን (ህመም፣ ሞት፣ ድርቅ፣ ድህነት ወዘተ.) ያስከትላል ተብሎ ይታመናል፡፡ ነውሮችን መጣስ የፈጣሪንና የአያት ቅድመ አያቶችን ህግ ከመጣስ ይቆጠራል፡፡ በዚህም ምክንያት ነውሮች ሰዎች የፍርሃትና የጥፋተኝነት ስሜት እንዲሰማቸው የማድረግ ሃይል ያላቸው ናቸው፡፡ ይህ ባህሪያቸውም ነውሮች እንዲከበሩና ቀጣይነትም እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል፡፡

ሁሉም ነውሮች ተመሳሳይ የሆነ ጥንካሬና ተመሳሳይ የሆነ ቅጣት የላቸውም - የመጣስ እድላቸውም ተመሳሳይ አይደለም፡፡ ጥንካሬያቸው የሚወሰነው በአማኞቻቸው ብዛትና በቅጣቱ መጠን ነው፡፡ ይህን በሚመለከት Fershtman et al ( 2011፡143-145) ነውሮች የሚጣሱት በግለሰብ፣ በቡድን አለያም በማህበረሰብ ደረጃ ሲሆን፤ የሚጣሱትም ግለሰባዊ ወይም ቡድናዊ ፍላጎትን ከማሟላት አኳያ ሊሆን ይችላል ይላሉ፡፡ እንደ Fershtman et al እነሱን በጣሱት ላይ የሚወሰደው ቅጣትም እንደ ጥሰቱ አይነትና ደረጃ የተለያየ ሲሆን፤ ቅጣቱም፦ ጥሰቱን የፈፀመውን ግለሰብ ወይም ቤተሰቦቹን መግደል፣ ከአካባቢው ማባረር፣ ከትዳር ማፋታት፣ የገንዘብ መቀጮ፣ የአካል ቅጣት፣ እርግማን፣ ማስጠንቀቂያ ወዘተ. ሊሆን ይችላል ፡፡ የቅጣቱ አላማ ግን ጥሰቱን የፈፀመውን ግለሰብ ለመጉዳት ሳይሆን ከተቀጣው ግለሰብ በመማር ሌላው የማህበረሰብ ክፍል ለባህሉ ተገዥ እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡

## 2.1.3 የነውሮች ሚናና ምደባ

"ነውር የህሊና ፖሊስ ነው ወይም taboo is a form of thought police"

(Fershtman, etal. *2011:140*)

ነውሮች ለፈጠራቸውና ለሚገለገልባቸው ማህበረሰብ የየራሳቸው የሆነ አዎንታዊና አሉታዊ ሚና አላቸው፡፡ ይሁን እንጅ የሁሉንም ሃሳብ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ማካተት ስለማይቻል የተወሰኑትን ብቻ ቀጥሎ እጠቅሳለሁ፡፡

በነውሮች አዎንታዊ ሚና ዙሪያ ጥናት ካካሄዱ መካከል Chigidi (2009: 177-183) እና Omobola (2013: 223) ነውሮች ልጆችን የማስተማርና ባህሪያቸውን የመቅረፅ፤ በመሪና ተመሪ እንዲሁም በታላቅና ታናሽ መካከል የመከባበር ስሜትን የመፍጠር፤ መልካም

የሚባሉ ነባር ምግባራዊ ደምቦች እንዲከበሩ የማድረግ ወዘተ. ሚና አላቸው ይላሉ፡፡ Fershtman, et al (2011:*140*) በናይጀሪያዎቹ የዩርባ ጎሳዎች ነውሮች ላይ ባካሄዱት ጥናት ነውሮች ሞራላዊ እሴቶችንና ሰላምን የማስጠበቅ ቁልፍ ሚና እንዳላቸው ማረጋገጣቸውንና በዚህም በዩርባዎች ዘንድ ፖሊስ እንደማይታወቅ በመግለፅ የነውሮችን አዎንታዊ ሚና ያጎላሉ፡፡

Osei (2006፡ 45) ም

> "... ነውር ለሁሉም ማህበራዊ ስርዓት የማዕዘን ድንጋይ ነው፡፡ በነውሮች የማይመራ የማህበራዊ ስርዓት ለምሳሌ፡- የገዥዎችና ተገዥዎች፣ የፖለቲካዊ ህይወት፣ የቤተሰባዊና በአጠቃላይም ኢኮኖሚያዊ ህይወት አካል የለም"

> "... taboo is the cornerstone of the whole social order. There was no part of the social system that was not regulated and governed by taboos, like rulers and subjects, political life, family life as well as economic life."

በማለት የላይኞቹን ሃሳብ ያጠናክራሉ፡፡ Patrick, A (2015: 1)ም ነውሮች በተለይም በጥንት ልማድ የሚፀናና ድንገተኛ ከፍተኛ ለውጥን የሚቃወም ማህበረሰብ ነባር የሆኑ ባህላዊ ደምቦቹን (በአጠቃላይም የቆዩ ልማዶቹን) የሚያስቀጥልባቸው ያልተፃፉ የጋራ ደንቦች ናቸው በማለት ከፍ ሲል የተጠቀሱትን የነውር አዎንታዊ ሚናዎች ያጠናክራሉ፡፡ ይሄ ማለት ግን ነውሮች አሉታዊ ሚና የላቸውም ማለት አይደለም፡፡

ጥናቶች እንደሚያሳዩት በተለይም የአፍሪካውያን አንዳንድ ነውሮች በተከታዮቻቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- እንደ Osei (2006፡ 54) በብዙ የአፍሪካ አካባቢዎች የፕሮቲን ይዘት ያላቸው የምግብ ዓይነቶች ለልጆችና ለሴቶች ነውር ናቸው፡፡ እነዚህ አይነት ነውሮች ሰዎችን የተመጣጠነ ምግብ በማሳጣት ለበሽታ የሚዳርጉ ናቸው፡፡ በብዙዎቹ የአፍሪካ ባህሎች ሰው ሲሞት ለብዙ ቀናት የአካባቢው ሰዎች የእለት ተለት ስራቸውን ከማከናወን የሚቆጠቡ ሲሆን፤ እንዲህ አይነት ነውሮች ህዝቦችን ለድህነት ይዳርጋሉ፡፡ በብዙዎቹ የአፍሪካ ባህሎች ሴት ልጆችን አለማስገረዝ ነውር በመሆኑ ብዙዎቹ ሴት ልጆቻቸውን ያስገርዛሉ፡፡ እንዲህ አይነት ነውሮች በሴቶች ላይ አካላዊ ጉዳትንና የሰብአዊ መብት ጥሰትን ያስከትላሉ፡፡ ነውሮችን መጣስ ቅጣትን ያስከትላል፡፡ በአማኞቻቸው ወይም በተቀባያቸው ዘንድም የፍርሃትና ጥፋተኝነት ስሜትን በመፍጠር ስነ ልቡናዊ ጫናን ወዘተ. ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ Adewaraም (2012:134) የናይጀሪያዎቹ ዩርባ ጎሳዎች

የቅርብ ቤተሰብ ሲሞትባቸው እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ለሁለት ሳምንት ያህል ከእርሻ ስራቸው እንደሚታቀቡ በመግለፅ የOseiን ሃሳብ ይጋራሉ፡፡

Kikelomo (2005፡1) ደግሞ በናይጀሪያዎቹ ኢሳን (Esan) ነገዶች ላይ ባደረጉት ጥናት "... ነውሮች በዋናነት በሴቶች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ እንደሆኑና ይህም በአፍሪካ ባህል ውስጥ ሴቶች የተገለሉ፣ የተጨቆኑና ድምፅ አልባ እንዲሆኑ" ወይም "... taboos are to some extent more biased against women, so women are marginalized, oppressed and voiceless in traditional African societies" የሚያደርጉ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

ስለዚህ ነውሮች ለፈጠራቸው ማህበረሰብ ጠቀሜታ እንዳላቸው ሁሉ የጎንዮሽ ጉዳትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ነውሮችም እንዳሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ ቦታ ላይ ግን የምግብ ነውሮች አሉታዊ ተፅዕኖ ያላቸው ናቸው በሚለው የOsei ግኝት ላይ የተወሰነ ሃሳብ ማቅረብ ተገቢነት አለው፡፡ ምክንያቱም የOsei ግኝት በብዙዎቹ የመስኩ አጥኚዎች የሚደገፍ ቢሆንም የምግብ ነውሮች አዎንታዊ ሚናም እንዳላቸው በጥናታቸው ያረጋገጡ ሰዎችም አሉ፡፡ ለምሳሌ፦ Gadegbeku et al (2013፡21) አንዳንድ የአለርጂክ[5]ና ድብርት በሽታዎች አንዳንድ የምግብ አይነቶችን ከመጠቀም የሚነሱ እንደሆኑና እንደነዚህ አይነት የምግብ አይነቶችን ነውር ማድረግም ሰዎች ለተጠቀሱት አይነት የጤና ችግሮች እንዳይጋለጡ የማድረግ አዎንታዊ ሚና እንዳላቸው ይገልፃሉ፡፡ ስለሆነም ነውር የሚባሉ የምግብ አይነቶች ሁሉ አሉታዊ ሚና ብቻ ያላቸው ናቸው ማለት አይቻልም፡፡

ነውሮች በጊዜና በሁኔታዎች አስገዳጅነት የመለወጥና የመሻሻል ባህሪ እንዳላቸው ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ፦ Fershtman et al (2011: 140) እንዲህ ይላሉ፡፡

> የነውሮች አይነትና ያላቸው ፋይዳ በጊዜ ሂደት ሊለወጥ ይችላል። የተወሰኑ ነውሮች ሊዳከሙና ከናካቴውም ሊጠፉ፤ ሌሎች ደግሞ የበለጠ ሊጠናከሩ ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል የልጆች እና የህይወት ዋስትና መድህን ለዘመናት እንደነውር የሚቆጠር የነበረ ሲሆን በሂደት ግን ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል። የሰዎች የገላ ወይም የአካል ክፍል ንግድ በብዙ ማህበረሰቦች ውስጥ ነውር ቢሆንም በተወሰነ ገፅታው ግን አሁንም ድረስ ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል።

> The list of taboos and their importance may change over time. Some taboos may weaken or even disappear, while others may become stronger and more dominant. For example, child insurance and life insurance were for a long time taboos and then became

[5] የሰውነት አንዳንድ ምግቦችንና መድሃኒቶችን አለመቀበል ነው፡፡

acceptable. Trades of human organs are still a taboo in most societies, but some forms of trade became acceptable.

በመሆኑም በአንድ ወቅት አዎንታዊ ሚና የነበራቸው ነውሮች ሌላ ጊዜ አሉታዊ፣ በአንድ ወቅት አሉታዊ ሚና የነበራቸው ነውሮች ደግሞ ሌላ ጊዜ አዎንታዊ ሚና ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ስለዚህ የነውሮች አይነትና ሚና ሁል ጊዜ ባለበት የሚቆም ሳይሆን እንደ ጊዜውና እንደ አውዱ ሁኔታ ሊለዋወጥ የሚችል ነው፡፡

ነውሮችን መመደብ ለጥናት ከማመቸቱም በላይ አይነታቸውን በውል ለይቶ ለማወቅ ያግዛል፡፡ በነውሮች ላይ ጥናት ያደረጉ አጥኝዎች የጥናታቸውን አላማና በጥናታቸው ውስጥ ያስተዋሉትን ነጥብ መነሻ በማድረግ የየራሳቸውን ምደባ አካሂደዋል፡፡ ለምሳሌ፦ Chigidi (2009:175) በዚምባብዌ በሚገኙ የሾና ነገዶች ላይ ባደረጉት ጥናት ነውሮችን ህይዎትን በትክክለኛ መንገድ መምራትን የሚያሳዩ፣ ትክክለኛ ስለሚባለው የእርግዝና ሁኔታ የሚያትቱ፣ ከአደጋ መጠበቅን የሚጠቁሙ፣ መልካም ስለሚባለው ምግባር የሚያነሱ፣ ጤናማ ስለሆነ የአኗኗር ስርዓት የሚያነሱ፣ ከእርክሰት (Danger) የሚጠብቁ፣ ንፅህናን (Purity) የሚያጎለብቱ በሚል መድበዋቸዋል፡፡ እኝህ ሰው Douglas (1966:161- 162) ከተለመደው ወጣ ያለ ነገር ሁሉ ያረክሳል ማለት እንደማይቻል መግለፃቸውን በመግለፅ ነገር ግን በሾና ጎሳዎች ዘንድ የጎሳው አባላት ከሚከተሏቸው ማህበራዊ ልማዶች ወጣ ያለ ድርጊት ወይም ተግባር ሁሉ ከእርክሰት ይቆጠራል ተብሎ እንደሚታመን በጥናታቸው ማረጋገጣቸውን ይገልፃሉ፡፡

Omobola (2013:224) በናይጀሪያ በሚገኙ ዩሩባ ነገዶች ላይ ባደረጉት ጥናት ነውሮችን ከአደጋ፣ ከሃይማኖት፣ ታላቅን ከማክበር፣ ከንጽህና፣ ከምግባራዊ እሴቶች እና ከአባካኝነት ጋር የተያያዙ በሚል መድበዋቸዋል፡፡ Ogunyemi (2007:4-5) ነውሮች ከሃገራቸው ውጭ በሚኖሩ አፍሪካዉያን ውስጥ ያላቸውን ቦታና ፋይዳ በሚመለከት ባካሄዱት ጥናት የድርጊት፣ የምግብ፣ የቋንቋ፣ የሃሳብ፣ የጽሁፍና የምልክት በሚል መድበዋቸዋል፡፡ Sorcar (2009:8) ደግሞ በህንድ ባህል ውስጥ ስለእነሱ መነጋገር ነውር የሆኑ ርዕሰ ጉዳዮችን በሚመለከት ባደረጉት ጥናት ነውሮችን ከድርጊት ወይም ሁኔታ እና ከተግባቦት ጋር የተያያዙ በሚል መድበዋቸዋል፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በማሳያነት የቀረቡትን አመዳደቦች ስንመለከት ሁሉም ማለት ይቻላል በመመደቢያ መስፈርትነት የተጠቀሙት የነውሮችን ጭብጥና ይዘት ነው፡፡

በመሆኑም በመካከላቸው የአገላለጽ ልዩነት ካልሆነ በቀር መሰረታዊ የሚባል ልዩነት ያላቸው ናቸው ለማለት አይቻልም፡፡ ይሁን እንጅ ነውሮች መመደብ ያለባቸው የሚገኙበትን አካባቢ መሰረት ባደረገ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ ከተደረጉት ምደባዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 2.2 ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፍ

ይህ ንዑስ ርዕስ ጥናቱን የሚመሩ የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ ንድፈ ሃሳቦችን ምንነትና የተመረጡበትን ምክንያት የሚመለከት መረጃ የቀረበበት ነው፡፡ የፎክሎር ጥናት የሰዎችን የተለያዩ የህይወት ዘርፎች የሚዳስስ ነው፡፡ በመሆኑም፤ ከተለያዩ የማህበረሰብ የጥናት መስኮች ጋር የተለያዩ ንድፈ ሃሳቦችንና የመተንተኛ ስልቶችን የሚጋራ ዲሲፕሊን ነው፡፡ ይህ ጥናትም ከፎክሎር ጥናት የሚመደብ ስለሆነ መረጃዎችን ሰብስቦ ለመግለፅና ለመተንተን የተለያዩ ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፎችን በቅንጅት መጠቀምን ይጠይቃል፡፡

የዚህ ጥናት ርእሰ ጉዳይ ማህበራዊ ስሪት ከሆነው ባህል ውስጥ የሚመደብ ስለሆነ ጥናቱ የማህበረሰብ እውቀት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ የተመረጠው ዋናው ንድፈ ሃሳብ የማህበራዊ ግንባታ ስነ እውቀት ሆኖ በትርጓሜ (Interprative) ውስጥ የሚካተት ነው፡፡ በተጨማሪነትም ከማህበራዊ ግንባታ ስነ እውቀት ጋር የመደጋገፍ ባህሪ ያለው ስነ ፋይዳ የተሰኘ ንድፈ ሃሳብ ተካቷል፡፡

### 2.2.1 የማህበራዊ ግንባታ ስነ እውቀት ንድፈ ሀሳብ

**ዕውቀት** ፦ የሰው ልጅ የሚኖርበትን አካባቢና የዓለምን ምንነት፣ የክስተቶችን አመጣጥና ምክንያት የሚረዳበት ዘዴና ችሎታ ነው (Pehkonen እና Anu, 2003: 3)፡፡ እነዚህ ሰዎች እውቀት በዋናነት ነባራዊና ህሊናዊ በሚል በሁለት ሊከፈል እንደሚችል ይገልፃሉ፡፡ እንደ እነሱ **ነባራዊ እውቀት** (objective knowledge) ፦ ይዘቱ በነባራዊ እውነታ የሚወሰን፣ ነባራዊ እውነታን በትክክል የሚያንፀባርቅ ስለሆነም በማህበራዊ ተግባር ላይ የሚመሰረትና ዓላማውም የተግባር መመሪያ ሆኖ የሚያገለግል እውቀት ነው፡፡ ነባራዊ እውቀት ተጨባጩን ሁኔታ የሚያስረዳ፣ ሚስጥሩንም በትክክል ለመመርመር የሚጥር መደበኛና የጋራ የሆነ እውቀት ነው፡፡ **ህሊናዊ እውቀት** (subjective knowledge) ፦ ደግሞ በሰው ንቃተ ህሊና ውስጥ የነባራዊው ዓለም ነፀብራቅ የሆኑ ግላዊና ማህበራዊ ኑሮን የሚገልፁ

አስተሳሰቦችን የያዘ፣ ከልምድና ድግግሞሽ የሚገኝ ኢ- መደበኛና የግለሰብ ወይም የአንድ ቡድን የሆነ ዳሰሳዊ ዕውቀት ነው፡፡

ይህ ጥናት በአንድ በተወሰነ ባህል ውስጥ ያለውን በልምድና በተግባራዊ ድግግሞሽ የሚለመደውን፣ መሰረቱ ህዝባዊ ፈጠራና ልምምድ የሆነውን፣ በማህበረሰቡ ውስጥ የተፈጠረውንና በማህበረሰቡ ውስጥ ተግባራዊ የሚደረገውን እውቀትና እምነት የሚመለከት ስለሆነ የጥናቱ ትኩረት ህሊናዊ እውቀት ላይ ነው፡፡

**ስነ እውቀት** (epistemology) ፦ Denzin እና Yvonna (2000፡ 10) "ስነ እውቀት የእውቀትን ተፈጥሮ፣ መጠነ ርዕይና አጠቃላይ መርሆዎች የሚያጠና የፍልስፍና ዘርፍ ነው" ወይም "epistemology deals with the nature of knowledge, scope and general basis" ይላሉ፡፡ Mhaka (2014፡373) የስነ እውቀት ጥናት የሚያተኩረው በእውቀት ምንነትና መሰረቶች ላይ ሲሆን፤ በተለይም የእውቀት መነሻና መሰረቶች ምንድናቸው? የእውቀትስ አመጣጡ እንዴት ነው? የእውቀት ዳር ድንበሩ እስከየት ነው? እውነትነቱስ በምን ይለካል? የሚሉትን ጥያቄዎች መመርመር ላይ ነው በማለት የDenzin እና Yvonnaን ሃሳብ ያጠናክራሉ፡፡

**የማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ** (Social constructionist theory) ፦ እውቀት በማህበረሰብ እርስ በርሳዊ መስተጋብርና ስምምነት የሚፈጠር፣ በግለሰቦች አመለካከት ላይ የተመሰረተና ሊለወጥም የሚችል ነው የሚል ሃሳብ ባላቸው *Berger እና Luckmann* አማካይነት የተፈጠረ ንድፈ ሃሳብ ነው (Given, 2008፡816)፡፡ እንደ *Berger እና Luckmann* ዕውቀት ተፈጥሯዊ ሳይሆን ማሕበራዊ ስሪት የሆነ፤ የሰው ልጅ የሚኖርበትን አካባቢና የዓለምን ምንነት፣ የክስተቶችን አመጣጥና ምክንያት ከልምዱ ተነስቶ የሚረዳበት ዘዴና ችሎታ ነው፡፡

Sims እና Stephens (2005፡58) የገሃዱ ዓለም እውቀት ወይም የገሃዱ ዓለም እውነታ በማህበረሰብ የተገነባ ነው ይላሉ፡፡ በማስከተልም እያንዳንዳችን የየግላችንን ነገሮች ወይም ሁሴቶች እንፈጥራለን፤ በማስከተልም በግል የፈጠርናቸውን በጋራ እንገነባቸዋለን፤ ከዚያም ከግንዛቤያችንና ከልምዳችን በመነሳት ያለማረጋገጫ ወይም ያለክርክር እውነት አድርገን በጋራ እንስማማባቸዋለን በማለት የ*Berger እና Luckmann*ን ሃሳብ ይጋራሉ፡፡ እንደ Sims እና Stephens የአንድ ማህበረሰብ ፎክሎሮች ለምሳሌ፦ ስርዓተ ክንውኖች፣ ልማዳዊ እምነቶችና ነውሮች ወዘተ. ሁሉ ማህበራዊ ስሪቶች ናቸው፡፡

በዚህ ንድፈ ሃሳብ መሰረት ማሕበረሰቡ ያዋቀረው እውቀት ለግለሰብም ሆነ ለማሕበረሰብ እኩል የሚሰራ ድንጋጌ ሲሆን፤ ግለሰቦች ማሕበረሰቡ በገነባቸው ድንጋጌዎች ይጠቀማሉ፣ ይመራሉ፣ ከድንጋጌው ሲያፈነግጡም ይቀጣሉ፡፡ የማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ ዋነኛ ትኩረት ማህበራዊ እውቀቶች እንዴት ተፈጠሩ? አንድ ማህበረሰብ በአካባቢው ላሉ ሁነቶች እንዴት ባለ መንገድ ትርጓሜ ይሰጣቸዋል? እንዴትስ ይገልፃቸዋል? ሰዎች በመካከላቸው የሚፈጥሩት እርስበርሳዊ ግንኙነት እውቀትን በመፍጠር ረገድ የሚጫወተው ሚና ምንድነው? የሚሉትን ጥያቄዎች መመርመር ላይ ነው (Crotty, 1998:8)፡፡ እንደ Crotty ከእነዚህ ከተመረመሩትና ከታወቁት ነገሮች በመነሳት ስለማይታወቁት ነገሮች ለመገመት መሞከርም የዚህ ንድፈ ሃሳብ አንዱ ግብ ነው፡፡ ስለዚህ ማህበራዊ ግንባታ አብዛኞቹ የሰዎች ማህበራዊ ጠባያትና ባህሪያት የሚፈጠሩትና የሚለመዱት በባህላዊ፣ ማህበራዊና ታሪካዊ አውዶች ውስጥ ነው የሚል እይታ ያለው ንድፈ ሃሳብ ነው ማለት ይቻላል፡፡

Jimmy - Gama (2009:95) በማላዊያን ልማዳዊ እምነቶች ዙሪያ ባደረጉት አንድ ጥናት ላይ እንደገለፁት የአንድን ማህበረሰብ ልማድ፣ እምነት፣ ነውር ወዘተ. ለመግለፅ የማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ ወሳኝ ስልት ነው፡፡ እንደ እሳቸው በተጠቀሱት ባህላዊ ገፅታዎች ውስጥ የሚስተዋሉ ተምሳሌቶችን ውክልናና በማህበረሰቡ ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ ለመመርመርም ይህ ንድፈ ሃሳብ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ ስለዚህ የተምሳሌቶች ትርጓሜ (Symbolic Interpretation) የማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ አንዱ አካል ነው ማለት ይቻላል፡፡

**ተምሳሌታዊ ትርጓሜ** ፦ አንድ መረጃ ተምሳሌቶችን መሰረት ባደረገ መልኩ የሚተረጎምበት፤ በወካዩና በተወካዩ ነገር መካከል ያለው ግንኙነት የሚመረመርበት ስልት ነው (Isiguzo, 2008:8)፡፡ በአፍሪካውያን ባህሎችና ተምሳሌቶች ዙሪያ ጥናት ካካሄዱ መካከል Mhaka (2014፡ 373) እንደሚገልፁት የአፍሪካውያን ህይዎትና ባህል በተምሳሌቶች የተሞላ ሲሆን፤ በተለይም ነውሮች የዚህ ጥሩ ማሳያ ናቸው፡፡

ይህ ጥናት ተጠኝዎቹ የሊቦ ከምከም ወረዳ የማህበረሰብ ክፍሎች ስለነውሮች ያላቸውን ከልምድ የተገኘ እውቀት፤ ከዚህ እውቀታቸው ተነስተውም አካባቢያቸውንና ዓለምን የሚረዱበትን ባህላዊ ፍልስፍና የሚመረምር ነው፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን በማህበረሰቡ ነውሮች ውስጥ ያሉትን ተምሳሌቶች ማህበራዊ ውክልናና ማህበረሰቡ የሚሰጣቸውን ትርጉም፣ ነውሮቹ በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ተፅዕኖ ወዘተ. መመርመርም የዚህ ጥናት ዓላማ ነው፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጥናት የስነ እውቀት እና የማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳቦችን

በማቀናጀት የማህበራዊ ግንባታ ስነ እውቀት (*Social* Constructionist *Epistemology)* የተሰኘ ንድፈ ሃሳብ adopt ተደርጓል፡፡

## 2.2.2 ስነ ፋይዳ

ስነ ፋይዳ (Axiology)፦ የፋይዳዎችን አመጣጥ፣ ይዘት፣ ፍች፣ ተፅዕኖ ወዘተ. የሚያጠና የፍልስፍን ዘርፍ ነው (Mhaka, 2014፡ 373)፡፡ በዘርፉ ላይ ጥናት ካካሄዱ መካከል Bascom (1954: 334) እንደሚገልፁት የስነ ፋይዳ ምርምር መሰረቱ ማብራራት ነው፡፡ ይሁን እንጅ የፎክሎር ጥናት አውድን መሰረት የሚያደርግ ስለሆነ በፎክሎር ዙሪያ የሚደረግ የፋይዳ ጥናት ከማብራራት ይልቅ ፎክሎሩ በማህበረሰቡ ውስጥ ባለው ትርጓሜና ጠቀሜታ ዙሪያ ፍቺ ወይም ትርጓሜ መስጠት ላይ ያተኩራል፡፡

የስነ ፋይዳ ንድፈ ሃሳብ ባህል ወይም ፎክሎር በማህበረሰብ ውስጥ ማህበራዊ ፋይዳ ወይም ተግባር አለው ብሎ የሚነሳ ነው (Sims እና Stephens, 2005፡174)፡፡ እንደ Sims እና Stephens ማንኛውም የፎክሎር ዘርፍ በህይወት የሚኖረው የሚያበረክተው አስተዋፅኦ እስካለው ድረስ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም እንደእነሱ ማንኛውም የፎክሎር ዘርፍ የተወሰኑ ማህበራዊ፣ ባህላዊ ወይም ስነልቡናዊ ፍላጎቶችን የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው በአንድ ማህበረሰብ ፎክሎር ዙሪያ የሚካሄድ ጥናት ፎክሎሮቹ ለማህበረሰቡ ለምንና እንዴት እንደሚጠቅሙ መመርመርን ይጠይቃል፡፡

በስነ ፋይዳ ንድፈ ሃሳብ መሰረት ባህላዊ ተቋማት የአንድን ህብረተሰብ አባላት ቁሳዊና ስነልቡናዊ ፍላጎቶች የሚያሟሉ ናቸው ፡፡ ስለሆነም የባህላዊ ተቋማቱ ሚና የሚሆነው እነዚህ ፍላጎቶች የሚሟሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ላይ ነው (Mhaka, 2014፡ 382) ፡፡ ይህ ሰው ከሞት ጋር በተያያዙ ነውሮች ዙሪያ ባደረጉት አንድ ጥናት ውስጥ እንደገለፁት ነውሮች ሰዎች የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ከሚፈጥሩባቸው የጭንቀት ስሜት ለመገላገል የሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የስነ ፋይዳ ዘዴ በገለፃ የቀረቡ መረጃዎች የቀረቡበትን ትርጓሜ እና ያላቸውን ፋይዳ መመዘኛ ነው፡፡ ይህ ጥናትም የሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ ነውሮችን ፍችና ትርጓሜ በመመርመር ያላቸውን ፋይዳ ማሳየት አንዱ ዓላማው ነው፡፡ ባህልን ለማህበረሰቡ ከሚሠጣቸው ጠቀሜታዎች አኳያ እየተመለከቱ ማጥናት ደግሞ ማህበረሰቡ ስለራሱ፣

ስለአካባቢውና ስለዓለም ያለውን አመለካከት ለማወቅ ዓይነተኛ መንገድ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠኝው ማህበረሰብ ከነውሮች ጋር በተያያዘ የሚከውናቸውና የሚገልፃቸው የተለያዩ ባህላዊ ጉዳዮች ለማህበረሰቡ የሚኖራቸውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ስነ ልቡናዊ ፋይዳ ለመመርመር የስነ ፋይዳ ንድፈ ሃሳብ ወሳኝ ሚና አለው፡፡ ስለሆነም የስነ ፋይዳ ንድፈ ሃሳብ ከማህበራዊ ግንባታ ስነ እውቀት ንድፈ ሃሳብ ጋር ተቀናጅቶ በዚህ ጥናት ውስጥ ተግባር ላይ ውሏል፡፡

## 2.3 የቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ይህ ክፍል በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገራት ነውሮች ዙሪያ የተደረጉ የተወሰኑ ቀደምት ጥናቶች የሚቃኙበት ነው ፡፡

### 2.3.1 በኢትዮጵያ ነውሮች ዙሪያ የተሰሩ ቀደምት ጥናቶች

የጥናቱ ትኩረት በሆነው ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ የተሰሩ ቀደምት ጥናቶችን ለመፈለግ የቤተ መፃህፍትና የመረጃ መረብ ዳሰሳ ተካሂዷል፡፡ በዚሁ መሰረትም የኢትዮጵያውያንን ነውሮች የዳሰሰና በአማርኛ ቋንቋ የተጻፈ አንድ የሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ ተገኝቷል፡፡ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፉ ደግሞ አንድ ሞጁልና ሶስት ሳይንሳዊ መጽሄቶች ላይ የወጡ መጣጥፎች ተገኝተዋል፡፡ በዚሁ መነሻነትም በአማርኛ ቋንቋ የተጻፈውን በማስቀደምና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፉትን በማስከተል በተፃፉበትና በታተሙበት ዘመን ቅደም ተከተል መሰረት (ከሩቅ ወደቅርብ) ከዚህ በታች በአጭሩ ተቃኝተዋል፡፡

ዋልተንጉስ (2007) "ተፈጥሮን መናቅ፣ ሥጋን ማክበር፣ ለክፉ ዐይን አጋላጭ ክስተት፣ በምስራቅ ጎጃም በሚገኘው የጎዛምን ማህበረሰብ እምነት" በሚል ርዕስ የሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፋቸውን ሰርተዋል፡፡ የጥናታቸው ዋና አላማ ተጠኝው ማህበረሰብ በክፉ ዓይን እምነት ላይ ያለውን እሳቤና እምነቱ እንዲከሰት ያደረገውን ምክንያት መግለፅ ነው፡፡ አላማቸውን ከግብ ለማድረስም የተለያዩ ንድፈ ሃሳቦችንና የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም መረጃዎችን ሰብስበው ትንተናና ማብራሪያ አቅርበዋል፡፡ በጥናታቸው የትንተናና ማብራሪያ ክፍልም በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ ለክፉ አይን የሚያጋልጡ የተለያዩ አውዶች እንዳሉ አንስተዋል፡፡ የክፉ ዐይን አጋላጭ አውዶች ያሏቸውን ሲያነሱም የዚህ ጥናት ርእሰ ጉዳይ ከሆኑት ነውሮች ጋር የተያያዙ የተወሰኑ ሃሳቦችንም አቅርበዋል፡፡

በጥናታቸው ግኝት መሰረት በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ ለክፉ ዐይን ያጋልጣሉ ከሚባሉ በርካታ ጉዳዮች መካከል ነውሮችን መጣስ እንደ አንድ ምክንያት ተደርጎ ተወስዷል፡፡ በዚሁ መነሻነትም ማህበረሰቡ ከክፉ ዐይን ጋር በተያያዘ የሚተገብራቸው ያሏቸውን የተወሰኑ "ነውሮች" በጥናታቸው ውስጥ አንስተዋል፡፡

በማሳያነት፦ በጨለማ ዋሽንት መንፋትም ሆነ ክራር መምታት፣ በክረምት ጋቢቻ መፈፀም፣ ማዕድ ላይ ምንም ሳያስቀሩ ወይም ሳያስተርፉ መብላት፣ የከብትንም ሆነ የበግን የመጀመሪያ ግልገል ገበያ አውጥቶ መሸጥ፣ በግራ እጅ ማንኛውንም ስራ ማከናወን፣ ወዘተ. በማህበረሰቡ እምነት ነውር እንደሆነ አስፍረዋል፡፡ ነውር የሆኑበት ምክንያትም የተጠቀሱት ነገሮች ለክፉ ዐይን አጋላጭ የሆኑ ክስተቶች ናቸው ተብሎ ስለሚታመን እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በመጨረሻም ማህበረሰቡ የክፉ ዐይን ጥቃትን የሚከላከልባቸው በርካታ መንገዶች እንዳሉት ያነሱ ሲሆን፣ ከመከላከያ መንገዶች መካከልም የማህበረሰቡን ነውሮች ማክበር አንዱ እንደሆነ አንስተዋል፡፡

Mbaya (2002) "Linguistic Taboo in African Marriage Context: A Study of the Oromo *Laguu" በሚል ርዕስ በኦሮሚያ ክልል ኢሊባቡር አካባቢ ጥናት አድርገዋል፡፡ የጥናታቸው ዋና ዓላማ በኦሮሞ ባህል ከጋብቻ ጋር በተያያዘ ነውር ናቸው የተባሉ ቃላትንና ነውር ለመሆናቸው የሚሰጡ ምክንያቶችን መመርመር ነው፡፡ በጥናት ግኝታቸው መሰረት በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ ባል፣ ሚስት፣ እንዲሁም የባልም ሆነ የሚስት ቤተሰቦች እርስበራሳቸው በተለመደውና በታወቀው ስማቸው መጠራራት ነውር እንደሆነ አንስተዋል፡፡ ነውር የመሆናቸው ዋና ምክንያትም በተለመደው ስም መጠራራታቸው በተጠሪዎቹም ሆነ በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ አንዳች መጥፎ አጋጣሚን (ለምሳሌ ፦ በሽታ፣ ሞት፣ የምርት መቀነስ ወዘተ.) ያስከትላል ተብሎ ስለሚታመን እንደሆነ አንስተዋል፡፡ በዚህ ምክንያትም ከፍ ሲል የተጠቀሱት አይነት ሰዎች የተለመደውን ስም በመጥራት ፋንታ አንተ፣ አንቺ፣ እሱ፣ እሳቸው፣ የእኔ ባል/ ሚስት፣ የቤተሰቡ መሪ ወዘተ. የሚሉ ምትክ ስሞችን እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል፡፡*

*በመጨረሻም በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ ነውሮችን መጣስ ቅጣት ሊያስከትል የሚችለው ጥሰቱን በፈፀመው ግለሰብ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌላው የአካባቢው ማህበረሰብ ላይም ጭምር ነው ተብሎ እንደሚታመን አንስተዋል፡፡ ይህ አይነት እምነት በመኖሩም በተጠኘው አካባቢ ነውሮችን የመጣስ ሁኔታ እምብዛም እንደሆነና ይልቁንም በጣም እንደሚከበሩ ጠቅሰዋል፡፡*

*አንዳንዴ ግን ባህላዊ ክልከላዎች ሊጣሱ የሚችሉበት አጋጣሚ እንዳለ አንስተዋል፡፡ ይህ ሊሆን የሚችልበት አጋጣሚም በአካባቢው አንዳች ተፈጥሯዊም ይሁን ሰው ሰራሽ አደጋ በሚፈጠርበት ጊዜ በምትክ ስሞች መግባባት ሳይቻል ሲቀር (በአካባቢው ይሄን የምትክ ስም የሚጋሩ ብዙዎች ስለሚሆኑ) እንደሆነ በመጥቀስ ጽሁፋቸውን ቋጭተዋል፡፡*

Dawit et al. (2005) "Harmful Traditional Practices in Ethiopia" በሚል ርዕስ በጤናው ዘርፍ ለተሰማሩ አካላት የሚያገለግል አንድ የስልጠና ሞጁል አዘጋጅተዋል፡፡ የጽሁፉ ዋና አላማ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች በጤና ላይ የሚያስከትሉትን ተጽዕኖ በሚመለከት ለጤና ባለሙያዎች የሚያገለግል የስልጠና ሞጁል ማዘጋጀት ነው፡፡ የሞጁሉ አዘጋጅዎች በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች ተዘዋውረው የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ከ140 በላይ የሚሆኑ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን እንዳገኙና ከእነዚህ መካከልም ከምግብ ጋር የተያያዙ ነውሮች ተጠቃሽ እንደሆኑ  አንስተዋል፡፡ በዳሰሳ ጥናታቸው ካገኙት መረጃ በመነሳትም በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል ነፍሰ ጡር ሴቶች፣ የሚያጠቡ እናቶችና ህፃናት ለተወሰኑ የምግብ ነውሮች የተጋለጡ እንደሆኑ አንስተዋል፡፡ የነውሮቹ መነሻም በዕርግዝና ወቅት የፕሮቲን ይዘት ያላቸው ምግቦችን መመገብ የምጥ መክበድን (በቀላሉ መውለድ አለመቻልን) ያስከትላል፤ የቪታሚን ይዘት ያላቸውን ምግቦች መመገብ ደግሞ የሚወለዱት ልጆች አስቀያሚ ገጽታ ያላቸውና በሽተኛ እንዲሆኑ ያደርጋል የሚል እምነት ስላለ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

በመጨረሻም እነዚህና መሰል የምግብ ነውሮች በነፍሰ ጡር ሴቶች፣ በሚያጠቡ እናቶችና በልጆች ላይ የተመጣጠነ የምግብ እጥረትን በማስከተል ለተለያዩ የጤና ችግሮችና ለሞት እንደሚዳርጉ አንስተዋል፡፡ በማስከተልም እነዚህና መሰል የምግብ ነውሮች እንዲወገዱ ለማድረግ የጤና ባለሙያዎች ለሴቶችና በአጠቃላይም ለየአካባቢው ማህበረሰብ ስለምግብ ክልከላዎች ጉዳት ማስተማር ይጠበቅባቸዋል የሚል የመፍትሄ ሃሳብ አቅርበዋል፡፡

Yeshambel (2013) "The Role Of Cultural Practices In Trees Management Practices Among The Qemant Community Chilga Woreda (District) Ethiopia" *በሚል ርዕስ ጥናት አድርገዋል፡፡* የጥናታቸው ዋና ዓላማ የቅማንት ማህበረሰብ በደን ጥበቃና እንክብካቤ ላይ ያለውን ሃገር በቀል እውቀትና ባህላዊ ትግበራ በመመርመር ለዘላቂ ልማት ያለውን ፋይዳ ማሳየት ነው፡፡ ይህን አላማ ከግብ ለማድረስም ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶችን ተጠቅመዋል፡፡

ከማህበረሰቡ ሃገር በቀል እውቀቶች መካከልም ባህላዊ እምነቶችንና ነውሮችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ሰብስበዋል፡፡ *በጥናታቸው ግኝትም የማህበረሰቡ ሃገር በቀል እውቀቶችና ባህላዊ ትግበራዎች ለአካባቢ ደን ጥበቃ ጉልህ አስተዋፅኦ ያላቸው መሆኑን አንስተዋል፡፡ በማሳየትም ማህበረሰቡ የህገ ልቡና ሃይማኖት ተከታይ እንደሆነና የእምነት ስርዓቱን የሚፈፅመውም ከቀደምቶቹ በተረከበው ጫካ ውስጥ እንደሆነ፤ ጫካውም የእምነት መፈፀሚያ የተከበረ ቦታቸው እንደሆነ አንስተዋል፡፡*

*በዚህ ምክንያትም ጫካው የሚጠብቀን አምላክ የሚኖርበት ቦታ ነው ብለው ስለሚያምኑ ይህን ጫካ በማምለኪያነት ከመጠቀም ባለፈ ለሌላ ማንኛውም አገልግሎት ማዋል በማህበረሰቡ ዘንድ ነውር እንደሆነ አንስተዋል፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን ይህን ነውር በመተላለፍ ጫካውን ለተለያየ ግላዊ ጠቀሜታ ማዋል (መቁረጥ፣ ማቃጠል፣ በውስጡ ያሉ እንስሳትን ማደን ወዘተ.) ከፈጣሪያቸው የሚያጣላና የሚያስቀስፍ ተግባር ተደርጎ እንደሚታመን አንስተዋል፡፡ በአንፃሩ ግን በቴክኖሎጅ ለውጥ፣ በሌላው የማህበረሰብ ክፍል ጫና፣ እንዲሁም በማህበረሰቡ የኢኮኖሚ ዝቅተኛነትና መሰል ምክንያቶች ማህበረሰቡ ለዘመናት ያዳበራቸው እነዚህ ባህላዊ ትግበራዎች አሁን አሁን በማህበረሰቡ ልጆች ሳይቀር በመጣስ ላይ መሆናቸውን አንስተዋል፡፡ በጥናታቸው ማጠቃለያ ላይም የቅማንት ማህበረሰብ በረጅም ጊዜ ህይዎቱ ያዳበረው ይህ ባህላዊ ትግበራ የአካባቢ ተፈጥሮን በመንከባከብ ረገድ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ እንዳለው* በመጠቆም ጥናታዊ ጽሁፋቸውን ቋጭተዋል፡፡

Nejimu *(2015)* “Food Taboos and Misconceptions Among Pregnant Women of Shashemene District” በሚል ርዕስ *ጥናት አድርገዋል ፡፡ የጥናታቸው ዋና ዓላማ በሻሸመኔ አካባቢ የሚኖሩ ነፍሰ ጡር ሴቶች ስለምግብ ነውሮች ያላቸውን ግንዛቤና ለክልከላዎቹም የሚሰጡትን ምክንያት መመርመር ነው፡፡ በጥናታቸው ግኝትም በመረጃ ሰጭነት ካሳተፏቸው መካከል 49 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች በዕርግዝናቸው ጊዜ ተልባ፣ ማር፣ ወተት፣ እንቁላል፣ ስብነት ያለው ስጋ፣ ፍራፍሬና አትክልት ከመመገብ እንደሚቆጠቡ መገንዘባቸውን አንስተዋል፡፡ የነውሩ ዋና ምክንያትም* እነዚህ ምግቦች፡- በፅንሱ ጭንቅላት ላይ ይለጠፋሉ፤ የሚወለዱት ልጆች ስብ የበዛባቸው እንዲሆኑ ያደርጋሉ፤ በቀላሉ መውለድ ያለመቻልን (የምጥ መጠንከርን) ያስከትላሉ፤ ውርጃን ያመጣሉ፤ ለቡዳ መንፈስ ያጋልጣሉ፤

የተስተካከለ ቅርጽ የሌላቸው ልጆች እንዲወለዱ ያደርጋሉ ወዘተ. ተብሎ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ስለሚታመን እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም ይህ እምነት በአካባቢው ሊስፋፋ የቻለው እናቶች በአብዛኛው ያልተማሩ ስለሆኑ በዕርግዝና ጊዜ ሊወሰድ ስለሚገባው ምግብ ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ በመሆኑ እንደሆነ አንስተዋል፡፡ ግንዛቤያቸው ዝቅተኛ ስለሆነም እናቶችና ህፃናት ለተመጣጠነ የምግብ ዕጥረትና ለሌሎች መሰል በሽታዎች የመጋለጥ ዕድላቸው ከፍተኛ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በማስከተልም ይሄን ችግር ለመቅረፍ የጤና ባለሙያዎችና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ ለነፍሰ ጡር ሴቶችና በአጠቃላይም ለአካባቢው ማህበረሰብ ስለ ምግብ ክልከላዎች ጉዳት፣ ስለ ተመጣጠኑ ምግቦች ጠቀሜታ ሊያስተምሩ እንደሚገባ በመጠቆም ጽሁፋቸውን ቋጭተዋል፡፡

ከዚህ በላይ በአጭሩ የተቃኙት ጥናቶች ነውሮችን በቀጥታም ሆነ በእግረ መንገድ ስለሚያነሱ ከዚህ ጥናት ጋር የተወሰነ ተቀራራቢነት አላቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል የMbaya፣ የYeshambel እና የNejimu ስራዎች ትኩረታቸውን ነውር ላይ ያደረጉ ሲሆኑ፣ የነDawit እና የዋልተንጉስ ስራዎች ግን ነውርን በእግረመንገድ የተመለከቱ ናቸው፡፡

ስለሆነም ነውር ላይ ትኩረት ከማድረግ አኳያ የMbaya፣ የYeshambel እና የNejimu ስራዎች ለዚህ ጥናት ከሌሎቹ በበለጠ ቅርበት አላቸው፡፡ የMBAYA ጥናትም ሆነ ይህ ጥናት ነውርን ርዕሰ ጉዳያቸው በማድረጋቸው ይቀራረባሉ፡፡ ሆኖም የMBAYA ጥናት በቋንቋ አጠቃቀም ነውሮች ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ ይህ ጥናት ግን ከቋንቋ አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ነውሮችን ስለማይመረምር ሁለቱ ስራዎች የተለያዩ ናቸው፡፡

የYeshambel ጥናትም ሆነ ይህ ጥናት ነውርን ርዕሰ ጉዳያቸው በማድረጋቸውና የነውሮችን ሚናም የሚያነሱ በመሆናቸው ይቀራረባሉ፡፡ ሆኖም በYeshambel ጥናት ውስጥ ነውሮች የተነሱት ከአዎንታዊ ሚናቸው አኳያ ብቻ ነው፡፡ የተሰበሰበውና የተተነተነውም አንድን ርዕሰ ጉዳይ ማለትም በማምለኪያ ቦታነት የሚያገለግልን ጫካ ከማምለኪያነት ውጭ ለሌላ ማንኛውም አገልግሎት ማዋል በማህበረሰቡ ዘንድ ነውር መሆኑን የሚገልፅ አንድ ነውር ብቻ ነው፡፡ ይህ ጥናት ግን ነውሮች የሚዘወተሩባቸውን ከአንድ በላይ የሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች በስፋት በመዳሰስ የነውሮችን አዎንታዊና አሉታዊ ሚና የተመለከተ ስለሆነ ሁለቱ ስራዎች ካላቸው የትኩረት ነጥብ አኳያ ሰፊ ልዩነት አላቸው፡፡

የNejimuን ጥናት ስንመለከት፦ የእሳቸውም ሆነ ይህ ጥናት ነውርን ርዕሰ ጉዳያቸው በማድረጋቸው፣ ሁለቱም ከምግብ ጋር የተያያዙ ነውሮችን ስለሚያነሱ ይቀራረባሉ፡፡ ይሁን እንጅ የNejimu ጥናት ያተኮረው ከእርግዝና ጋር በተያያዙ የምግብ ነውሮች ጉዳት ላይ ብቻ ነው፡፡ ይህ ጥናት ግን ከእርግዝናም በተጨማሪ ከሌሎች ርዕሰ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ የምግብ ነውሮችን አዎንታዊና አሉታዊ ገፅታ በስፋት ይዳስሳል፡፡ የNejimu ጥናት ከምግብ አይነቶች ውጭ ከምግብ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ነውሮች አልተመለከተም፡፡ ይህ ጥናት ግን ከምግብ አይነቶችም በተጨማሪ ከምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ጋር የተያያዙ ነውሮችንም ይመለከታል፡፡ ስለሆነም በNejimuና በዚህ ጥናት መካከል ሰፊ የትኩረት ልዩነት አለ፡፡

ነውርን በእግረመንገድ የዳሰሱትን ጥናቶች ስንመለከት፦ የነDawit ጥናት ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች በሴቶችና ህፃናት ጤና ላይ የሚያስከትሉትን ተጽዕኖ የሚዳስስ ሲሆን፣ ከጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች መካከል የምግብ ነውሮች እንደሚጠቀሱ አንስተዋል፡፡ ሆኖም ትኩረት ያደረጉት እንደ Nejimu ጥናት ሁሉ ከምግብ ጋር የተያያዙ ነውሮችን ጉዳት መግለጽ ላይ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ከምግብ ጋር የተያያዙ ነውሮች በሴቶችና ህፃናት ላይ ይበልጥ ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉ ቢሆኑም ወንዶችንም ይመለከታሉ፡፡ ከምግብ ጋር የተያያዙ ነውሮች በእርግጥ ጉዳታቸው ሊያመዝን ቢችልም የእነሱ አማኝ ለሆነው ማህበረሰብ የሚሰጡት ጠቀሜታም አላቸው፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት እነዚህን ሁሉ በጥልቀት በመዳሰስ የነውሮችን አዎንታዊና አሉታዊ ገፅታ የሚያሳይ በመሆኑ ከነDawit ጥናት በእጅጉ ይለያል፡፡

የዋልተንጉስን ጥናት ስንመለከት፦ የጥናቱ ዋና ዓላማ ነውሮችን ማጥናት አይደለም፡፡ ይሁን እንጅ አጥኚው ማህበረሰቡ ስለ ክፉ ዐይን ያለውን እሳቤና እምነቱ እንዲከሰት ያደረገውን ምክንያት ሲመረምሩ ነውሮችም የልማዳዊ እምነቶች አካል ስለሆኑ የተወሰኑ ነውሮችን በምሳሌነት አንስተዋል፡፡ ስለሆነም የዋልተንጉስ ጥናት የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት የሆኑትን ነውሮች በተወሰነ መልኩም ቢሆን በማንሳቱ፣ ሁለቱም ጥናቶች ልማዳዊ እምነትን መሰረት ያደረጉ በመሆናቸው በሁለቱ ጥናቶች መካከል የተወሰነ የጋራ ባህሪ ይታያል፡፡ ይሁን እንጅ በዋልተንጉስ ስራ ውስጥ ነውሮች የተነሱት ከክፉ ዐይን አጋላጭ አውዶች መካከል እንደ አንድ ምክንያት ተደርገው እንጅ ራሱን የቻለ ቦታና ርዕስም ተሰጥቷቸው አይደለም፡፡ ይሄ ጥናት ግን ነውሮችን ዋና ርዕሰ ጉዳይ በማድረግ ተጠኚው ማህበረሰብ ስለ

እነሱ ምንነትና አፈጣጠር ያለውን እሳቤ፣ እነሱን አስመልክቶ የሚከተላቸውን እምነቶችና የሚፈፅማቸውን ልማዳዊ ድርጊቶች ወዘተ. በስፋትና በጥልቀት የሚመረምር ነው፡፡ ስለሆነም የዋልተንጉስ ጥናት በዚህ ክፍል ውስጥ የተቃኘው የተወሰኑ ነውሮችን ያነሳ መሆኑን ለመጠቆም ያህል እንጅ በሁለቱ ጥናቶች መካከል ሰፊ የትኩረት ልዩነት ይታያል፡፡

*በአጠቃላይ* በሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ ነውሮች ላይ ያተኮረው *ይህ ጥናት ነውሮችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ከቤተ መፃህፍት፣ ከመረጃ መረብና በዋነኛነትም ከመስክ በመሰብሰብ ተጠኝው ማህበረሰብ ስለእነሱ ምንነት ያለውን እሳቤ፤ በተጠኝው ማህበረሰብ ዘንድ ተዘውታሪ የሆኑትን ነውሮችና የሚሰጡ ምክንያቶችን፤ በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ሚና እና የማህበረሰቡን ፍልስፍና በማሳየት ረገድ ያላቸውን ቦታ ወዘተ. በጥልቀት የሚመረምር ነው፡፡*

*ስለሆነም ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሁሉም ስራዎች ማለት ይቻላል በሃገራችን ነውሮች ላይ በቂ ጥናት አለመደረጉን ለማሳየት ያህል የቀረቡ እንጅ ይህ ጥናት ከተጠቀሱት ስራዎች ጋር የሰፋ የአላማ፣ የትኩረትና የአጠናን ስነ ዘዴ ወዘተ. ልዩነት አለው፡፡*

## 2.3.2 በውጭ ሃገራት ነውሮች ላይ የተደረጉ ጥናቶች

ከኢትዮጵያ ውጭ ባሉ ሃገራት ነውሮች ዙሪያ ከተደረጉ ጥናቶች መካከል ከዚህ ጥናት ጋር ቅርበት ያላቸው ስራዎች ከቤተ መፃህፍትና ከመረጃ መረብ ተዳሰዋል፡፡ በዚሁ መሰረትም አንድ የሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት እና አምስት ሳይንሳዊ መጽሄቶች ላይ የወጡ መጣጥፎች የተዳሰሱ ሲሆን፤ በታተሙበት ዘመን ቅደም ተከተል መሰረት (ከሩቅ ወደ ቅርብ) ከዚህ በታች በአጭሩ ተቃኝተዋል፡፡

Chigidi (September, 2009) "Shona Taboos: The Language of Manufacturing Fears for Sustainable Development» በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናታቸው ዋና ዓላማ በዚምባብዌ የሚገኙት የሾና ህዝቦች ባህላዊ ክልከላዎች ልጆች የአካባቢው ህዝብ አምኖ ለተቀበላቸው ባህላዊ እሴቶች ተገዥ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ ያላቸውን ሚና መመርመር ነው፡፡

በጥናታቸው ውጤት የሾናዎቹ ባህላዊ ክልከላዎች ልጆች በአካባቢው ክልክል ናቸው የተባሉ ነገሮችን ከመፈፀም እንዲቆጠቡ በሚል የሚፈጠሩ የማስፈራሪያና የባህሪ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች እንደሆኑ አንስተዋል፡፡ የማስፈራሪያና የመቆጣጠሪያ መሳሪያ ናቸው ሲባል ግን ልጆች ወላጆቻቸውን፣ ታላላቆቻቸውን፣ እራሳቸውን፣ ጓደኞቻቸውን፣ አካባቢያቸውን እና በአጠቃላይም ሃገራቸውን እንዲወዱ የሚያደርጉ እንጅ እንዲሸበሩና የተለየ ስነልቡናዊ ጫና እንዲደርስባቸው የሚያደርጉ እንዳልሆኑም አንስተዋል፡፡

በጥናታቸው የማጠቃለያ ክፍልም አንድ ማህበረሰብ ልጆቹን ደንብና ስርዓት የሚያሲዝባቸው የራሱ የሆኑ ባህላዊ ክልከላዎች ከሌሉት ያ ማህበረሰብ የጋራ የሚላቸው እሴቶች ሊኖሩት እንደማይችል፣ እነዚህ የጋራ የሆኑ እሴቶች ከሌሉት ደግሞ ማህበራዊ ህይዎቱ ለአደጋ የተጋለጠ እንደሚሆን አንስተዋል፡፡

በመጨረሻም ባህላዊ ክልከላዎች ልጆች መልካም ዜጎች እንዲሆኑ የማድረግ ከፍተኛ አቅም ያላቸው አካባቢያዊ እውቀቶች እንደሆኑ፣ እነዚህን እውቀቶች በአግባቡ መጠቀም ደግሞ ቀጣይነት ላለው ልማት ወሳኝ ሚና እንዳለው በመጥቀስ ጥናታዊ ጽሁፋቸውን ቋጭተዋል፡፡

Sorcar (March, 2009) “Teaching Taboo Topics Without Talking About Them: An Epistemic Study Of A New Approach To HIV/AIDS Prevention Education In India” በሚል ርዕስ የሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ የጥናታቸው መሪ ጥያቄ ክልክል ስለሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች በግልጽ መነጋገር በማይቻልበት ባህል ውስጥ ስለ እነሱ ማስተማር ይቻላል? የሚል ነው፡፡ የጥናታቸው ዋና ዓላማም በተጠኘው አካባቢ ባህል ስለ እሱ መወያየት ክልክል ነው ተብሎ የሚታመንበትን “ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ” በማሳያነት በመውሰድ ስለዚህ ርዕሰ ጉዳይ በግልጽ መወያየት አለመቻል ከጤና አኳያ ሊያስከትል የሚችለውን ችግር በመመርመር ከፍ ሲል ለቀረበው ጥያቄ በቂ ምላሽ መስጠት ነው፡፡

በጥናታቸው በህንድ ሃገር ከሚገኙ ሁለት የሁለተኛ ደረጃና ሁለት ኮሌጆች በድምሩ 386 ተማሪዎችን አካተዋል፡፡ በጥናት ውጤቱ መሰረትም፦ በህንድ ሃገር ውስጥ ስለ እነሱ በግልጽ መወያየት ፈፅሞ የተከለከለ ነው ከሚባሉ ርዕሰ ጉዳዮች መካከል ኤች. አይ. ቪ. ኤድስ በቀዳሚነት እንደሚጠቀስ፣ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ለመወያየት መሞከርም ሆነ ቃሉን መጥራት ከባለጌነትና ሴሰኛነት እንደሚያስቆጠር አንስተዋል፡፡ በዚህ ምክንያትም በህንድ ሃገር ትምህርት ቤቶች ውስጥ ስለ ኤች. አይ. ቪ. ኤድስና በአጠቃላይም ስለወሲባዊ ግንኙነት ማስተማር ባህላዊ ውግዘትን እንደሚያስከትል ማረጋገጣቸውን ገልፀዋል፡፡

በጥናታቸው ማጠቃለያ ላይም በህንድ ሃገር ከፆታና ከወሲባዊ ግንኙነት ጋር ተያያዥነት ስላላቸው ርዕሰ ጉዳዮች በይፋ መነጋገር፣ እነዚህን ርዕሰ ጉዳዮች የትምህርት አካል ማድረግ ባህላዊ ውግዘትን የሚያስከትል በመሆኑ ምክንያት በዛ ሃገር ስለበሽታው ያለ ግንዛቤ አነስተኛ እንደሆነ አንስተዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በርካታ ህንዳውያንና በዛ አካባቢ የሚኖሩ ሌሎች ዜጎች በኤድስ በሽታ እንደሚሞቱ አንስተዋል፡፡ በመጨረሻም በአንድ ባህል ውስጥ ስለ እነሱ በግልጽ መናገር ፈጽሞ የተከለከለ ነው ከሚባሉ ርዕሰ ጉዳዮች (taboo topics) ራስን በማራቅ ስለ እነሱ ለማስተማርና ለውጥ ለማምጣት መሞከር ከባድ መሆኑን አንስተዋል፡፡ በማስከተልም መምህራን እነዚህን መሰል ርዕሰ ጉዳዮች ለማስተማር ሲያስቡ ነውር ነው የሚባለውን ርዕሰ ጉዳይ በቀጥታ ከመንካት ይልቅ ዘይቤያዊ አነጋገሮችን፣ አስደሳች የሆኑ ቃላትን እና የጨዋታ ለዛ ያለው ቋንቋን ሊጠቀሙ እንደሚገባ በመጠቆም ጽሁፋቸውን ቋጭተዋል፡፡

Stifel et al. (2011) “Taboos, Agriculture and Poverty” በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናታቸው ዋና ዓላማ በማዳጋስካር በሚኖሩ ህዝቦች ውስጥ የሚገኙ የስራ ነውሮች በአካባቢው የግብርና ስራና በሃገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚ ዙሪያ ያላቸውን ተፅዕኖ መመርመር ነው፡፡ *የጥናታቸው ዋነኛ የምርምር ጥያቄዎችም የስራ ነውሮች ለምርት መቀነስና ድህነት መንስኤ ናቸው? የስራ ነውሮችን በማስወገድስ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ይቻላል? የሚሉ ናቸው፡፡ ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስም በአካባቢው የሚኖሩ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን (ሃይማኖትን፣ ፆታን፣ የትምህርት ሁኔታን ታሳቢ በማድረግ) በናሙናነት በመጠቀም መረጃ ሰብስበዋል፡፡ በትንተናቸው ግኝትም በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ ህዳር ወር የሙት መንፈስ የሚያርፍበት ወር ነው ተብሎ እንደሚታመንና በዚህም ማህበረሰቡ በተጠቀሰው ወር ውስጥ ማንኛውንም የግብርና ስራ እንደማያከናውን አንስተዋል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ በተለይ ረቡዕና እሁድ ገድ የሌላቸውና የሰይጣን ቀናት ተብለው እንደሚፈረጁና በዚህ ምክንያት  የተጠቀሱት ቀናት ማህበረሰቡ ለግብርና ስራ አመች አይደሉም ብሎ የሚያስባቸውና ስራ የማያከናውንባቸው ቀናት እንደሆኑ ገልጸዋል፡፡*

*የባህላዊ እምነት ተከታዮች የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ከሆኑት የማህበረሰቡ ክፍሎች የበዙ የስራ ክልከላዎች (ስራ የማይሰሩባቸው ቀናቶች) እንዳሉባቸው አንስተዋል፡፡ ከፆታ አንፃር ሲታይም በወንዶች የሚመራ ቤተሰብ በሴቶች ከሚመራ ቤተሰብ የበለጠ የስራ*

ክልከላዎች እንዳሉበት ጠቅሰዋል፡፡ ከማህበረሰቡ የትምህርት ሁኔታ አኳያ ሲታይም ያልተማረው የማህበረሰቡ ክፍል ከተማረው ክፍል የበዛ የስራ ነውሮች እንዳሉት ገልፀዋል፡፡

በጥናታቸው ማጠቃለያም ተጠኚው ማህበረሰብ በሳምንት ቢያንስ ሁለት ቀን የግብርና ስራ እንደማይሰራ ገልጸዋል፡፡ ስራ የማይሰራባቸው ቀናት የአካባቢው ማህበረሰብ እርስ በርሱ የሚጠያየቅባቸውና በዚህም ግንኙነቱን የሚያጠናክርባቸው ስለሆኑ ከዚህ አኳያ የስራ ነውሮች አዎንታዊ ሚና እንዳላቸው አንስተዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የማህበረሰቡ የስራ ነውሮች በአካባቢው የግብርና ስራ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩና ማህበረሰቡን ለድህነት እንደሚያጋልጡ ገልፀዋል፡፡ በመጨረሻም በማህበረሰቡ ውስጥ ስራ የማይሰራባቸው ቀናት ለመብዛታቸው መነሻው የማህበረሰቡ አብዛኛው ክፍል ያልተማረ በመሆኑ እንደሆነ፤ የዚህ መፍትሄውም ማህበረሰቡን በማስተማር የግንዛቤ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ እንደሆነ በመጠቆም ጥናታቸውን ቋጭተዋል፡፡

Selvi and Ramachandran (2012) “Socio-cultural Taboos Concerning Menstruation: A Micro Level Study in the Cuddalore District of Tamil Nadu, India” በሚል ርዕስ በጋራ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናታቸው ዋና ዓላማ በህንድ ሃገር “Cuddalore” በሚባል አካባቢ ከሴቶች የወር አበባ ማየት ጋር በተያያዘ ተግባራዊ የሚደረጉ ነውሮችንና ተያያዥ ጉዳዮችን መመርመር ነው፡፡ ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስም በተጠቀሰው አካባቢ በገጠርና በከተማ የሚኖሩ ያገቡና ያላገቡ በድምሩ 600 ሴቶችን በናሙናነት በመውሰድ መረጃ ሰብስበዋል፡፡

በትንተናቸው ክፍልም በተጠኚው አካባቢ የሚኖሩ ሴቶች የወር አበባ በሚያዩበት ወቅት ህፃናትን መያዝ፤ ወደ ሃይማኖታዊ ስፍራዎችም ሆነ ስርዓተ ክንውን ወደሚፈፀምባቸው ቦታዎች መሄድ፤ ከሌሎች ሰዎች ጋር የመመገቢያም ሆነ የመኝታ ቁሳቁሶችን መጋራት ወዘተ. እንደሚከለከሉ አንስተዋል፡፡ ለእነዚህና መሰል ክልከላዎች የሚሰጡ ምክንያቶችም ሴቶች የወር አበባ በሚያዩበት ወቅት ንፁህ አይደሉም ተብሎ ስለሚታመን እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በጽሁፋቸው የማጠቃለያ ክፍል ውስጥም በህንድ ባህል መሰረት የወር አበባ ከሃይማኖትም ሆነ ከባህል አንፃር ንፁህ ካለመሆን ጋር የሚያያዝ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በማስከተልም በተጠኚው አካባቢ የወር አበባ ላይ ባሉ ሴቶች ላይ ጎልተው ከሚታዩ ማህበረ - ባህላዊ ክልከላዎች መካከል ወደ ሃይማኖታዊ ተቋማትና ስርዓተ ክንውን

ወደሚፈፀምባቸው የክብረ በዓላት ቦታዎች ከመሄድ የሚደረጉ ክልከላዎች ዋነኞቹ እንደሆኑ በመጥቀስ ጽሁፋቸውን ቋጭተዋል፡፡

Kuzma et al. (*2013*) "Food taboos and traditional customs among pregnant women in Papua New Guinea: Missed opportunity for Education in antenatal clinics" *በሚል ርዕስ በጋራ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናታቸው ዋና ዓላማ ከእርግዝና ጋር በተያያዘ የሚከለከሉ ባህላዊ ምግቦችን ምንነትና የሚከለከሉባቸውን ምክንያቶች መተንተንና ሰንዶ ማስቀመጥ ነው፡፡ ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስም ከሶስት የተለያዩ ጎሳዎች የተውጣጡ 176 በእርግዝና ላይ ያሉ ሴቶችን በመጠቀም መረጃ ሰብስበዋል፡፡*

*በትንተናቸው ውስጥም ከሰበሰቧቸው የምግብ ነውሮች መካከል በስፋት የሚገኙት በፕሮቲን የበለፀጉ ምግቦች እንደሆኑ አንስተዋል፡፡ እነዚህ አይነት ምግቦች ነውር የሆኑበት ምክንያትም ማህበረሰቡ በፕሮቲን የበለፀጉ ምግቦች ፅንስ ስለሚያፋፉ በእርግዝና ላይ ያሉ ሴቶች ቢመገቧቸው በወሊድ ጊዜ ይቸገራሉ፣ ክልከላዎችን በመጣሳቸውም ያልተስተካከለ ቅርፅ ያላቸውና በሽተኛ የሆኑ ልጆችን ይወልዳሉ የሚል አስተሳሰብ ስላለ እንደሆነ አንስተዋል፡፡ በእርግዝና ላይ ያሉ ሴቶች ከምግብ ክልከላዎች በተጨማሪ ለሌሎች ልማዳዊ ድርጊቶችም የተጋለጡ እንደሆኑ አንስተዋል፡፡ በማሳያነትም በአካባቢያቸው ሰው ሲሞት የሟች ቤተሰቦችና ሌሎች ለማስተዛዘኛ የሚያመጡትን ምግብ መብላት እንደማይችሉና የዚህም ምክንያቱ  ለፅንሱ ጤንነት አይበጅም የሚል እምነት ያለ በመሆኑ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ወንድ ልጅ በእርግዝና ላይ ባሉ ሴቶች ቤት ውስጥ ገብቶ ምግብ መመገብ እንደማይችልና የዚህም ዋናው ምክንያት ይሄን ያደረገ ወንድ በግብረ ስጋ ግንኙነት ህይወቱ ደካማ ይሆናል (ብልቱ ይሞትበታል) ተብሎ ስለሚታመን እንደሆነ አንስተዋል፡፡*

*ከትንተና ውጤታቸው በመነሳትም ከእርግዝና ጋር ለተያያዙ የምግብ ክልከላዎች መኖር ዋነኛው ምክንያት የምግብ ክልከላዎችንና ሌሎች ልማዳዊ ድርጊቶችን ጉዳት በሚመለከት የአካባቢው ማህበረሰብ ያለው ዕውቀት ዝቅተኛ በመሆኑ እንደሆነ አንስተዋል፡፡ ማህበረሰቡ ያለው ዕውቀት ዝቅተኛ የሆነውም በተጠኝዎቹ አካባቢዎች በመደበኛ ትምህርት ቤቶች እና በጤና ተቋማት ስለጉዳዩ በቂ ትምህርት ስለማይሰጥ  እንደሆነ ገልፀዋል፡፡* በጥናታቸው ማጠቃለያም ከፍ ሲል የተጠቀሱት አይነት የምግብ ነውሮችና ከዚሁ ጋር የተያያዙ ሌሎች ልማዳዊ ድርጊቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሱ እንደመጡ አንስተዋል፡፡ ሆኖም ሙሉ በሙሉ

ተወግደዋል ማለት እንደማይቻልና በዚሁ ምክንያትም በርካታ እናቶችና ህፃናት አሁንም ለበሽታና ለሞት እየተዳረጉ እንደሆነ በመጠቆም ጥናታቸውን ቋጭተዋል፡፡

Mhaka (2014) "Rituals and Taboos Related To Death As Repositories of Traditional African Philosophical Ideas: Evidence From The Karanga of Zimbabwe" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናታቸው ዋና ዓላማ በዚምባብዌ በሚገኙት የ"Karanga" ህዝቦች ውስጥ ከሞት ጋር በተያያዘ የሚተገበሩ ነውሮችን መመርመር ነው፡፡ ጥናታቸውን ከግብ ለማድረስም *በቀብር ስርዓተ ክንውን ላይ ቢያንስ ከአምስት ጊዜ በላይ የተሳተፉና እድሜያቸው ከ50 - 60 የሚሆኑ 20 ሰዎችን በመጠቀም መረጃ ሰብስበዋል፡፡*

*በጥናታቸው የመረጃ ትንተና ክፍል ውስጥም በተጠኝው አካባቢ፡-* አንድ ሰው ከሞተ በኃላ መንፈሱ እየመጣ ቤተሰቦቹን ይጎበኛል ተብሎ እንደሚታመንና ነገር ግን ከቀብር መልስ በቤተሰቦቹ ቤት እሱን ሊረብሸው የሚችል ከፍተኛ የሆነ የለቅሶም ሆነ የንግግር ድምፅ ከሰማ፣ ከመቀበሩ በፊት አስከሬኑ ካልታጠበ መንፈሱ ለጉብኝት አይመጣም ተብሎ እንደሚታሰብ አንስተዋል፡፡ አንድ ሰው ሲሞት አስከሬኑ ታጥቦ ካልተቀበረ ሞት ሳያጥቡ ወደ ቀበሩት ቤተሰቦቹና የአካባቢው ሰዎችም ይተላለፋል፣ የሟችን ገላ በማንኛውም መንገድ የነኩና የቀብር ጉድጓድ የቆፈሩ ወይም አፈሩን የነኩ ሰዎች ሁሉ የነኩበትን እጃቸውን ሳይታጠቡ ሰውን ቢጨብጡ ሞት ወደ ተጨበጡት ሰዎች ይተላለፋል ተብሎ እንደሚታመን አንስተዋል፡፡

በተጨማሪም ባጠኑት ማህበረሰብ ውስጥ ሰው ከሞተ በኋላም ህይወት አለው ተብሎ እንደሚታመን በጥናታቸው ማግኘታቸውን ገልፀዋል፡፡ በሌላ በኩል ግን ከሞት በኋላ ህይወት አለ የሚለው አስተሳሰብ የአፍሪካውያን ብቻ እንደሆነ የሚገልፁ መረጃዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል፡- Baloyi (ዓ.ም የለውም፣ ገፅ 236) የተባሉ አጥኝ ከሞት በኋላ ህይወት አለ የሚለውን የMhaka ሃሳብ ተቀብለው ነገር ግን ይሄ አስተሳሰብ የአፍሪካውያን እንደሆነ፣ በአውሮፓ አሜሪካውያን ዘንድ ያለው አስተሳሰብ ግን ከሞት በኃላ ህይወት የለም (የሰው ልጅ የህይወት ዑደት በፅንሰት ይጀመራል - በሞት ይቋጫል) የሚል እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

Mhaka *በተጠኝው አካባቢ ባህል መሰረት አንድ ሰው ቢሞትና ከጎረቤት ሌላ በጠና የታመመ ሰው ቢኖር ለሟቹ ማልቀስ የተከለከለ እንደሆነና የዚህም ዋናው ምክንያት ለሞተው ሰው ማልቀስ የታመመውን ሰውም ለሞት ይዳርጋል የሚል እምነት ስላለ እንደሆነ*

*አንስተዋል፡፡ ከቀብር ሳይመለሱ ወደ ቤት የሚይመለስ የፍየል ስጋ ሁሉም ለቀስተኛ መቅመስ እንዳለበትና የዚህም ዋናው ምክንያት ሞት ከለቀስተኛው ጋር ወደ ሰፈር አብሮ እንዳይመለስ ከሚል እምነት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ አንድ ህፃን ጥርስ ከማውጣቱ በፊት ቢሞት በደረቅ መሬት መቅበር ክልክል እንደሆነና የዚህም ዋናው ምክንያት ህፃኑ በደረቅ ቦታ ላይ ከተቀበረ የሟች እናት መካን ትሆናለች፣ በአካባቢውም ድርቅ ይከሰታል ተብሎ ስለሚታመን እንደሆነ አንስተዋል፡፡* ሰው ሲሞት የአካባቢው ሰዎች ለብዙ ቀናት (ምን ያህል ቀን እንደሆነ አልገለፁም) የእለት ተለት ስራቸውን ከማከናዎን እንደሚቆጠቡም ገልፀዋል፡፡ የእነዚህ ሁሉ ክልከላዎች *ዋናው ምክንያትም ሞትን ከመፍራት የሚመነጭ እንደሆነ አንስተዋል፡፡*

በጥናታቸው ማጠቃለያም በዚምባብዌ የሚገኙት የ“Karanga” ህዝቦች ነውሮች “Karanga”*ዎች* ስለዓለም ያላቸውን ፍልስፍናና ዕውቀት ለመረዳት ቁልፍ *መሳሪያዎች* ሆነው እንዳገኟቸው ይገልፃሉ፡፡ በመጨረሻም በሌሎች ተመሳሳይ የአፍሪካ አካባቢ ባህሎች ውስጥም እነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች በጥልቀት ቢመረመሩ፤ በተለያዩ ስርዓተ ትምህርቶች ውስጥም ተካተው በትምህርትነት እንዲሰጡ ቢደረግ የሚል አስተያየት በማቅረብ ጥናታቸውን ቋጭተዋል፡፡

*በውጭ ሃገራት ነውሮች ዙሪያ የተካሄዱትና ከዚህ በላይ በአጭሩ የተቃኙት ጥናቶች ነውሮችን በቀጥታ ስለሚያነሱ ከዚህ ጥናት ጋር የተወሰነ ተቀራራቢነት አላቸው፡፡* ከዚህ *በላይ የተቃኙት ሁሉም ጥናቶች በአንድ አንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ትኩረት ባደረጉ ነውሮች* ላይ (እንደቀረቡበት ቅደም ተከተል ከምግባር፣ ቋንቋ፣ ስራ፣ የወር አበባ፣ ምግብና ሞት ጋር የተያያዙ) የተካሄዱ ናቸው፡፡ *ይህ ጥናት ግን ከአንድ በላይ በሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ የሚፈጠሩና የሚተገበሩ ነውሮችን በጥልቀት የዳሰሰ ነው፡፡ ስለሆነም በተጠቀሱት ጥናቶችና በዚህ ጥናት መካከል ሰፊ የትኩረት ነጥብ ልዩነት ይታያል፡፡*

ከእነዚህ *መካከል* የእነ Stifel፣ የነKuzmaና የMhaka ጥናቶች ከሌሎች የበለጠ ለዚህ ጥናት ቅርበት አላቸው፡፡ ሆኖም እነዚህ ጥናቶችና የእኔ ጥናት ልዩነት የላቸውም ማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ፡- የእነ Stifel ጥናት የስራ ነውሮች አሉታዊ ሚና ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡ የእኔ ጥናት ግን አሉታዊ ጎናቸውን ብቻ ሳይሆን አወንታዊ ጎናቸውንም ይመለከታል፡፡ የነKuzma ጥናት ትኩረቱን ያደረገው ከእርግዝና ጋር በተያያዙ የምግብ ነውሮች ላይ ብቻ ነው፡፡ የእኔ ጥናት ግን ከእርግዝናም በተጨማሪ ከሌሎች ርዕሰ ጉዳዮች

ጋር የተያያዙ የምግብ ነውሮችን አዎንታዊና አሉታዊ ገፅታም በስፋት ይዳስሳል፡፡ የነKuzma ጥናት ከምግብ አይነቶች ሌላ ከምግብ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ነውሮች አልተመለከተም፡፡ የእኔ ጥናት ግን ከምግብ አይነቶችም በተጨማሪ ከምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ጋር የተያያዙ ነውሮችንም ይመለከታል፡፡ የMhaka ጥናትም ከሞት ጋር በተያያዘ ነውር የሚባሉ ነገሮችን ከመዘርዘር ባለፈ የነውሮች አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ሚና ምን እንደሆነ አያሳይም፡፡ የእኔ ጥናት ግን ከሞት ጋር የተያያዙ ነውሮችን አዎንታዊና አሉታዊ ሚና በዝርዝር ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ከፍ ሲል የቀረቡት ስራዎች ነውሮች ሊኖራቸው የሚችለውን አዎንታዊና አሉታዊ ሚና በግልፅ አያሳዩም፡፡ የእኔ ጥናት ግን የነውሮችን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ሚና በስፋት ይመለከታል፡፡ የተጠቀሱት ጥናቶችና ይህ ጥናት በተጠኝ ሃገር፣ ባህልና ቋንቋም ፈፅሞ የተራራቁ ናቸው፡፡ ስለሆነም በተጠቀሱት ጥናቶችና በእኔ ጥናት መካከል ሰፊ የዓላማና የትኩረት ነጥብ ልዩነት ይታያል፡፡

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተጠኝውን ርዕሰ ጉዳይ የሚመለከቱ ክለሳ ድርሳናት የተቃኙ ሲሆን፤ በሚቀጥለው ምዕራፍ ደግሞ የጥናቱ ስነ ዘዴ ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ስነዘዴ ፦

ይህ ምዕራፍ የጥናቱ አይነት፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴና አተገባበር፣ የመረጃ ምደባና አተናተን ሂደት ምን እንደሚመስል ማብራሪያ የቀረበበት ክፍል ነው፡፡

### 3.1 የጥናቱ አይነት

ከጥናት ዓላማ፣ ከሚሰበሰቡ የመረጃ አይነቶች፣ ከአተናተን ዘዴዎችና በአጠቃላይም ከምርምር አካሄድ አኳያ ጥናቱ አይነታዊ ገላጭ ምርምር ነው፡፡ ዓይነታዊ ገላጭ ምርምር አንድ ጉዳይ ተነስቶ ጉዳዩ ምን እንደሚመስል ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት አድርጎ በገለፃና በሃተታ መልክ በማቅረብ ስለነገሩ ምንነትና ትክክለኛ ባህሪ ሰፊና የዳበረ ማብራሪያ የሚሰጥበት ነው (Jupp, 2006፡ 248 - 249; Kothari, 2004 ፡ 3)፡፡ እንደ Jupp እና Kothari ይህ የምርምር ዓይነት ውስን አካባቢን፣ ውስን መረጃ ሰጭዎችንና ውስን መረጃዎችን በመውሰድ የሚጠናውን ርዕሰ ጉዳይ በስፋት፣ በጥልቀትና በዝርዝር የሚፈትሽ ነው፡፡ እንደ Vanderstoep እና Deirdre (2009፡8) ይህ የምርምር ዓይነት በቀላሉና በግልፅ ለማይታዩ የሰው ልጅ ስሜቶች፣ ልማዳዊ እምነቶችና እውቀቶች ማህበራዊና ባህላዊ ትርጉም መስጠት ላይ የሚያተኩር የምርምር አይነት ነው፡፡

ይህ ጥናት ተጠኝው ማህበረሰብ ስለ ነውሮችና ተያያዥ እምነታዊ ገለፃዎች ምንነትና ባህሪያት ያለውን ግንዛቤ፣ እምነት፣ እውቀት፣ ስነልቡና ወዘተ. በመቃኘት በገለፃ ስልት ለማቅረብ የሚሞክር ነው፡፡ የሰዎች አስተሳሰብ፣ እውቀት፣ እምነት ወዘተ. ያለው ደግሞ በሰዎች አዕምሮ ውስጥ ሲሆን፤ ነውሮች የዚህ አንድ ማሳያ ናቸው፡፡ በሰዎች አዕምሮ ውስጥ ያለ መረጃ ደግሞ ከራሳቸው ከሰዎቹ በሚገኝ መረጃ አማካይነት የሚገለጽና የሚተነተን እንጅ ይህን ያህል ነው ተብሎ በቁጥር የሚለካ ወይም የሚሰፈር አይደለም፡፡ ስለሆነም ጥናቱ በግልፅ ለማይታዩት የተጠኝው ማህበረሰብ ስሜቶች፣ ልማዳዊ እምነቶች፣ እውቀቶች ወዘተ. ማህበራዊና ባህላዊ ትርጉም መስጠት ላይ የሚያተኩር ስለሆነ ከአይነታዊ ገላጭ ምርምር የሚመደብ ነው፡፡

## 3.2 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴና አተገባበር

የፎክሎር ዋናው የመረጃ ምንጭ ከመስክ የሚገኝ መረጃ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ጥናቱን የተሟላ ለማድረግ ሲባል የዚህ ጥናት መረጃዎች የተሰበሰቡት ከካልዓይ እና ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ነው፡፡

### 3.2.1 የካልዓይ መረጃዎች አሰባሰብ ዘዴና አተገባበር

ካልዓይ መረጃዎች ከቤተ መፃሕፍትና ከመረጃ መረብ ከሚገኙ መፃሕፍት፣ መጽሄቶች፣ የጥናት ዘገባዎችና ክለሳ ድርሳናት፣ እንዲሁም ጥናቱ በሚካሄድበት አካባቢ ከሚገኙ አስረጅ ጽሁፎች፣ ቁሳቁሶች፣ ፎቶዎች፣ ካርታዎች ወዘተ. የሚገኙ መረጃዎች ናቸው፡፡ በዚሁ መሰረትም ከቤተ መጻሕፍትና ከመረጃ መረብ ፤ እንዲሁም በተጠኘው አካባቢ በተለያዩ ተቋማትና በግለሰቦች እጅ የሚገኙ የታተሙም ሆኑ ያልታተሙ ካልዓይ የጽሁፍ መረጃዎች ላይ ዳሰሳ ተደርጓል፡፡

በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተፃፉ የተለያዩ ጽሁፎችን በማንበብና በተለያዩ ጽሁፎች ላይ ተደጋግመው የተነሱ ሃሳቦችን በመለየት ለስራው የተሻሉ መረጃዎችን ለመውሰድ ጥረት ተደርጓል፡፡ ካልዓይ መረጃዎች የተሰበሰቡትም ሆነ በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት በዋናነት የግለ ገለፃ ስልትን በመጠቀም (ሃሳባቸውን አሳጥሮ ወይም ጨምቆና ጥናቱ ወደሚካሄድበት ቋንቋ በመተርጎም) ነው፡፡ ቀጥተኛ ጥቅስ አብዛኛውን ጊዜ የሚያገለግለው የቃላት ብያኔ ከአንድ ምንጭ ሲወሰድና ቀጥተኛ ጥቅሱ በራስ አባባል ከሚቀርበው የተሻለ ጠንካራ መልዕክት የሚያስተላልፍ ሲሆን ነው (ያለው፣ 2004፡ 83 - 92፤ Belay and Abdinasir, 2015፡ 137)፡፡ እንደነዚህ ሰዎች ቀጥተኛ ጥቅስ እየወሰዱ የጥቅስ ድርድር ማብዛት የስራውን አንባቢ ያሰለቻል፣ አጥኚው የሌሎችን ሃሳብ ተረድቶና ጨምቆ በራሱ መንገድ የመግለፅ አቅሙንም አያሳይም፡፡ ስለሆነም ሃሳቡን ብቻ በመውሰድ በራስ ቋንቋና አገላለፅ አሳጥሮ ወይም ጨምቆ ማቅረብ ተመራጭ ነው፡፡

በዚሁ መሰረትም በእንግሊዝኛ ቋንቋ በተፃፉ መረጃዎች ላይ የመረጃዎቹን መልዕክት ወይም ይዘት በማያዛባ አኳሃን ነፃ ትርጉም (Free translation) በማካሄድና ሃሳባቸውን በመጭመቅ ወደ አማርኛ ቋንቋ እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡ በአማርኛ ቋንቋ የተፃፉ መረጃዎችም በዚሁ መንገድ ሃሳባቸው ተጨምቆ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በዚህ ስልት መረጃዎች ሲወሰዱም የተወሰዱት መረጃዎች የተዓማኒነት ደረጃቸው ዝቅ እንዳይል በሚል መረጃው የተወሰደበት ጽሁፍ ርዕስ፣ የጸሃፊው ስም፣ የህትመት ዘመንና ሃሳቡ የተወሰደበት ገጽ እንዲሰፍር

ተደርጓል፡፡ ሆኖም ቀጥተኛ ጥቅስን መጠቀም በራስ አባባል ሃሳቡ አጥሮ ወይም ተጨምቆና ተተርጉሞ ከሚቀርበው የተሻለ መልዕክት ሊያስተላልፍ ይችላል ተብሎ በታመነበትና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተጽፎ በተገኘ ካልዓይ መረጃ ላይ ሃሳቡ በተገኘበት ቋንቋ እንዳለ እንዲሰፍር ተደርጎ የአማርኛ አቻ ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡

## 3.2.2 የቀዳማይ መረጃዎች አሰባሰብ ዘዴና አተገባበር

ይህ ርዕስ የመረጃ አሰባሰብ ሂደትን እና የመረጃ አሰባሰብ ዘዴና አተገባበርን የሚመለከቱ ንዑሳን ርዕሰ ጉዳዮች የቀረቡበት ነው፡፡

### 3.2.2.1 የመረጃ አሰባሰብ ሂደት

ቀዳማይ መረጃዎች ከሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ ባለቤቶች ጋር ተገናኝቶ በሚደረግ የመረጃ ስብሰባ አማካይነት የሚገኙ መረጃዎች ናቸው፡፡ በዚሁ መሰረትም ቀዳማይ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ወደተጠኝው አካባቢ ከመሄዴ በፊት ከክፍለ ትምህርቱ የትብብር ደብዳቤ አፃፍኩ፤ ለመረጃ አሰባሰብ ሂደቱ አጋዥ የሚሆኑ መሳሪያዎችንም አዘጋጀሁ፡፡ በማስከተልም ታህሳስ 10 ቀን 2008 ወደ ተጠኝው ወረዳ በመሄድ ከመስተዳድር ሃላፊዎች፣ ባለሙያዎችና የባህል ኤክስፐርቶች ጋር ተዋወቅኩ፡፡ ከአካባቢው ማህበረሰብና ባህል ጋር የተወሰነ ቅደመ ትውውቅ ስለነበረኝ አካባቢውን ለመተዋወቅ ብዙም ጊዜ ሳላጠፋ ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑና አካባቢውን መሰረት ያደረጉ መረጃዎችን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች በሰነድ ፍተሻ አማካይነት ለሶስት ተከታታይ ቀናት ያህል ሰበሰብኩ፡፡

ቁልፍ መረጃ አቀባዮችን፣ ተጠኝ ቀበሌዎችንና መረጃ አቀባይ ግለሰቦችን ወደ መምረጥ ስራ ከማለፌ በፊት ከወረዳው አስተዳደር ጽህፈት ቤት "ለሚመለከተው ሁሉ" የሚል የትብብር ደብዳቤ አጽፌ ያዝኩ፡፡ ይህን የትብብር ደብዳቤ ካገኜሁ በኋላ በወረዳው ውስጥ ባሉ ቀበሌዎች ሁሉ ያለምንም ችግር መንቀሳቀስ ቻልኩ፡፡ በማስከተልም የቀበሌ መረጣና መረጃ አቀባይ ግለሰቦች ምልመላ በማካሄድ የቅኝት ስራ ለማከናወን ሞከርኩ፡፡ ተጠኝ ቀበሌዎችንና መረጃ አቀባይ ግለሰቦችን ለመምረጥ ዓላማ ተኮር ናሙናን መሰረት አደረኩ፡፡ ዓላማ ተኮር ናሙና ከጥናቱ ዓላማ በመነሳት ተመራማሪው የጥናቴ ትኩረት የት አካባቢ ቢሆን ይሻላል? ከተጠኝው አካባቢስ የትኞቹ የማህበረሰብ ክፍሎችና መረጃ ሰጭዎች ቢሳተፉ አስፈላጊውን መረጃ ላገኝባቸው እችላለሁ? የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት ናሙናውን የሚመርጥበት ስልት ነው (Dawson, 2007:51) ፡፡ ስለሆነም በአካባቢው ረዘም ላለ ጊዜ የኖሩና ቀደም ሲልም በሌላ ጥናት የተዋወኳቸውን ሰዎችና በእነሱ አማካኝነት

ሌሎችንም በማፈላለግ አላማዬን አስተዋወቅኩ፡፡ በዚህም ስለ አካባቢው ባህልና ታሪክ ከሌሎች የተሻለ ዕውቀት አላቸው የሚባሉ ሰዎችንና የሚገኙባቸውን ከ10 በላይ የሚሆኑ ቀበሌዎች ጠቆሙኝ፡፡

የተጠቀሱት አይነት መረጃ ሰጭዎች የሚገኙባቸው ናቸው በተባሉ ቀበሌዎች ሁሉ በመዘዋወር አጠቃላይ የሆነ ዳሰሳና የሙከራ ጥያቄ አቀረብኩ፡፡ በየአካባቢዎቹ ካካሄድኩት ዳሰሳና ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡ ምላሾች በመነሳትም የወረዳውን አጠቃላይ ስዕል ሊያሳዩ የሚችሉ ሆነው ያገኘኋቸውን ቀበሌዎችና የሚጠናውን ርዕሰ ጉዳይ በሚመለከት የተሻለ እውቀት የነበራቸውን መረጃ ሰጭዎች የመምረጥ ስራ አከናወንኩ፡፡ በዚሁ መሰረትም አዲስ ዘመን፣ ይፋግ፣ ብራ አቦ፣ ሚካኤል ደብር፣ ብርኩቴ እና አግድ ቅርኛ የሚባሉ ቀበሌዎችን መረጥኩ፡፡ ስለሚጠናው ጉዳይ ከሌሎች የተሻለ መረጃ ካላቸው ሰዎች መካከልም ሙሉ ፈቃደኛ የሆኑትን በመለየት መረጃ በማቀበል ስራው እንዲሳተፉ አደረግኩ፡፡

በመረጃ ሰጭነት እድሜያቸው ከ18 - 80 አመት የሆኑ 30 ወንድና 20 ሴት በድምሩ 50 ሰዎች ተሳትፈዋል፡፡ የፎክሎር መረጃ በማንኛውም የዕድሜ ክልል ውስጥ ካሉ ሰዎች የሚገኝ ቢሆንም የተከማቸ ባህላዊ እውቀት የሚገኘው ግን በማህረሰቡ ውስጥ ካሉ በእድሜ የገፉት ዘንድ ነው (Patrick, B. 1992: 93) ፡፡ በዚሁ መነሻነትም በመረጃ ሰጭዎች የዕድሜ ምርጫ ወቅት በዕድሜ በገፉት ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ ከጠቅላላ መረጃ ሰጭዎቹ መካከልም 30 ያህሉ ዕድሜያቸው 60ና ከዚያ በላይ የሆኑ አረጋውያንና አረጋውያት እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

ለአንድ ጥናት የሚያስፈልገው የቁልፍ መረጃ አቀባይ ናሙና ብዛት ምን ያህል ሊሆን እንደሚገባው ቁርጥ ያለ መልስ የሚሰጥ መረጃ ባይገኝም ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ጠቅላላ መረጃ ሰጭዎች ውስጥ ስለሚጠናው ርዕሰ ጉዳይና በአጠቃላይም ስለ አካባቢው ባህልና ታሪክ ከሌሎች የተሻለ ዕውቀት ያላቸው 10 ወንዶችና 5 ሴቶች በድምሩ 15 ሰዎች በአውራ መረጃ አቀባይነት አገልግለዋል፡፡

በቃለ መጠይቅ ከተሳተፉት መካከል ስለርዕሰ ጉዳዩ በአንፃራዊነት ከሌሎች የተሻለ እውቀትና መረጃ ያላቸው 21 ሰዎች ተመርጠው በተተኳሪ የቡድን ውይይት ተሳትፈዋል፡፡ በአንድ ቡድን ውስጥ ሊካተት የሚችለው የታሳታፊ ብዛት ከ5 - 12 ሰው ሲሆን፣ ቁጥሩ

ከ12 ቢበልጥ ግን ውይይቱን ለመቆጣጠር ያስቸግራል (Bloor et al, 2001:26-28)፡፡ በዚሁ መነሻነትም ለተተኳሪ የቡድን ውይይት የተመረጡት ሰዎች እያንዳንዳቸው 7 አባላትን በያዙ ሶስት ቡድኖች እንዲዋቀሩ ተደርጓል፡፡ ለቡድን ውይይት የቀረቡትም በቡድን ውይይት ቢዳብሩ የመረጃውን የትክክለኛነት ደረጃ ከፍ ሊያደርጉ የሚችሉ የተወሰኑ ጥቅልና አወያይ የሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ናቸው፡፡

በመስክ መረጃ ስብሰባ ወቅት የተለያየ ማህበራዊ ደረጃ (Social status) ያላቸውን ሰዎች በመረጃ ሰጭነት ማሳተፍ የሚሰበሰበውን መረጃ የጥራትና ትክክለኛነት ደረጃ ከፍ ያደርገዋል በሚልም የመረጃ አቀባዮቹ ስብጥር እድሜን፣ ጾታን፣ የትምህርት ሁኔታን፣ የስራ ባህሪን ወዘተ. ያካተተ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

በመረጃ ሰጭዎች ናሙና አመራረጥ ወቅት ለዓላማ ተኮር ስልት በአጋዥነት ጠቋሚ ናሙና ስልት (Network or snowball sampling) ተግባራዊ ተደረገ፡፡ ጠቋሚ ናሙና የሚባለው - በሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ እውቀቱ ያለው አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን አለኝ የሚለውን መረጃ ከሰጠ በኋላ ተጨማሪ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ሌሎች ሰዎችን ወይም ቡድኖችን እንዲጠቁሙ በማድረግ መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ነው (ያለው፣ 2004፡132-134) ፡፡ በመሆኑም መረጃዎችን ከተለያዩ ሰዎች ለመሰብሰብ ሲባል ይህ ስልት ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

ይህን ጥናት ለማካሄድ ትልመ ጥናት (proposal) ለማዘጋጀት ወደ መስክ የተደረገውን ጉዞ ሳይጨምር አራት ዙር የመስክ ላይ ምልልስና የአምስት ወር ቆይታ የተደረገ ሲሆን፤ በእነዚህ ዙሮች በተደረገው የመስክ ጉዞ የተከናወኑ ተግባራት ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

የመጀመሪያው ዙር የመስክ ስራ ከታህሳስ 10 እስከ ጥር 20/ 2008 ባለው ጊዜ የተከናወነ ነው፡፡ በዚህ ዙር የተጠኘውን አካባቢ ዳራ የሚገልፁና ለተጠኘው ርዕሰ ጉዳይ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ለምሳሌ፡- የአካባቢውን ስነ ህዝብ፣ መልክዓምድር፣ የቆዳ ስፋት፣ አሰፋፈር፣ ሃይማኖት፣ ታሪክ፣ የአየር ጠባይ ወዘተ. የሚመለከቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች በሰነድ ፍተሻ አማካይነት ሰበሰብኩ፡፡ ለጥናቱ ወደ ተመረጡት ቀበሌዎች በመሄድና ለተመረጡ መረጃ ሰጭዎች ጥያቄዎቹን ለመመለስ፣ ላለመመለስ፣ ለማቋረጥ መብት እንዳላቸው በማረጋገጥና ቃለ መጠይቅ በማካሄድ በሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎችን የሚያጠናክሩ ተጨማሪ መረጃዎችን ሰበሰብኩ፡፡ ማህበረሰቡ በሚፈፅማቸው ስርዓተ ክንውኖችና እምነቶች (በለቅሶ፣ ገበያ፣ ድግስ ቦታዎች፤ ዛር በሚከወንባቸው ወዘተ. ቤቶች)

ተገኝቼ ጥልቅ ምልከታና ቃለ መጠይቅ አደረግኩ፡፡ በማስከተልም ማህበረሰቡ የሚያከናውናቸውን የዕለት ተለት የስራ ተግባራት በመቃኘት የማህበረሰቡን የስራ ባህልና ፍላጎት ደረጃ የሚጠቁሙ መረጃዎችን በምልከታና በቃለ መጠይቅ ሰበሰብኩ፡፡ ለተጠኚው አካባቢና ለተጠኚው ርዕሰ ጉዳይ  እንደ ዳራ ሆነው የሚያገለግሉ መረጃዎችን ከሰበሰብኩ በኋላም የጥናቱ ዋነኛ ትኩረት ወደሆነው "ነውር" በመሸጋገር ማህበረሰቡ በእሱ ዙሪያ ያለውን እውቀት፣ ልምድና ትግበራ በሚመለከት ከመረጃ ሰጭዎች ጋር ተወያየሁ፡፡

በተመረጡት ቀበሌዎች ውስጥ በዋነኛነት ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ተግባራት ካከናወንኩ በኋላ ከመረጃ ሰጭዎቹ ጋር ቀጣይ ቀጠሮ በመያዝ የመጀመሪያው ዙር የመረጃ ስብሰባ ስራ ተጠናቀቀ፡፡ ከመስክ መልስም የተሰበሰቡትን መረጃዎች የማጥራትና ግልፅነት የጎደላቸውን የመለየት ስራ ካከናወንኩ በኋላ ለሁለተኛው ዙር መረጃ ስብሰባ ወደ ቦታው ተመለስኩ፡፡

ሁለተኛው ዙር የመስክ ስራ የተከናወነው ከየካቲት 5 እስከ መጋቢት 10/ 2008 ባለው ጊዜ ነው፡፡ በዚህ የመረጃ ስብሰባ ወቅትም በመጀመሪያ ዙር ከተሰበሰቡት መረጃዎች መካከል ማብራሪያ በሚያስፈልጋቸው ላይ ተጨማሪ መረጃ በመፈለግ የማጥራት ስራ አከናወንኩ፡፡ በመቀጠልም በነውሮች ምንነት፣ ባህሪና ሚና ወዘተ. ዙሪያ ማህበረሰቡ ያለውን እሳቤ በሚመለከት በመጀመሪያው ዙር መረጃ ስብሰባ ወቅት የተሻለ ተሳትፎ ከነበራቸው አምስት መረጃ ሰጭዎች ጋር ጥልቅ ተናጠላዊ ቃለ መጠይቅ አካሄድኩ፡፡ ሰባት ሰው የተሳተፈበት አንድ የቡድን ውይይትም አደረኩ፡፡ በዚህም በተጠኚው ማህበረሰብ ውስጥ ተዘውታሪ የሆኑ ነውሮችን ምንነት፤ ከነውሮች ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ ልማዳዊ ድርጊቶችንና ነውር የመሆናቸውን ምክንያት የሚመለከቱ መረጃዎችን ሰበሰብኩ፡፡

በዋነኛነት ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ተግባራት በማከናወንና ከመረጃ ሰጭዎች ጋር ቀጣይ ቀጠሮ በመያዝ የሁለተኛው ዙር የመረጃ ስብሰባ ስራ ተጠናቀቀ፡፡ ከመስክ እንደተመለስኩም  የተሰበሰቡትን መረጃዎች የማጥራት፣ ግልፅነት የጎደላቸውን መረጃዎች የመለየትና የተሰበሰቡትን የነውር አይነቶች በርዕሰ ጉዳይ የመመደብ ስራ አከናወንኩ፡፡ በርዕሰ ጉዳይ ለመመደብና ለማደራጀት ስሞክርም አብዛኞቹ ነውሮች ከምግብ፣ ሞትና የግብርና ስራ ጋር የተገናኙ ሆነው ተገኙ፡፡ ይህም በአካባቢው ነውሮች ከሚዘወተሩባቸው ርዕሰ ጉዳዮች መካከል ምግብ፣ ሞትና የግብርና ስራ ዋና ዋናዎቹ ሊሆኑ ይችላሉ ወደሚል ሃሳብ እንዳመራ አደረገኝ፡፡ ይሄንን በቀጣይ ዙር በማደርገው የመረጃ ስብሰባ ላይ ማረጋገጥ

ከቻልኩ ትኩረቴ የተጠቀሱት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሊሆን ይገባል የሚል ሃሳብ ይዤ ለሶስተኛ ዙር ወደ መስክ ተመለስኩ፡፡

ሶስተኛው ዙር የመስክ ስራ የተከናወነው ከሚያዚያ 1 እስከ ግንቦት 30/ 2008 ባለው ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ዙርም ወደ ተጠኚው አካባቢ በመመለስና ከመረጃ ሰጭዎቹ ጋር በመወያየት በአካባቢው ነውሮች ከሚዘወተሩባቸው ርእሰ ጉዳዮች መካከል ምግብ፣ ሞትና የግብርና ስራ ዋነኞቹ እንደሆኑ አረጋገጥኩ፡፡

በዚሁ መሰረትም የመረጃ ስብሰባዬም ሆነ የመረጃ ትንተናዬ ትኩረት ከምግብ፣ ሞትና የግብርና ስራ ጋር በተያያዙ ነውሮች ላይ እንዲሆን ወሰንኩ፡፡ ለዚህ የመረጃ ስብሰባም በሁለተኛው ዙር መረጃ ስብሰባ ወቅት የተሻለ ተሳትፎ የነበራቸውን አምስት ሰዎችና እነዚህ መረጃ ሰጭዎች በጉዳዩ ዙሪያ ከኛ የተሻለ እውቀት አላቸው ያሏቸውን ሌሎች ተጨማሪ ሶስት መረጃ ሰጭዎች በመጠቀም ጥልቅ ተናጠላዊ ቃለ መጠይቅ አካሄድኩ፡፡ ሰባት አባላት የተሳተፉበት አንድ ተተኳሪ የቡድን ውይይትም አካሄድኩ፡፡ በዚህም የተጠቀሱትን ርዕሰ ጉዳዮች በሚመለከት በሁለተኛ ዙር የተሰበሰቡትን መረጃዎች የሚያጠናክሩ መረጃዎችን ሰበሰብኩ፡፡ በተጨማሪነትም ማህበረሰቡ ስለተጠቀሱት ርዕሰ ጉዳዮችና ከእነሱ ጋር ተያያዥ ስለሆኑ ነውሮች ያለውን አስተሳሰብ እና የማህበረሰቡን የነውሮች ማስቀጠያ መንገዶች የሚመለከቱ መረጃዎችን ሰብስቤ የሶስተኛ ዙር የመረጃ ስብሰባ ስራው ተጠናቀቀ፡፡

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መልኩ በሶስት ዙር የተሰበሰቡ መረጃዎችን እንደያዟቸው ጭብጦች የማደራጀትና የመተንተን ስራ አከናወንኩ፡፡ በማስከተልም ከተደራጁትና ከተተነተኑት መረጃዎች መከከል ከምግብና ሞት ጋር በተያያዘ በተሰበሰቡ፣ በተደራጁና በተተነተኑ መረጃዎች ላይ ተዘጋጅቼ ለደረጃ ማበልፀጊያ ተቋቁሞ ቀረብኩ፡፡

በደረጃ ማበልፀጊያ ተቋቁሞ ላይ የተሰጡኝን አስተያየቶች መሰረት በማድረግ ከጥር 1 እስከ ጥር 15/ 2009 የቆየ አራተኛ ዙር የመስክ ጉዙ አደረኩ፡፡ በዚህ የመስክ ጉዞ ወቅትም በሶስቱ ዙሮች የመረጃ ስብሰባ ወቅት ንቁ ተሳታፊ ከነበሩ መረጃ ሰጭዎች መካከል አስራ ሁለት ከሚሆኑት ጋር ጥልቅ ተናጠላዊ ቃለ መጠይቅ በማድረግ የመረጃ ዳግም ማጣራትና ባለፉት ዙሮች የተሰበሰቡ መረጃዎችን በተጨማሪ መረጃ የማጠናከር ስራ አከናወንኩ፡፡ ከመስክ መልስም በዚህ ዙር የተሰበሰቡትን መረጃዎች በቀደሙት ሶስት ዙሮች ከተሰበሰቡ

መረጃዎች ጋር የማዋሃድ ስራ ፈፀምኩ፡፡ በማስከተልም መረጃዎችን እንደየባህሪያቸው ትርጉም ሊሰጡ በሚችል አኳሃን አደራጅቼ ተረጎምኩ፡፡

ከፍ ሲል የተጠቀሱትንና መሰል መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ስራ ላይ የዋሉ ሲሆን፤ ምንነታቸውና የተመረጡበት ምክንያት ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

### 3.2.2.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና አተገባበር

በፎክሎር መረጃ ስብሰባ ላይ ከተለመዱት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መካከል ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ዋነኞቹ ናቸው (Mouton and Hendrik 1988፡91; Rugg, 2006: 100)፡፡ ይሁን እንጅ ሁሉም የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች የየራሳቸው የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎን ስላላቸው በአንዱ ዘዴ የተገኘውን መረጃ በሌላኛው ዘዴ ማመሳከር ተገቢ እንደሆነ እነዚሁ ምሁራን ይመክራሉ፡፡

በዚሁ መነሻነትም ከአንድ በላይ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶችን በመጠቀምና በአንዱ ስልት የተገኘውን መረጃ በሌላኛው ስልት በማረጋገጥ የጥናቱን ውጤታማነት ከፍ ለማድረግ ሲባል ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ሁሉም የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች በዚህ ጥናት ውስጥ ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

**ምልከታ**፦ ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መረጃ ሰብሳቢው ከሚጠናው ህዝብ ጋር አብሮ በመሆንና፣ በሚከውናቸው ድርጊቶች ውስጥም በመሳተፍ መረጃ ሰጭዎቹ የሚያደርጉትንና የሚናገሩትን ነገር፤ የሚያሳዩትን ስሜትና ባህሪ በቅርበት ሆኖ እያየና እየሰማ በመዘገብ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው (Goldstein,1964: 77; O'reilly, 2012: 84)፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ በጋራም ሆነ በተናጠል ባከናወናቸው ከአስር በላይ የአመጋገብ ስርዓቶች እና በፈፀማቸው ከአምስት በላይ የለቅሶ ስርዓት ክንውኖች ላይ በመገኘት ተሳትፏዊ ምልከታ አድርጌያለሁ፡፡ ማህበረሰቡ በሚከውናቸው የግብርና ስራዎች ለምሳሌ፦ በእርሻ፣ በአጨዳ፣ በውቂያና በበራይ ወዘተ. ስራዎች ላይ ስለሚፈፅሟቸው ልማዶች በአካል ተገኝቼ ተመልክቻለሁ፡፡ ማህበረሰቡ ልማዳዊ እምነቱን በሚፈፅምባቸው ወንዞች፣ ተራሮችና ሜዳዎች ላይ በመገኘት የሚፈፅማቸውን ልማዳዊ ድርጊቶች ተመልክቻለሁ፡፡

ሰዎች ሲናገሩ፣ ሲያደርጉና ሲያከናውኑ ሃሳባቸው፣ እምነታቸው፣ አመለካከታቸውና ጠባያቸው ስለሚገለፅ ምልከታው ጥሩ የመረጃ ምንጭ ሆኖ አገልግሎኛል፡፡ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች እንዳይረሱም በአጭር የጽሁፍ ማስታወሻ እንዲያዙ ተደርጓል፡፡

**ቃለ መጠይቅ ፦** ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በሚፈለገው መረጃ ዙሪያ እውቀት ካለው ሰው ጋር ፊት ለፊት ተገናኝቶ በሚካሄድ ጥያቄና መልስ መረጃ የሚሰበሰብበት ስልት ነው (Julia, 2008: 208)፡፡ የፎክሎር ጥናት በባህሪው የጽሁፍ መጠይቅ በትኖ በሚገኝ መረጃ ላይ ተመስርቶ የሚከናወን አይደለም፡፡ መረጃ ሰብሳቢው ከመረጃ ሰጭዎች ጋር በአካል በመገኘት መረጃ ሰጭዎቹ ከሚሰጡት መረጃ በተጨማሪ ያላቸውን ስሜት፣ አገላለጽ፣ የአካል እንቅስቃሴ ወዘተ. ሁሉ መከታተልን የሚጠይቅ ነው (Schoemaker, 1990፡6) ፡፡

ይህ ጥናት ከመረጃ ሰጭዎች ዘንድ በአካል በመገኘት መረጃ ሰጭዎች ስለ ነውሮች ምንነትና ባህሪ ያላቸውን ፍልስፍና የሚመረምር ነው፡፡ ስለሆነም በሚጠናው አካባቢ ተገኝቶ መረጃ ሰጭዎቹ ምን አሉ? ምን አደረጉ? የሚለውን በመከታተል መረጃ መሰብሰብን የሚጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ያልተደራጀ (unstructured) ቃለ መጠይቅ ዋነኛው የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መረጃ ሰጭዎች ስለሚጠናው ነገር ያላቸውን አስተያየት፣ አመለካከት፣ ዝንባሌ ወዘተ. በነፃነት እንዲገልፁ እድል የሚሰጥ ስለሆነ በርካታና ጥልቅ መረጃን ለመሰብሰብ ያስችላል (Goldstein, 1964: 108-109)፡፡

ያልተደራጀ ቃለ መጠይቅ ከሚባሉት መካከል ጥልቅ ቃለ መጠይቅ (In-depth interview) አንዱ ነው (Marvasti, 2003: 21) ፡፡ እንደ Marvasti ጥልቅ ቃለ መጠይቅ ተጠያቂዎቹ ስለአንድ ነገር ያላቸውን የውስጥ ዝንባሌ፣ አመለካከት፣ አረዳድና አተያይ፣ በጥቅሉም ስለራሳቸው ወይም ስለአንድ ነገር ያላቸውን ድብቅና ውስጣዊ ስሜት በጥልቀት ለመመርመር ወይም “to gain hidden perceptions & feelings of respondents” የሚያገዝ ስልት ነው፡፡ ይህ ጥናትም የነውሮችን መንስኤ ምክንያት በመመርመር የተጠኘውን ማህበረሰብ አመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ ልምድና ባህሪ የሚያጠና ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ ጉዳዩን በጥልቀትና በስፋት መመርመርን ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም ለጥናቱ የሚያስፈልጉት መረጃዎች ጥልቅ ቃለ መጠይቅ በማካሄድ የተሰበሰቡ ናቸው፡፡

መረጃዎች ሲሰበሰቡም ዲጅታል መቅረፀ ድምፅና የጽሁፍ ማስታዎሻ ስራ ላይ ውለዋል፡፡ ይህም ሆኖ ግን በቃለ መጠይቅ አማካይነት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ሁሉ ትክክል ናቸው ለማለት ያስቸግራል፡፡ ስለሆነም በቃል የተነገሩትን መረጃዎች በምልከታ በማረጋገጥ፤ ከአንድ ሰው የተገኘን መረጃ በተጨማሪ ሌላ መረጃ ሰጭ በማረጋገጥ፤ አንድን መረጃ በሚመለከት ለአንድ ሰው በተለያየ መንገድ በተደጋጋሚነት በመጠየቅ ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ ተሞክሯል፡፡

**ቡድን ተኮር ውይይት** ፦ ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በቃለ መጠይቅ ወቅት በበቂ ሁኔታ ላልተመለሱ ጉዳዮች ጥልቅና ዝርዝር መረጃ ለማግኘት የሚያግዝ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ነው (Bloor, 2001:11)፡፡ ይህ ስልት አንዱ መረጃ ሰጭ የሚረሳውንም ሆነ ስለጉዳዩ ካለው የእውቀት ማነስ በተነሳ ሊዘለው የሚችለውን ሃሳብ ሌላው እየሞላ የተሻለ መረጃ እንዲገኝ ለማድረግ፤ በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎችንና የተሰጡ ምላሾችን በድጋሚ ለማረጋገጥ የሚያስችል ነው፡፡ በዚሁ መሰረትም ሰዎች በቡድን እየተወያዩ የተሻለ መረጃ እንዲሰጡ ለማድረግ ሲባል ይህ ስልት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የጥናቱ የመረጃ አሰባሰብ ሂደት በቀረበበት ቀደም ባለው ክፍል እንደተጠቀሰው ቡድን ተኮር ውይይቱ ከሶስት ቡድኖች ጋር የተካሄደ ሲሆን፤ ቡድኖችም አንድ የወንድ፣ አንድ የሴት እና አንድ ሁለቱንም ጾታ ያካተቱ ናቸው፡፡ ከወንዶች ቡድን ጋር በነውር ምንነት፣ አይነትና የመከልከላቸው ምክንያቶች ዙሪያ፤ ከሴቶች ቡድን ጋር ለሴቶችና ህፃናት ነውር በሆኑ ጉዳዮችና ምክንያቶቻቸው ዙሪያ ውይይት ተካሂዷል፡፡ ሁለቱንም ፆታ ካካተተው ቡድን ጋር ደግሞ ከነውሮች ጋር በተያያዙ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ እነሱን መጣስ ሊያስከትል በሚችለው ቅጣትና በነውሮች ሚና ዙሪያ ሰፊ ውይይት ተደርጓል፡፡ በሶስቱም ቡድኖች ውስጥ የተካሄዱ ውይይቶች በመቅረፀ ድምፅና በአጭር የጽሁፍ ማስታወሻ አጋዥነት ተከናውነዋል፡፡

በአጠቃላይ ከመስክ የተገኙ ቀዳማይ መረጃዎች ከዚህ በላይ በተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና በሌሎች አጋዥ መሳሪያዎች (መቅረፀ ድምፅ፣ ማስታወሻ ደብተር) አማካይነት የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ በመቅረፀ ድምጽ አጋዥነት የተወሰዱ የቃል መረጃዎች ወደ ጽሁፍ በሚገለበጡበትና በሚደራጁበት ጊዜ ሃሳባቸውን አሳጥሮ በማቅረብ፤ በጽሁፍ ማስታወሻ በሚወሰድበት ጊዜም የተነገረውን ሁሉ ቃል በቃል ሳይሆን ሃሳቡን በማያዛባ መንገድ አጭር ማስታዎሻ በመውሰድ የተከናወኑ ናቸው፡፡ በመሆኑም መረጃዎቹ ወደጥናቱ

ጽሁፍ ውስጥ የተካተቱት በዋናነት የግለ ገለፃ ስልትን በመጠቀም (ሃሳባቸውን በማሳጠር ወይም በመጭመቅ) ነው፡፡ በዚህ መንገድ የተገኙ መረጃዎችን መረጃው የተሰበሰበበትን ቀንና ቦታ፣ እንዲሁም መረጃ ሰጭዎቹ ፈቃደኛ እስከሆኑ ድረስ ሙሉ ስምና አድራሻቸውን በማስፈር የመረጃውን ተዓማኒነት ከፍ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ ሆኖም የተናጋሪዎቹ ቀጥተኛ አገላለፅ በራስ አገላለፅ ከሚቀርበው የተሻለ መልዕክት ሊያስተላልፍ ይችላል ተብሎ በታመነበት ቦታ ላይ የመረጃ ሰጭዎቹ ሃሳብ እንዳለ ተወስዷል፡፡

የዚህ ጥናት መረጃዎች የተሰበሰቡት አርቲፊሻል አውድን መሰረት ባደረገ መልኩ ነው፡፡ አርቲፊሻል አውድ ፦ አንድ መረጃ ከተፈጥሯዊ አውዱ ውጭ ማንኛውም አቀባይ በተገኘበት ጊዜና ቦታ የሚሰበሰብበት አውድ ነው (ፈቃደ፣ 1991፡ 123፤ Goldstein, 1964፡ 80-84) ፡፡ ይህ አውድ የተመረጠው በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛው ምክንያት ነውሮችን ለመሰብሰብ በዋነኛነት ሲከወኑ ከተፈጥሯዊ አውዳቸው ማየትን የግድ የሚሉ አለመሆናቸው ነው፡፡ ሁለተኛውና ዋናው ምክንያት ግን እነሱን ከተፈጥሯዊ አውዳቸው ለመሰብሰብ ቢታሰብም የሚከወኑበትን ትክክለኛ ወቅትና አጋጣሚ ማወቅን የሚጠይቁ መሆናቸው ነው፡፡ ልማዳዊ እምነትና ከእሱ የሚመደቡት ነውሮች ማህበረሰቡ በማንኛውም ጊዜ፣ ቦታና ሰዓት የሚጠቀምባቸው ናቸው (Schoemaker, 1990፡ 51) ፡፡ እንደ Schoemaker "… እምነቶች ያሉት የሰዎች አዕምሮ ውስጥ" ወይም "… Beliefs exist only in peoples' head" ነው ። ስለሆነም እነሱን ከተፈጥሯዊ አውዳቸው ማጥናት አስቸጋሪ ነው፡፡

በመሆኑም ነውሮች በዋነኛነት ሁኔታው ሲፈቅድ በተገኘው አጋጣሚ (ጊዜ፣ ቦታና ሰዓት) የሚከወኑ እንጅ ቀጠሮ ተይዞላቸው የሚቀርቡ አይደሉም፡፡ ስለሆነም ተፈጥሯዊ አውድን ተጠቅሞ መረጃ ለመሰብሰብ ለጥናቱ የተመደበው ጊዜና የገንዘብ ሁኔታም የሚፈቅድ አይሆንም፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጥናት የሚሆኑ የመስክ መረጃዎች የተሰበሰቡት ከተገኘው መረጃ ሰጭ መረጃን ለመሰብሰብ የሚያስችለውን አርቲፊሻል አውድ መሰረት በማድረግ ነው፡፡

## 3.3 የመረጃና ውጤት አተናተንና አተረጓጎም ሂደት

ይህ ጥናት አይነታዊ እንደመሆኑ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት የተሰበሰቡትን መረጃዎች የመላሾችን ምክንያት ጨምቆና በጭብጥ ከፋፍሎ በመመርመርና በመተርጎም ስለነገሩ ፋይዳ፣ ጭብጥ፣ ፍሬ ነገር አስተያየት መስጠትን ይጠይቃል፡፡

በዚሁ መሰረትም የተሰበሰቡ መረጃዎች በመልክ በመልካቸው እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጅ ከመስክ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለማደራጀት ሲሞከር አንድ ነውር ከአንድ በላይ ይዘቶች ውስጥ ሊመደብ የሚችልበት አጋጣሚ ተስተውሏል፡፡ ለምሳሌ ያህል ፦ በእርግዝና ላይ ያለች ሴት በማህበረሰቡ ባህል መሰረት ለለቅሶ ቤት የተዘጋጀ ምግብን መመገብ አትችልም፡፡ በአካባቢው ሰው ሞቶ ከሆነ ሟች ከመቀበሩ በፊት የአካባቢው ሰው ማንኛውንም የግል ስራ ማከናወን አይችልም፡፡ በዚሁ መሰረትም የመጀመሪያውን ክልከላ ብንመለከት  ከምግብም ሆነ ከሞት ነውሮች ውስጥ ሊመደብ ይችላል፡፡ ሁለተኛው ክልከላም ከስራም ሆነ ከሞት ነውሮች ውስጥ ሊመደብ ይችላል፡፡ ይሁን እንጅ የመጀመሪያው ክልከላ የሚቀርበው ከምግብ ይልቅ ከሞት ጋር ለተያያዙ ነውሮች ነው፡፡ ሁለተኛው ክልከላም ከስራ ይልቅ ከሞት ጋር ለተያያዙ ነውሮች የቀረበ ነው፡፡

በመሆኑም ሊፈጠር የሚችለውን የይዘት መዛነቅ ለማቃለል ሲባል ከአንድ በላይ ይዘቶች ውስጥ ሊመደብ የሚችል አንድ ነውር ጎልቶ በሚታየው አንድ ይዘት ውስጥ ብቻ እንዲካተት ሆኗል፡፡ ይሁን እንጅ ለዚህ ጥናት ሲባል የተሰበሰቡት መረጃዎች ሊመደቡ የሚገባቸው በዚህ ጥናት ውስጥ በቀረቡበት መንገድ ብቻ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ሁሉንም በጋራ ሊያግባባ የሚችል የመመደቢያ መስፈርት ስለሌለ  የመረጃ ምደባ ጉዳይ በዋናነት በተገኘው መረጃና በአጥኝው እይታ የሚወሰን ነው፡፡

ለዚህ ጥናት ሲባል የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተን የተመረጠው ዓይነታዊ መረጃ ከሚተነተንባቸው ዘዴዎች መካከል አንዱ የሆነው የጭብጥ ትንተና ስልት ነው፡፡ የጭብጥ ትንተና፦ ሰዎች ስለአንድ ርዕሰ ጉዳይ ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል? ሰዎች በዛ ርዕሰ ጉዳይ የማመናቸው ምክንያት ምንድ ነው? ለምንስ ይጠቀሙበታል? ለሚሉ ጥያቄዎች አውዳዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ፍች ለመስጠት አመች የሆነ ዘዴ ነው (Vaismoradi et al, 2013፡ 400)፡፡ የጥናቱ ዋና አላማም ማህበረሰቡ ስለነውር ያለው ግንዛቤ ምን ይመስላል? በነውር ለምን ያምናል? ለምንስ ይጠቀምባቸዋል? ለሚሉ ጥያቄዎች አውዳዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ፍች መስጠት ስለሆነ የጭብጥ ትንተና ስልት ለዚህ ጥናት አመች ነው፡፡

የተሰበሰቡት መረጃዎች ትርጉም ሊሰጥ በሚችል መልኩ እንዲቀናበሩ ከተደረገ በኃላ ከየምድቡ ውስጥ ማሳያ የሚሆኑ መረጃዎች እየቀረቡ ጭብጭን መሰረት ያደረገ የመረጃ ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡ የመረጃ ትንተናውም የተሰበሰቡት መረጃዎች በየያዙት ጭብጥ

በምዕራፍ ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን፤ በየመረጃ ትንተና ምዕራፎቹ ውስጥ የተገኙ አበይት የጥናቱ ውጤቶችም በየምዕራፎቹ መጨረሻ ላይ ተጠቃለው እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡

በመጨረሻም በመረጃ ትንተናው በተገኙ የተወሰኑ የጥናቱ ውጤቶች ላይ የውጤቶችን ምንነት፣ ውጤቶቹ ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በሌሎች ከተገኙ የጥናት ውጤቶች ጋር ያላቸውን ተመሳስሎና ልዩነት በሚመለከት የራሴ ትንተና በክለሳ ድርሳን ክፍል ከተነሱ ሃሳቦች ጋር እየተናበበ የውጤት ትንተናና ትርጓሜ ተካሂዶባቸዋል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጥናቱ የተከተለው የአጠናን ዘዴ ምን እንደሚመስል ከዚህ በላይ የቀረበ ሲሆን፤ በሚቀጥለው ምዕራፍ ደግሞ የተጠኘው አካባቢያዊ ዳራ ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የጥናቱ ትኩረት አካባቢ ማስተዋወቂያ ፦

ይህ ምዕራፍ የተጠኘው አካባቢ አጭር ትውውቅና አጠቃላይ ዳራ የቀረበበት ነው፡፡

### 4.1 የሊቦ ከምከም ወረዳ አጭር ትውውቅ

ሊቦ ከምከም ወረዳ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ ከሚገኙ 11 ዞኖች መካከል አንዱ በሆነው በደቡብ ጎንደር ዞን ውስጥ ከሚገኙ 10 ወረዳዎች (የዞኖችን ዝርዝር በካርታ “ሀ” ፣ የወረዳዎችን ዝርዝር ደግሞ በካርታ “ለ” ውስጥ ይመልከቱ) አንዱ ነው፡፡

ወረዳው በሰሜን ከበለሳ ወረዳ፣ በደቡብ ከፎገራ ወረዳ፣ በምስራቅ ከእብናት ወረዳ እና በምዕራብ ከጣና ሃይቅና ከጎንደር ዙሪያ ወረዳ የሚዋሰን ሲሆን፤ በ29 የገጠርና በ5 የከተማ ቀበሌዎች (የቀበሌዎችን ዝርዝር በካርታ “ሐ” ውስጥ ይመልከቱ) የተዋቀረ ነው (የሊቦ ከምከም ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት፣ 2003፡2)፡፡

የሊቦ ከምከም ወረዳ አስተዳደር መቀመጫና ዋና ከተማ አዲስ ዘመን ትባላለች፡፡ ይህች ከተማ ከባህር ዳር ጎንደር የሚያልፈው የአስፓልት መንገድ ዳሯን ነክቷት የሚያልፍ ከተማ ናት፡፡ ከተማዋ ከአዲስ አበባ በ652፣ ከክልሉ ዋና ከተማ ከባህር ዳር በ80 እና ከዞኑ ዋና ከተማ ከደብረ ታቦር በ67 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡

አዲስ ዘመን ከተማ ጥር 21 ቀን 1942 በዘመኑ የበጌምድርና ሰሜን ጠቅላይ ገዥ በነበሩት በቢትወደድ አንዳርጋቸው መሳይ ተመስርታለች (የሊቦ ከምከም ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት፣ ጥቅምት 2000 ፡4)፡፡ ይህች ከተማ ከመመስረቷ በፊት የወረዳው ዋና ከተማ ጣራ ገዳም ነበረች፡፡ ጣራ ገዳም ከአዲስ ዘመን ከተማ በ12 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በጥቅጥቅ ደን ተሸፍና የምትገኝ ታሪካዊ ስፍራ ናት፡፡ ጣራ ገዳም በአሁኑ ወቅት በሊቦ ከምከም ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች መካከል አንዷ ናት፡፡ የአካባቢው የእድሜ ባለፀጋዎች እንደሚገልፁት ጣራ ገዳም የተፈጥሮ አቀማመጧ ለከተማ መስፋፋት አመች አለመሆኑ፣ በአካባቢው በቂ ውሃ አለመኖሩ፣ አካባቢው ሃይማኖታዊ ተቋማት የበዙበት ስለሆነ መነኮሳት መንፈሳዊ አገልግሎት ለመስጠት መቸገራቸው ለከተማዋ ወደ አዲስ ዘመን መቀየር ምክንያቶች ናቸው ፡፡

## 4.2 የሊቦ ከምከም ወረዳ አጠቃላይ ዳራ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የወረዳውን የህዝብ ሁኔታ፣ ቋንቋና ሃይማኖት፤ የአየር ጠባይና መልክዓምድራዊ ገፅታ፤ የኢኮኖሚና መሰረተ ልማት ሁኔታ፤ የዝምድና መፍጠሪያና የመረዳጃ መንገዶች፣ የቤተሰብ ማህበራዊ ሚናና የስርዓተ ፆታ ሁኔታ፣ ልማዳዊ እምነቶች እና የባህል ለውጥና መሻሻል የሚመለከቱ ጉዳዮች ተዳሰዋል፡፡

### 4.2.1 የህዝብ ሁኔታ፣ ቋንቋና ሃይማኖት

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን እ.ኤ.አ በ2007 ባካሄደው የቤቶችና ህዝብ ቆጠራ ውጤት መሰረት የወረዳው የህዝብ ብዛት 198,374 ሲሆን፤ ከዚህ ቁጥር ውስጥ 100,951 ወንዶች ፣ 97,423 ያህሉ ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ ከወረዳው ጠቅላላ የህዝብ ብዛት ውስጥ 22,050 የሚሆነው በከተማ የሚኖር ሲሆን፤ 176,324 ያህሉ ደግሞ በገጠር የሚኖር ነው፡፡ ሊቦ ከምከም በዋነኛነት የአማራ ህዝብ የሚኖርበት ወረዳ ሲሆን፤ በተወሰነ መልኩ ግን የነገዴ ማህበረሰብ አባላት፣ እንዲሁም የትግራይና የኦሮሞ ብሄር ተወላጆች ይኖሩበታል፡፡

ከሊቦ ከምከም ወረዳ ህዝብ መካከል 99.86 % ያህሉ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሲሆን፤ 0.09% ያህሉ የትግርኛ፣ 0.05 % ያህሉ ደግሞ የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው፡፡ በወረዳው ውስጥ የኦርቶዶክስ፣ እስልምናና ፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ህዝቦች የሚኖሩ ሲሆን፤ ከእነዚህ መካከል 98% ያህሉ የኦርቶዶክስ ክርስትና፣ 1.5 % ያህሉ የእስልምና፣ 0.5 % ያህሉ ደግሞ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡ በገጠር ከሚኖረውና የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ ከሆነው ህዝብ መካከል በደጋና ወይና ደጋ አካባቢዎች የሚኖረው ህዝብ በግል እምነቱ የጠበቀ ጽናት ያለው፣ ለመንፈሳዊ ህይወቱ ቅድሚያ የሚሰጥ፣ ፆምን የሚያዘወትርና በዚህ ወቅትም እራሱን ከተለያዩ ምግብና መጠጦች የሚያርቅ ነው፡፡ በቆላማው አካባቢዎች የሚኖረው ህዝብ ደግሞ በአንፃሩ አመጋገቡ ስጋዊ ፍላጎቱን በመጥቀም ላይ ያተኮረና ወደዘመናዊነት አስተሳሰብ የመቅረብ ባህል ያለው ነው (የሊቦ ከምከም ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት፣ ጥቅምት 2000 ፡4)፡፡

የወረዳው የህዝብ አሰፋፈር (በተለይም በገጠር ቀበሌዎች የሚኖረው የህብረተሰብ ክፍል) ሁኔታ በዋነኛነት ሙያንና የአኗኗር ልማድን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በመሆኑም ሊቦ ከምከም አርሶ አደሮችና የተለያዩ የጥበበ ዕድ  (የሸክላ፣ ብረት፣ ቆዳ፣ ሸማ) ባለሙያዎች ሳይቀላቀሉ እራሳቸውን ለይተው በአንድ አካባቢ ብቻ የሚሰፍሩበት ወረዳ ነው፡፡ ለምሳሌ

፦ አርሶ አደሮችና የጥበበ ዕድ ባለሙያዎች አንድን ቀበሌ በብዛት ተጋርተው ከሚኖሩባቸው መካከል "ብራ አቦ" የሚባል ቀበሌ ተጠቃሽ ሲሆን፤ የቀበሌው የተወሰነ አካል የአርሶ አደሩ ጎጥ እየተባለ ሲጠራ ሌላው የቀበሌው አካል ደግሞ የጥበበ ዕድ ባለሙያዎች ጎጥ እየተባለ ይጠራል፡፡ በአርሶ አደሩ ሰፈር የጥበበ ዕድ ባለሙያ የለም - በጥበበ ዕድ ባለሙያዎች ሰፈር አርሶ አደር የለም፡፡ የዚህ ደግሞ ዋናው ምክንያት አርሶ አደሩ የጥበበ ዕድ ባለሙያዎችን የመናቅና የማግለል የቆየ ልማድ ስላለው ነው (አቶ ገብረአብ ደሴ፣ ቃመ፣ ታህሳስ 20/ 2008)፡፡

የነገዴ ማህበረሰብ አባላትም በዚህ ወረዳ በተለይም 'አግድ ቅርኛ' በምትባል ቀበሌ ውስጥ የሚኖሩ ሲሆን፤ አሰፋፈራቸውም እንደ ጥበበ ዕድ ባለሙያዎቹ ሁሉ ራሱን በቻለ ጎጥ (ሰፈር) የተወሰነ ነው፡፡ የዚህም ዋናው ምክንያት ነገዴዎች ሌላው የአካባቢው ህብረተሰብ የማይመገባቸውን የባህር እንስሳት ይመገባሉ፤ ተባርከው ያልታረዱ ወይም በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች የሞቱ የቤት እንስሳትን ይበላሉ በሚል ማህበረሰቡ ስለሚያገላቸው ነው (አቶ ገብረአብ ደሴ፣ ቃመ፣ ታህሳስ 20/ 2008)፡፡

## 4.2.2 የአየር ጠባይና መልክዓምድራዊ ሁኔታ

እንደ ሊቦ ከምከም ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት (2003፡2) መረጃ የወረዳው የቆዳ ስፋት 1081.57 ስኩየር ኪሎ ሜትር ሲሆን፤ የህዝቡ የአሰፋፈር ጥግግትም በአንድ ኪሎ ሜትር 198.49 ሰው ይሆናል፡፡ የወረዳው መልክዓምድራዊ አቀማመጥ ከባህር ወለል በላይ ከ1800 - 22850 ሜትር ከፍታ አለው፡፡ መልክዓምድራዊ አቀማመጡም 42 % የሚሆነው ሜዳማ፣ 30 % የሚሆነው ወጣገባማ፣ 21 % የሚሆነው ተራራማ፣ 1% የሚሆነው ሸለቋማ የመሬት አቀማመጥ ያለው ሲሆን፤ 6% ያህሉ ደግሞ በውሃ የተሸፈነ ነው፡፡ የወረዳው የአየር ንብረት ደጋማ፣ ወይና ደጋማና ቆላማ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ 22 % ያህሉ ደጋማ፣ 73 % ያህሉ ወይና ደጋማ፣ 5 % ያህሉ ደግሞ ቆላማ የአየር ንብርት አለው፡፡ የወረዳው አማካኝ የሙቀት መጠን ከፍተኛው 27.9 ዲግሪ ሴንቲግሬድ፣ ዝቅተኛው ደግሞ 11.1 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ነው፡፡ የአካባቢው አማካኝ ዓመታዊ የዝናብ መጠንም ከ900 - 1400 ሚሊ ሜትር ይደርሳል፡፡

### 4.2.3 የኢኮኖሚና መሰረተ ልማት ሁኔታ

በወረዳው ገጠራማ አካባቢዎች የሚኖረው የህብረተሰብ ክፍል ዋነኛው መተዳደሪያው ግብርና ነው፡፡ በገጠር ከሚኖረው ህዝብ መካከል 1% የሚሆነው በተለያዩ የእደ ጥበብ ስራዎች (በሸክላ፣ ብረት፣ ቆዳ፣ ሽማ … ስራዎች) እና ዓሳ ማስገር  የሚተዳደር ሲሆን፤ 0.5% የሚሆነው ደግሞ በአነስተኛ የንግድ ስራዎች የሚተዳደር ነው ፡፡ በከተማ የሚኖረው ህዝብ ደግሞ በዋነኛነት በንግድ፣ በተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ተቀጥሮ በመስራት እና በቀን የጉልበት ስራዎች የሚተዳደር ነው፡፡ ቁጥራቸው በውል ባይታወቅም የነገዴ ማህበረሰብ አባላት ከፍ ሲል ከተገለፀው የገጠሩና የከተማው ህዝብ በተለየ ሁኔታ ኑሮአቸውን በጣና ሃይቅ ዳርቻ በማድረግና አሳ በማስገር ህይወታቸውን ይመራሉ፡፡

በዚህ ወረዳ እንደየአካባቢው ስነ ምህዳራዊ ሁኔታ የተለያዩ የብዕር፣ የአገዳ፣ የፍራፍሬና አትክልት ውጤቶች ይመረታሉ፡፡ ወረዳው በዋነኛነት የሚታወቀው ግን በሩዝ፣ ሽንኩርት፣ ቲማቲምና የቢራ ገብስ ምርቱ ነው፡፡ በወረዳው ውስጥ የሚኖረው አርሶ አደር በባህላዊ መንገድ የእንስሳት እርባታ ያከናውናል፡፡

በወረዳው ለኮንስትራክሽን አገልግሎት ዘርፍ የሚውል የአሸዋ ምርት፤ ለሸክላና ለጡብ ምርት የሚሆን የአፈር ክምችት ይገኛል፡፡ ለመስኖ አገልግሎት በመዋል የአካባቢውን ኢኮኖሚ ሊያሳድጉ የሚችሉ መለስተኛና ትልልቅ ወንዞች (ለምሳሌ ፦ ርብ፣ ሽኒ፣ ሳቫን፣ ዳንጉራ ወዘተ.) በወረዳው ውስጥ ይገኛሉ፡፡ በወረዳው ውስጥ ታሪካዊ የሆኑና የቱሪዝም መስህብ በመሆን ለአካባቢው ማህበረሰብ ኢኮኖሚ ጠቀሜታን ሊያስገኙ የሚችሉ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ  ቦታዎች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ከሆኑ የቱሪዝም መስህቦች መካከል ጣራ ገዳም ጥቅጥቅ ደን፣ አምባ ጥቅጥቅ ደን፣ ዋሻ እንድሪያስ ቤተ ክርስቲያን፣ ወይን ዋሻ ተክለሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ወዘተ. ይጠቀሳሉ፡፡ በእነዚህ ቦታዎች ውስጥም የተለያዩ ጥንታዊ ቅርሶች የሚገኙ ሲሆን፤ ከእነሱ መካከልም የነገስታት ስጦታዎች፣ ዘውዶችና የብራና መጽሃፎች ወዘተ. ይገኛሉ (የሊቦ ከምከም ወረዳ ማስታወቂያ ጽህፈት ቤት፣ 2001፣ 10 - 11)፡፡ ይሁን እንጅ እንደ ወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት (ጥቅምት 2000 ፡3) መረጃ በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ህዝቦች እነዚህን ሃብቶች በአግባቡ አልተጠቀሙባቸውም፡፡ የገጠሩ ህብረተሰብ አሁንም ድረስ የባህላዊ አስተራረስና

የአኗኗር ዘዴን የሚከተልና ወደ ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴ ብዙም ዘልቆ ያልገባ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት አብዛኛው የወረዳዋ ህዝብ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

በወረዳው ውስጥ 5 አፀደ ህፃናት፣ 40 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት፣ 60 የመጀመሪያ ደረጃ፣ 2 የሁለተኛ ደረጃ፣ 1 የመሰናዶ፣ 1 የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኮሌጅ በድምሩ 109 የሚሆኑ የትምህርት ተቋማት ይገኛሉ፡፡ በወረዳው ውስጥ 1 የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል፣ 8 ጤና ጣቢያዎች፣ 36 ጤና ኬላዎች በድምሩ 45 የሚሆኑ የጤና ተቋማት ይገኛሉ፡፡ በወረዳው ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ ቀበሌዎች ከወረዳው ዋና ከተማ (አዲስ ዘመን)ና እርስበርሳቸው የሚያገናኝ የጠጠር መንገድ አላቸው፡፡ በወረዳው ውስጥ ካሉት ቀበሌዎች መካከል 26 የሚሆኑት የመስመር አልባ ስልክ ተጠቃሚዎች ሲሆኑ፤ 3 የከተማና 8 የገጠር ቀበሌዎች ደግሞ የኤሌክትሪክ መብራት ሃይል ተጠቃሚ ናቸው (የሊቦ ከምከም ወረዳ ማስታወቂያ ጽህፈት ቤት፣ 2001፣ 12)፡፡

## 4.2.4 የዝምድና መፍጠሪያና መረዳጃ ተቋማት

የሊቦ ከምከም ማህበረሰብ የእርስ በርስ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቱን ለማጠናከር ዝምድና የሚፈጥርባቸውና የሚተጋገዝባቸው የተለያዩ ባህላዊ ተቋማት አሉት፡፡ ማህበረሰቡ ማህበራዊ ግንኙነትን ከሚፈጥርባቸው መንገዶች መካከል አንዱና ዋነኛው ዝምድና ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ዝምድና የሚፈጠረው በዋነኛነት በጋብቻና በሃይማኖት ስነ ስርዓት በሚበጅ ዝምድና አማካይነት ነው፡፡ ማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነትን የሚፈጥርባቸው የተለያዩ ሃገር በቀል የሆኑ የመተጋገዣ ተቋማት አሉት፡፡ ከእነዚህም መካከል እድር፣ እቁብ፣ ወንፈል (ደቦም ይሉታል)፣ ሰንበቴ እና ማህበር ወዘተ. ይጠቀሳሉ፡፡ ማህበረሰቡ ዝምድና ከሚፈጥርባቸውና እርስበርሱ ከሚደጋገፍባቸው ሃገር በቀል ማህበረ ኦኮኖሚያዊ ተቋማት መካከል ጋብቻ፣ እድር፣ እቁብና ወንፈል ከዚህ በታች በአጭሩ ተቃኝተዋል፡፡

በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ ዋነኛው የማህበራዊ ግንኙነት መመስረቻ መንገድ ጋብቻ ነው፡፡ ስለሆነም በአካባቢው ጋብቻ እንዲሁ በዘፈቀደ (ተጋቢዎቹ ስለተፈላለጉ ብቻ) የሚከናወን አይደለም፡፡ ማህበረሰቡ ወግ ልማዱን መሰረት አድርጎ በተቀበላቸው የክልከላና የፈቀዳ ህጎች አማካይነት የሚከናወን ነው፡፡ እነዚህ የክልከላም ሆኑ የፈቀዳ ህጎች በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ ከወላጆች ወደ ልጆች እየተሸጋገሩ የመጡ የሚከበሩና የማይጣሱ ህጎች ናቸው፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ጋብቻ ለመመስረት የማያበቁ የተለያዩ ጉዳዮች አሉ፡፡ አንደኛው ለጋብቻ የማያበቃው ጉዳይ በዘመዳሞች ወይም አንድ የዘር ሃረግ ባላቸው ሰዎች መካከል የሚፈፀም ጋብቻ ነው፡፡ በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ ከሰባት ቤት በታች የሆነ የስጋ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል ጋብቻ አይፈፀምም፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ከሰባት ቤት በታች የሚደረግ ጋብቻ ነውር ነው፡፡ በመሆኑም ይሄን ነውር የጣሰ ጋብቻ በዚህ መንገድ የሚወለዱ ልጆች ማየት ወይም መስማት የተሳናቸው ወይም ሌላ የአካልና የአእምሮ ጉድለት ያላቸው ይሆናሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ይሄ ብቻም ሳይሆን ይሄን ህግ ጥሶ ጋብቻ የፈፀመ ሁሉ ከተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶችም ይገለላል፡፡

በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ ለጋብቻ የማያበቃው ሌላኛው ጉዳይ የስራ ባህሪያቸው የተለያየ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚፈፀም ጋብቻ ነው፡፡ ማህበረሰቡ በስራ ባህሪው ገበሬ፣ ነጋዴ፣ የመንግስት ሰራተኛ፣ የጥበበ ዕድ ባለሙያ/ባለእጅ ወዘተ. በሚል የተከፋፈለ ነው፡፡ ገበሬው፣ ነጋዴው፣ የመንግስት ሰራተኛው ወዘተ. ከጥበበ ዕድ ባለሙያዎች ጋር ጋብቻን አይፈፅምም፡፡ ምክንያቱም የአካባቢው ማህበረሰብ ከቀደምቶቹ በወረሰው ባህል መሰረት እነዚህን የማህበረሰብ ክፍሎች ያገላቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ከእነሱ ጋር መጋባት ነውር በመሆኑ የጥበበ ዕድ ባለሙያዎች ጋብቻ የሚፈፅሙት ከእነሱ ተመሳሳይ የስራ ባህሪ ካላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር ብቻ ነው፡፡

በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ ለጋብቻ የማያበቃው ሌላኛው ጉዳይ የጤንነት ሁኔታ ነው፡፡ ማህበረሰቡ እንደ ቁምጥና[6]፣ ዝሆኔ[7] የመሳሰሉ በሽታዎች በዘር የሚተላለፉ ናቸው ብሎ ያምናል፡፡ በመሆኑም በተጠቀሱት አይነት በሽታዎች ተጠቂ የሆኑ ሰዎች ከሌሎች ጋር ጋብቻ የመፈፀም እድላቸው በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ አንዳንድ መረጃ ሰጭዎች እንደሚናገሩት እነዚህ አይነት ሰዎች ለጋብቻ የማይፈለጉት በተላላፊ በሽታ ተይዘዋል ተብሎ በመታመኑ ብቻ አይደለም፡፡ ማህበረሰቡ እነዚህን ሰዎች ቡዳ፣ አጥንተ ሰባራ ይላቸዋል፡፡ ስለዚህ በተጠቀሱት ምክንያቶች መነሻነት ማህበረሰቡ ከእነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር ጋብቻ አይፈፅምም፡፡

Mossa (2006፡54) ም በዚሁ ማህበረሰብ ዙሪያ ባደረጉት አንድ ጥናት ላይ እነዚህ አይነት ሰዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ለጋብቻ ስለማይመረጡ እስከህይወታቸው ፍፃሜ ድረስ

---

[6] መላ ሰውነትን የሚያቆስል፣ የሚቆራርጥ ደዌ ስጋ፡፡

[7] እግር የሚያሳብጥ በሽታ ነው ፡፡

የማያገቡበት አጋጣሚ እንዳለ አንስተዋል፡፡ እንደሳቸው በማህበረሰቡ አጠራር ባሪያና ቡዳ ተብለው የሚፈረጁ ሰዎችም በማህበረሰቡ ውስጥ ለጋብቻ አይፈለጉም፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ ጋብቻ ለመፈፀም "ዘር"፣ "የጤና ሁኔታ" እና "ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ" ዋነኞቹ መስፈርቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም ማህበረሰቡ በደሙ፣ በአጥንቱ፣ በኢኮኖሚያዊ አቅሙ አቻዬ ነው ከሚለው ጋር ጋብቻ ይመሰርታል፡፡ አቻዬ አይደለም ከሚለው ጋር ደግሞ የጋብቻውን ጉዳይ ወደጎን በመተው ሌላውን ማህበራዊ ህይዎት እየተጋራ ይኖራል፡፡ ይሄ ሲባል ግን ባህል በጊዜና በሁኔታዎች አስገዳጅነት የመለዋወጥ ባህሪ ስላለው ከዚህ በላይ የተነሱት የጋባቻ መስፈርቶች ሁሉ ዘላለማዊ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም አንዳንድ መረጃ አቀባዮች እንደነገሩኝ ከፍ ሲል የተጠቀሱት አንዳንዶቹ የጋብቻ መስፈርቶች በጊዜ ሂደት እየተጣሱ ወይም ተቀባይነታቸው እየቀነሰ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- አሁን አሁን ዝምድናን እስከ 7 ቤት ሳይጠብቁ የመጋባት፣ የማህበረ ኢኮኖሚያዊ ደረጃቸው አቻ ባልሆኑ ሰዎች መካከልም ጋብቻ የመፈፀም ሁኔታ እየታየ ነው (ወ/ሮ ሃይማኖት አስማረ፣ ቃመ፣ ጥር 15/ 2008)፡፡ እንደኚህ መረጃ ሰጭ እንዲህ አይነት ጋብቻ የሚፈጽሙት ቁጥራቸው በጣም ውስን የሆኑ ሰዎች ሲሆኑ፤ አሁንም ድረስ ግን የማህበረሰቡን ህግ ሽሮ ጋብቻ የሚፈፅምን ሰው የአካባቢው ማህበረሰብ (ቤተሰብን ጨምሮ) የማግለል ሁኔታ ይስተዋላል፡፡

ማህበረሰቡ ማህበራዊ ግንኙነቱን ይበልጥ ለማጠናከር ሌሎች ተጨማሪ ማህበረ ኦኮኖሚያዊ ተቋማትንም ይፈጥራል፡፡ በሚፈጥራቸው ማህበረ ኦኮኖሚያዊ ተቋማት አማካይነትም በጋራ እየተሰባሰበ ይደጋገፋል፣ ኢኮኖሚያዊ አቅሙንም ያጠናክራል፡፡ ማህበረሰቡ ማህበራዊ ግንኙነቱን ከሚያጠናክርባቸውና እርስ በርሱ ከሚደጋገፍባቸው ሃገር በቀል ተቋማት መካከል አንዱ እድር ነው፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ የእድር መሰረታዊ ተግባሩ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ሞት ባጋጠመ ጊዜ የሟችን ቤተሰብ በጉልበት፣ በገንዘብና በስነ ልቡና መደገፍ ነው፡፡ የእድር አባል ለመሆን በአንድ ሰፈር ከመኖርና የእድሩን ደንብ ከመፈፀም ያለፈ ግዴታ ወይም የሚጠየቅ መስፈርት የለም፡፡ አንድ ግለሰብ ማንኛውም ሃይማኖት፣ ሙያ፣ ቋንቋና ብሄረሰባዊ ማንነት ያለው ቢሆን ለእድሩ ደንብ እስከተገዛ ድረስ አባል ከመሆን የሚያግደው ነገር የለም፡፡ የእድሩ አባል የሆነ ሰው ቤተሰብ በሚሞትበት ጊዜ እያንዳንዱ የእድሩ አባል ለማስተዛዘኛ የሚሆን እንጀራና ወጥ ያዋጣል፡፡ በዚህ መንገድ ማህበረሰቡ እርስ በርሳዊ መደጋገፍንና መቀራረብን ያዳብራል፡፡

ማህበረሰቡ ማህበራዊ ግንኙነቱን የሚያጠናክርበትና የሚተጋገዝበት ሌላኛው ሃገር በቀል ተቋም  እቁብ ነው፡፡ እቁብ በውስጡ የተሰባሰቡት አባላት የጋራ ገንዘባቸውን በየተራ ወይም በእጣ በሚወሰን ቅደምተከተል እንዲደርሳቸው የሚያደርግ ተቋም ነው፡፡ ይህ ተቋም እንደ እድር ሁሉ የተለያየ እምነት፣ ሙያ፣ ቋንቋና ብሄረሰባዊ ማንነት ያላቸውን ሰዎች የሚያስተሳስር ተቋም ነው፡፡

ተጠኝው ማህበረሰብ ማህበራዊ ግንኙነቱን የሚያጠናክርበትና የሚተጋገዝበት ሌላኛው ሃገር በቀል ተቋም ደቦ ነው፡፡ የደቦ ዋና አላማው ስራን በየተራ በጋራ መስራት ቢሆንም በእድሜ መግፋትና በጤና እክል ምክንያት መስራት የማይችሉ ሰዎችን ስራ በደቦ  ማከናወንም በአካባቢው የተለመደ ነው፡፡ ይህ የደቦ ስርዓት በዕለቱ ስራው እየተሰራለት ያለው ግለሰብ ምግብና መጠጥ  የሚያቀርብበትና ሳቅ ጨዋታም የሚደምቅበት ነው፡፡ በመሆኑም፤ ስራን ከማቅለሉም ባሻገር የሰዎችን ማህበራዊ ግንኙነት የማጠናከር ሚናውም ከፍተኛ ነው፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትንና መሰል ሃገር በቀል ተቋማትን በማስቀጠል ረገድ የተጠኝው አካባቢ ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ በእድሜ የገፉ ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች ዕድሜ ከፍተኛ እውቀትንና ልምድን የሰጣቸው ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን በእድሜ የገፉ ሰዎች ለሞት የቀረቡ ስለሆኑ በሃሳባቸውና ንግግራቸው መካከል ሃሰትን አይቀላቅሉም ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህ ምክንያትም በአካባቢው ማህበረሰብ ውስጥ የእድሜ ባለፀጎች ይከበራሉ፤ የተናገሩትም ከእውነታ ይቆጠራል፡፡ ይህ በመሆኑም የተጣሉትን የማስታረቅና በማህበረሰቡ መካከል መልካም የሆነ ግንኙነት እንዲፈጠር የማድረግ ሃይላቸው የላቀ ነው፡፡

## 4.2.5 የቤተሰብ ማህበራዊ ሚናና የስርዓተ ፆታ ሁኔታ

ቤተሰብ ፡- የስጋ ዝምድና ያላቸው፣ በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ስብስብ ነው፡፡ በተጠኝው አካባቢ አንድ ቤተሰብ የሚባለው ባል፣ ሚስትና ያላገቡ ልጆችን የሚያካትት ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ግን አጎት፣ አክስት፣ የእህት ወይም የወንድም ልጅ፣ አያት ወዘተ. ያካትታል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ የልጆችን ባህሪ ቅርፅ በማስያዝ ረገድ ቤተሰብ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ የቤተሰቡ መሪ ወንዶች ናቸው፡፡ ባል ራሱን የቤተሰቡ ተምሳሌትና ማህበራዊ መሪ፣ ሚስቱንና ልጆቹን ከአንዳች አደጋ ጠባቂ ብቸኛው ሰው አድርጎ ይሾማል፡፡ በሴቶች ከሚከናወኑ የተወሰኑ ስራዎች በስተቀር እራሱን የቤተሰቡ

ሁለንተናዊ ሃላፊና መሪ፤ ልጆችን በትክክለኛው መንገድ ቀርፆ በማሳደግ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና ያለው አድርጎ ያስቀምጣል፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ልጆችን የመመገብና የመንከባከብ ስራ የሴቶች (ሚስቶች) ብቻ ሃላፊነትና ግዴታ ተደርጎ ይታሰባል፡፡

በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ የስርዓተ ፆታ ልዩነት የሚጀምረው ልጆች ገና እንደተወለዱ ነው፡፡ ወንድ ልጅ ከሴት ልጅ የበለጠ ቦታና ክብር ይሰጠዋል፡፡ ከዚህም በተነሳ በአካባቢው ወንድ ልጅ መወለዱ እንደተሰማ የልጁ አባት በጣም ይደሰታል "የኔ መኩሪያ" በማለት ይፎክራል፡፡ ከቤቱ ወጥቶ በአካባቢው በመንጎራደድም ብስራቱን ለሁሉም ያሰማል፡፡ ልጁ ጀግና፣ ደም መላሽ፣ ጠንካራ ገበሬ እንዲሆንለትም ይመኛል፡፡ የተወለደችው ሴት ከሆነች ደግሞ ኣባት በመደሰት ፋንታ ያዝናል - ራሱን እድለ ቢስ አድርጎም ይቆጥራል፡፡ እናትም ወንድ ልጅ ወለደች መባሉ የበለጠ ያስደስታታል - ሆኖም ግን በወንድና በሴት ልጆቿ መካከል ልዩነት አታደርግም፡፡ ነገር ግን ሴት ልጂ በቤት ውስጥ እንድትውልና የቤት ውስጥ ስራን እንድታከናውን፤ ወንድ ልጂ ግን ከቤት ውጭ እንዲውልና በቤት ውስጥ መገኘት ያለበትም በምሳ፣ ራትና ምኝታ ጊዜ እንዲሆን ትፈልጋለች፡፡

በአካባቢው ደንብ መሰረት ማንኛውም ልጅ ማህበረሰቡ መልካም የሚለው ባህሪ እንዲኖረው ይጠበቅበታል፡፡ ለዚህም ከልጁ ወላጆች በተጨማሪ ዘመዶች፣ ጎረቤቶችና የአካባቢው አዛውንቶችም ትልቅ ሃላፊነት አለባቸው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ስርቆት፣ ውሸት፣ ስድብ፣ ትልቆችን አለማክበር ወዘተ. የመጥፎ ባህሪ መገለጫወች ናቸው፡፡ ይህን ጉዳይ በሚመለከት መረጃ ከሰጡ ሰዎች መካከል አቶ ገብረአብ ደሴ (ቃመ፣ ታህሳስ 20/ 2008) እንዲህ በማለት ይገልፃሉ፡፡

> በአካባቢው አንድ ልጅ እነዚህንና መሰል ድርጊቶችን ለምሳሌ፡- ስርቆት ቢፈፅም ድርጊቱን የፈጸመው ልጅ ብቻ ሳይሆን የልጁ ወላጆችም ሆኑ ጎረቤቶች በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ይወገዛሉ፡፡ ልጅን መክረውና ገስፀው ማሳደግ የማይችሉ ተብለው መጥፎ ስም ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያትም ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ጋብቻ እንዳይፈፅሙ እስከ መከልከል ይደርሳሉ፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ልጆች የሚያድጉት የአካባቢውን ባህላዊ የስራ ክፍፍል እየተማሩ ነው፡፡ በአካባቢው አንዳንድ የስራ አይነቶች ወንዶች ብቻ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ሁለቱም ፆታዎች የሚያከናውኗቸው ሲሆኑ፤ ብዙዎቹ የስራ አይነቶች ግን ለሴቶች ብቻ የተተው ናቸው፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ላም ማለብ፣ አጥር ማጠር፣ ማረስ የመሳሰሉት በወንዶች የሚከናወኑ

የስራ አይነቶች ናቸው፡፡ ለቤት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ገበያ ወጥቶ መግዛት፣ የማገዶ እንጨት መሰብሰብ፣ ከብት መጠበቅ፣ ማረም፣ መውቃትና መሰል ስራዎች ደግሞ ሁለቱም ሊያከናውኗቸው የሚችሉ ናቸው፡፡ ሴት ልጆች በቤት አካባቢ በርካታ ስራዎችን የሚያከናውኑ ሲሆን፤ ከዋና ዋናዎቹ መካከልም እንጀራ መጋገር፣ እህል መፍጨት/መውቀጥ፣ ውሃ ከወንዝ መቅዳት፣ ወጥ መስራት፣ የቤተሰቡን ልብስ ማጠብ፣ ልጆችን መመገብና መንከባከብ፣ ቤት ማፅዳት የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ነገር ግን ከወንዶች የበለጠ ሰፊ ስራ የሚሰሩት (በስራ የሚጠመዱት) ሴቶች ሲሆኑ፤ በቤት ውስጥና ከቤት ውጭ ባሉ ሌሎች የግብርና ስራዎች ላይ በቀን ቢያንስ ለ18 ሰዓት ያህል ይሰራሉ፡፡ ከመረጃ ሰጭዎች መካከል ወ/ሮ ሃይማኖት አስማረ (ቃመ፣ ጥር 15/ 2008) እንደገለፁት "ሴቶች ሊያርፉ የሚችሉት ምሳና ራታቸውን ሲበሉ ብቻ ነው"፡፡ እንደ ወ/ሮ ሃይማኖት ልጆችም በቤት ውስጥና ከቤት ውጭ ባሉ ሌሎች የግብርና ስራዎች ላይ በመሳተፍ ወላጆቻቸውን እንዲያግዙ የሚጠበቅባቸው ሲሆን፤ እንደ እናቶች ሁሉ ሴት ልጆች ከወንድ ልጆች የበለጠ ሰፊ ጊዜያቸውን በስራ ያሳልፋሉ፡፡

የተጠኘው አካባቢ ሴቶች ለተለያዩ ክልከላዎች የተዳረጉ ናቸው፡፡ ሴቶች ወንዶችን ለማሳሳት የተፈጠሩ ተደርገው የሚታሰቡ ሲሆን፤ ያሳስታሉ ከሚባሉበት ሁኔታ መካከል አለባበሳቸው ይጠቀሳል፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ እምነት ሴቶች በአለባበሳቸው ተጋልጠውና የገላቸውን ቅርፅ የሚያሳይ ጠባብ ልብስ ለብሰው ከታዩ ወንዶችን በቀላሉ ያሳስታሉ (ወንዶች ሳያስቡት የግብረ ስጋ ግንኙነት ወደመሻት ስሜት እንዲገፋፉ ያደርጋሉ) ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህም ሴቶች አጭርና ጠባብ የሆነ ልብስ (ለምሳሌ፦ አጭር ቀሚስ፣ ጡትና እምብርትን የሚያሳይ ልብስ፣ ሱሪ ወዘተ.) እንዲለብሱ አይፈቀድላቸውም፡፡ ይህን በሚመለከት መረጃ ከሰጡ ሰዎች መካከል አቶ ስለሽ መኮንን (ቃመ፣ ጥር 15/ 2008) እንዲህ ይላሉ፡፡

> ሴት ልጅ ተጋልጣ ከሄደች ጭኗ፣ ዳሌዋና የመሳሰሉት የሰውነት ክፍሎቿ ስለሚታዩ የወንዶችን አይምሮ ትለውጣለች፡፡ በዚህም ግዜ ወንዶች ይሳሳታሉ፡፡ እሷም ትሳሳታለች፡፡ ባህላችንን ጥሳ ከለበሰች ሰይጣን ይሳፈራታል፡፡ እናም በአካባቢው ያሉ ወንዶች ዘንድ እንደ ጥሩ ሴት ስለማትታይ ትዳር አትይዝም፡፡ ይዛ ከነበረም ባሏ ይፈታታል፡፡

ስለሆነም የአካባቢው ሴቶች ሰፋና ረዘም ያለ (ገላቸውን ወይም አካላዊ ቅርፃቸውን በቀላሉ ሊያሳይ የማይችል) አለባበስን እንዲከተሉ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በማህበረሰቡ ዘንድ አንዳንድ የመዋቢያ አይነቶች ሰይጣንን ይስባሉ፣ ያስለክፉሉ፣ ያስረግማሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ሴቶች በቀላሉ ለመጥፎ መንፈስ የሚጋለጡና ደንጋጣዎች ናቸው ተብሎም ይታሰባል፡፡ በዚህ መነሻነትም ማህበረሰቡ ለሴቶች የማይፈቅዳቸው የመዋቢያ አይነቶች አሉት፡፡ ለምሳሌ፡- ቅንድብ መቀንደብ፣ አፍንጫ መበሳት፣ ወርቅ ማድረግ የመሳሰሉ ድርጊቶች የተከለከሉ ናቸው፡፡

አንዲት ሴት ፈጣሪ በሰጣት ውበት ላይ ተጨማሪ ውበት በመፈለግ ቅንድቧን ብትቀነደብ፣ አፍንጫዋን ብትበሳ ድርጊቷ ፈጣሪን ስለሚያስቆጣ ወደ ሲኦል (ገሃነብ) ትወረወራለች ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ድርጊቱ የአካባቢውን ደንብ በመጣስ የሚፈፀም ስለሆነ በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ የሆነ ውግዘትና እርግማን ይደርስባታል፡፡ በዚህም እንደ ጓደኞቿ የመዳርና ወግ ማዕረግ የማየት እድሏ ሁሉ የተዘጋ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ወርቅ ሠይጣን ይስባል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህ እምነት መነሻነትም ሴት ልጅ ወርቅ አድርጋ በምትወጣበት ጊዜ ፊተ ገጿን ወይም አፏን ሰይጣን ያጣምማታል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ወርቅ ከወደቀ ሰይጣን ስለሚደብቀው በቀላሉ አይገኝም ይባላል፡፡ በመሆኑም ሴቶች ወርቁ ሲሰወርባቸው ከፍተኛ የሆነ የድንጋጤ ስሜት ስለሚፈጠርባቸው (በተፈጥሯቸው ደንጋጦች ስለሆኑ) ለተለያዩ በሽታዎች ይጋለጣሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለሆነም በማህበረሰቡ ውስጥ እንደ ቅንድብ መቀንደብ ሁሉ በወርቅ ማጌጥም ለሴቶች የተከለከለ ነው፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ለሴት ልጅ በአደባባይ መናገር፣ ድምጿን ከፍ አድርጋ ማውራትና መሳቅ የተነወረ ድርጊት ነው፡፡ እንደ ማህበረሰቡ አመለካከት ሴት ልጅ ድምጿን ከፍ አድርጋ ማውራትና መሳቅ ብቻ ሳይሆን አንገቷን ቀና አድርጋ መመልከትም አልተፈቀደላትም፡፡ ማህበረሰቡ ለዚህ እንደ ምክንያት የሚያቀርበው ከአዳምና ሄዋን ጋር በተያያዘ የሚነገርን ሃይማኖታዊ አስተምህሮ መነሻ ያደረገ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ በሚመለከት ከመረጃ ሰጭዎች መካከል አቶ ገብረአብ ደሴ (ቃመ፣ ታህሳስ 20/ 2008) እንዲህ ይላሉ፡፡

> እናታችን ሔዋን የምድር ንግስት በነበረችበት ግዜ በሰይጣን ተሳስታ ከእግዛቤር በላይ ለመሆን በመፈለግ እግዛቤር አትብሉ ያላቸውን ዕፀ በለስ ቆርጣ በላች - አዳምንም እንዲበላ በማድረግ  አሳሳተችው፡፡ በዚህ ግዜ ፀጋዋ በሙሉ ስለተገፈፈ ባጠፋችው ጥፋት በማፈሯ የተነሳ ቀና ብላ ፈጣሪን ማየት አልቻለችም ነበር፡፡ ከዚያ ግዜ ጀምሮ ሴቶች ስለተረገሙ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ቢስቁና ቢናገሩ ይቀሰፋሉ፡፡ ልሳናቸውም ይዘጋል፡፡

ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ ሴቶች ከቤት ውጭ ያለን ችግር ለመፍታት አቅምም ጉልበትም የላቸውም፣ አይን አፋር ስለሆኑ ሌሎችን ተናግረው ማሳመን አይችሉም ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህም ምክንያት የማህበረሰቡን ችግር ለመፍታት፣ የተጣላን ለማስታረቅ፣ የጋብቻ ጥያቄ ለመጠየቅ በሽማግሌነት አይመረጡም፡፡ ሴቶች በአንድ በኩል የመርሳት ችግር ያለባቸውና በዚህም የሰሙትንና ያዩትን ነገር ሙሉ በሙሉ መግለፅ የማይችሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የዋህና ሰው እንዲጎዳ የማይሹ ስለሆኑ ያዩትንና የሰሙትን በግልፅ መመስከር የማይፈልጉ ናቸው ይባላል፡፡ በዚህ መነሻነትም በአካባቢው ሴቶች ለምስክርነት ተመራጭ አይደሉም፡፡ እንደ አቶ ስለሽ መኮንን (ቃመ፣ ጥር 15/ 2008) ሴቶች የግድ ምስክር መሆን ካለባቸው እንኳ ከወንዶች ጋር ተቀላቅለው ነው፡፡

በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ ሴቶች ባዩት ቅፅበታዊ ነገር ተነስተው የያዙትን ሃሳብ በድንገት የመቀየር፣ የያዙትን ቀጠሮ የመርሳት ችግር አለባቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ እምነት መነሻነትም ማህበረሰቡ ሴቶች አካባቢያቸውን በሃላፊነት እንዲያስተዳድሩ ፈቃዱም ፍላጎቱም አይደለም፡፡ ይህ ተግባር ለሴቶች የተከለከለበትን ምክንያት በሚመለከት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚነገር አንድ አፈ ታሪክ ያለ ሲሆን፤ አፈታሪኩም ከመረጃ ሰጭዎች መካከል አቶ ትግስቱ በላይ (ቃመ፣ የካቲት 12/ 2008) በሚከተለው መልኩ የገለፁት ነው፡፡

> በድሮ ግዜ አንድን አካባቢ ታስተዳድር የነበረች ሴት ነበረች፡፡ ከእለታት አንድ ግዜም በማህበረሰቡ መካከል ከፍተኛ የሆነ ጠብ ተነሳ፡፡ በዚህ ግዜ የተጣላውን ህዝብ ለማስታረቅ የአካባቢው ገዥ የነበረችው ንግስት በቦታው እንደምትመጣና ህዝቡ ተሰብስቦ እንዲቆያት አዘዘች፡፡ የተጣሉት ህዝቦችና ሌሎች ሽማግሎችም በሙሉ በቦታው ተገኝተው እሷን መጠበቅ ጀመሩ፡፡ ንግስቲቱም ጠቡን ለመፍታትና በአካባቢው ሰላም ለመፍጠር ወዳካባቢው በምትሄድበት ግዜ አንድ ወጣት በጫካው ውስጥ ከአንበሳ ጋር ሲታገልና አንበሳውን ሲገድል አየች፡፡ በዚህ ግዜ በልጁ ጀግንነት ትሳብና ሰዎችን ለማስታረቅ የነበረውን ቀጠሮ ረስታ ልጁን አስጠርታ ወደቤቷ በፈረስ ጭናው ተመለሰች፡፡ የአካባቢው ህዝብም በንግስቲቱ መቅረት ተበሳጭቶ ችግሩ ሳይፈታ ወደየቤቱ ተመለሰ ይባላል፡፡

በአጠቃላይ የማህበረሰቡ የቤተሰብ አወቃቀርና ልማድ ሴቶች ወንዶችን ከማገልገልና ልጅ ወልዶ ከማሳደግ ሌላ ሚና የላቸውም በሚል አስተሳሰብ የተቃኘና የወንዶች የበላይነት የሚንጸባረቅበት ነው ማለት ይቻላል፡፡

## 4.2.6 ልማዳዊ እምነቶች

ተጠኚው ማህበረሰብ የተለያዩ ልማዳዊ እምነቶች ተከታይ ሲሆን፤ ከነዚህም መካከል ከዛር፣ ከአድባር፣ ከጥንቆላ፣ ከቡዳ፣ ተፈጥሮን ከመቆጣጠር፣ ከሞት፣ በሽታን ከማባረርና ከማሸጋገር ወዘተ. ጋር የተያያዙ እምነት መራሽ ልማዶች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ እነዚህና መሰል የማህበረሰቡ ልማዳዊ እምነቶች በጥናቱ የተለያዩ የትንተናና ማብራሪያ ክፍሎች ውስጥ በተለያየ አጋጣሚ የሚነሱ ናቸው፡፡ በመሆኑም ከፍ ሲል ስለተጠቀሱት የማህበረሰቡ ልማዳዊ እምነቶች በዚህ ክፍል ውስጥ ሰፊ ገለፃ ማቅረብ አስፈላጊነቱ እምብዛም ነው፡፡ ይሁን እንጅ በአንድ በኩል የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ከልማዳዊ እምነቶች ጋር የተቆራኘ በመሆኑ፤ በሌላ በኩልም ይህ ምዕራፍ ተጠኚው ማህበረሰብ የሚተዋወቅበት ስለሆነ ስለተጠቀሱት የማህበረሰቡ ልማዳዊ እምነቶች ጥቆማ ሰጥቶ ማለፍ ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም ከፍ ሲል ስለተጠቀሱት የተጠኚው ማህበረሰብ የልማዳዊ እምነት ዘሮች ከዚህ በታች አጭር ገለፃ ቀርቧል፡፡

**ዛር** - አንድን ሰው የግሉ የሚያደርግ፣ የሚቆጣጠርና እንዳሻው የሚያደርግ መንፈስ ሰፍሮበታል ብሎ ማመን ነው፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ እምነት ዛሮች የክርስቲያን፣ የሙስሊም ወዘተ በሚል የሚከፋፈሉ ሲሆን፤ የተለያዩ ዛሮች የየራሳቸው ስም፣ ምስ (ዛሩ የሚፈልገው ነገር)፣ አጎራር፣ መለከፊያና መተላለፊያ መንገድ አላቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ በማህበረሰቡ እምነት ዛር የተለያዩ ባህሪያት ያሉት ሲሆን፤ አንዳንዱ ዛር ባለዛሩ ዛሩ የማይፈልገውን ከማድረግ መቆጠብን ይጠይቃል ይባላል፡፡ ለምሳሌ፦ አንዳንዱ ዛር ዛሩ ያረፈበትን ሰው ስራ ከመስራት ይከለክላል ይባላል፣ አንዳንዱ ደግሞ ባለዛሩ ሰው የታመመንም ሆነ የሞተን ሰው እንዲነካ አይፈቅድለትም ይባላል፡፡ በተጠኚው ማህበረሰብ ዛር ለሰፈረባቸው ሰዎች ብቻ የሚፈቀዱ ነገሮች (ምግብ፣ መጠጥ፣ ልብስ ወዘተ.) ያሉ ሲሆን፤ ለእነሱ ብቻ የተፈቀደን ነገር ሌላ ሰው ከነካ ይታመማል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለሆነም የባለዛሮች ንብረትም ሆነ ባለዛሮቹ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የተፈሩና የተከበሩ ናቸው፡፡

**አድባር** - ተጠኚው ማህበረሰብ አድባርን "ቆሌ" በሚልም ይጠራዋል፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ እምነት "ቆሌ" በአንድ አካባቢ፣ ሰፈር ወይም በአንድ ግለሰብ ቤት ውስጥ የሚኖርና የአካባቢውን ሰላም፣ የሰዎችን ጤናና ንብረት የሚጠብቅ መንፈስ ነው፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብ ሰው ያልሆኑ የተወሰኑ ግዑዛን ነገሮች (ለምሳሌ፦ ወንዞች፣ ሜዳዎች፣

ተራሮች፣ ዋሻዎች ወዘተ.) የዚህ መንፈስ ማደሪያዎች ስለሆኑ መለኮታዊ ሃይልና የማዳን ስልጣን አላቸው ብሎ ያምናል፡፡ በዚህ ምክንያትም የአካባቢው ማህበረሰብ ከተወሰኑ ተራሮች፣ ዛፎችና ወንዞች ጋር የተያያዙ ልማዳዊ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

ለምሳሌ፡- ብልብ ውሃ በሚባል ቀበሌ ውስጥ አንጎና ውያላ የሚባሉ ተራሮች ያሉ ሲሆን፤ የአካባቢው ማህበረሰብ በየዓመቱ በእነዚህ ተራሮች በመገኘት ምግብና መጠጥ አዘጋጅቶ ያከብራል፡፡ በእነዚህ ተራሮች ስር ለሚደረገው ዓመታዊ ከበራ ወንድ ቀይ ዶሮና ቡላ ፍየል ይዘጋጃል፡፡ የተጠቀሱትን ተራሮች ለማክበር የሚዘጋጀው ምግብ ወደቤት አይመለስም፡፡ ምክንያቱም ምግብና መጠጡ ወደቤት ከተመለሰ ቆሌዎቹ ስለሚቆጡ በአካባቢው ሰላምና ጤና ይጠፋል ተብሎ ይታመናል፡፡ የተጠቀሱት ቦታዎች የተቀደሱ ናቸው ተብሎ ስለሚታመን የምግብና መጠጥ ዝግጅቱ ሲጠናቀቅ በዝግጅቱ የታደሙት ሁሉም ሰዎች ምግብ በተዘጋጀበት አመድ ፊታቸውን፣ ክብቶቻቸውንና ሌላም ንብረታቸውን ይቀባሉ፡፡ በሁለቱም ተራሮች ላይ አሉ የሚባሉት ቆሌዎች የየራሳቸው መጠሪያ ስም ያላቸው ሲሆን፤ የአንጎ ተራራው “ባዲገዝ” ፣ የውያላው ደግሞ “ሃሳኔ” በመባል ይጠራሉ፡፡

ከፍ ሲል በተጠቀሰው ቀበሌ ውስጥ አንድ ትልቅ ዋርካ ዛፍ ያለ ሲሆን፤ ይህ ዛፍ አካባቢውን የሚጠብቅ መንፈስ የሚኖርበት ነው ይባላል፡፡ ስለሆነም የአካባቢው ማህበረሰብ ዛፉን ቅቤ በመቀባት ይለማመናል፣ ለመንፈሱ ዶሮ ከነነፍሱ ይጥላል፡፡ ዶሮው እንደተጣለ ከተወሰነ ደቂቃ በኋላ ማን እንደበላው ሳይታወቅ ይጠፋል፡፡ በዛፉ አካባቢ ብቻን በቀንም ሆነ በማታ አይኬድም፡፡ ዋርካው ከተቆረጠ በቆራጩም ሆነ በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ በሽታና ሞት ያስከትላል፡፡ ስለሆነም ዋርካው አይቆረጥም - ለመቁረጥ የሚያስብም የለም (አቶ ገብረአብ ደሴ፣ ቃመ፣ ታህሳስ 25/2008) ፡፡

በተጠኘው አካባቢ ርብ የሚባል ወንዝ ያለ ሲሆን፤ ይህ ወንዝ አባ ወርቄ የሚባል ቆሌ የሚኖርበት ነው ይባላል፡፡ በመሆኑም የአካባቢው ማህበረሰብ በወንዙ ዳር ተገኝቶ ቡና በማፍላትና ዶሮ በማረድ ወንዙን ያቋድሳል፡፡ እኔም የአካባቢው ማህበረሰብ ቡና በማፍላት ከቡናው ወደ ወንዙ ሲደፉና ሲለማመን፤ ዶሮ አርዶ ወደ ወንዙ ውስጥ ሲጥል ጥር 18/ 2008 በአካል ተገኝቼ ተመልክቻለሁ፡፡

የሚሸት ነገር (ምግብና መጠጥ) ይዞ ወንዙን የሚሻገር ሰው ከያዘው ነገር ቀንሶ ወንዙ ላይ ይጥላል፡፡ አዝማሪ እንኳ ወንዙን ሲሻገር አባ ወርቄን ለማስደሰት ማሲንቆ ገዝግዞ ያልፋል፡፡

ምክንያቱም ሰዎች እነዚህን ነገሮች ሳይፈፅሙ ወንዙን ከተሻገሩ አባ ወርቄ ስለሚቆጡ በራሳቸውም ሆነ በቤተሰባቸው ላይ በሽታ ይጥሉባቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከመረጃ ሰጭዎች መካከል ወ/ሮ ዳሳሽ እምሩ (ቃመ፣ ጥር 18/2008) እንደገለፁት “አሁን አሁን ግን ቄሶች ለወንዙ ምግብም ሆነ መጠጥ ነገርም ሌላ ነገር ሁላ መጣል ለሰይጣን ማብላት ነው እያሉ ስለሚያወግዙ እየተተወ ነው፡፡ አዝማሪዎችም ዝም ብለው ይሻገራሉ”፡፡ በርብ ወንዝ አካባቢ በእኩለ ቀንና በማታ ሰዓት ላይ በወንዙ ውስጥ የአባ ወርቄ ቡና ሲወቀጥ ይሰማል፣ የሰው ድምፅም ይሰማል፣ መብራት ሲበራም ይታያል (አቶ ደስታው አባይነው፣ ቃመ፣ ጥር 18/2008)፡፡ በተጠቀሱት ተራሮችና ዛፎች ስር የሚከወኑ ልማዳዊ እምነቶችንና ድርጊቶችን ሲከወኑ የማየት እድል አላጋጠመኝም፡፡

**ጥንቆላ** - ማህበረሰቡ እርኩስ መንፈስን የሚያባርሩ (የሚያስለቅቁ)፣ ሌሎች ሰዎች የማያዩትን ማየት የሚችሉና ከአምላክ ጋር መገናኛ የተለየ ተሰጥኦና ቋንቋ ያላቸው የተወሰኑ ሰዎች አሉ ብሎ ያምናል፡፡ እነዚህ አይነት ሰዎች ለእኛ ጤና፣ ሰላም፣ ሃብትና ፍቅር ለመስጠት የተፈጠሩ ናቸው ብሎ ያስባል፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ እነዚህ ሰዎች ሃብትና ጤናን ለማግኘት፣ ራስን ከጠላት ለመጠበቅ፣ ምቀኛን ለማጥፋት፣ ፍቅር ለማስያዝ፣ የወደፊት እጣ ፋንታንና የቦታ ክፍልን ለማወቅና መሰል ጉዳዮች መፍትሄ ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለሆነም ማህበረሰቡ ሁሉን የማወቅ ሃይል አላቸው ብሎ ወደሚያስባቸውና እውቅና ወደሰጣቸው ሰዎች በመሄድ ደጅ ይጠናል - ያስደግማል፡፡ ከእነሱ ዘንድ ሄዶ ለችግሩ መፍትሄ ሳያገኝ እንደማይመለስም ያምናል፡፡ ከዚህ እምነቱ በመነሳትም ለእነዚህ አይነት ሰዎች ከፍተኛ ቦታና ክብር ይሰጣል፡፡

**ቡዳ** - የተጠኘው አካባቢ ማህበረሰብ ቀልባቸው ያረፈበትን ሰውም ሆነ እንሰሳ የሚያሳምም ወይም የሚገድል፤ ሰብል እንዳያፈራ ወዘተ. የሚያደርግ ክፉ አይን ያላቸው ሰዎች አሉ ብሎ ያምናል፡፡ ክፉ አይን አላቸው የሚላቸውን ግለሰቦችም ቡዳ በሚል ይጠራቸዋል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው ማህበረሰብ ክፉ አይን በዘር ግንድ የሚወረስ ነው ብሎ ያምናል፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብ ቡድንነት የምቀኝነት፣ የቅናት ወይም የእርኩስ መንፈስ ባህሪ ያለው ስለሆነ የቡዳ አይን የሚያጠቃው በዋነኛነት ሃብት ያላቸውን ሰዎች፣ መልከ ግቡዎችን (ቆንጆዎችን)፣ ሙሽሮችንና ህፃናትን ነው ብሎ ያምናል፡፡

ማህበረሰቡ የቡዳ መንፈስን በጣም ይፈራል፡፡ ከመፍራቱ ብዛትም በተለይም በማታ ቡዳ የሚለውን ቃል እንኳ አያነሳም፡፡ ምክንያቱም ቡዳ የሚለው ቃል ሲጠራ ቡዳዎቹ

ስለሚሰሙ ከቤተሰቡ ውስጥ ሰው ይታመማል ወይም ይሞታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ማህበረሰቡ የቡዳ መንፈስ የሚያጠቃው የሚፈራን ሰው ነው፤ ቡዳዎች በጨለማ ወደጅብነት ይቀየራሉ፤ የሞተን ሰው ወደቤታቸው ወስደው ነፍስ እንዲዘራበት በማድረግ አገልጋያቸው ያደርጉታል ብሎ ያምናል፡፡ በተጠኘው አካባቢ ማህበረሰብ እምነት አንድ ገና በእግሩ መሄድ ያልጀመረን ህፃን ልጅ ቡዳ ከበላው ቡዳው ቶሎ እንዲያድግለት ስለሚፈልግና ስለሚጠብቀው ፈጥኖ በእግሩ ይሄዳል፡፡ በልጅነታቸው ቡዳ በልቷቸው የዳኑ ሰዎች እስከህይወታቸው ፍፃሜ ድረስ ተልባ አይበሉም፡፡ ምክንያቱም ተልባ ከበሉ የቡዳው መንፈስ ተመልሶ ይይዛቸዋል ይባላል፡፡

በቡዳ የተጠቁ ሰዎች መርፌ አይወጉም፡፡ ምክንያቱም ቡዳ መርፌ ስለማይወድ ከተወጉ ወዲያውኑ ይሞታሉ ይባላል፡፡ በቡዳ የተጠቁ ሰዎች የያዛቸው የቡዳ መንፈስ ለቅቄያለሁ ብሎ እስካለፈለፈና መልቀቁም እስካልተረጋገጠ ድረስ ጠላ አይጠጡም፣ ስጋና ተልባ አይበሉም፣ ብረት ነክ ነገሮችን (ሃብል፣ ቀለበት…) አያደርጉም፡፡ ምክንያቱም በማህበረሰቡ እምነት መሰረት እነዚህ ነገሮች የቡዳ መንፈሱ እንዳይለቅ ያደርጋሉ፡፡

**ተፈጥሮን መቆጣጠር -** በተጠኘው ማህበረሰብ እምነት የተለያዩ ተፈጥሯዊ ሁነቶችን ለምሳሌ መብረቅን፣ ፀሃይን፣ ዝናብን፣ በረዶን ወዘተ. የመቆጣጠር ወይም በተፈለገው መንገድ የማዘዝ ሃይል አላቸው የሚባሉ ግለሰቦች አሉ፡፡ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ተፈጥሯዊ ሁነቶች መካከል የማህበረሰቡን ከበረድ ጋር የተያያዙ ልማዳዊ እምነቶች በማሳያነት ቀጥሎ እንመልከት፡፡ በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ "ጸሎተ በረድ" በመድገም በረድ ሰብልን እንዳይመታ ይጠብቃሉ ተብሎ የሚታመንባቸው ሰዎች አሉ፡፡ ይህን አስመልክቶ ከመረጃ ሰጭዎች መካከል አቶ ስለሽ መኮንን (ቃመ፣ ጥር 15/2008) "የበረድ ደጋሚዎች በረድ የቀላቀለ ዝናብ በሚጥልበት ጊዜ ድጋም በማድረግ በረዱ ቆሞ ንፁህ ዝናብ ብቻ እንዲወርድ ያደርጋሉ" ይላሉ፡፡ እንደ አቶ ስለሽ እነዚህ ሰዎች በአካባቢው አንድ የተጣሉት ሰው ቢኖር በረድ የእሱን ሰብል ወይም ሌላ ንብረት ብቻ ለይቶ እንዲያጠቃ የማድረግ ሃይልም አላቸው፡፡ በዚህ ምክንያትም በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ የበረድ ደጋሚ የሚባሉ ሰዎች ትልቅ ክብር አላቸው፣ ማህበረሰቡ ከእነሱ ጋር እንዳይጣላም ይጠነቀቃል፡፡ የበረድ ደጋሚ እየተባለም የአካባቢው ማህበረሰብ እህል እያዋጣ (አሁን አሁን በእህሉ ፈንታ ጥሬ ገንዘብ ማዋጣትም ተጀምሯል) ሙሉ ወጫቸውን ይሸፍናል፡፡

በማህበረሰቡ ዘንድ የበረድ ደጋሚዎች በህይወታቸው ሙሉ የማይመገቧቸው የምግብ ዘሮች አሉ፡፡ ከእነዚህ የምግብ ዘሮች መካከል ተልባ፣ ድንችና ጎመን ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ የክልከላው ዋናው ምክንያትም የበረድ ደጋሚዎች እነዚህን የምግብ ዘሮች ከተመገቧቸው የሚያከናውኑት ድጋም አይሰራም ተብሎ ስለሚታመን ነው (አቶ ደስታው አባይነው፣ ቃመ፣ ጥር 18/2008)፡፡

በበረድ ደጋሚዎቹ ከሚከናወነው "ጸሎተ በረድ" በተጨማሪ የአካባቢው ማህበረሰብም በረድን ለማስቆም የሚያከናውናቸው ሌሎች ልማዳዊ ድርጊቶችም አሉ፡፡ ማህበረሰቡ በረድ በሚጥልበት ጊዜ በቤት ውስጥ እየነደደ ያለን ፍም እሳት በማጭድ ላይ አድርጎ ሶስት ጊዜ "እልል" በማለት ከቤት በር ላይ ይጥላል፡፡ ይህን ማድረግም በረድን ያስቆማል ብሎ ያምናል፡፡

**ሞት** - ተጠኝው ማህበረሰብ ከሞትና ግድያ ጋር በተያያዘ ይበጃሉ የሚላቸውና የተለያዩ ልማዳዊ እምነቶችን የሚፈፅምባቸው የተለያዩ ድርጊቶች ያሉት ሲሆን፣ የተወሰኑትን ቀጥሎ ለአብነት ያህል እንመልከት፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ምክንያቱን በውል በማያውቁት ሁኔታ ወንድ ልጅ በወለዱ ቁጥር በተከታታይ የሚሞትባቸው ሰዎች አሉ፡፡ ይሄ አይነት ችግር የሚከሰተው ወንድ ልጅን የሚገድል ቀናተኛ የሆነ ክፉ መንፈስ ስላለ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ወንድ ልጅን የሚገድለው ይሄ ቀናተኛ መንፈስ የሚኖረውም በእናቶች ላይ ነው ይባላል፡፡ በመሆኑም የአካባቢው ማህበረሰብ ባህላዊ እውቀቱን መሰረት በማድረግ ለችግሩ መፍትሄ ይፈልጋል፡፡ መፍትሄውም በተከታታይ ወንድ ልጅ ሲወልዱ የሚሞትባቸው ወላጆች በቀጣይ ወንድ ልጅ በሚወልዱበት ጊዜ ልጁ እንደተወለደ እናት ግራ ጆሮውን እንድትበላው ማድረግ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡

ከዚህ እምነት በመነሳትም ልጁ እንደተወለደ የልጁ እናት ሳትሰማና ሳታይ ባዕድ የሆነ ሰው ተፈልጎ የግራ ጆሮውን ቆርጦ ከምግብ ጋር በመቀላቀል የልጁ እናት እንድትጎርሰው ይደረጋል፡፡ እናቲቱ እንደጎረሰችውም ወዲያውኑ የልጅሽን ጆሮ በላሽው ተብሎ ይነገራታል፡፡ በዚህ ጊዜ እናትየዋ ስትደነግጥ እሷ ላይ ያለውና ወንድ ልጅን የሚገድለው መንፈስ ከላይዋ ላይ ወጥቶ ይጠፋል ይባላል፡፡ በመሆኑም የልጁ ጆሮ ከተቆረጠ አካሉ የጎደለ ስለሚሆን፣ ቀናተኛው መንፈስ ደግሞ አካሉ የጎደለ ነገርን ስለማይወድ፣ ግራም ክፉ መንፈስን ማስደንገጫ ስለሆነ ጆሮው የተቆረጠ ልጅ አይሞትም (አቶ ቢሆነኝ አጠቃ፣ ቃመ፣ ሚያዚያ 3/2008)፡፡ ስለሆነም የተጠቀሰው ስርዓት ከተከናወነ በቀጣይ የሚወለዱ ልጆች

አይሞቱም ተብሎ ይታመናል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ሞት እናት የአብራኳ ክፋይ የሆነውን ልጇን ጆሮ እስከመብላት የሚያደርስ አስፈሪ ክስተት ነው፡፡ እኔም በአካባቢው ባደረኩት ምልከታ ጆሯቸውን በእናቶቻቸው የተበሉ ናቸው የተባሉ (ቆራጣ ጆሮ  ያላቸው) ሰዎች እንዳሉ ለማየት ችያለሁ፡፡

ማህበረሰቡ ደምን ለመመለስ ከሚደረግ ግድያ ጋር በተያያዘ የሚፈፅማቸው የተለያዩ ልማዳዊ እምነቶችና ድርጊቶችም አሉት፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ የደም ውርስ ወይም የሟች ቤተሰብን ገዳይ መበቀል የተለመደ ባህል ነው፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብ የሟች ቤተሰብን ገዳይ መበቀል በተበቃዩ ላይ ተጨማሪ አደጋንም ሊያስከትል ይችላል ብሎ ያምናል፡፡ ስለሆነም የአካባቢው ማህበረሰብ ደም ምለሳን ሲያስብ ገድ እንዲቀናኝ በሚል የተለያዩ ልማዳዊ ድርጊቶችን ይፈፅማል፡፡ ለምሳሌ፦ በደም ምለሳ (በደም ውርስ) የሚፈለግን ሰው ለመግደል ሲኬድ ቀይ ዶሮ አርዶ የቤት በር ላይ በደሙ እጅን ታጥቦ መሄድ ይቀናል (ገድ ይሆናል) ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይሄን ሳያደርጉ ወደ ተገዳይ ቤት መሄድ ግን ገድ ፊቷን ሊገደል ወደታሰበው ሰው ስለምታዞር ደም ለመመለስ በሚሄደው ሰው ላይ ሞትን ያስከትላል ተብሎ ይታመናል፡፡ በተጨማሪም ሰውን ለመግደል ጥይት አቀባብሎ የሄደ ሰው ሊገድለው የፈለገውን ሰው አጥቶ ከተመለሰ ያቀባበለውን ጥይት ወደሰማይ መተኮስ አለበት ይባላል፡፡ ይሄን ሳያደርግ የቀረ ሰው ግን ያቀባበላት ጥይት ተባርቃም ቢሆን ራሱን (ያቀባበለውን ሰው) ትገድለዋለች ተብሎ ይታመናል፡፡

ማህበረሰቡ ሞትን ይጠራሉ የሚላቸውና ከዚህ አስተሳሰቡ ተነስቶም የማይፈጽማቸው፣ ሌሎች እንዲፈፅሟቸውም የማይፈቅዳቸው በርካታ ድርጊቶች አሉት፡፡ በማሳያነት ከነጠላና ጋቢ አለባበስ ጋር የተያያዙ ድርጊቶችን እንመልከት፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ለሴት ልጅ ነጠላ፣ ለወንድ ልጅ ጋቢ የተለመደ የዘወትር አለባበስ ነው፡፡ በአካባቢው ሰው በሚሞትበት ጊዜ ለሴቶች  የነጠላቸውን ጥለት ዘቅዝቆ መልበስ የተለመደ ሲሆን፣ ሰው ሳይሞት ይህን መፈጸም ግን ድርጊቱ  ሞትን የሚጠራ ወይም የሞት ምልክት ተደርጎ ይታሰባል፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ወንድ ልጅ ወደለቅሶ ቦታ ሲሄድ ቀኝ እጁን ከጋቢው ማውጣት የተለመደ ሲሆን፣ በአካባቢው ሰው ሳይሞት ይህን  መፈፀም ግን ድርጊቱ እንደነጠላ መዘቅዘቅ ሁሉ ሞትን የሚጠራ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በመሆኑም ነጠላ ዘቅዝቆ መልበስና ቀኝ እጅን ማውጣት በአካባቢው የሞተ ሰው ያለ መሆኑን ጠቋሚ ሲሆኑ፣ ለሴት ልጅ ሰው

ሳይሞት ነጠላ ዘቅዝቆ መልበስ፣ ለወንድ ልጅ ቀኝ እጅ ማውጣትና መሰል ድርጊቶች በማህበረሰቡ ዘንድ የጥሩ ነገር ተምሳሌት ተደርገው አይወሰዱም፡፡

**በሽታን ማባረርና ማሸጋገር** - እንደተጠኘው ማህበረሰብ የተለያዩ ልማዳዊ እምነቶችንና ድርጊቶችን በመፈፀም አንዳንድ  በሽታዎችን ከታመሙ ሰዎችም ሆነ ከአካባቢው ማባረር ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፦ በአካባቢው ሞኝ ባገኝ (ከአንገት በላይ የሆነን የአካል ክፍል የሚያጠቃ ተላላፊ በሽታ መጠሪያ ነው) የሚባል በሽታን በጅራፍ ወይም በጥይት ድምጽ ማባረር ይቻላል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለሆነም በጨለማ ሰዓት ጅራፍ በማጮህ ወይም ጥይት በመተኮስ ይህን በሽታ ከታመሙት ሰዎችና ከአካባቢው የማባረር ተግባር ይከናወናል፡፡

አንድ ሰው በንኪት በሽታ ሲታመም (ንኪት ጠቅ የሚያደርግ፣ ቀስፎ የሚይዝ የህመም አይነት መጠሪያ) የተለያዩ ምግቦችን አዘጋጅቶ በመጣል ይህን በሽታ ከሰውየው ላይ ማባረር ይቻላል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህን ስርዓት ለመፈፀም ሁለት ሰዎች ይመረጡና እነዚህ ሰዎች ብረት ነገሮችንና ከታማሚው ሰው ቤት የሚዘጋጁ እንደ ወተት፣ ቆሎ፣ ፈንዲሻ፣ ኑግና እንቁላል የመሳሰሉ የምግብ አይነቶች በመያዝ ወደአውራ መንገድ ይሄዳሉ፡፡ ከእነዚህ የምግብ አይነቶች ጋር በሽታው አብሮ ይሄዳል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ከቦታው ላይ እንደደረሱም ሶስት ጊዜ ይሰግዱና ወደግራ ዞረው የተዘጋጁትን ምግቦች ይጥላሉ፡፡ ምግቦቹን እንደጣሉም ወደ ኋላ ዞረው ሳያዩ (ዞረው ካዩ የተሸኘው በሽታ ተከትሎ ይመጣል ተብሎ ይታሰባል) ወደታመመው ሰው ቤት ይመለሳሉ፡፡ እንደተመለሱ ወደቤት ከመግባታቸው በፊት ከታማሚው ሰው ሳር ቤት ጥቀርሻ ይመዘዝና በሩ ላይ በእሳት ይቀጣጠላል፡፡ በማስከተልም ምግቦቹን ጥለው የመጡት ሰዎች ያንን የጠቀርሻ እሳት ረግጠው ይገባሉ፡፡ ከቤት የተወሰዱት የምግብ አይነቶች አውራ ጎዳና ላይ መጣላቸው በሽታውን ሃላፊ አግዳሚ ሰው ይዞት እንዲሄድ ያደርጋል፤ የቤቱ ጥቀርሻ በእሳት እንዲቀጣጠል በመደረጉና ሰዎች ረግጠውት በመግባታቸውም ታማሚውን የሚያቃጥለው በሽታ  እንደሳቱ ነዶ እንዲጠፋ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ አንድን በሽታ ከታመሙ ሰዎችም ሆነ ከአካባቢው ማባረር ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ወደራስ መላበስም (አንድን በሽታ ከአንድ ሰው ወደሌላ ሰው ማስተላለፍ) ይቻላል ተብሎ ይታመናል፡፡ በተለይ ልጆች በሆነ በሽታ በሚታመሙ ጊዜ ወላጆች የእኛ  ቆሌ ነው ያመመው፣ ያመማት ብለው ያስባሉ፡፡ በዚህ ምክንያትም ወላጆች የተለያዩ ልማዳዊ እምነቶችንና ድርጊቶችን በመፈፀም የልጆቻቸውን በሽታ ወደራሳቸው ያሸጋግራሉ፡፡ ይህን

ስርዓት ለመፈፀም የሚያስፈልገው ዋነኛው ነገር ቅቤ ነው፡፡ ቅቤ ይዘጋጅና የታመመው/ችው ልጅ እራሳቸውን እንዲቀቡ ይደረጋል፡፡ በማስከተልም የታማሚዎቹ አባት፣ እናት ወይም ስለታመሙት ልጆች ሃላፊነት የሚሰማው ሌላ ሰው ከታማሚዎቹ ላይ የተቀባውን ቅቤ እያነሱ ራሳቸውን ይቀባሉ፡፡ በዚህ ጊዜም ከልጆች ላይ የነበረው በሽታ ቅቤውን ወደራሳቸው ወደቀቡት ሰዎች ይተላለፋል ተብሎ ይታመናል፡፡

በአጠቃላይ ተጠኚው ማህበረሰብ የተለያዩ ልማዳዊ ድርጊቶችን የሚፈፅምባቸው በርካታ ልምዳዊ እምነቶች፣ ከእምነቶቹ ጋር የተያያዙ ነውሮች፣ እንዲሁም ለእምነቶቹና ተያያዥ ነውሮቹ አብነት የሚያደርጋቸው ትረካዎችም አሉት፡፡ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ከበርካታዎቹ መካከል የተወሰኑ ማሳያዎች ብቻ ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ የጥናቱ ትኩረት የሆኑት ነውሮች በዋናነት ከልማዳዊ እምነቶች ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ በመሆናቸው የማህበረሰቡን ነውሮችና ልማዳዊ እምነቶች ነጣጥሎ ማየት አይቻልም፡፡ ስለሆነም ከማህበረሰቡ የተሰበሰቡ ነውሮች የውጤት አቅርቦት፣ ትንተናና ማብራሪያ በተካሄደባቸው ምዕራፎች ውስጥ ከነውር ጋር የተያያዙ ልማዳዊ እምነቶች በጥልቀት ተፈትሸዋል፡፡

## 4.2.7 የባህል ለውጥና መሻሻል

በተጠኚው ማህበረሰብ ባህሎች ላይ እየታዩ ያሉ ወቅታዊ ለውጦች የዚህ ጥናት የትኩረት ነጥቦች አይደሉም፡፡ ይሁን እንጅ ይህ ምዕራፍ የተጠኚውን አካባቢና ህዝብ ባህላዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ወዘተ. ሁኔታ ለጽሁፉ አንባቢዎችና ለቀጣይ አጥኚዎች የማስተዋወቅ ሚና ያለው ነው፡፡ ጥናቱም ባህል ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ ስለሆነም በማህበረሰቡ ባህሎች ላይ ያሉ ለውጦችን የሚያሳዩ የተወሰኑ መረጃዎችን መጠቆም የማህበረሰቡ ባህሎች ያሉበትን ወቅታዊ ሁኔታ ለማወቅም ሆነ በቀጣይ በአካባቢው ባህል ዙሪያ ማጥናት ለሚሹ የተወሰነ ፍንጭ ይሰጣል፡፡ በዚሁ መነሻነትም በመረጃ ስብሰባ ወቅት ከተገኙ መረጃዎች መካከል በማህበረሰቡ ባህሎች ላይ ያሉ ለውጦችን የሚያሳዩ የተወሰኑ መረጃዎች በዚህ ክፍል ቀርበዋል፡፡

ባህል በባህሪው ሁል ጊዜ ቋሚ ወይም እንደነበረ ሆኖ የሚቀጥል ሳይሆን ባለው ተጨባጭ ሁኔታና ባለው ጊዜያዊ ፍላጎት የመለወጥ፣ የመሻሻል እና ከእናካቴውም የመክሰም ባህሪ የሚታይበት እንደሆነ የነውር ባህሪያት በተነሳበት ምዕራፍ ሁለት ውስጥ ተገልጿል፡፡ ከዚህ አኳያ የማህበረሰቡ ባህሎች ያሉበትን ሁኔታ ስመለከት አብዛኞቹ ጥንተ መልካቸውን

እንደያዙ ያሉ ሲሆኑ፤ አንዳንዶቹ ግን በመለወጥና በመጥፋት ሂደት ላይ ያሉ ናቸው፡፡ እየተለወጡና እየተሻሻሉ ካሉ የማህበረሰቡ ባህሎች መካከል የተወሰኑት ከዚህ በታች በአጭሩ ተቃኝተዋል፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ እየተለወጡ ካሉ ባህሎች መካከል ከጋብቻ ጋር የተያያዙ ባህሎች ይጠቀሳሉ፡፡ ከመረጃ ሰጭዎች መካከል ወ/ሮ ሃይማኖት አስማረ (ቃመ፣ ጥር 15/ 2008) እንደገለፁት በሊቦ ከምከም ወረዳ በተለይም በገጠሩ አካባቢ ያለ እድሜ ጋብቻ ለረጅም ዘመናት ሲከናወን የኖረ ባህል ነው፡፡ እንደ እሳቸው አሁን አሁን ግን ያለዕድሜ ጋብቻ ሴት ልጆች በወሊድ ጊዜ ምጥ እንዲጠብቅባቸው  እንደሚያደርግ፣ የሁለቱም ተጋቢዎች ዕድሜ ቤተሰብ ለማስተዳደር ስለማይፈቅድላቸውም ለፍች እንደሚዳርግ መንግስት እያስተማራቸው በመሆኑ እየቀረ ያለ ባህል ነው፡፡  በሌላ በኩል ግን ቀደም ሲል በጋብቻ ጊዜ ይሰጥ የነበረው ጥሎሽ[8]  ከ5 እስከ 6 ብር የነበረ ሲሆን፤ አሁን ላይ ግን ከ150 እስከ 300 ብር ይሰጣል፡፡ ስለዚህ የአካባቢው ማህበረሰብ ልጆቹን ዕድሜያቸው ለጋብቻ ሲደርስ ወደ መዳር እየተሸጋገረ መጥቷል፡፡ የማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ እየተሻሻለና የብር የመግዛት አቅም እየቀነሰ መምጣቱ ለጥሎሽ የሚከፈለው የገንዘብ መጠን ቁጥሩ እየጨመረ እንዲሄድ ምክንያት ሆኗል፡፡ በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ ጋብቻ ለመፈፀም “ዘር” እና “ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ” ዋነኞቹ መስፈርቶች ነበሩ፡፡ አሁን አሁን ግን የተጠቀሱት የጋብቻ መስፈርቶች እየተጣሱ ወይም ተቀባይነታቸው እየቀነሰ ነው፡፡

በማህበረሰቡ ዘንድ የቤት አሰራርም ለውጥ እየተካሄደበት ያለ ሌላኛው ጉዳይ  ነው፡፡ በገጠር የሚኖረው የአብዛኛው ማህበረሰብ ቤት ግድግዳው በእንጨት የተሰራ ሆኖ ጣሪያው ደግሞ በሳር የተከደነ ነበር፡፡ ይህ አይነት የቤት አሰራር ግን ግድግዳው በእንጨት መሰራቱ እንዳለ ሆኖ ጣሪያው የሚለብሰው ሳር ግን በቆርቆሮ እየተለወጠ ነው፡፡ እንደመረጃ ሰጭዎች የዚህ ለውጥ መነሻዎች የአካባቢው የደን ሽፋንና ሳር ከጊዜ ወደጊዜ እየቀነሰ መምጣቱ፤ ማህበረሰቡ ቆርቆሮ ከሳር የበለጠ ዕድሜ ይኖረዋል የሚል አስተሳሰብ እየያዘ መምጣቱና ቆርቆሮ የሃብት ምልክትም ተደርጎ መወሰዱ ናቸው (አቶ ገብረአብ ደሴ፣ ቃመ፣ ታህሳስ 25/2008)፡፡ ስለሆነም በአሁኑ ሰኣት በአካባቢው ገጠራማ አካባቢዎች ሁሉ የሳር ቤቶች በመጥፋት ላይ ያሉ ናቸው፡፡ ይህን ጉዳይ መረጃ ለመሰብሰብ በተንቀሳቀስኩባቸው አካባቢዎችም መመልከት ችያለሁ፡፡

---

[8] በጋብቻ ስነ ስርዓት ላይ ከወንዱ ሙሽራ ለሙሽሪት (ለሴቷ) የሚሰጥ ገፀ በረከት፣ ስጦታ፡፡

የቤት ቁሳቁሶችም በማህበረሰቡ ውስጥ እየተለወጡ ካሉ ባህሎች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል፡- በማህበረሰቡ ውስጥ በገጠርም ሆነ በከተማ ለምግብ ማብሰያነት የሚያገለግለውና ድስት የሚያርፍበት ምድጃ የሚሰራው ከሶስት ተንቀሳቃሽ ድንጋዮች ወይም ሸክላዎች ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የህዝቡን ህይዎት ለመለወጥና ለማሻሻል በሚያደርጉት ድጋፍ ጊዜና ማገዶ ቆጣቢ የሆነ ዝግ ምድጃ መጠቀም የጀመሩ የማህበረሰቡ አባላት አሉ፡፡ ከመረጃ ሰጭዎች መካከል ወ/ሮ የምስራች ወርቂ (ቃመ፣ ግንቦት 21 /2008) ግን "ዝግ ምድጃ ወጥ አያጣፍጥም፣ እናም ብዙም ሰው አይወደውም" ይላሉ፡፡ ሆኖም ግን ከድንጋይ ወይም ከሸክላ የሚሰራውና ማህበረሰቡ ለዘመናት እየተጠቀመበት የመጣው ምድጃ በፍጥነትም ባይሆን በዝግታ እየተለወጠ ያለ ቁስ ነው፡፡

የማህበረሰቡ የባህል መገለጫ የሆኑ አንዳንድ ልማዳዊ እምነቶችም እየተለወጡ - አንዳንዶቹም ጭራሽ እየጠፉ/እየተወገዱ ያሉ ናቸው፡፡ ስለሆነም ሁሉንም ማንሳት ስለማይቻል የተወሰኑትን ብቻ እዚህ ቦታ ላይ እንመልከት፡፡ ለምሳሌ፡- ቀደም ሲል በየዓመቱ ግንቦት አንድ ቀን በንፍሮ በሚከበር (የንፍሮ በኣል[9] ፣ ግንቦት ልደታም ይባላል) በኣል ጊዜ የተዘጋጀው ንፍሮ ከመቀመሱ በፊት የተወሰነ ቆንጥሮ በመውሰድ መስቀለኛ መንገድ ላይ መበተን የአካባቢው በሽታ ከንፍሮው ጋር አብሮ እንዲሸኝ (አልፎ ሂያጅ መንገደኛ ይዞት እንዲሄድ) ያደርጋል ተብሎ ይታመን ነበር፡፡ በዚህ መነሻነትም ከተዘጋጀው ንፍሮ ላይ ህፃናት የተወሰነ ይዘው መስቀለኛ መንገድ ላይ በትነው ሳይመለሱ ሰዎች ንፍሮውን መቅመስ አይችሉም ነበር፡፡ ቀደም ባለው ዘመን በአካባቢው አባ ወርቄ እየተባለ የሚጠራ ወንዝ እሱን ሳያቋድሱት የሚሻገሩ ሰዎችን ለበሽታ ይዳርጋል ተብሎ ይታመን ነበር፡፡ በመሆኑም የሚሸት ነገር (ምግብና መጠጥ) ይዞ ወንዙን የሚሻገር ሰው ሁሉ ከያዘው ነገር ቀንሶ ወንዙ ላይ ጥሎ ያልፍ ነበር፡፡ ቀደም ባለው ዘመን ቡናን ያለ ቁርስ ማቅረብ የቤቱን ወይም የአካባቢውን ቆሌ ስለሚያስቆጣ በአካባቢው ላይ አንዳች መጥፎ ገጠመኝ ያስከትላል ተብሎ ይታሰብ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያትም በማህበረሰቡ ዘንድ

[9] ንፍሮ፡- ተቀቅሎ በጣም የበሰለ ወይም የሞከከ እንደ ባቄላ፣ አተር፣ ስንዴ፣ ቦቀሎ ያለ የጥራጥሬ እህል አይነት፤ ምግብ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች ዘንድ ግንቦት አንድ ቀን የድንግል ማሪያም የልደት ቀን ነው፡፡ በመሆኑም የንፍሮ በኣል ወይም ግንቦት ልደታ ማሪያም ከቤት ውጭ በሊባኖስ ተራራ ላይ ስትወለድ በአካባቢው የነበሩ እረኞች ቅድስት ሃናን (የማሪያምን እናት) ንፍሮ ይዘው ስለጠየቋት እሱን ለማሰብ በየዓመቱ ግንቦት አንድ ቀን ከቤት ውጭ ንፍሮ በጋራ እየተበላ የሚከበር ነው፡፡

ቡና ተፈልቶ ያለ ቁርስ አይቀርብም ነበር፡፡ ከዚህ በላይ በማሳያነት ከተጠቀሱት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ይፈፀሙ የነበሩ ልማዳዊ እምነቶች በአሁኑ ወቅት እየተለወጡና በሂደትም እየጠፉ ያሉ ናቸው፡፡ መረጃ ሰጭዎች እንደሚገልፁት ለነዚህ ልማዳዊ እምነቶች መለወጥና መጥፋት ዋነኛው ምክንያት የሃይማኖት አባቶች ድርጊቶቹ ሰይጣናዊ እንጅ ሃይማኖታዊ መሰረት የሌላቸው ናቸው በሚል ማህበረሰቡን እያስተማሩና እያወገዙ ስለሆነ ነው (አቶ ገብረአብ ደሴ፣ ቃመ፣ ታህሳስ 20/ 2008)፡፡

የማህበረሰቡ መገለጫ የሆኑ የቆዩ  የአኗኗር ስልቶችም (ለምሳሌ፡- እንደ አለባበስ፣ አመጋገብ፣ የፀጉር አሰራር፣ አነጋገርና አመለካከት ያሉ) ለውጥ እየተካሄደባቸው ያሉ ናቸው፡፡ እነዚህ አይነት ለውጦች ግን ማህበረሰቡ እየተቀበላቸው ሳይሆን አጥብቆ እየተቃወማቸው ያሉ ለውጦች ናቸው፡፡ መረጃ ሰጭዎች እንደሚናገሩት እነዚህ ለውጦች በቴክኖሎጅ ልውውጥ ማደግና አካባቢውን የሚጎበኙ የሃገር ውስጥና የውጭ ዜጎች ይዘውት በሚመጡት ባህል ተፅዕኖ ምክንያት እየተፈጠሩ ያሉ ናቸው፡፡ ይህን በሚመለከት ወ/ሮ ስመኝ አዳነ (ቃመ፣ ታህሳስ 28/2008) "በአካባቢያችን ጥሩ ባህል ነበረን፡፡ አሁን ግን የሚመጡ ፈረንጆይ ባህላችን ስለማያውቁ ባካባቢያችን ነውር የሆኑትን ሁላ እየፈፀሙ ማህበረሰቡም ባህላችነን አጠፋብን እያለ እያዘነ ነው" ይላሉ፡፡ አቶ ደስታው አባይነውም (ቃመ፣ ታህሳስ 28/ 2008) ፡-

> እኔ ወላጆቼ ከእናትና አባታቸው የወረሷቸውን ጥሩ ጥሩ ባህሎች እያስተማሩኝ ነው ያሳዳጉኝ፡፡ ትልቅን ማክበር፣ በመንገድ ላይም አዋቂዎችን ቆሞ ማሳለፍ፣ አባቶች ያቆዩትን ባህል ማክበር፣ ታሪክን መጠበቅ ያሳድጋል፣ ዕድሜ ይጨምራል እየተባልን ነው ያደግነው፡፡ አሁን እኔ እንደማየው ግን ብዙ ልጆች ወላጆች የሚነግሯቸውን እሽ አይሉም፡፡ ስለድሮው ባህል ስንነግራቸው ይስቁብናል፡፡ ከተማ አካባቢ የሚኖሩትም የገጠር ልጆችም ወደ ከተማ እየሄዱ መጥፎ ነገር ይሰራሉ፤ ትምርት ቤት ሳይሆን ጫትና ፊልም ቤት ይውላሉ፡፡ ብዙ ወጣቶች አካባቢያችንን ለመጎብኘትና ወደ ጎንደር ለማለፍ የሚመጡ የውጭ ዜጋዎችን ሲከተሉ ነው እሚውሉት፡፡ እነሱን እያዩ እንደነሱ ለመሆን በፆም ቀን ጠዋት ተነስተው ያገኙትን ሁላ ይበላሉ፣ ፀጉራቸውን ያጎፍራሉ፣ ሱሪያቸውን ዝቅ ዝቅ ያረጋሉ፡፡ ውሏቸው ሁላ ፊልም ቤት ስለሆነ ማህበረሰቡ የማይናገረውን የብልግና ቃላት ይናገራሉ፡፡ ስንነግራቸውም ምናገባችሁ ይሉናል፡፡ እና የድሮው ባህላችን እየጠፋ ስለሆነ ያሳዝናል፡፡

በማለት የወ/ሮ ስመኝን ሃሳብ ይጋራሉ፡፡

በአጠቃላይ የማህበረሰቡ ባህሎች በለውጥ ሂደት ላይ ያሉ ናቸው፡፡ ስለሆነም እዚህ ቦታ ላይ ለማንሳት የተሞከረው የተወሰኑ ለውጦችን ለማሳየት ያህል እንጅ የተለወጡት ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች ብቻ ናቸው ማለት አይደለም፡፡

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠኘውን አካባቢና ማህበረሰብ ለማስተዋወቅ ተሞክሯል፡፡ ከዚህ በሚከተሉት ተከታታይ ሶስት ምዕራፎች ደግሞ ከማህበረሰቡ የተሰበሰቡ ነውሮች የመረጃ አቅርቦት፣ ትንተናና ውጤት ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## የምግብ ነውሮች የመረጃ አቅርቦት፣ ትንተናና ውጤት ፦

ይህ ምዕራፍ የሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ ስለምግብ አይነቶች ምርጫ፣ አዘገጃጀት አመጋገብና ከዚሁ ጋር ስለተያያዙ ነውሮች ያለውን ባህላዊ አስተሳሰብ፣ እውቀት፣ ልምድና ትግበራ በሚመለከት ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች ቀርበው የተተነተኑበትና በመጨረሻም የተገኙ የጥናቱ ዋና ዋና ውጤቶች ተጠቃለው የቀረቡበት ነው፡፡

## 5.1 የመረጃ አቅርቦትና ትንተና

ምግብ ፦ በእለት ተለት ህይወታችን ውስጥ በየቤታችን ከምንመገባቸው ጀምሮ በአደባባይ በጋራ እስከምንጠቀምባቸው ድረስ ያሉትን የተለያዩ የምግብና መጠጥ አይነቶችን፣ አዘገጃጀታቸውንና አመጋገባቸውን ሁሉ የሚያጠቃልል ሰፊ ጽንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት ውስጥ ምግብ ሲባል የምግቦቹን አዘገጃጀትና አመጋገብም ያካተተ ነው፡፡

የምግብ አዘገጃጀት ሲባል በዋናነት ምግብ እንዴት ይዘጋጃል? እነማን ያዘጋጁታል? ለነማን ይዘጋጃል ? የሚሉ ጉዳዮችን የሚመለከት ነው፡፡ አመጋገብ ሲባል ደግሞ የተዘጋጀው ምግብ እንዴት ይቀርባል? እንዴት ይበላል? ምን ላይ ተሁኖ ይበላል? የተመጋቢዎቹ አቀማመጥ ምን ይመስላል? ተመጋቢዎቹ እነማን ናቸው? የሚሉ ጉዳዮችን የሚመለከት ነው፡፡

በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ከምግብ አይነት ምርጫ ጋር የተያያዙ ነውሮች ሲባል ማህበረሰቡ ባህሉን መሰረት በማድረግ በነውርነት የሚፈርጃቸውን የምግብ አይነቶች ማለት ነው፡፡ ከምግብ አዘገጃጀት ጋር የተያያዙ ነውሮች ሲባል ደግሞ ከአዘጋጅዎቹና ከሚዘጋጅላቸው ሰዎች ማንነት ጋር በተያያዘ ማህበረሰቡ በነውርነት የሚፈርጃቸውን ድርጊቶች የሚመለከት ነው፡፡ ከአመጋገብ ጋር የተያያዙ ነውሮች ሲባልም በአመጋገብ ስር የሚካተቱ በሚል ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ማህበረሰቡ ነውር የሚላቸውን ድርጊቶች ለማለት ነው፡፡

## 5.1.1 የምግብ አይነት ምርጫና ተያያዥ ነውሮች እውቀት፣ ልምድና ትግበራ

"ነውሩን የበላ ጥርሱ ይሰበራል - በቁምጥና በሽታ ይያዛል"፡፡

(አቶ ገብረአብ ደሴ፣ ቃመ፣ ታህሳስ 15/2008)

የሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ እንደአካባቢው መልክዓምድርና የአየር ሁኔታ የተለያዩ የምግብ እህሎችን ያመርታል፡፡ በአካባቢው በስፋት ከሚገኙትና ለምግብነት ከሚውሉት መካከል ስጋ፣ ወተትና የወተት ተዋፅኦዎች፣ ጤፍ፣ ገብስ፣ አተር፣ ሽምብራ፣ ማሽላ፣ ባቄላ፣ ጓያ፣ ሩዝ፣ ተልባ፣ ፓፓያ፣ አናናስ፣ ሙዝ፣ ማንጎ፣ ድንች፣ ሸንኩርት፣ ቲማቲም፣ ማር፣ ቡና የመሳሰሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ይሁን እንጅ ማህበረሰቡ ከፍ ሲል የተጠቀሱትና መሰል በአካባቢው የሚገኙት የእህል፣ የእንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ወዘተ. ዘሮች ሁሉ ጠቃሚ ናቸው ብሎ አያምንም፡፡ ስለሆነም የማህበረሰቡ የምግብ ምርጫ እንዲሁ በዘፈቀደ የሚከናወን ሳይሆን አካባቢያዊ ባህልንና እውቀትን መሰረት አድርጎ የሚፈፀም ነው፡፡

የሊቦ ከምከም ወረዳ አንዳንድ የምግብ አይነቶች ሊበሉ (ለምግብነት ሊውሉ) የማይገባቸው ናቸው ብሎ የሚያምን፤ ለምን እንደማይበሉም የራሱ ምክንያቶች ያሉትና ለዚህም ገዥ የሆኑ የምግብ ነውሮችን የሚፈጥር ማህበረሰብ ያለበት አካባቢ ነው፡፡ ማህበረሰቡ የፈጠራቸው የምግብ ነውሮች ተቀባይነትና ቀጣይነት እንዲኖራቸውም አካባቢያዊ እውቀቱንና በተደጋጋሚ ሙከራ ያዳበራቸውን ልምዶቹን ተጠቅሞ የራሱን ማብራሪያ ያቀርባል - እንዳይጣሱም ጥበቃ ያደርጋል፡፡ በዚሁ ክፍል መነሻ ላይ የቀረበው አባባልም ማህበረሰቡ ነውሮቹን የሚያስቀጥልባቸው የተለያዩ ስልቶች እንዳሉት አንዱ ማሳያ ነው፡፡

ይሂ ማለት ግን ነውር የሚባሉ የምግብ አይነቶች ለምን ነውር እንደተባሉና ነውሮች ሊኖራቸው ስለሚችል ጥቅምና ጉዳትም ሁሉም የማህበረሰቡ ክፍል በቂ መረጃ አለው ማለት አይደለም፡፡ በዕርግጥ! ብዙው ሰው አንዳንድ የምግብ አይነቶች ለምን ነውር እንደሆኑ የየራሱ ሆነ የሚሰጠው ምክንያት እንዳለውና አንዳንዶቹ ግን ነውር ስለመሆናቸው እንጅ ለምን ነውር እንደሆኑ እንደማያውቁ በመረጃ ስብሰባ ወቅት መገንዘብ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ግን ብዙው ሰው ነውሮች ከጥቅም ባለፈ ጉዳትም ሊኖራቸው ይችላል የሚል እምነት እንደሌለው ከማህበረሰቡ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ፦ የነውሮች ጥቅምና

ጉዳት ምንድነው? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ ከሰጡ ሰዎች መካከል ወ/ሮ ስመኝ አዳነ (ቃመ፣ ታህሳስ 28/2008) "ደሞ ከጥቅም በቀር ምን ጉዳት አላቸው?" ይላሉ፡፡ እንደ ወ/ሮ ስመኝ ነውሮች የአካባቢው ማህበረሰብ ከቀደምቶቹ የወረሳቸው፣ እሱም በየጊዜው የሚፈጥራቸውና ወጣቱ ትውልድ ታላለቆቹ ያቆዩትን ባህል እንዲያከብርና እንዲጠብቅ የሚያስተምርባቸው ናቸው፡፡ ይህን ሃሳብ አቶ ሙሉቀን ዘውዱ (ቃመ፣ የካቲት 7/2008) እና ወ/ሮ የምስራች ወርቁም (ቃመ፣ ግንቦት 21 /2008) ይጋሩታል፡፡

ከፍ ሲል የተጠቀሰው አባባልም ሆነ ከምግብ አይነት ምርጫ ጋር በተያያዘ ከማህበረሰቡ የተሰበሰቡትና ከዚህ በታች የቀረቡት ነውሮች ማህበረሰቡ ስለምግብና ተያያዥ ነውሮች ያለው እውቀትና ልምድ ምን እንደሚመስል ከፍ ሲል በመንደርደሪያነት የቀረበውን ሃሳብ የሚያጎለብቱ ናቸው፡፡

ማህበረሰቡ ስለምግብ ያለውን እውቀትና ልምድ ለመረዳት የሚያስችሉ 25 የሚሆኑ የምግብ ነውሮች ተሰብስበዋል፡፡ ይሁን እንጅ የተሰበሰቡትን ነውሮች ሁሉ እዚህ ቦታ ላይ አንድ በአንድ መዘርዘር ቦታው አይደለም፡፡ በመሆኑም ከመስክ የተሰበሰቡት ሁሉም የምግብ ነውሮች ነውር የሆኑ የምግብ አይነቶችንና ነውር የሆኑበትን ምክንያት በሚገልጽ መልኩ በአባሪ - አንድ "ሀ" ውስጥ ከተራ ቁጥር 1- 25 ቀርበዋል፡፡

በዚሁ መነሻነትም በአባሪ "ሀ" ውስጥ የሰፈሩት ነውሮች ከነውር አጠቃላይ አይነቶች አኳያ ሲታዩ እንዴት ሊመደቡ እንደሚችሉ፣ የነውሮቹ ዋነኛ ትኩረት በየትኞቹ የማህበረሰቡ ክፍሎች ላይ እንደሆነና ለየነውሮቹ የተሰጡ ምክንያቶች ባላቸው የጋራ ባህሪ ሲደራጁ ምን ገፅታ እንዳላቸው ከዚህ በታች ጥቅል መረጃ ቀርቧል፡፡

በአባሪ "ሀ" ውስጥ የቀረቡት መረጃዎች ከነውር አይነቶች አኳያ ሲታዩ የማህበረሰቡ የምግብ ነውሮች ቋሚ እና ጊዜያዊ በሚል ምድብ የሚካተቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም በአባሪው ውስጥ ከቀረቡት መካከል 15 የሚሆኑት (በተራ ቁጥር 1፣ 2፣ 3፣ 4፣ 5፣ 15፣ 16፣ 17፣ 18፣ 19፣ 20፣ 21፣ 22፣ 24ና 25 ስር የተጠቀሱት) ከቋሚ ፤ 10ሩ ደግሞ (በተራ ቁጥር 6፣ 7፣ 8፣ 9፣ 10፣ 11፣ 12፣ 13፣ 14ና 23 ስር የቀረቡት) ከጊዜያዊ የምግብ ነውሮች ሊመደቡ የሚችሉ ናቸው፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ቋሚ የምግብ ነውሮች የሚባሉት ለማህበረሰቡ አባላት በሙሉ ወይም ከማህበረሰቡ አባላት መካከል ለተወሰኑ ክፍሎች (ለግለሰቦች፣ ለአንድ የቤተሰብ አባላት) ሁልጊዜ ወይም በቋሚነት ክልክል የሆኑ ምግቦችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ጊዜያዊ የሚባሉት ደግሞ ከማህበረሰቡ አባላት መካከል ለተወሰኑ ክፍሎች ወይም ለማህበረሰቡ አባላት በሙሉ ለተወሰነ ጊዜ (ለምሳሌ፡- በእርግዝና፣ በተወሰነ የዕድሜ እርከን፣ በህመም፣ በፆም ወዘተ. ወቅት) ክልክል የሆኑ ምግቦችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡

በአባሪው ውስጥ የቀረቡት ነውሮች በማህበረሰቡ የተለያዩ አባላት ላይ የሚተገበሩ ሲሆኑ፣ ነውሮቹ ትኩረት ያደረጉባቸውን የማህበረሰቡ አባላት፣ ነውሮቹ በአባሪ ክፍሉ ውስጥ የሚገኙበትን ተራ ቁጥርና በየምድቡ ውስጥ የሰፈሩ ነውሮችን ብዛት በሚያሳይ መልኩ በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡

**ሰንጠረዥ - 1 ነውሮች ትኩረት ያደረጉባቸው የማህበረሰቡ አባላት፡-**

| ተ/ቁ | የነውሮቹ ትኩረት የሆኑት የማህበረሰቡ አባላት | ነውሩ በአባሪው ውስጥ የሚገኝበት ተራ ቁጥር | የነውር ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት | 1፣2፣3፣4፣5፣9፣18፣22፣23ና 25 | 10 |
| 2 | በእርግዝና ላይ ያሉ እናቶች | 7፣8፣10፣11፣12፣13ና 14 | 7 |
| 3 | ሴቶች | 16፣17፣19ና 20 | 4 |
| 4 | ወንዶች | 15፣21ና 24 | 3 |
| 5 | አዲስ የተወለዱ ህፃናት | 6 | 1 |

ይህ ጥናት አይነታዊ እንደመሆኑ በምልከታ፣ በቃለመጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት የተሰበሰቡት መረጃዎች በጭብጥ እየተከፋፈሉ የመላሾች ምክንያት ተጨምቆ ሊቀርብ ይገባል፡፡ በዚሁ መሰረትም ከመስክ ለተሰበሰቡትና በአባሪው ውስጥ ለሰፈሩት ከምግብ ምርጫ ጋር የተያያዙ ነውሮች ማህበረሰቡ የሰጣቸው ምክንያቶች ባላቸው የጋራ ባህሪ ሲደራጁ በ4 ጭብጦች ተከፍለው ሊቀርቡ የሚችሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም በ4 ጭብጦች ስር የተጠቃለሉት ምክንያቶች ነውሮቹ በአባሪ ውስጥ የሚገኙበትን ተራ ቁጥርና በየምድቡ ውስጥ የሰፈሩ ነውሮችን ብዛት በሚያሳይ መልኩ በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡

**ሰንጠረዥ - 2 ለነውሮች ማህበረሰቡ የሰጣቸው ምክንያቶች፦**

| ተ/ቁ | የነውሩ ምክንያት | ነውሮቹ በአባሪው ውስጥ የሚገኙበት ተራ ቁጥር ከ --- እስከ --- | የነውር ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ጤና | 1 - 14 | 14 |
| 2 | ትዳር | 15 — 20 | 6 |
| 3 | ድርቅና ድህነት | 21 - 23 | 3 |
| 4 | አለመረጋጋት | 24 - 25 | 2 |

በዚሁ መሰረትም ከመስክ ከተሰበሰቡትና በሰንጠረዥ ላይ በ4 በጭብጥ ተከፋፍለው ከቀረቡት 25 መረጃዎች መካከል ሌሎችን ይወክላሉ የተባሉ 12 ነውሮችና ነውር ለመሆናቸው የተሰጡ ምክንያቶች በማሳያነት ቀርበው ከዚህ በታች አጭር የመረጃ ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡

## 5.1.1.1 የጤና መታወክን የሚያስከትሉ የምግብ አይነቶች

ተጠኝው ማህበረሰብ ሁሉም የምግብ ዘሮች ለጤንነቴ ጠቃሚዎቼ ናቸው የሚል እምነት የለውም፡፡ በመሆኑም፤ ማህበረሰቡ ከጤና ጋር በተያያዘ ነውር ከሚላቸውና በአባሪ አንድ “ሀ” ውስጥ ከቀረቡት የምግብ አይነቶች መካከል ተልባ፣ ባቄላ፣ ስጋ፤ እንገርና ሙዝ በማሳያነት ቀጥሎ ተገልጸዋል፡፡

**ተልባ** ፦ ፍሬው ቅባትነት ያለው እህል ነው፡፡ ተልባ በሚቆላበት፣ በሚወቀጥበትና በሚበላበት ጊዜ ሽታው ከፍተኛ ነው፡፡ ስለሆነም፤ በተጠኝው ማህበረሰብ ዘንድ የተልባ ሽታ [እ]ርኩስ መንፈስን የመጥራት ሃይል አለው ተብሎ ይታመናል፡፡ በማህበረሰቡ እምነት ተልባ የ[እ]ርኩስ መንፈስ ማደሪያ ነው፡፡ በዚህ ባህሪው ምክንያትም፤ ትምህርት እንዲገባ፣ ጠላት እንዳያጠቃ ወዘተ. በሚል ድግምት ያሰሩ ሰዎች፤ በአንድ ወቅት በቡዳ መንፈስ ተይዘው የዳኑ ሰዎች፣ የበረድ ደጋሚዎች በእድሜ ዘመናቸው ሁሉ ተልባን አይመገቡም፡፡ ምክንያቱም ተልባ ድግምትን የመሻር፣ የዳነ ህመምን የመቀስቀስ፣ በሽታን የመደበቅ ሃይል ስላለው የድግምት ያሰሩ ሰዎች እሱን ከበሉ የተደረገላቸው ድግምት አይሰራም፡፡ ይሄን በሚመለከት መረጃ ከሰጡ ሰዎች መካከል አቶ ገብረአብ ደሴ (ቃመ፣ ታህሳስ 25/2008)

በአንድ ወቅት በቡዳ መንፈስ ተይዘው የዳኑ ሰዎች ከተመገቡትም ይዟቸው የነበረው የቡዳ መንፈስ ተመልሶ ይይዛቸዋል፡፡ ተልባን በጊዜያዊነት የሚከለክሉ የማህበረሰቡ አባላትም አሉ፡፡ ሰዎች በቡዳ መንፈስ መያዛቸው ከታወቀ "መንፈሱ ከታማሚዎቹ ለቆ እስኪወጣ"[10] ድረስ በመንፈሱ የታመሙት ሰዎች ተልባ እንዲበሉ አይፈቀድም፡፡ ምክንያቱም ተልባ ከበሉ የያዛቸው የቡዳ መንፈስ ይደበቃል፣ ያደፍጣል፣ ታማሚዎቹ እንዳይለፈልፉ አፋቸውን ይዘጋቸዋል ይላሉ፡፡

እንደ አቶ ገብረአብ የበረድ ደጋሚዎችም ተልባን አይመገቡም፡፡ ምክንያቱም እሱን ከበሉ "የደገሙት የበረድ ድጋም አይሰራም"፡፡ ተልባ ሰዎች ትምህርት እንዳይገባቸው፣ የማሰብ ሃይላቸው ደካማ እንዲሆን ሁሉ ያደርጋል፡፡ ስለሆነም በተጠኝው ማህበረሰብ ዘንድ ተልባ ከፍ ሲል ለተጠቀሱት አይነት ሰዎች ብቻም ሳይሆን ለአጠቃላዩ የማህበረሰቡ አባላትም ለሽያጭ ካልሆነ በቀር ለምግብነት ተመራጭ አይደለም፡፡ ለምግብነት መዋል ካለበት እንኳ ሰው ከመቅመሱ አስቀድሞ በሚቆላበትም ሆነ በሚወቀጥበት ጊዜ ከተልባው ጥቂት ቆንጥሮ መሬት ላይ መድፋት (ለመሬቱ ማቅመስ) ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ሽታው ጠርቶት የመጣው ክፉ መንፈስ መሬት ላይ የተደፋውን ቀምሶና ረክቶ ስለሚመለስ ቀጥሎ ለሚመገበው ሰው የክፉ መንፈስ ጥንውት አያሰጋውም (ወ/ሮ በለጡ ካሴ፣ ቃመ፣ ታህሳስ 25/2008 ፤ ወ/ሮ ስመኝ አዳነ፣ ቃመ፣ ታህሳስ 28/2008)፡፡ በዚህም ምክንያት ማህበረሰቡ ተልባን የማምረት ፍላጎቱ ዝቅተኛ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ተልባ ምርቱ ትንሽ የሆነ (ብዙም ውጤት የሌለው)፣ ለምነት ያለው መሬትም የማይመቸው ተደርጎም ይወሰዳል፡፡ ስለሆነም ማህበረሰቡ እሱን ማምረት ካለበት እንኳ የሚዘራው ለሌላ እህል ብዙም ምቹ ያልሆኑና የአፈር ለምነታቸውም ዝቅተኛ የሆኑ ጠጠራማ ማሳዎችን መርጦ ነው፡፡ በተዘራ ሌላ እህል ዳር ለዳር በመዝራት እህሉን ሊበሉ የመጡ እንሰሳት ከተልባው ላይ እንዲጀምሩ በማድረግ ከመሃል የተዘራውን እህል ከእንሰሳቱ ለመታደግ እሱን እንደጊዜያዊ መከላከያ አጥር ለመጠቀም የሚዘሩትም አሉ፡፡

**ባቄላ** ፦ ብዙውን ጊዜ በሽሮ፣ በአሹቅና በንፍሮ መልክ ለምግብነት የሚውል የአበባ እህሎች ወገን ሲሆን፤ ይህ የእህል አይነት ብዙ ጊዜ በማህበረሰቡ ለምግብነት የሚመረጥ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በማህበረሰቡ ውስጥ ባቄላን መመገብ ለዳፍንት በሽታ እና ለሆድ ቁርጠት ይዳርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ ከሚያምኑት መካከል አቶ ካሴ መንግስቱ

[10] መንፈሱ በታማሚዎቹ አማካይነት ለቅቄያለሁ ብሎ እስኪለፈልፍ ድረስ ለማለት ነው፡፡

(ቃመ፣ የካቲት 7/2008) የተባሉ መረጃ ሰጭ አንድ ሰው ባቄላ በመብላቱ አይኑ እንደጠፋ ልጅ እያሉ ከወንድ አያታቸው እንደሰሙ ይናገራሉ፡፡ አቶ ሞገስ ይሁነኝ (ቃመ፣ የካቲት 7/2008 ) የተባሉ መረጃ ሰጭም ባቄላ ለሽያጭ ካልሆነ በቀር ለምግብነት የሚመረጥ እህል አለመሆኑን በመግለፅ የአቶ ካሴን ሃሳብ ይጋራሉ፡፡ ወ/ሮ ማርታ ተሰማ (ቃመ፣ የካቲት 8/2008) የተባሉ መረጃ ሰጭም ባቄላ በማህበረሰቡ ዘንድ የተጠላ መሆኑን "ከልጅ ክፉ ዲቃላ - ከእህል መጥፎ ባቄላ" በሚል አባባል ገልፀውታል፡፡ ይህ አባባል ማህበረሰቡ ለባቄላ ያለውን ጥላቻ የሚያሳይ ነው፡፡

በሌላ በኩል ግን አብዛኛው ሰው የማይመገበው ቢሆንም አንዳንድ ሰዎች አሁን አሁን የቆየውን የማህበረሰቡን ደንብ በመጣስ ባቄላን ለምግብነት እየተጠቀሙበት እንደሆነ መረጃ የሰጡ ሰዎችም አሉ፡፡ ለምሳሌ፦ ወ/ሮ ማርታ ተሰማ (ቃመ፣ የካቲት 7/2008) የተባሉ መረጃ ሰጭ አሁን አሁን ድህነትም እየሰፋ ስለመጣና ወጣቱም ቢበላ ደሞ ምን ችግር አለው በማለት እየበላው እንደሆነና በዚህም እንደሚያዝኑ ይገልፃሉ፡፡ ሆኖም ግን አብዛኞቹ መረጃ ሰጭዎች እንደሚስማሙበት ባቄላ አሁንም ድረስ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈራና ለምግብነት የማይመረጥ የምግብ አይነት ነው፡፡ ባቄላ ለምግብነት መዋል ካለበት እንኳ ከሌሎች እህሎች ጋር ተደባልቆ እንጅ ብቻውን ለምግብነት የሚመረጥ አይደለም፡፡

ስጋ ፦ በተጠኝው ማህበረሰብ እምነት ስጋ ተመጋቢዎቹን ለተለያዩ በሽታዎች የማጋለጥ አጋጣሚው ከፍተኛ ነው፡፡ ስለሆነም በማህበረሰቡ ውስጥ ስጋ በዘፈቀደ የሚመገቡት ሳይሆን የሚበላውን እንሰሳ አይነት፣ ባህሪ፣ የቆዳ ቀለም ወዘተ. ሁሉ በጥንቃቄ መፈተሽን የሚጠይቅ ነው፡፡ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በተለይም ጥቁር የቆዳ ቀለም ያላቸው እንሰሳት ስጋ በማህበረሰቡ ዘንድ ለምግብነት ተመራጭ አይደሉም፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ጥቁር ቀለም የመጥፎ፣ የክፉ፣ ቅዱስ ያልሆኑ ነገሮች ተምሳሌት ነው፡፡ ስለሆነም በአካባቢው ከሚገኙና ሊታረዱ ከሚችሉ የቤት እንሰሳት መካከል ጥቁር የቆዳ ቀለም ያላቸው እንሰሳት (ለምሳሌ፦ በግ፣ ፍየል፣ ዶሮ፣ ከብት) የ[እ]ርኩስ መንፈስ ማደሪያ ናቸው ተብሎ ስለሚታሰብ እንዲበሉ ያልተፈቀዱ ናቸው፡፡ እነሱን ለምግብነት መጠቀም ለመጥፎ መንፈስ ስለሚያጋልጥ በተመጋቢዎቹ ላይ አይነስውርነትን ያስከትላል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከመረጃ ሰጭዎች መካከል ወ/ሮ አያልነሽ ብርሃኑ (ተተኳሪ የቡድን

ውይይት[11]፣ ሚያዚያ 30/2008) ጥቁር የቆዳ ቀለም ያላቸውን እንሰሳት ስጋ በመብላት ደርሷል ተብሎ በአንድ ወቅት ከእናታቸው የተነገራቸውን አንድ ገጠመኝ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

> ሚካኤል ደብር በሚባለው ቀበሌ ውስጥ አንድ ባልና ሚስት ይኖሩ ነበር፡፡ እነሂ ባልና ሚስት በቅዱስ ዮሃንስ (የዘመን መለወጫ) በዓል እለት ጥቁር ፍየል አርደው ሲበሉና ሲጠጡ ከዋሉ በኋላ ተኙ፡፡ በጠዋት ከእንቅልፋቸው ሲነሱ ግን የባልና ሚስቱ አይን ጠፍቶ ተገኘ፡፡ የአካባቢው ሰውም አይናቸው የጠፋው ጥቁር ቀለም ያለው ፍየል ስላረዱ የቤታቸው ቆሌ ተጣልቷቸው ነው ብሎ አመነ፡፡ ከዚያን ግዜ ጀምሮም የአካባቢው ሰው አይናችን ይታወራል ብሎ ስለሚፈራ ጥቁር የቆዳ ቀለም ያላቸውን እንሰሳት በተለይም በአመትባል ግዜ ማረድ አቆመ፡፡

ከዚህ በመነሳትም የአካባቢው ማህበረሰብ ጥቁር የቆዳ ቀለም ያላቸውን እንሰሳት በጉልበታቸው፣ በወተትና የወተት ተዋፅኦዎቻቸው ከመጠቀምና ለሽያጭ ከማዋል በቀር ስጋቸውን አይመገብም፡፡

**እንገር** ፦ ሰዎች፣ የቤት እንሰሳት … እንደወለዱ የሚያወጡት የመጀመሪያው ወፍራም ወተት ሲሆን፤ በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ ይህ የምግብ አይነት ተፈላጊነት የለውም፡፡ ማህበረሰቡ በእርግዝና ጊዜ በተለይም በወሊድ ሰዓት እናቶችን እንደሰይጣንና አጋንንት የመሰለ መጥፎ መንፈስ ይፈታተናቸዋል - ከአጠገባቸውም አይርቅም ብሎ ያምናል፡፡ በዚህ እምነቱ ምክንያትም እንገር የተሰኘውን የእናት ጡት የመጀመሪያ ወተት ገና የተወለዱ አዲስ ልጆች እንዲወስዱት አይፈልግም፡፡ ከተወሰደም እሱን የወሰዱ ልጆች ጉሮሯቸው ይቆስላል ተብሎ ይታመናል፡፡

ለዚህም ማህበረሰቡ የራሱ የሆነ ማብራሪያ አለው፡፡ እንደ ወ/ሮ ዳሳሽ እምሩ እና ወ/ሮ በለጡ ካሴ (ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ የካቲት 10/ 2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው) በወሊድ ጊዜ እናቲቱን ለመፈታተን ከአጠገቧ ያለው ክፉ መንፈስ ልጆች ሲጠቡ ሲያይ ስለሚቀና ለህመም ይዳርጋቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ ምክንያትም እናቶች እንደወለዱ ልጆች ከመጥባታቸው በፊት የመጀመሪያውን ወተት መሬት ላይ ያፈሳሉ፡፡ ምክንያቱም በአጠገባቸው ያለው ቀናተኛ ክፉ መንፈስ መሬት ላይ የፈሰሰውን

[11] ወ/ሮ አያልነሽ የተተኳሪ የቡድን ውይይት ቡድን - ሶስት (የቡድን አባላቱ ዝርዝርና የቡድኑ መለያ ቁጥር በአባሪ ገፅ ላይ ሰፍሯል) አባል ሲሆኑ፤ ከቡድኑ አባላት መካከል ከፍ ሲል የእሳቸው ስም ብቻ የቀረበው በአንድ በኩል የተጠቀሰውን ሃሳብ አጉልተው የተናገሩት እሳቸው መሆናቸውን ለመግለፅና በሌላ በኩልም የሁሉንም አባላት ስም ዝርዝር እንዳለ ማቅረብ አስፈላጊነት የለውም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጅ ሃሳቡን ሌሎቹም የቡድኑ አባላት በጋራ የተስማሙበት ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት ውስጥ በተተኳሪ የቡድን ውይይት ከተሳተፉት መካከል የተጠቀሰው ከቡድኑ መካከል የአንድ ሰው ስም ብቻ ሆኖ ሃሳቡ ግን የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው፡፡

ቀድሞ ስለሚቋደስ በልጆች ላይ ጉዳትን አያመጣባቸውም፡፡ ስለሆነም እናቶች የተጠቀሰውን መሬት ላይ የማፍሰስ ስርዓት ካከናወኑ በኋላ ቀጣዩን ወተታቸውን ያለስጋት ለልጆቻቸው ይሰጣሉ፡፡

ለማሳያ ያህል እናቶች ሲወልዱ የሚፈፅሙት ጉዳይ ተነሳ እንጅ በማህበረሰቡ ውስጥ የቤት እንሰሳት ሲወልዱም ቀደም ሲል የተነሳው የክፉ ርኩስ መንፈስ ጉዳይ እዚህ ላይም ይነሳል፡፡ በመሆኑም እንደ ላም፣ ፍየል፣ በግ የመሳሰሉ እንሰሳት በሚወልዱበት ጊዜም የመጀመሪያው ወተታቸው መሬት ላይ እንዲፈስ ይደረጋል፡፡

**ሙዝ** ፡- በተጠኘው ማህበረሰብ አካባቢ በብዛት ይመረታል፡፡ በመሆኑም የአካባቢው ማህበረሰብ ይህን የፍራፍሬ አይነት በስፋት ለምግብነት ይጠቀምበታል፡፡ ይሄ ማለት ግን ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ያለገደብ የሚጠቀሙት የምግብ አይነት ነው ማለት አይደለም፡፡ በእርግዝና ላይ ያሉ እናቶች ሙዝን እንዲመገቡ የአካባቢው ልማድ አይፈቅድም፡፡ ምክንያቱም እናቶች በእርግዝና ላይ እያሉ ሙዝ ከበሉ የውርጃ ችግር ያጋጥማቸዋል፤ እንደአጋጣሚ ሆኖ ውርጃ ባያጋጥማቸው እንኳ ሙዝ ጽንስን የማፋፋት ባህሪ ስላለው በወሊድ ወቅት እናቶች በቀላሉ መውለድ እንዳይችሉ ያደርጋል (ወ/ሮ ማርታ ተሰማ፣ ቃመ፣ የካቲት 7/2008 ፤ ወ/ሮ በለጡ ካሴ፣ ቃመ፣ የካቲት 8/2008)፡፡ ስለሆነም በማህበረሰቡ ውስጥ ሙዝ በእርግዝና ላይ ላሉ እናቶች የሚፈቀድ የምግብ አይነት አይደለም፡፡

ይሄ ማለት ግን እዚህ ቦታ ላይ ሙዝ በማሳያነት ተነሳ እንጅ ከመስክ የተሰበሰቡና በአባሪ ውስጥ የቀረቡት መረጃዎች እንደሚያሳዩት ሩዝ፣ ጨው፣ እንቁላል፣ አሳ፣ ፓፓያና አናናስም በእርግዝና ላይ ያሉ እናቶች እንዲመገቧቸው የሚፈቀዱ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም ከተመገቧቸው የሚወለዱት ልጆች የቆዳ ቁስለት ያለባቸው፣ በቀላሉ ለበሽታ የሚጋለጡ እንዲሆኑ ፤ በእናቶች ላይ የምጥ መጥበቅን፣ የአተነፋፈስ ችግርን፣ ውርጃን፣ በወሊድ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ የደም መፍሰስን ወዘተ. ያስከትላሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

በእርግዝና ላይ ያሉ ሴቶች የሚከለከሏቸው የምግብ አይነቶችና ለክልከላዎቹ የሚሰጡ ምክንያቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ሴቶች በእርግዝና ላይ ሲሆኑ ከበርካታ የምግብ አይነቶች እንደሚታቀቡ፣ የሚመገቡትን የምግብ መጠንም እንዲቀንሱ እንደሚፈለግ የሚያመላክቱ

ናቸው፡፡ "ስትወልድ የምትበላውን በእርግዝናዋ ጨረሰችው" የሚለው የማህበረሰቡ የተለመደ አባባልም የዚሁ አንድ ማሳያ ነው፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚያሳዩት በማህበረሰቡ ውስጥ አንዳንድ የምግብ አይነቶች የጤና መታወክን ብቻ ሳይሆን የትዳር አጋር ማጣትንም የሚያስከትሉ ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡

### 5.1.1.2 የትዳር አጋር ማጣትን የሚያስከትሉ የምግብ አይነቶች

በማህበረሰቡ ውስጥ ትዳር መመስረት የሚፈለግና የሚከበር ጉዳይ ሲሆን፤ በተለይም ሴቶች ቶሎ ወደትዳር እንዲገቡ ይፈለጋል፡፡ ምክንያቱም ሴት ልጅ ቶሎ ካላገባች ባለጌ ትሆናለች፣ የወንድ ጓደኛ ይዛ ላልተፈለገ እርግዝናና ለበሽታ ትጋለጣለች፣ ቤተሰቧንም ታሰድባለች ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ ምክንያትም ማህበረሰቡ ወደትዳር ያልገቡ ሴቶችን ትዳር ለመያዝ የሚያስችል ዕድሜ ላይ ቢደርሱም ባይደርሱም በተለያዩ ስነቃሎቹ አማካይነት በመቀስቀስ ወደ ትዳር እንዲገቡ ይገፋፋል፡፡ ይሄን አስመልክቶ ከመረጃ ሰጭዎች መካከል አቶ በየነ ምናሉ (ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ የካቲት 7/2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው) "ባል የሌላት ሴት የመንገድ ላይ እሸት" ናት በማለት ይገልፃሉ፡፡ ይሁን እንጅ ወደትዳር ህይወት መግባት ብቻውን የማህበረሰቡን ፍላጎት ሙሉ አያደርግም፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ትዳር ከተያዘ በኋላ ከትዳር አጋር ጋር ጸንቶ መኖር ትዳር ከመመስረትም በላይ የሚፈለግና የሚከበር ትልቅ ነገር ነው፡፡

ማህበረሰቡ የሚያከብረውና በህይዎቱ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ትዳር አንዳች እንከን እንዲገጥመው አይፈልግም፡፡ ማህበረሰቡ ሴት ልጅ ቶሎ ወደትዳር መግባት አለባት ብሎ እንደሚያምን ሁሉ በትዳሯ ፀንታ የመኖር ችግር ያለባትም ብዙ ጊዜ ሴት ልጅ ናት ብሎም ያምናል፡፡ አግብተው የፈቱ ሰዎች (በተለይም ሴቶች) በማህበረሰቡ ዘንድ ለሌሎች ሰዎች ፍችን የሚያስተምሩ፣ ለማህበረሰቡ ጥሩ አርዓያ የማይሆኑ ተደርገው ይታሰባሉ፡፡ እንደ ወ/ሮ አይናለም ግርማ (ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ የካቲት 10/2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው) አግብተው የፈቱ ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ የጥሩ ነገር ምሳሌ፣ የጥሩ ዝምድና መፍጠሪያ ተደርገው ስለማይታሰቡ በቀጣይ ሌላ የትዳር አጋር የማግኘት ዕድላቸው ጠባብ ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም ማህበረሰቡ ወደትዳር የገቡ ሴቶች ህይወታቸውን ከትዳር አጋራቸው ጋር ማጥበቅ እንዳለባቸው፤ ከባላቸው የተፋቱ ሴቶች ቀጣዩ ህይወታቸው

እንደማያምር ምሳሌያዊ አነጋገሮቹን በመጠቀም ያስጠነቅቃል፡፡ ለምሳሌ ያህል ፦ አቶ ትግስቱ በላይ (ቃመ፣ የካቲት 12/2008) ይህን ጉዳይ "በጋለሞታ ቤት ሁሉ ይጣላበት" በሚል ይገልፁታል፡፡

በማህበረሰቡ ዘንድ ትዳር ተጋቢዎቹ ሲፈልጉ በቀላሉ የሚመሰርቱት፣ ሳይፈልጉ ደግሞ የሚያፈርሱት ሳይሆን አስቀድሞ የአካባቢውን ባህል መሰረት ያደረገ ሰፊ ምክክር ተደርጎበት የሚፈፀም ነው፡፡ ስለተጋቢዎቹ በሚደረገው ምክክር ውስጥ ከሚነሱ የተለያዩ ጉዳዮች መካከል ተጋቢዎቹ ትዳራቸውን ለማስቀጠል የሚያስችል መልካም ባህሪ አላቸው ወይ? የሚለው መሰረታዊ ነገር ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ የተጋቢዎች መልካም ባህሪ የሚገመገምባቸው የተለያዩ መስፈርቶች ያሉ ሲሆን፤ ከመስፈርቶቹ መካከል የተጋቢዎቹ የምግብ ምርጫ ሁኔታ አንዱ ነው፡፡

በማህበረሰቡ እምነት አንዳንድ የምግብ አይነቶች ሰዎች መልካም ጠባይ እንዳይኖራቸውና ከማህበረሰቡ ባህል ያፈነገጡ እንዲሆኑ በማድረግ የትዳር አጋር እንዲያጡ ወይም ትዳራቸውን እንዲያፈርሱ መንስኤ የሚሆኑ ናቸው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ከትዳር ጋር በተያያዘ ነውር ከሚላቸውና በአባሪ አንድ "ሀ" ውስጥ ከቀረቡት የምግብ አይነቶች መካከል ቅልጥም፣ የዶሮ ፈረሰኛና ራስ ምላስ ይገኙበታል፡፡

**ቅልጥም** ፦ በማህበረሰቡ ውስጥ ቅልጥም (የበግ፣ የፍየል፣ የዶሮ) ማንኛውም ሰው ያለገደብ እንዲመገበው የማይፈቀድ የስጋ አይነት ነው፡፡ ቅልጥምን እንዲመገቡት ከማይፈቀድላቸው የማህበረሰቡ አባላት መካከል በዋናነት ሴቶች ይጠቀሳሉ፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ከሴቶች በበለጠ ከባድ ስራ የሚያከናውኑት ወንዶች እንደሆኑና ቅልጥም ደግሞ አካልን የሚያጠነክር ስለሆነ ቅልጥምን መብላት ያለባቸው ወንዶች ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ ቅልጥም የወንድ ልጅ ስለሆነ እሱን የበላች ሴት ልጅ በማህበረሰቡ ዘንድ ባለቤቷን የማታከብር፣ በሴት ወግ ልማድ ያላደገች፣ ወንዳወንድ በመባል ትወገዛለች፡፡ በዚህም የትዳር አጋር እንዳታገኝ ትደረጋለች (ወ/ሮ አይናለም ግርማ፣ ቃመ፣ የካቲት 7/2008፤ እማሆይ ድንቄ ካሳ፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ የካቲት 10/ 2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው )፡፡ ስለሆነም ቅልጥም ሴትነትን ወይም የሴትነትን ባህሪ የሚያሳጣ የስጋ አይነት ተደርጎ ይታሰባል፡፡

ቅልጥም ማህበረሰቡ ከፍተኛ ክብር የሚሰጠው የምግብ አይነት ነው፡፡ በመሆኑም እንደሴቶቹ ሁሉ ለሁሉም ወንዶችም የሚፈቀድ አይደለም፡፡ ከወንዶችም የተለየ ክብር

ለሚሰጣቸው ሰዎች የሚቀርብ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ክብር ከሚሰጣቸው ወንዶች መካከል አማቾች (የልጅ፣ የእህት፣ የዘመድ … ባሎች) ቀዳሚ ናቸው፡፡ በመሆኑም ቅልጥም ክብር የሚሰጠው የስጋ አይነት ስለሆነ እንዲመገበው የሚሰጠውም ለአማች ነው፡፡ ይህን በሚመለከት አቶ ሙሉቀን ዘውዱ (ቃመ፣ የካቲት 7/2008) አማች እያለ ቅልጥምን ለሌሎች መስጠት አማቹ ክብር አልተሰጠኝም፣ በቤተሰቦችሽ ተንቄያለሁ በሚል ሚስቱን እስከመፍታት ሊያደርሰው ይችላል ይላሉ፡፡ ወ/ሮ አዲሴ ያለውም (ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ ሚያዚያ 30/2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው) "አማች በተገኘበት ግብዣ ላይ ሌላ ትልቅ ክብር ያለው (በዕድሜም ሆነ ሌሎች ሁኔታዎች ከአማች በላይ የሆነ) ሰው ቢኖር እንኳ ቅልጥምን ለአማች መስጠት ግድ ነው" በማለት የላይኛውን ሃሳብ ያጠናክራሉ፡፡

**የዶሮ ፈረሰኛ** ፡- በማህበረሰቡ ውስጥ የዶሮ ፈረሰኛ እንደቅልጥም ሁሉ ለሴቶች የተከለከለ የስጋ አይነት ነው፡፡ ማህበረሰቡ ሴቶች የዶሮ ፈረሰኛን እንዳይበሉ የሚከለክላቸው "ፈረሰኛ" ለሚለው ቃል ከሚሰጠው ትርጉምና ዶሮን መባረክ ካለበት ሰው ማንነት በሚመነጩ ምክንያቶች ነው፡፡

ማህበረሰቡ "ፈረሰኛ" የሚለውን ቃል "ከፈረስ ጋላቢነት"፣ "ከጦረኛነት" ጋር በማያያዝ ይተረጉመዋል፡፡ በማህበረሰቡ ባህል መሰረት ፈረስ መጋለብ፣ ከፍተኛ ሃይልና ጉልበትን በሚጠይቁ የጦርነት ዘርፎች ላይ መሳተፍ ደግሞ ለወንዶች ብቻ የተተው ናቸው፡፡ በመሆኑም የዶሮ ፈረሰኛን እንዲበላ የሚፈቀድለት ብዙ ጉልበትን ያወጣል የሚባለው ወንድ ልጅ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ የመባረክ ስልጣን የተሰጠው ለወንዱ ነው፡፡ በመሆኑም ዶሮ የሚባርከው የቤቱ አባወራ ካለ እሱ፣ አባወራ ከሌለም ህፃንም ይሁን አዋቂ ሌላ ወንድ ልጅ ተፈልጎ ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም የዶሮ ፈረሰኛን ለመብላት የአካባቢው ባህል የሚፈቅደው ዶሮውን ለባረከው ወንድ ልጅ ነው፡፡ እንዳጋጣሚ ሆኖ የታረደው ዶሮ ለመብል በሚቀርብበት ጊዜ የባረከው ሰው በአካባቢው ከሌለና ርቆ ሄዶ ከሆነም የዶሮ ፈረሰኛው በቤቱ ውስጥ ያለን ወንድ ልጅ ይመለከታል (ወ/ሪት ፍሬ ዘር አድማሱ፣ ቃመ፣ የካቲት 12/2008፤ ወ/ሪት ቦሰና ድሌ፣ ቃመ፣ መጋቢት 8/2008) ፡፡ በመሆኑም የዶሮ ፈረሰኛ ምንጊዜም ለወንድ ልጅ ብቻ የተፈቀደ ነው፡፡ ነገር ግን አንዲት ሴት በስህተትም ይሁን ሆን ብላ የዶሮ ፈረሰኛ ከበላች በወንዶች

ላይ የበላይነት ስሜት ስለምታሳድር ለወንድ ልጅ አትታዘዝም፣ ለትዳሯም ታማኝ አትሆንም፣ የማህበረሰቡን ደንብም ጥሳለች ተብላ ከማህበረሰቡ ትገለላለች፡፡

በዚህም ትዳር ላይ ያለች ከሆነች የባሏንም ሆነ የራሷን ቤተሰቦች ታሰድባለች፤ ያላገባች ከሆነችም የማህበረሰቡን ባህል የጣሰች በመሆኗ የትዳር አጋር ለማግኘት ትቸገራለች፡፡ ስለሆነም ሴቶችም የዶሮ ፈረሰኛ ብንበላ ከማህበረሰቡ እንገለላለን፣ የትዳር አጋርም እናጣለን ብለው ስለሚፈሩ ይሄን የስጋ አይነት ለመብላት አያስቡትም፡፡

**ራስ ምላስ ፦** ራስ ምላስም እንደ ቅልጥምና የዶሮ ፈረሰኛ ሁሉ ለሴት ልጅ የማይፈቀድ የምግብ አይነት ነው፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብ "ምላስ" የሚለውን ቃል "ምላሰኛ"፣ "ለፍላፊ"ና "ተናጋሪ" በሚል እሳቤ ይተረጉመዋል፡፡ ስለዚህ ራስ ምላስን መብላት "ምላሰኛ"፣ "ለፍላፊ"ና "ተናጋሪ" ያደርጋል ብሎ ያምናል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ሴቶች በተፈጥሯቸው ምላሰኛ፣ ለፍላፊና ሚስጥር የማይጠብቁ ተደርገው ይታሰባሉ፡፡ ስለሆነም ሴቶች ምላስ ከበሉ የበለጠ ለፍላፊ ይሆናሉ ተብሎ ስለሚታመን እሱን እንዲበሉ የአካባቢው ልማድ አይፈቅድላቸውም፡፡

ሴት ልጅ አድማጭ እንጅ ተናጋሪ እንድትሆን አይፈለግም፡፡ ጥሩ ምግባር ያላት ሴት ዋናው መመዘኛዋ ዝምተኛነቷ ነው፡፡ ይሁን እንጅ እንደ አቶ በለጠ ማስረሻ (ቃመ፣ የካቲት 12/ 2008) እና አቶ ድንቁ በላይነህ (ቃመ፣ የካቲት 12/ 2008) ሴት ልጅ ራስ ምላስ ከበላች ጥሩ የተባለ ምግባሯን ታጣለች፣ ምላሳም ስለምትሆን ባሏንም ሆነ የአካባቢውን ማህበረሰብ ትዳፈራለች፡፡ ስለሆነም ለሴቶች ራስ ምላስ የተከለከለ ሲሆን፤ ክልከላውን መጣስም ጥሰቱን በፈፀሙት ሴቶች ላይ አዲስ የትዳር አጋር ማጣትን፣ ይዘውት ከቆዩት ትዳርም ፍችን ያስከትላል፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በማህበረሰቡ ውስጥ አንዳንድ የምግብ አይነቶች የትዳር አጋር ማጣትን ብቻ ሳይሆን ድርቅና ድህነትንም ያስከትላሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

### 5.1.1.3 ለድርቅና ድህነት የሚያጋልጡ የምግብ አይነቶች

በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ አንዳንድ የምግብ አይነቶችን ለምግብነት መጠቀም ለምግብነት በዋሉት (እንስሳት፣ እህል ወዘተ.) ዝርያዎች ላይም ሆነ በአካባቢው ላይ

ያልተጠበቀ ድርቅና ድህነትን ያስከትላል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ከድርቅና ድህነት ጋር በተያያዘ ነውር ከሚላቸውና በአባሪ አንድ "ሀ" ውስጥ ከቀረቡት የምግብ አይነቶች መካከል የላም ስጋና እልበት በማሳያነት ቀርበው ከዚህ በታች አጭር ገለፃ ቀርቦባቸዋል፡፡

**ላም** ፦ በማህበረሰቡ ውስጥ ላም የሃብት፣ የጥንካሬ፣ የለምለምነት፣ የእናትነት ተምሳሌት ነች፡፡ በመሆኗም ማህበረሰቡ ላምን በማራባትና በመንከባከብ በምትወልዳቸው ጥጆቿና በወተቷ ከመጠቀም ሌላ እሷን አርዶ የመብላትም ፍላጎት የለውም፡፡ ይሁን እንጅ የማህበረሰቡን ህግ ጥሶ አንድ ሰው ላምን ቢያርድ ጥሰቱ ፈጣሪን የሚያስቆጣ ተግባር ስለሆነ የአራጁም ሆነ ሌሎች የአካባቢው ላሞች መውለድ ያቆማሉ፤ አካባቢውም በድርቅ ይጠቃል (እማሆይ ድንቄ ካሳ፣ ቃመ፣ የካቲት 12/ 2008 )፡፡ በአካባቢው አሁንም አልፎ አልፎ ድርቅ የሚከሰት ሲሆን፤ እንደ እማሆይ ድንቄ የድርቁ መንስኤም በድሮ ጊዜ በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ላም አርደው ስለበሉ አካባቢው በመረገሙ ነው፡፡

ማህበረሰቡ ለላም ያለውን ክብር የሚገልፀው እሷን አርዶ ለምግብነት ባለመጠቀም ብቻም አይደለም፡፡ በአካባቢው ላምን ለእርሻ አገልግሎት መጠቀምም የተነወረ ተግባር ነው፡፡ በላም ቢታረስም ተግባሩን ፈጣሪ ስለማይወደው የታረሰው መሬት እህል አያበቅልም ተብሎ ይታመናል፡፡

**እልበት** ፦ በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ እልበት የፆም ወቅት ምግብ ነው፡፡ በመሆኑም፤ እልበትን ከፆም ቀናት ውጭ ለምግብነት መጠቀም በማህበረሰቡ ዘንድ የተፈቀደ አይደለም፡፡ ምክንያቱም እልበትን ከፆም ወቅት (በተለይም ከ40 ቀኑ የፋሲካ ፆም) ውጭ ባሉ ሌሎች ጊዜያት መመገብ የላም ስጋን እንደመብላት ሁሉ ጥሰቱን በፈጸሙት ግለሰቦችም ሆነ በአካባቢው ማህበረሰብ ላሞች ላይ መውለድ ያለመቻልን ፤ በአካባቢው ላይም የድርቅ አደጋን ያስከትላል ተብሎ ይታመናል፡፡

በአካባቢው እልበትን ከፆም ወቅት ውጭ መመገብ ክልክል የሆነበት የራሱ መነሻ ታሪክ እንዳለው ቄስ አስማማው ዋሴ (ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ ሚያዚያ 30/ 2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው) እንደሚከተለው ነግረውኛል፡፡

> በድሮ ጊዜ በአካባቢው በከብት እርባታ የሚተዳደር አንድ ዘላን ነበር፡፡ ዘላኑም ሁል ጊዜ የሚመገበው በእርጎ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ 40 ፆም መጣና

> ዘላኑ መያም የግድ ሆነበት፡፡ በያም ጊዜ በእርጎ መብላት ስለማይችልም የሚበላበት ነገር ስላጣ ተጨነቀ፡፡ ጭንቀቱን የተረዳቸው ሚስቱም ከእርጎ ጋር የሚመሳሰል (እንደ እርጎ ነጭ ቀለም ያለው) ማባያ አዘጋጀችለት፡፡ የተዘጋጀለትም እልበት ነበር፡፡ ዘላኑም እልበቱ እርጎ እየመሰለው ያሙ እስኪያልቅ ድረስ እሱን እየተመገበ ቆየ፡፡ ነገር ግን እልበቱን ስለለመደው ያሙ ካለቀ በኋላም በእልበት መብላቱን ቀጠለ፡፡ ከዚያ በኋላ ግን የዘላኑ ላሞች መውለድ አቆሙ፣ በአካባቢውም ድርቅ ሆነ፡፡

እንደአፈ ታሪኩ በአካባቢው እልበትን ከያም ጊዜያት ውጭ መመገብ ነውር የሆነው፣ እልበት የሚባል የምግብ አይነትም የተጀመረው ዘመኑ ባይታወቅም የዘላኑ ላሞች መውለድ አቆሙ፣ በአካባቢውም ድርቅ ተከሰተ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በማህበረሰቡ ባህላዊ እሳቤ መሰረት ከያም ቀናት ውጭ እልበትን መመገብ በአካባቢው ውግዘትን ያስከትላል፡፡ ይህን ጉዳይ አቶ አባይነው ጥጋቡ (ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ የካቲት 7/2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው) "ተንኮለኛ መበለት በያም ዶሮ በፋሲካ እልበት" በሚል ምሳሌያዊ አነጋገር ይገልፁታል፡፡ ይሄ ምሳሌያዊ አነጋገር የአካባቢው ማህበረሰብ ከያም ውጭ በሆኑ ቀናት እልበትን እንዳይጠቀም የሚያስተምር - ከዚያም ሲያልፍ የሚያስጠነቅቅ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በማህበረሰቡ ውስጥ አንዳንድ የምግብ አይነቶች ድርቅና ድህነትን ብቻ ሳይሆን የተረጋጋ ህይወት ማጣትንም ያስከትላሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

### 5.1.1.4 ለተረጋጋ ህይወት ማጣት መንስኤ የሆኑ የምግብ አይነቶች

በተጠኚው ማህበረሰብ ዘንድ አንዳንድ የምግብ አይነቶች ተመጋቢያቸው የተረጋጋ ህይወትን እንዳይመራ ምክንያት ይሆናሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ የተረጋጋ ህይዎት ከማጣት ጋር በተያያዘ ነውር ከሚላቸውና በአባሪ አንድ "ሀ" ውስጥ ከተጠቀሱት የምግብ አይነቶች መካከል የዶሮ ክንፍና ነጠላ ዶሮ በማሳያነት ቀርበዋል፡፡

**የዶሮ ክንፍ ፡-** ማህበረሰቡ የዶሮ ክንፍን በአየር ላይ እየተንሳፈፉ ለመብረር ከሚያስችል የአዕዋፋት የአካል ክፍል ጋር ያያይዘዋል፡፡ "ክንፍ" በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ያለመረጋጋት፣ በአንድ አካባቢ ፀንቶ ለመኖር ያለመቻልና የባተሌነት ተምሳሌት ነው፡፡ በዚህ መነሻነትም በተጠኚው ማህበረሰብ ዘንድ የዶሮ ክንፍ ማንኛውም ሰው ያለገደብ

እንዲመገበው የሚፈቀድ የስጋ አይነት አይደለም፡፡ እሱን እንዲመገቡት ከማይፈቀድላቸው የማህበረሰቡ አባላት መካከል ወንዶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በማህበረሰቡ እምነት ወንድ ልጅ በባህሪው በአንድ ቦታ ረግቶ መኖር አይችልም፡፡ በዚህ ባህሪው ላይ የዶሮ ክንፍ ከበላ ደግሞ የበለጠ ያለመረጋጋት፤ ከወላጆቹም ሆነ ከትውልድ አካባቢው ርቆ የመሄድ፤ በአንድ አካባቢ ተረጋግቶና ትዳር መስርቶ የመኖር ችግር ይገጥመዋል፡፡ ከወንዶች ጋር ሲነፃፀሩ ሴቶች በአካባቢያቸው የመቆየት፣ በወላጆቻቸው ቁጥጥር ስር የመሆን አጋጣሚያቸው ከፍ ያለ ነው፡፡ ስለሆነም፤ የዶሮ ክንፍን በመብላት አለመብላት ረገድ በሴቶች ላይ የተለየ ጫና የለባቸውም፡፡ እንደማህበረሰቡ ሴት ልጅ የዶሮ ክንፍ ብትበላም ከአካባቢዋ ርቃ የመሄድ እድሏ ጠባብ ነው - ይሄን ለማድረግ ድፍረቱም የላትም፡፡ ከወላጆቿ ርቃ ሄደች ከተባለም ከባሏ ቤት አያልፍም፡፡

በመሆኑም የዶሮ ክንፍን በሚመለከት ማህበረሰቡ ትልቅ ጫና የሚያደርገው ወንድ ልጆች እንዳይመገቡት ነው፡፡ በአካባቢው ባህል ወንድ ልጅ አካባቢውን የሚያስጠራ፣ ድንበር የሚያስከብር፣ የቤተሰብ ሰብሳቢ፣ በችግር ጊዜ ጋሻና መከታ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ በመሆኑም ወላጆች ወንድ ልጆቻቸው ከፊታቸው እንዲርቁ አይፈልጉም፡፡ ከእነሱ ርቀው ሄደው ራሳቸውን በሚለውጥ ስራ ላይ ከሚሰማሩ እንኳ ከአጠገባቸው ሆነው አብረው ቢራቡ ይመርጣሉ (አቶ በለጠ ማስረሻ፣ ቃመ፣ የካቲት 12/2008)፡፡ ስለሆነም ወንዶች የዶሮ ክንፍን እንዳይበሉ ማህብረሰቡ አጥብቆ ይከላከላል፡፡

**ነጠላ ዶሮ**[12] ፦ ማህበረሰቡ "ነጠላ"ን ጥላቢስ፣ ከውካዋ፣ ዘዋሪ… የሚል ትርጉም የሚሰጠው ሲሆን፤ ነጠላ ዶሮ ውስጥ ያለውን "ነጠላ"ም ከጥላቢስነት፣ ከውካዋነት፣ ዘዋሪነት ጋር ያያይዘዋል፡፡ በዚህ ምክንያትም በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ ነጠላ ዶሮን የሚበላ ሰው በአንድ አካባቢ ተረጋግቶ መኖር የማይችል፣ ልቡ ሁሌም መንገደኛ የሆነ፣ የያዘው የጨበጠው ሁሉ ረድኤት የሌለው በአጠቃላይም "ውቃቢ የራቀው" ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡

[12] ነጠላ ዶሮ የሚባሉት እጥፍ፣ ድርብ ወይም መንታ ያልሆነ ኮከን (ቁንጮ) ያላቸው ሲሆኑ፤ እጥፍ፣ ድርብ ወይም መንታ የሆነ ኮከን (ቁንጮ) ያላቸው ደግሞ ድርብ ዶሮዎች ይባላሉ፡፡

የአካባቢው ማህበረሰብ ከእያንዳንዳችን ጋር አብሮ የሚኖርና የሚጠብቀን "ውቃቢ አምላክ" አለ ብሎ ያምናል፡፡ በዚህ መነሻነትም፤ እያንዳንዱ የማህበረሰቡ አባል ውቃቢ አምላኩ የሚፈልገውን በማድረግ፣ የማይፈልገውን ደግሞ ባለማድረግ ማስደሰት ይፈልጋል፡፡ ይህ የማህበረሰቡ ጠባቂ የሆነው ውቃቢ አምላክ ከማይወዳቸው ነገሮች አንዱ ነጠላ ዶሮ ነው (አቶ ያለው ደርሶ፣ ቃመ፣ የካቲት 12/2008)፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ከክፉ ነገር ይጠብቀኛል ብሎ የሚያምንበት ውቃቢ አምላክ የማይፈልገውን ነገር በመፈፀም ውቃቢ እንዲርቀው ስለማይፈልግ ነጠላ ዶሮን በምግብነት አይጠቀምም፡፡ በዚህ ምክንያትም ገበያ ላይ በሚደረግ የዶሮ ሽያጭ ዋጋ ሳይቀር የነጠላ ዶሮ ዋጋ ከድርብ ዶሮ ዋጋ በጣም ያነሰ ነው፡፡ እኔም ለመረጃ በተንቀሳቀስኩባቸው የገበያ አካባቢዎች ይሄንን ተመልክቻለሁ፡፡

በአጠቃላይ ከመስክ ከተሰበሰቡትና ማህበረሰቡ ነውር ከሚላቸው የምግብ አይነቶች መካከል በተወሰኑት ላይ ከዚህ በላይ የመረጃ ትንተና በማካሄድ ማህበረሰቡ ስለምግብና የምግብ አይነት ነውሮች ያለው እሳቤና ትግበራ ምን እንደሚመስል በጥቂቱ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ከዚህ በማስከተል ደግሞ ማህበረሰቡ ስለምግብ አዘገጃጀት፣ አመጋገብና ተያያዥ ነውሮች ያለው እውቀት፣ ልምድና ትግበራ ምን እንደሚመስል ተቃኝቷል፡፡

## 5.1.2 የምግብ አዘገጃጀት፣ አመጋገብና ተያያዥ ነውሮች እውቀት፣ ልምድና ትግበራ

የሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ ሁሉም የምግብ አይነቶች ጠቃሚዎቹ ናቸው ብሎ እንደማያምን ሁሉ አንዳንድ የምግብ አዘገጃጀቶችና የአመጋገብ ልምዶችም ለጤንነቱ፣ ለአብሮነቱና በአጠቃላይም ለማህበራዊ ህይወቱ አይበጁኝም የሚል እምነት አለው፡፡ ከዚህ እምነቱ በመነሳትም ያለውን አካባቢያዊ እውቀትና የረጅም ጊዜ ልምዱን ተጠቅሞ የራሱን የምግብ አዘገጃጀትና የአመጋገብ ሁኔታ የሚመሩ ነውሮችን ይፈጥራል፡፡ በፈጠራቸው ነውሮቹ አማካይነትም ትክክል ነው ብሎ ያመነበትን የምግብ አዘገጃጀትና የአመጋገብ ደንብ እየተገበረ ህይዎቱን ይገፋል - ለተከታዮቹም ይሄኑ በቃል እያስተላለፈ ይቀጥላል፡፡ ትክክል አይደለም ብሎ ያመነበትን የምግብ አዘገጃጀትና የአመጋገብ ልምድም ለምን ትክክል እንዳልሆነ ማብራሪያ ያቀርባል፡፡ ከልምዱ ካዳበራቸው ገጠመኞቹ ተነስቶም ትክክል አይደሉም የሚላቸውን ድርጊቶች መፈፀም ሊያስከትል የሚችለውን ችግር በማንሳት ህጉን ያስከብራል - ያስጠነቅቃል፡፡

ማህበረሰቡ ስለምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ያለውን እውቀትና ልምድ ለመረዳት የሚያስችሉ 32 ያህል ነውሮች ተሰብስበዋል፡፡ ከመስክ የተሰበሰቡት የነውር አይነቶችና ነውር የሆኑበት ምክንያት በአባሪ - አንድ “ለ” ውስጥ ከተራ ቁጥር 26 — 57 ተዘርዝረዋል፡፡ በዚሁ መነሻነትም በአባሪው ውስጥ የቀረቡት የማህበረሰቡ ከምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ጋር የተያያዙ ነውሮች ዋነኛ ትኩረት በየትኞቹ የማህበረሰቡ ክፍሎች ላይ እንደሆነና ለየነውሮቹ የተሰጡ ምክንያቶች ባላቸው የጋራ ባህሪ ሲደራጁ ምን ገፅታ እንዳላቸው ከዚህ በታች ጥቅል መረጃ ቀርቧል፡፡

በአባሪው ውስጥ የቀረቡት ነውሮች ትኩረት ያደረጉባቸው የማህበረሰቡ አባላት፣ በአባሪው ውስጥ የሚገኙበት ተራ ቁጥርና ብዛት በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ - 3 የነውሮቹ ትኩረት የሆኑት የማህበረሰቡ አባላት፦**

| ተ/ቁ | የነውሮቹ ትኩረት የሆኑት የማህበረሰቡ አባላት | ነውሮቹ በአባሪው ውስጥ የሚገኙበት ተራ ቁጥር | የነውሮቹ ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት | 26፣27፣28፣29፣31፣33፣34፣35፣37፣38፣39፣40፣42፣44፣45፣46፣47፣48፣49፣50፣51፣52፣54፣55ና 56 | 25 |
| 2 | ሴቶች | 32፣36፣41ና 53 | 4 |
| 3 | ወንዶች | 43ና 57 | 2 |
| 4 | ህፃናት | ነውር 30 | 1 |

በምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት የተሰበሰቡት መረጃዎች በጭብጥ እየተከፋፈሉ የመላሾቹ ምክንያት ተጨምቆ ሲቀርብ በአባሪው ውስጥ የቀረቡት ነውሮች በ4 ጭብጦች ስር ሊካተቱ የሚችሉ ናቸው፡፡ በዚሁ መሰረትም በ4 ጭብጦች ስር የተጠቃለሉት ምክንያቶች ነውሮቹ በአባሪ ውስጥ የሚገኙበትን ተራ ቁጥርና በየምድቡ ውስጥ የሰፈሩ ነውሮችን ብዛት በሚያሳይ መልኩ በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡

**ሰንጠረዥ - 4 የነውሩ ምክንያት፦**

| ተ/ቁ | የነውሩ ምክንያት | ነውሮቹ በአባሪው ውስጥ የሚገኙበት ተራ ቁጥር ከ --- እስከ --- | የነውር ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ንጥፈትና ድህነት | 26 — 31 | 6 |
| 2 | በረከት ማጣት | 32 - 38 | 7 |
| 3 | ውግዘት | 39 - 40 | 2 |
| 4 | የጤና መታወክ | 41 - 57 | 17 |

በዚሁ መሰረትም ከመስክ ከተሰበሰቡትና በሰንጠረዡ ላይ በ4 በጭብጥ ተከፋፍለው ከቀረቡት 32 መረጃዎች መካከል ሌሎችን ይወክላሉ የተባሉ 14 ነውሮችና ነውር ለመሆናቸው የተሰጡ ምክንያቶች በማሳያነት ቀርበው ከዚህ በታች አጭር የመረጃ ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡

### 5.1.2.1 ንጥፈትና ድህነትን የሚያስከትሉ የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ልምዶች

በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ በምግብ አዘገጃጀና አመጋገብ ዙሪያ የሚፈፀሙ አንዳንድ ድርጊቶች የምግብ ምንጭ በሆኑት የእንሰሳትና የእህል ዘሮች ላይ መንጠፍንና መድረቅን፣ በተመጋቢዎቹ ሰዎች ላይም ድህነትን የሚያስከትሉ ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ማህበረሰቡ ከምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ጋር በተያያዘ ንጥፈትና ድህነትን ያስከትላሉ በሚል ነውር ከሚላቸው ድርጊቶች መካከል እጅን ከመታጠብ፣ ከመሶብ አቀራረብ፣ ከተመጋቢዎች አቀማመጥና መሰል ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ ድርጊቶች ይጠቀሳሉ፡፡ ከተጠቀሱት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ በማህበረሰቡ ውስጥ ነውር የተባሉ የተወሰኑ ድርጊቶች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

#### በወተትና እርጎ በልቶ እጅን መታጠብ

በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ ወተትና እርጎን (የላም ልጅም ይሏቸዋል) ተጠቅሞ እጅን መታጠብ የእነሱ ምንጭ የሆነችው ላም እንድትነጥፍ፣ እንድትደርቅ ያደርጋል፡፡ እንድትነጥፍና እንድትደርቅ ብቻ ሳይሆን እስከመጨረሻው እንዳትወልድም ያደርጋል

ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህን በሚመለከት አቶ ሙሉቀን ዘውዱ (ቃመ፣ የካቲት 15/ 2008) እንደሚከተለው ነግረውኛል፡፡

> በወንዞች አካባቢ የሚገኝ አባ ወርቄ የሚባል ጅን (ሰይጣን) አለ፡፡ ይህ ጅን ወተት ነገሮችን ስለሚወድና የላሞችን ወተት ስለሚጠጣ ላሞች ባሉበት አካባቢ አይጠፋም፡፡ በመሆኑም ሰዎች በወተትና እርጎ በልተው እጃቸውን በውሃ ሲታጠቡ ይበሳጫል፡፡ በዚህ ምክንያትም የላሟን ወተት በመስለብ ወይም በመውሰድ ድርጊቱን የፈፀሙትን ሰዎች ይቀጣቸዋል፡፡

አቶ አለበል ደሴ (ቃመ፣ የካቲት 15/ 2008) የተባሉ መረጃ ሰጭ እንደነገሩኝ ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ ከላሞች አካባቢ አይጠፋም የሚባለውና አባ ወርቄ የሚል ስም የተሰጠው ጅን በወተትና እርጎ በልቶ እጅን መታጠብ ብቻ ሳይሆን የሰዎች ጩኸትና ድምጽም ይረብሸዋል፡፡ በመሆኑም በአካባቢው ሰዎች ላም እያለቡ ድምጽ አያሰሙም፡፡ ድምጽ ካሰሙ በሁኔታው በመበሳጨት የላሞችን ወተት ይወስዳል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ይህ ጅን ከብት አርቢ እንደሆነ፣ የጅን ውላጅ (ድቅል)ም እንደሚባዛ ወይም እንደሚራባ ይታመናል፡፡ በመሆኑም የአካባቢው ማህበረሰብ ከጅን ጋር ለማዳቀል በአካባቢው አባወርቄ የሚባለው ጅን አለ ተብሎ በሚታመንበት ወንዝ አካባቢ ላሞቹን ያሳድራል፡፡

ስለሆነም በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ላም ትልቅ ክብር እንዳላት ሁሉ የእሷ ውጤቶች የሆኑት ወተትና እርጎም የተከበሩ ናቸው፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው በማህበረሰቡ ውስጥ እነሱን አለማክበርም ላሟን ለድርቀትና ንጥፈት በማጋለጥ በሰዎች ላይ ድህነትን የሚያስከትል ነው፡፡ በመሆኑም የአካባቢው ማህበረሰብ በወተትና እርጎ ከበላ በኋላ እጁን በመታጠብ ፋንታ አንዱን እጁን ከሌላኛው ጋር እሸት እሸት በማድረግ ወደ ስራው ይሰማራል፡፡ የማለብ ስራ በሚያከናውንበት ወቅትም ድምፅ ከማሰማት ራሱን ይቆጥባል፡፡

## እንጀራን ቆርጦ ማቅረብ

በማህበረሰቡ ውስጥ አንዳንድ የአመጋገብ ልምዶች ደግሞ ለምግብነት የሚውሉትን እንሰሳት ማንጠፍ ብቻ ሳይሆን በተመጋቢዎቹ ላይ ድህነትንም የሚያስከትሉ ናቸው፡፡ አሁን አሁን በተለይም በከተሞች አካባቢ እንጀራን በቁርጥ መልክ እያዘጋጁ በየግል ሳህን ይዞ መቀመጥ የተለመደ ባህል እየሆነ መጥቷል፡፡ በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ ግን ለአዲስ እንግዳ ሰውም ሆነ ለራስ ቤተሰብ እንጀራን ቆርጦ ማቅረብ የተነወረ ተግባር ነው፡፡ በማህበረሰቡ

አስተሳሰብ አንድን እንጀራ ለሁለትና ሶስት ቆርሶ ማቅረብ የንፉግነት፣ ስስታምነት ባህሪ ነው፡፡ የተቆራረጠ፣ የተከፋፈለ ወይም ሙሉነቱን ያጣ ነገር ሁሉ የረድኤት ማጣት ምልክት ነው - ችግር ጠሪ ነው፡፡ በመሆኑም እንጀራን ቆርጦ ማቅረብ በማህበረሰቡ ዘንድ መጥፎ ስም ያሰጣል፣ ከተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶችም እስከ መገለል ያደርሳል፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ የአንድን ሰው ወይም የአካባቢ ደህንነት የሚጠብቅ ወይም ግርማ ሞገስ የሚሰጥ "ቆሌ" አለ ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይህ ቆሌ የጎደለ፣ የተቆረሰ ነገር አይወድም፡፡ ሙሉ ነገር ይወዳል፡፡ ስለሆነም የተቆረሰ እንጀራ መሶብ ላይ ከቀረበ ቆሌው ስለሚቆጣ የምግቡ አቅራቢዎች የሚሰሩት፣ የሚያቀርቡት ነገር ሁሉ ረድኤት እንዳይኖረው ይረግማቸዋል፣ ድህነትንም ያመጣባቸዋል (አቶ ድንበሩ አባይነህ፣ ቃመ፣ የካቲት 15/2008)፡፡ ስለሆነም ማህበረሰቡ ለእንግዳም ሆነ ለራሱ ሙሉ እንጅ ቁርጥ እንጀራ አያቀርብም፡፡ በአንዳንድ አጋጣሚዎች ወደ ከተሞች አካባቢ ሄዶ እንጀራ ተቆርጦ ሲቀርብ ሲመለከትም ባየው ነገር ያፍራል - ያዝናል፡፡

እኔም መረጃ ለመሰብሰብ በተንቀሳቀስኩባቸው የገጠር አካባቢዎች ሁሉ ቁርጥ እንጀራ አልቀረበልኝም፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን ለእንግዳ አንድ እንጀራ ብቻ አይቀርብም በሚል ሁለት ሙሉ እንጀራ ያቀረቡልኝ ቤተሰቦችም አጋጥመውኛል፡፡

## በዕድሜ ከሚበልጡ ሰዎች በላይ ተቀምጦ መመገብ

በማህበረሰቡ ውስጥ ትልቅ ክብር ከሚሰጣቸው ነገሮች መካከል ሞሰብ አንዱ ነው፡፡ ማህበረሰቡ የሞሰብን ክብር ከሚገልፅባቸው መንገዶች መካከል ደግሞ የተመጋቢዎቹ የአቀማመጥ ሁኔታ ይጠቀሳል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ሰዎች ሞሰብ ላይ የሚቀርቡት የእድሜ ደረጃቸውን ታሳቢ ባደረገ አኳሃን ነው፡፡ የተመጋቢዎቹ የአቀማመጥ ሁኔታ ለመመረቅም ሆነ ለመረገም የራሱ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ይህን አስመልክቶ መረጃ ከሰጡ ሰዎች መካከል ወ/ሮ ብርቱካን ሙላቱ (ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ ሚያዚያ 30/2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው) እንዲህ ይላሉ፡፡

> በባህላችን ልጆች ከወላጆቻቸው ጋርም ሆነ ከሌሎች ሽማግሎችና አዛውንቶች ጋር አብረው ማድ አይቆርሱም፡፡ ልጆችም በሁሉ ነገር ቅድሚያና ክብር በዕድሜ ለሚበልጣቸው ሰው መስጠት እንዳለባቸው እየተነገራቸው ስለሚያድጉ አብረን ካልበላን አይሉም፡፡ ይኸን በማድረጋቸውም ከትልቅ ቦታ ያውላችሁ - ዕድሜ ከፀጋ ይስጣችሁ የሚል ምርቃትን ያሰጣቸዋል፡፡ ይኸን ካላደረጉ ግና ባለጌ

ወልዶ ባለጌ ያሳደጋቸው ይባላሉ፡፡ ቤተሰባቸውንም ያሰድባሉ፡፡ የአባቶች ዕርግማንም ድሃ ያረጋቸዋል፡፡

በመሆኑም በማህበረሰቡ ውስጥ ልጆች ከትልልቆች ጋር አንድ ሞሰብን እንዲጋሩም ሆነ ከአዋቂዎች በላይ ተቀምጠው እንዲመገቡ አይፈቀድም፡፡ ይህን ተላልፎ መገኘት ለታላላቆች ክብር ካለመስጠት፣ በጥሩ ቤተሰብ ውስጥ ካለማደግ የሚመነጭ ነው ተብሎ የሚታመን ሲሆን፤ ውጤቱም ጥሰቱን የሚፈፅሙ ልጆች በቀጣይ ህይወታቸው ውስጥ በሰሩትና ባሰቡት ነገር ሁሉ ውጤታማ የማይሆኑ፤ በዚህ ምክንያትም ህይወታቸውን ሁሉ በድህነት የሚገፉና እድሜያቸውም ያጠረ እንዲሆን ያደርጋል ይባላል፡፡

ሆኖም ከሞሰብ ጋር የተያያዙትና ከፍ ሲል የተጠቀሱት ነውሮች ሁሉ አሁንም ድረስ ሙሉ በሙሉ እየተከበሩ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ ከመረጃ ሰጭዎች መካከል አቶ ደስታው አባይነው (ቃመ፣ መጋቢት 5/ 2008) እንደገለፁት አብዛኞቹ የአካባቢያችን ልጆች ለታላላቆችም ሆነ ለሞሰብ ትልቅ ክብር ያላቸው ቢሆንም አሁን አሁን ግን እነዚህ ደንቦች በልጆች እየተጣሱ ነው፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ የሞሰብ ክብር የሚገለፀው ግን በተመጋቢዎቹ እድሜን መሰረት ያደረገ አቀማመጥ ብቻም አይደለም፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ሞሰብ ላይ ቀርቦ ወሬ፣ ሳቅ፣ ዋዛ ፈዛዛ አይፈቀድም፡፡ በሁለት ጉንጭ ማላመጥ፣ እየበሉ ማውራት፣ ሰው ሲበላ ማየት፣ ሞሰብ ሳይነሳ አቋርጦ መነሳት፣ ለሞሰብ ምንም ሳያስተርፉ መመገብ የመሳሰሉት ሁሉ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው ድርጊቶች ሲሆኑ፤ እነሱን መተላለፍም ድርጊቱ ያልተባረከ ስለሆነ ውጤቱ ድህነት ነው፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በማህበረሰቡ ውስጥ በአንዳንድ የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ዙሪያ የሚፈፀሙና የሚከናወኑ ድርጊቶች ንጥፈትና ድህነትን ብቻ ሳይሆን በረከት ማጣትንም ያስከትላሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

### 5.1.2.2 በረከትን የሚያሳጡ የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ልምዶች

ማህበረሰቡ ከፈጠራቸውና ከሚተገብራቸው የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ደንቦች ያፈነገጡ ልማዶች በማህበረሰቡ ውስጥ የስግብግብነትና ችኩልነት፣ የስስታምነትና ራስ ወዳድነት መገለጫ ባህሪያት ናቸው፡፡ በመሆኑም እንዲህ አይነት የምግብ አዘገጃጀቶችና አመጋገቦች ሁሉ በረከትን የሚያሳጡ ናቸው፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ማህበረሰቡ ከምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ጋር በተያያዘ በረከትን ያሳጣሉ በሚል ነውር ከሚላቸው ድርጊቶች መካከል ከአመጋገብ ሁኔታ፣ ምግብን ለማቅረብም መሟላት ካለባቸው ቅድመ ሁኔታዎችና መሰል ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ ድርጊቶች ይጠቀሳሉ፡፡ በዚሁ መሰረትም ከተጠቀሱት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ በማህበረሰቡ ውስጥ ነውር የተባሉ የተወሰኑ ድርጊቶች ቀርበው ከዚህ በታች የመረጃ ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡

## በግራ እጅ መመገብ

በማህበረሰቡ ውስጥ አንድ ምግብ በረከት አለው ሲባል ተመጋቢዎቹን ማጥገብ፣ ማርካት ችሏል ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጅ ሰዎች ለመመገብ መሶብ ላይ ሲቀርቡ የሚከተሏቸው አንዳንድ የአመጋገብ ልምዶች በልተው እንዳይጠግቡና እንዳይረኩ ያደርጋሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ የዚህ አይነት ችግርን ያስከትላሉ ተብሎ ከሚታመንባቸው የአመጋገብ ልምዶች መካከል በግራ እጅ መመገብ ዋነኛ ተጠቃሽ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ "ግራ" የመከራ፣ የጭንቀት፣ ያልተለመደና የእንግዳ ክስተት ወኪል እሳቤ ነው፡፡ በተለያዩ አውዶች ውስጥ የቃሉ አጠቃቀም ቀናነት ለጎደለው፣ ለማያዝዙበትና ለማይገዙበት ወጣ ያለ ሃሳብ፣ ገድ ለሌለው ነገር መገለጫ ሆኖ የሚጠቀስ ነው፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ማንኛውንም አይነት ስራ ለማከናወን ማለትም ምግብ ለመቁረስ፣ እቃ ለማንሳት፣ ለመቀበል፣ ለማቀበል፣ ሰላምታ ለመለዋወጥ ወዘተ. ሁሉ ተመራጩ ቀኝ እጅ ነው፡፡ ማህበረሰቡ "ቀኝ"ን የሚረዳው "ቅን" በሚለው ፍችው ነው፡፡ ቅን መሆን ማለት ባወቁትና በለመዱት ነገር መገዛት ማለት  ነው፡፡ ከመረጃ ሰጭዎች መካከል አባ ፍቅረ ማሪያም (ቃመ፣ የካቲት 25/ 2008) "ቀኝ" የመልካም ዕድሎችና የበረከት ማግኘት፤ "ግራ" ደግሞ የመጥፎ ዕድሎችና የበረከት ማጣት መገለጫዎች ናቸው ይላሉ፡፡ ስለሆነም በማህበረሰቡ ውስጥ በግራ እጅ መመገብ ከማህበራዊ ልማዶች ማፈንገጥና ለስርዓት አለመገዛት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህ አይነት ማፈንገጥ ደግሞ በተመጋቢዎቹ ላይ በልቶ አለመጥገብን፤ ለምግብነት በቀረበው እህል ላይም ረድኤትና በረከት አለመኖርን ያስከትላል ተብሎ ይታመናል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ በግራ እጅ መመገብ ብቻም ሳይሆን ምግብን ለሌሎች በግራ እጅ መስጠትም ሆነ ከሌሎች መቀበልም በረከትን የሚያሳጡ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

## ሴት ልጅ ግብር ውሃ ሳትወጣ ምግብ ማቅረብ

በማህበረሰቡ ውስጥ ሴት ልጅ ግብር ውሃ ሳትወጣ ምግብ ማቅረብም ለበረከት ማጣት ምክንያት ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በተጠኘው ማህበረሰብ በተለይም በገጠር ቀበሌዎች አካባቢ ሴት ልጅ ግብር ውሃ የምትወጣው (የምትፀዳዳው ) በቀን ሁለት ጊዜ (ጠዋትና ማታ) ነው፡፡ በከተሞች አካባቢ እንደሚኖሩ ሴቶች በፈለጉት ጊዜና ሰዓት እንዲፀዳዱ የአካባቢው ልማድ አይፈቅድላቸውም፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ከተጠቀሱት ጊዜያት ውጭ ለሴት ልጅ ግብር ውሃ መውጣት ከባለጌነት ያስቆጥራል - ድርጊቱም የትዳር አጋር እስከማሳጣት ሊያደርስ ይችላል፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ የአንዲት ሴት የቀን ውሎ የሚጀመረው ወንዶች ከመነሳታቸው በፊት በጠዋት ተነስታ በመፀዳዳት ነው፡፡ በጠዋት ከተፀዳዳች በኋላ የቤተሰቡን ቁርስ ታበስላለች - ታቀርባለች፡፡ በቀን ስለማትፀዳዳ የቤተሰቡን ምሳም ታበስላለች - ታቀርባለች፡፡ እንደቤተሰቡ የአቅም ሁኔታም በቁርስና በምሳ፣ በምሳና በዕራት መካከል ለቤተሰቡ የሚሰራ ነገር ካለም ምግብ ትሰራለች - ታቀርባለች፡፡ የቀኑ ውሎ በዚህ መንገድ ከተገባደደ በኋላ የሴቷ ቀጣይ ተግባር የሚሆነው የቤተሰቡን እራት መስራት ነው፡፡ ይሁን እንጅ በአካባቢው የዕራት ጊዜ በአማካኝ ከምሽቱ ከ2 — 3 ሰዓት ገደማ ስለሆነ ምግብ ከማቅረቧ በፊት ሁለተኛውንና በቀኑ ውስጥ የመጨረሻዋ የሆነውን የመፀዳዳት ተግባር ከፈፀመች በኋላ እራት ታቀርባለች፡፡

ሴቷ የተጠቀሱትን ጊዜያት ተጠቅማ ግብር ውሃ ሳትወጣ ምግብ አታቀርብም፡፡ ይህን በሚመለከት አቶ ድንበሩ አባይነህ (ቃመ፣ የካቲት 25/ 2008) የተባሉ መረጃ ሰጭ "ሴቷ ግብር ውሃ ሳትወጣ ምግብ ብታቀርብ የቀረበው እህል ተመጋቢዎቹን አያጠግብም፣ የቀረበው ምግብ ብቻ ሳይሆን የቤቱ እህል በጠቅላላ ረድኤት በረከት አይኖረውም" ይላሉ፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን ከግብር ውሃ በፊት ምግብ ያቀረበች ሴት የነካችው፣ የሰራችው፣ ያየችው ሁሉ ረድኤት አይኖረውም፡፡ የቤቱን እህልም አይጥ ይበላዋል ይባላል፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በማህበረሰቡ ውስጥ በአንዳንድ የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ዙሪያ የሚፈፀሙና የሚከናወኑ ድርጊቶች በረከት ማጣትን ብቻ ሳይሆን ውግዘትንም ያስከትላሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

## 5.1.2.3 ውግዘትን የሚያስከትሉ የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ልምዶች

ውግዘት ፦ ሰዎች በሚፈፅሙት መጥፎ ድርጊትና ሁኔታ ምክንያት ከሌሎች የሚደርስባቸው ነቀፌታ፣ ርግማንና መገለል ነው፡፡ በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ አንድ ሰው የሚወገዝባቸው የተለያዩ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን፤ ከምክንያቶቹ መካከል ከምግብ አዘጋጅዎች ማንነት ጋር የተያያዙ ልማዶች ይጠቀሳሉ፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ አንዳንድ የማህበረሰቡ አባላት ያዘጋጁትን ምግብ መመገብ ማህበረ ባህላዊና ሃይማኖታዊ መገለልን ያስከትላል ፡፡ በማህበረ ባህላዊ ገፅታው ከተለያዩ የዕለት ተለት ማህበራዊ ግንኙነቶች መታገድንና መገለልን ያመጣል፡፡ በሃይማኖታዊ ገፅታው ደግሞ ወደሃይማኖታዊ ተቋማት የመሄድና በተቋማቱ የመገልገል መብትን ያሳጣል፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ማህበረሰቡ ከምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ጋር በተያያዘ ውግዘትን ያስከትላሉ በሚል ነውር ከሚላቸው ድርጊቶች መካከል ከምግብ አዘጋጅዎች ማንነት ጋር የተያያዙ ድርጊቶች የሚጠቀሱ ሲሆን፤ የተወሰኑት ከዚህ በታች ቀርበው የመረጃ ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡

### ነገዴዎች ያዘጋጁትን ምግብ መመገብ

በተጠኝው ወረዳ ውስጥ ከአብዛኛው የአካባቢው ነዋሪ የተለየ የአመጋገብ ልምድ ያላቸው የነገዴ ማህበረሰብ አባላት ይኖራሉ፡፡ የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ በቀረበበት ምዕራፍ 4 ውስጥ እንደተገለፀው ነገዴዎች በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የማይፈቀዱ የባህር ውስጥ እንሰሳትን (ጉማሬ፣ አንባዛ ...)፤ ተባርከው ያልታረዱ ወይም በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች የሞቱ የቤት እንሰሳትን ይመገባሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ ምክንያትም የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ የሆነው ማህበረሰብ እነሱ ያዘጋጁትን ምግብ መመገብን የክርስትና ሃይማኖትን ስርዓትና የአካባቢውን የአመጋገብ ልማድ ከመጣስ ጋር አስተሳስሮ ይመለከተዋል፡፡ ይህን በሚመለከት መረጃ ከሰጡ ሰዎች መካከል አቶ ድንቁ በላይነህ (ቃመ፣ መጋቢት 5/ 2008) "... ነገዴዎች ያዘጋጁትን ምግብ የበላ ሰው የረከሰ፣ ሃይማኖቱን የጣለ ማለት ነው፡፡ እናም ወደ ደብር (ቤተ ክርስቲያን ለማለት ነው) እንዲሄድ አይፈቀድለትም" ይላሉ፡፡

በክርስትና ሃይማኖት ተከታዩ ማህበረሰብ እምነት ነገዴዎች ቀደም ሲል በተጠቀሱት የአመጋገብ ልማዶቻቸው ምክንያት ከአካባቢው ባህላዊና ሃይማኖታዊ ስርዓት ያፈነገጡ ናቸው፡፡ ከማህበራዊ ልማዶች ማፈንገጥና ለስርዓት አለመገዛት ደግሞ በክርስትና ሃይማኖት ተከታዩ ማህበረሰብ ዘንድ ከመርከስ ወይም ንፁህ ካለመሆን ይቆጠራል፡፡ በመሆኑም ተጠኝው የክርስትና እምነት ተከታይ ማህበረሰብ ነገዴዎች ያዘጋጁትን ምግብ ከመመገብ የተቆጠበ ነው፡፡ ያዘጋጁትን ምግብ አለመጠቀም ብቻም ሳይሆን እነሱ ከገቡበት ቤት ገብቶም አይመገብም፡፡ ይህን በሚመለከት አቶ በላይ ዋለ (ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ የካቲት 7/ 2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው) እንዲህ ይላሉ፡፡

> እነሱ ከገቡበት ቤት የገባ ሰው ከአካባቢው ማህበረሰብ መገለል ይደርስበታል፡፡ ረክሷል ተብሎ ስለሚታመንም ወደሃይማኖታዊ ተቋማት እንዳይሄድ ይከለከላል፡፡ በዚህ ምክንያትም፤ ነገዴዎች እንደገቡበት ሳያውቅ ገብቶ የተመገበ ሰው ቢኖር እንኳ እንዳወቀ ፀበል ይረጫል፡፡ ባለምግብ ቤቶቹም ነገዴዎች ከቤታቸው ከገቡ ሌላ ተጠቃሚ አይገባም ስለሚባል ከመጀመሪያውም እንዲገቡ አይፈቅዱላቸውም፡፡ ምናልባት ሳይታወቁ ከገቡም እነሱ የገቡበት ቤት የገበያ ገድ የለውም ተብሎ ስለሚታመን ባለምግብ ቤቶቹ ማንነቱን ያላወቁት ሰው ገብቶ በወጣ ቁጥር ቤታቸውን በውሃ ይረጫሉ፡፡

በተጠኝው የክርስትና እምነት ተከታይ ማህበረሰብ ዘንድ የገበያ ገርጋሪ መንፈስን ለማውጣትና ደንበኛን ለመሳብ የንግድ ቤትን ውሃ መርጨት ትልቅ መፍትሄ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

በሌላ በኩል ግን ነገዴዎች ያዘጋጁት ምግብ ቢበላ ችግር የለውም የሚሉ መረጃ ሰጭዎችም አሉ፡፡ ለምሳሌ ያህልም፦ ወጣት ታጠቅ ቢሆነኝ (ቃመ፣ መጋቢት 5/ 2008) እንዲህ ይላል፡፡

> እኔ የነገዴ ማህበረሰብ ልጅ የሆነ አንድ የትምህርት ቤት ጓደኛ አለኝ፡፡ ከእሱ ጋር ብዙ እናወራለን፡፡ እና ሲያወራኝ ወላጆቼ አማራው አይወደንም፡፡ አብሮን ምግብም አይበላም እያሉ ይነግሩኛል ይለኛል፡፡ እኔ ግን ወላጆቼ ከሱ ጋር አብረህ አትታይ - ሌላ ጓደኛ አብጅ በኖርንበት አገር አታስወቅሰን ስለሚሉኝ ነው እንጅ አብሬው ብበላም ደስ ይለኝ ነበር፡፡ እሱ እንደነገረኝ ምግባችንም አይለያይም፡፡

## ቆዳ ሰሪዎች ያዘጋጁትን ምግብ  መመገብ

ተጠኝው የክርስትና እምነት ተከታይ ማህበረሰብ ከብዙሃኑ የተለየ የአመጋገብ ልምድ ያላቸው የማህበረሰቡ ክፍሎች ያዘጋጁትን ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ከሚኖረው አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል የተለየ የስራ ባህሪ ያላቸው የማህበረሰቡ ክፍሎች ያዘጋጁትን ምግብም አይመገብም፡፡ የተለየ የስራ ባህሪ ካላቸው መካከል ቆዳ ሰሪዎች ይጠቀሳሉ፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ቆዳ ሰሪዎች የተለያዩ የቆዳ ውጤቶችን እንዲሰሩለት የአካባቢው ማህበረሰብ በሚሰጣቸውም ሆነ እራሳቸው በሚገዙት ቆዳ ላይ የሚገኘውን የስጋ ቅንጣቢ ወጥ ሰርተው ይመገባሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን ለስራቸው አመች እንዲሆን ረዘም ላለ ጊዜ ውሃ ውስጥ ዘፍዝፈው ካቆዩት በኋላ በሚያወጡት ቆዳ ላይ ተለጥፎ የሚያገኙትን የስጋ ቅንጣቢም ይመገባሉ፡፡ ቆዳውን የሚያገኙትም በአካባቢው በሚኖሩ የክርስትናም ሆነ የእስልምና እምነት ተከታዮች ህግ ተባርኮ ከታረደ እንሰሳ ነው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ቆዳ ሰሪዎች ያዘጋጁትን ምንኛውንም ምግብ አይበላም (ዲያቆን ብርሃኔ ያረጋል፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ የካቲት 7/ 2008)፡፡ ምክንያቱም እንደዲያቆን ብርሃኑ  ከእነሱ ቤት ገብቶ መመገብ ማለት በአንድ በኩል የአካባቢው ባህል የማይፈቅደውን ምግብ መመገብ በመሆኑ ድርጊቱ የማህበረሰቡን ባህል ከመጣስ ይቆጠራል፡፡ በሌላ በኩልም እንሰሳው በየትኛው ሃይማኖት ተከታይ እንደታረደ ስለማይታወቅ ሃይማኖታዊ ስርዓትንም ከመጣስ ይቆጠራል፡፡ በመሆኑም ድርጊቱ ርክሰትን በማስከተልና ንፅህናን በማሳጣት ማህበረ ባህላዊም ሆነ ሃይማኖታዊ ውግዘትን የሚያስከትል ተደርጎ ይታሰባል፡፡

በመስክ የመረጃ ስብሰባ ወቅት ማረጋገጥ እንደተቻለው ነገዴዎችም ሆኑ ሌሎች የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች (ቆዳ፣ ብረት፣ ሸክላ … ሰሪዎች) ሌላው የማህበረሰብ ክፍል ያዘጋጀውን ምግብ በየትኛውም ጊዜና ቦታ ይመገባሉ፡፡ ከሌላው ማህበረሰበብ ጋር በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎችም ይሳተፋሉ፡፡ ሆኖም ግን ከሌላው ማህበረሰብ ጋር በሚፈጥሯቸው ማህበራዊ ግንኙነቶች ወቅት ሌላው ማህበረሰብ ያዘጋጀውን ምግብ በጋራ ሲመገቡ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ተቀላቅለው መቀመጥ አይችሉም፡፡ አቀማመጣቸውም  ሌላው ማህበረሰብ ከሚቀመጥበት ቦታ ከታች በኩል ነው፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በማሳያነት የቀረቡት ድርጊቶች ማህበረሰቡ ውግዘትን ያስከትላሉ፣ ያረክሳሉ በሚል ነውር ከሚላቸው የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ሁኔታዎች መካከል

የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በአንዳንድ የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ዙሪያ የሚፈፀሙና የሚከናወኑ ድርጊቶች ደግሞ የጤና መታወክን የሚያስከትሉ ናቸው፡፡

### 5.1.2.4 የጤና መታወክን የሚያስከትሉ የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ልምዶች

የማህበረሰቡ የምግብ አይነት/ምርጫና ተያያዥ ነውሮች በተነሱበት ቀደም ባለው ክፍል አንዳንድ የምግብ አይነቶች በተመጋቢያቸው ላይ የጤና መታወክን ያስከትላሉ ተብሎ እንደሚታመን ተነስቷል፡፡ እንደዚሁ ሁሉ ከማህበረሰቡ ደንብ ያፈነገጡ አንዳንድ የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ልምዶችም የጤና መታወክን ያስከትላሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ማህበረሰቡ ከምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ጋር በተያያዘ የጤና መታወክን የሚያስከትሉ ናቸው በሚል በነውርነት ከሚፈርጃቸው መካከል ከምግብ አዘጋጅዎች ማንነት፣ ከእንግዳ አቀባበል፣ የተዘጋጁ ምግቦችን ከመመገብና መሰል ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ድርጊቶች ይጠቀሳሉ፡፡ በዚሁ መሰረትም ከተጠቀሱት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ በማህበረሰቡ ውስጥ ነውር የተባሉ የተወሰኑ ድርጊቶች ቀርበው ከዚህ በታች የመረጃ ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡

#### ሴት ልጅ የአድባር መስዋዕት ምግብን ማዘጋጀት

በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ በአካባቢው የሚኖርና የአካባቢውን ሰውም ሆነ እንስሳ ጤና የሚጠብቅ "አድባር" አለ ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለሆነም አካባቢውን ይጠብቃል፣ ሰውንም ሆነ እንሰሳትን ከአደጋ ይታደጋል ተብሎ የሚታመንበት ጠባቂ መንፈስ ይኖርባቸዋል ተብለው በሚታሰቡ ወንዞች፣ ሜዳዎች፣ ተራራዎችና ትልልቅ ዛፎች ስር በአመት አንዴ በጋራ ተገኝቶ መስዋዕት በማቅረብ ጠባቂ መንፈሱን መለማመንና በሽታን መሸኘት በአካባቢው የተለመደ ነው፡፡

ይህ የአደባባይ ስርዓት ከበራ በተለያዩ ባህላዊ ምግብና መጠጦች ታጅቦ የሚከናወን ነው፡፡ ለከበራው የሚያስፈልገው በግ ወይም ፍየል የሚታረደው፣ ለማባያ የሚሆነው ወጥ የሚሰራው እዛው ከበራ የሚደረግበት ቦታ ላይ ነው፡፡ ለስርዓተ ከበራው የሚሆነውን ወጥ የመስራትም

ሆነ ተመጋቢዎችን የማስተናገድ ስራው የሚከናወነው በወንዶች ነው፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ ውስጥ ሴቶች በዕለት ተለት የምግብ ማዘጋጀት ስራዎች የተጠመዱ ናቸው፡፡ በአመት አንዴ በሚካሄደው በዚህ የአደባባይ የምግብ ዝግጅት ስራ ላይ ግን የዘወትር ስራቸው የሆነውን ምግብ የማዘጋጀትና የማስተናገድ ድርሻ በወንዶች ይነጠቃሉ፡፡ ማህበረሰቡ በዚህ የአደባባይ ስርዓት ከበራ ላይ ምግብ የማዘጋጀቱን ስራ ከሴቶች የሚነጥቀው ሴቶች ንፁህ አይደሉም፤ ወንዶች ደግሞ ንፁሆች ናቸው ከሚል እሳቤ በመነሳት ነው፡፡

በየ28 ቀኑ የወር አበባ ማየት ለሴቶች የተሰጠ ተፈጥሯዊ ፀጋቸው ነው፡፡ በዚህ ተፈጥሯዊ ሁነት ምክንያትም ምናልባት ንፁህ ሆነው ቆይተው በድንገት የወር አበባ ሊመጣባቸው ይችላል፡፡ በዚህ መነሻነትም በማህበረሰቡ ዘንድ ሴቶች በተፈጥሯቸው ንፁህ አይደሉም ተብሎ ይታሰባል፡፡ አንዳንድ መረጃ ሰጭዎች እንደሚናገሩት የአደባባይ ስርዓት ከበራው የሚካሄድለት አድባር ንፁህ የሆነ ነገር ያስደስተዋል፡፡ ስለዚህ ሴቶች በዚህ የምግብ ዝግጅት ላይ እንዲሳተፉ አይፈቀድም፡፡ ምክንያቱም ሴቶች ምግቡን ካዘጋጁ የአካባቢው አድባር ስለሚቆጣ በተመጋቢዎቹ ላይም ሆነ በአካባቢው እንስሳት ላይ ያልተጠበቀ በሽታን ያመጣል (አቶ ድንቁ በላይነህ፣ ቃመ፣ መጋቢት 5/ 2008) ፡፡ ከመረጃ ሰጭዎች መካከል ወ/ሪት ፍሬዘር አድማሱ (ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ የካቲት 10/2008) ግን "አንዳንድ ወንዶች ዝም ብለው ሴቶችን በመናቅና በመጨቆን እኛ የበላይ ነን ስለሚሉ ነው እንጅ እኛም ምግቡን ብናዘጋጀው ችግር የለውም" በማለት የአቶ ድንቁን ሃሳብ ይቃወማሉ፡፡ ሆኖም ወ/ሪት ፍሬዘር ይህን ብትልም የአካባቢው ባህል ይህን የአደባባይ ስርዓት ከበራ ምግብ ሴቶች እንዲያዘጋጁት አይፈቅድም፡፡ በመሆኑም በዛን ቀን የሴቶች ድርሻ የምግብና መጠጥ ግብአቶችን፣ የመስሪያ ቁሰሳቁሶችን ከቤት ወደ ከበራ ቦታው በመውሰድ ለወንዶች ማስረከብና ወንዶች ያዘጋጁትን መመገብ ነው፡፡

የዕለቱ የምግብ ዝግጅትና መስተንግዶ ከተጠናቀቀ በኋላ ከተመጋቢዎች የተረፉ ምግብና መጠጦችም ሆኑ የመስሪያ ዕቃዎች ወደ ቤት አይመለሱም፡፡ ምክንያቱም የተጠቀሱት ነገሮች ወደ ቤት ከተመለሱ አድባሩ ስለሚቆጣ በአካባቢው ሰላምና ጤና ይጠፋል - በዕለቱ ወደ ጫካ፣ ተራራ፣ ገደል የተሸኘው የሰውም ሆነ የእንስሳት በሽታም ከተራረፉት ምግቦችና ከመስሪያ ዕቃዎች ጋር አብሮ ወደ ቤት ይመለሳል ተብሎ ይታመናል፡፡

## መካን ሴት በአራስ እህል ዝግጅት ላይ መሳተፍ

መካኖች በፈጣሪ የተረገሙ ስለሆኑ ሰውን የሚጎዳ ክፉ አይን (የቡዳ መንፈስ) ያደረባቸው ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ ምክንያትም በማህበረሰቡ ውስጥ የተጠሉና የሚፈሩ ናቸው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ መካንነት ከሴቶች ጋር የተያያዘ ነው፡፡ መካንነት በወንዶች ላይ ይኖራል ተብሎ አይታመንም፡፡ በዚሁ መነሻነትም መካን ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ጥሩ ግምት ስለማይሰጣቸው በአንዳንድ ማህበራዊ ግንኙነቶች ላይ ከተቀረው የአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በእኩልነት እንዲሳተፉ አይደረጉም፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት መካን ሴት በአራስ እህል ዝግጅት ላይ እንድትሳተፍ አይፈቀድላትም፡፡ ምክንያቱም ክፉ አይን ስላላት በአራሶቹም ሆነ በሚወለዱት ህፃናት ላይ ህመምን ታመጣለች ተብሎ ይታመናል፡፡ መካኖች እንዳይሳተፉ የሚከለከሉት በአራስ እህል ዝግጅት ላይ ብቻ አይደለም፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ መካኖች በምጥ ጊዜ ከቤት ውስጥ ገብተው ከሌሎች ሴቶች ጋር በመሆን በምጥ ላይ ላለችው እናት እንዲለማመኑላትም አይፈቀድም፡፡ ምክንያቱም እነሱ ከገቡ "ምጡ ይጠናል - ወሳጅ ይስባል" ተብሎ ይፈራል፡፡ ስለዚህ "ደጅ ሁናችሁ አግዙን አለማምኑን" በሚል ከተወሰኑ ሌሎች ሰዎች ጋር ተቀላቅለው ከቤት እንዲወጡ ይደረጋሉ፡፡ እነሱም ይሄ እንደሚባል ስለሚያውቁ አንዳንዶቹ ስሜታቸውን ተቆጣጥረው ከውጭ በመቀመጥ የብስራቱን ዜና ይከታተላሉ፡፡ አንዳንዶቹ ግን እስክትገላገል ድረስ ከመጀመሪያውም ያልሰሙ መስለው ከቤታቸው ይቆዩና እልል ሲባል ገብተው ይቀመጣሉ፡፡ ይህን በሚመለከት መረጃ ከሰጡ ሰዎች መካከል ወ/ሮ እማሆይ ድንቄ ካሳ (ቃመ፣ የካቲት 10/ 2008) እንዲህ በማለት ይገልፃሉ፡፡

> በምጥ ላይ ያለች ሴት እስክትገላገል ድረስ መሃኖች ወደ ቤት አይገቡም፡፡ የመውለዷ ምስራች እንደተነገረ ግን እንደማነኛውም ሰው ይገባሉ፡፡ ሌሎች ያዘጋጁትን "የማሪያም ምሳ[13]" ይቀምሳሉ፡፡ ከበሉ ከጠጡ በዋላም እንደሰው ሁላ "ማሪያም በሽልም ታውጣሽ[14]"፣ "ማሪያም ጭንሽን ታሙቀው[15]" ብለው መርቀው ይወጣሉ፡፡

ከመረጃ ሰጭዎች መካከል ወ/ሮ አጀቡሽ አለማ (ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ የካቲት 10/ 2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው) እንደተናገሩት ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ

---

[13] ሴት ስትወልድ የምትበላው የመጀመሪያው ገንፎ፡፡

[14] ጠያቂዎች አራስ ሴትን ጠይቀው በሚወጡ ጊዜ ከአራስ ቤት በደህና አምረሽ ውጭ በማለት ለአራሷ የሚመኙላት የመልካም ምኞት መግለጫ፡፡

[15] አራስ ሴት የአራስነት ጊዜዋን ጨርሳ በድጋሚ ለወሲባዊ ግንኙነት ብቁ እንድትሆን በመመኘት የሚነገር የመልካም ምኞት መግለጫ፡፡

ጨርሰው ያልወለዱ መካን ሴቶች ይቅርና ወልደው የሞተባቸው፣ ብዙ መውለድ ፈልገው ያልቻሉ ሰዎች ጭምር ልጅ በበዛበትና በአራስ ቤት ውስጥ ሲገኙ አይናቸው ይፈራል፡፡

## እንግዳ ሰውን ሳያበሉ መላክ

በማህበረሰቡ አካባቢ በአንድ ሰው ቤት አዲስ እንግዳ ሲገኝ የቤተሰቡ ደስታ ትልቅ ነው፡፡ ምክንያቱም እንግዳ በምድር ላይ እያለን ለሰራነው ደግም ሆነ መጥፎ ስራችን በላይኛው ቤት (ከሞት በኋላ አለ በሚባለው አለም) ምስክርነት የሚሰጥ ፈጣሪ የላከው "የእግዚሂር እንግዳ" ነው ይባላል፡፡

በመሆኑም በማህበረሰቡ ውስጥ እንግዳ ሲመጣ ቤት ያፈራውን አብልቶና አጠጥቶ መላክ የተለመደ ነው፡፡ በተቃራኒው ሳያበሉ መላክ ደግሞ የተነወረ ድርጊት ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ እንግዳን ምግብ ሳያበሉ መመለስ በእንግድነት በመጣው ሰው ላይ ጥነን (አንገትን የሚያጣምም በሽታ መጠሪያ ነው) የተባለ በሽታን ያመጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡ የጥነን በሽታ መነሻውም ረሃብ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ማህበረሰቡ ይሄን የሚልበትና የእንግዳ መቀበልን ተገቢነት የሚያጠናክርበት በአካባቢው ተከስቷል የሚለው አፈ ታሪክ ያለው ሲሆን ፤ታሪኩንም መረጃ ሰጭዎች እንዲህ በማለት ተርከውታል፡፡

> በድሮ ጊዜ አንድ በጣም ስስታምና ንፉግ የሆነ ሃብታም ሰው በአካባቢው ይኖር ነበር፡፡ ይህ ሰው ከዕለታት አንድ ቀን አንድ እንግዳ ሰው ወደቤቱ መጣበት፡፡ ነገር ግን የመጣውን እንግዳ እህል ውሃ ሳይለው ሸኘው፡፡ እንግዳውም በጣም ተርቦ ወደቤቱ እንደተመለሰ በ"ጥነን" በሽታ ታመመ፡፡ በዚህ ምክንያት አዋቂ (ጠንቋይ) ዘንድ ሄዶ ለህመሙ መፍትሂ እንዲሰጠው ጠየቀ፡፡ አዋቂውም ከዚህ በፊት ምግብ ያልበላህበትን ቤት በድንጋይ ብትመታ ትድናለህ አለው፡፡ ሰውየም በእንግድነት ሄዶ ያላስተናገደውን ሃብታም ሰው ቤት መደብደብ ጀመረ፡፡ በዚህ ጊዜ የአካባቢው ሰዎች ለምን የሰው ቤት እንደሚደበድብ ጠየቁት፡፡ ሰውየውም በእንግድነት ከቤቱ መጥቼ ሳያበላና ሳያጠጣ አባረረኝ፡፡ በዚህ የተነሳ ረሃብ ስለበዛብኝ ለበሽታ ተዳረኩ፡፡ አዋቂ ስጠይቅም የበሽታህ መድሃኒት ያልበላህበትን ቤት መምታት ነው ስላለኝ ከበሽታየ ለመዳን ነው በማለት ሃብታሙን ሰውየ በአካባቢው ማህበረሰብ ፊት አዋረደው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰዎች በጥነን በሽታ ሲታመሙ ያልበሉበትን ቤት በድንጋይ መደብደብ ጀመሩ፡፡ በዚህ የተነሳ አዲስ እንግዳ ሲመጣ ሳያበሉና ሳያጠጡ መላክ በአካባቢው ትልቅ ነውር ሆነ (አቶ ድንቁ በላይነህ፣ ቃመ፣ መጋቢት 5/ 2008)፡፡

ከዚህ አፈታሪክ መገንዘብ እንደሚቻለው እንግዳን ተቀብሎ በአግባቡ አለማስተናገድ ማህበረሰቡ ለህመም መንስኤ አድርጎ የሚወስደው አንዱ ጉዳይ ነው፡፡

## የባለዛር የተባሉ ነገሮችን መመገብ

በማህበረሰቡ ውስጥ ዛር የሰፈረባቸው ሰዎች ለዛር መንፈሳቸው ማረፊያና መለማመኛ በሚል በዋናነት የቤት እንስሳትን ለይቶ ማስቀመጥ የተለመደ ነው፡፡ ከእንስሳቱ መካከልም ዶሮና በግ ይጠቀሳሉ፡፡ ስለሆነም ለባለዛሮች ተብለው የተለዩ እንስሳትን ከእነሱ ውጭ የሆነ ሰው መብላት አይችልም፡፡ ምክንያቱም የእነሱ የተባሉ ነገሮችን መመገብ የዛር መንፈሱ ተቆጥቶ ወደ ተመገቡት ሰዎች እንዲተላለፍ ያደርጋል፣ በተመጋቢዎቹ ላይ ያልተገመተ በሽታን ያመጣል (ወ/ሮ አይናለም ግርማ፣ ቃመ፣ መጋቢት 5/ 2008)፡፡ እንደ ወ/ሮ አይናለም የባለዛር ተብለው የተለዩ እንስሳትን ባለዛሮቹ እያራቡና እየሸጡ በገንዘቡ ራሳቸው ይጠቀሙበታል፤ ብዙ የተለመደ ባይሆንም ለእነሱ የተባሉ እንስሳትን እራሳቸው ብቻ (በተለይም ዶሮንና እንቁላልን) ይበላሉ፡፡ ስለሆነም በተጠኝ ማህበረሰብ ውስጥ የባለዛር የተባሉ ንብረቶችን መመገብ የተከለከለ ተግባር ነው፡፡

## “የደጁ” ስርዓተ ከበራ የተዘጋጀ ምግብን ቤተዘመድ ያልሆነ ሰው መመገብ

በማህበረሰቡ ውስጥ ቤተዘመዶች ተሰባስበው በአመት አንድ ጊዜ በአካባቢያቸው ባለ አንድ ትልቅ ዛፍ ስር በጋራ (የፆታም ሆነ የእድሜ ልዩነት ሳይኖር) የሚያከብሩት “የደጁ” የተሰኘ ስርዓተ ከበራ አለ፡፡ “የደጁ” የተባለበት ምክንያት ከቤት ውጭ የሚከናወን ስርዓተ ከበራ በመሆኑ ነው፡፡ ስርዓተ ከበራውን የሚከናውኑት ቀንድ ያለው፣ አካሉ ያልጎደለና ያልተቀጠቀጠ (ያልሸናም ይሉታል) ወንድ ፍየል አርደው በጋራ በመመገብ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ አካሉ የጎደለና የሴት ጾታ ያለው ነገር ሁሉ የአካባቢውን ቆሌ የሚያስቆጣ ተደርጎ ይታሰባል፡፡

ፍየሉ የሚገዛው ሁሉም የስርዓቱ ተካፋዮች በሚያደርጉት የገንዘብ መዋጮ አይደለም፡፡ ከተሳታፊዎቹ መካከል የመግዛት አቅምና ፍላጎት ያለው ወይም ለቀጣዩ ዓመት በሰላም ቢያደርሰኝ ብሎ ለአካባቢው ቆሌ የተሳለ አንድ ሰው ይሄ የደጁ ይሁን ብሎ ገዝቶ ያቀርባል፡፡ በስርዓተ ከበራው ላይ ያልተገኘ ሰው አመቱ አይባረክለትም - የጤና መታወክም ያጋጥመዋል ተብሎ ስለሚታመን በግብዣው ላይ ቤተዘመድ የሆነ ሁሉ አይቀርም፡፡ በዚህ የምግብ ግብዣ ላይ ቤተዘመድ ያልሆነ ሰው አይሳተፍም፡፡ ይህን በሚመለከት መረጃ ከሰጡ ሰዎች መካከል አቶ ደስታው አባይነው (ቃመ፣ መጋቢት 5/ 2008) የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> የደጁ ተብሎ በተዘጋጀ እህል ውሃ ላይ ቤተሰብ ያልሆነ የአካባቢው ሰውም ሆነ አልፎ ሂያጅ መንገደኛ እንዲገኝ አይፈቀድለትም፡፡ እሱም ይህን ስለሚያውቅ በአካባቢው አይቀርብም - አይበላም፡፡ ከበላም የአካባቢው ቆሌ ስለሚቆጣ የበላው ሰው ይታመማል፡፡ የማህበረሰቡ አብሮ የመብላት የመጠጣት ባህል በዚህ ጊዜ ይሻራል፡፡ ቤተሰብ ያልሆነ ሆኖ ነገር ግን አብሮ የሚኖር እንደ ሰራተኛ አይነት ሰው አብሮ መሳተፍ ይችላል፡፡ የደጁን ያላደረገ ቤተሰብ ቢኖር ግን ሳር ቤቱ በነፋስ ይወሰድበታል፣ በቤተሰቡ ላይም በሽታ ይከሰታል፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ የደጁ ስርዓተ ክንውን አካባቢውንና ቤተሰቡን ይጠብቃል ተብሎ የሚታመነውን ቆሌ ለመለማመን በሚል የሚፈፀም ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ስርዓተ ክንውን አለመፈፀምም ሆነ በተወሰነ ጊዜ ጀምሮ ማቋርጥ ለአካባቢው ቆሌ ካለመታዘዝ የሚቆጠርና በዚህም ምክንያት ቤተሰቡን ለተለያዩ በሽታወች የሚዳርግ ተደርጎ ይታሰባል፡፡

## በጨለማ ውስጥ ሆኖ መመገብ

በማህበረሰቡ ውስጥ ጨለማ የሚፈራ ጊዜ ነው፡፡ በጨለማ ውስጥ ክፍቱን የተገኘ ነገር ሁሉ አስጠቂ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ብርሃን እያለቀ መሽትሽት ሲል በሩን ይዘጋል ያጠብቃል፣ ከቤት ውጭ ያለን እቃ ሁሉ ለቃቅሞ ያስገባል፡፡ የእንጀራ ሞሰቡን፣ የዱቄት ጉሽጉሻውን፣ የሊጥ ቡሃቃና ሌሎችም ለዕለትም ሆነ ለረጅም ጊዜ አዘጋጅቶ የሚጠቀምባቸውን ሁሉንም ምግቦችና የምግብ ማስቀመጫወች ይከዳድናል፡፡ የሊቦ ከምከም አባቶች ራት ከበሉ በኋላ የሚመርቁት “ራትና መብራት አይንሳችሁ” ብለው ነው፡፡ መብራት ብርሃን ነው፡፡ ራት የጨለማ ጊዜ ምግብ ነው፡፡ በጨለማ ሲበሉ ምን እንደሚበሉ ከማን ጋር እንደሚበሉ አይታወቅም፡፡ ይህን በሚመለከት አቶ ቢሆነኝ አጠቃ (ቃመ፣ ሚያዚያ 3/2008) “የጨለማ መብል ከሰይጣን ጋር አብሮ ሞሰብ መሰራት ነው፡፡ ራት እየተበላ እያለ መብራት ከጠፋ ሰዎች ሊጎርሱት ያነሱትን ያስቀምጣሉ፣ ሞሰቡን ከድነው ኩራዝ ሊለኩሱ ይሮጣሉ” ይላሉ፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ሰይጣን ሞሰብ በሚቀርብበት አካባቢ እንደማይጠፋ፣ በተለይም ጨለማ ደግሞ በዋነኛነት ሰይጣን የሚንቀሳቀስበት ጊዜ እንደሆነና በጨለማ ውስጥ ሆኖ የሚበላ ምግብ ተመጋቢወቹን ለህመም እንደሚዳርግ ይታመናል፡፡ በመሆኑም በማህበረሰቡ ውስጥ በጨለማ ውስጥ ሆኖ መመገብ የተከለከለ ድርጊት ነው፡፡ በተጨማሪም መብራት እያለም ቢሆን በሌሊት ቢርብ ምግብ አይበላም - ሞሰብም አይከፈትም፣ ውሃ ቢጠማ አይጠጣም፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን በማህበረሰቡ ውስጥ በምሽት ወደ ውስጥ የሚገባ እንጅ የሚወጣ ነገር

አይኖርም፡፡ የገባ አይወጣም - የመጣ ነገርም አይመለስም፡፡ ጎረቤታሞችም ሆኑ ዘመዳሞች ከመሸ በኋላ ዕቃ አይዋዋሱም፡፡ እሳት አይጫጫሩም - ጨው ቢጎድል፣ ዘይት ቢያንስ፣ እንጀራ ቢታጣ አበድሩን ብለው አይጠይቁም፡፡

## ጠላን እንደተቀዳ መጠጣት

በማህበረሰቡ ውስጥ የበሽታ አጋላጭ ክስተት ተደርጎ የሚወሰደው ሌላኛው ጉዳይ ጠላ የሚጠጣበት አኳሃን ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ጠላ ለ[እ]ርኩስ መንፈስም ሆነ በቀላሉ መጉዳት ለሚፈልግ ሰው አጋላጭ ነው በሚል ይፈራል፡፡ ጠላና የጠላ እህል በተዘጋጀበት አካባቢ [እ]ርኩስ መንፈስ አይጠፉም፡፡ ይሄ ክፉ መንፈስ የጠላ ጥንስሱን ይሰልበዋል - ጠላው አተላ (ዝቃጭ) እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ይህ ስለሚፈራም ጠላውን ከ[እ]ርኩስ መንፈስም እንዲጠብቁ የጠላ እህል በተዘጋጀበት እንስራ ጆሮ ላይ ብረት ነገሮች ይደረጋሉ፡፡ ስለዚህ በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ ጠላን ማዘጋጀት ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚሻ ትልቅ ጉዳይ ነው፡፡

በማህበረሰቡ እምነት ክፉ መንፈስ በጠላ ዝግጅት ጊዜ ብቻም ሳይሆን ዝግጅቱን አልፎ ለመጠጥ በተዘጋጀው ጠላ ውስጥም አይጠፉም፡፡ ስለሆነም ጠላ እንደ ዝግጅቱ ሁሉ አጠጣጡም በደንብና በስርዓት መከናወንን ይጠይቃል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ሰዎች በአንድ አጋጣሚ የተጣሉትን ሰው ከሚያጠቁባቸው መንገዶች መካከል አንዱና ዋነኛው ባዕድና ጎጅ ነገሮችን በጠላ ውስጥ ጨምሮ መስጠት ነው፡፡ በመሆኑም ከሆነ ቤት ሄደው ጠላ የቀረበላቸው ሰዎች ከመቅመሳቸው በፊት ጠላውን መሬት ላይ ያሳርፋሉ፡፡ ይህን አስመልክቶ መረጃ ከሰጡት መካከል ወ/ሮ ስፍራሽ መኮንን (ቃመ፣ መጋቢት 5/ 2008) ጠላ ከመቀመሱ በፊት መሬት ላይ እንዲያርፍ በመደረጉ "የሚጠጡ ሰዎችን ለመጉዳት የሚጠብቀው ክፉ መንፈስ ጠላው አፈር ሲነካ ይደነግጣል፣ የክፉ መንፈስ ወኪል የሆኑ ሰዎች ከጠላው ጋር የቀላቀሉት ጎጅ ነገር ካለም አፈሩ ይሽረዋል - ያረክሰዋል" በማለት ይገልፃሉ፡፡ ስለሆነም የአካባቢው ማህበረሰብ በጠላ ምክንያት ሊመጣብኝ ይችላል የሚል ስጋቱን የተሰጠውን ጠላ ከመጠጣቱ በፊት መሬት ላይ በማሳረፍ ይወጣል፡፡

ጠላን መሬት ላይ ሳያሳርፉ መጠጣት ብቻም ሳይሆን መሬት ላይ እንዲያርፍ ከተደረገ በኋላም ቢሆን አንስቶ በአንዴ ብዙ መጠጣት፣ ቆሞ መጠጣት አይፈለግም፡፡ ምክንያቱም በማህበረሰቡ ውስጥ የመጀመሪያ መጠጥን በአንዴ ብዙ መጠን መውሰድና ቆሞ መጠጣት ያሰክራል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለሆነም ጠላው ከመሬት ላይ ተነስቶ ትንሽ ከተቀመሰ በኋላ

እንደገና መሬት ላይ እንዲያርፍ ይደረጋል፡፡ ጠላም ሆነ ማንኛውም የሚጠጣ ነገር ሲቀርብ ሰዎች ቁጭ ብለው እንዲጠጡ ይደረጋል፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ በጠላ ምክንያት ሊመጣ ይችላል ተብሎ የሚፈራን ነገር የማስወገጃ ሌላኛው መንገድ ጠላውን ያዘጋጁና የሚጋብዙ ሰዎች በመጀመሪያ እነሱ ቀምሰው እንዲሰጡ ማድረግ ነው፡፡ በአካባቢ ጠላ አስጠቂ ነው ተብሎ ስለሚታመን ለመጠጣት ከተዘጋጁት ሰዎች ፊት ቀምሶ (ፉት ብሎ)[16] የመስጠት ባህል በአካባቢው የተለመደ ነው፡፡ በመሆኑም ጋባዦች ያዘጋጁት ጠላ ለጠላ ከሚያስፈልጉት ነገሮች ውጭ ምንም አይነት ሌላ ባዕድ ነገር እንዳልተቀላቀለበት ቢያውቁም እንኳ በአንድ በኩል የጠጭዎችን ጥርጣሬ ለማስወገድ፣ በሌላ በኩልም ቀምሶ መስጠት እንደባህል ስለተወሰደ የቀዱትን ጠላ ቀምሰው ይሰጣሉ፡፡

[16] ቀመሳው በመጠጫ እቃ ላይ ከተቀዳው ጠላ ትንሽ እጅ ላይ በማፍሰስና እሱን ጠጥቶ በማሳየት የሚገለፅ ሲሆን፣ ፉት ብሎ የሚለው ትንሽ ጠጥቶ ወይም ቀምሶ ለማለት ነው፡፡

## 5.2. በመረጃ ትንተናው የተገኙ የጥናቱ አበይት ውጤቶች

ማህበረሰቡ ከምግብ አይነት ምርጫ፣ አዘገጃጀትና አመጋገብ ጋር በተያያዘ ነውር የሚላቸውን ጉዳዮች በሚመለከት ተሰብስበው በተተነተኑት መረጃዎች ውስጥ የተገኙ የጥናቱ ዋና ዋና ውጤቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ማህበረሰቡ ክልክል ለሚላቸው የምግብ አይነቶች፣ አዘገጃጀትና አመጋገብ ልምዶች የሚሰጣቸው ምክንያቶች በዋናነት ጤናን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡

2. በማህበረሰቡ ውስጥ ክልክል ከሆኑ የምግብ አይነቶች መካከል ስጋ ቀዳሚ ነው፡፡

3. በማህበረሰቡ ውስጥ ሴቶች ንፁህ አይደሉም በሚል እነሱ እንዲሳተፉባቸው የማይፈቀዱ የምግብ ዝግጅቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ሴት ልጅ የአድባር መስዋዕት ምግብን ማዘጋጀት አትችልም፡፡

4. በማህበረሰቡ ውስጥ የተከፈለ ወይም ሙሉነቱን ያጣ ነገር ሁሉ የመጥፎ ገጠመኝ ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ለምሳሌ ፡- ለራስም ሆነ ለእንግዳ የተቆረሰ እንጀራ ማቅረብ ረድኤት የሚያሳጣ ድርጊት ተደርጎ ይታሰባል፡፡

5. ከምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ጋር የተያያዙ አንዳንድ የማህበረሰቡ ነውሮች ከአካባቢው ለየት ያለ የስራ ባህሪና አመጋገብ ባላቸው የማህበረሰቡ ክፍሎች ላይ ብቻ የሚተገበሩ ናቸው፡፡

6. ከምግብ አይነቶች ጋር የተያያዙት የማህበረሰቡ አብዛኞቹ ነውሮች ከሴቶች ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡

7. ማህበረሰቡ በእርግዝና ላይ ላሉ ሴቶች ነውር ከሚላቸው የምግብ አይነቶች መካከል የፕሮቲን ይዘት ያላቸው የምግብ ዓይነቶች በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ፡፡

8. አንዳንድ የማህበረሰቡ ነውሮች ችላ እየተባሉ ወይም እየተጣሱ ናቸው፡፡

9. በማህበረሰቡ ውስጥ ነውሮች ጉዳት ይኖራቸዋል ተብሎ አይታመንም፡፡

10. ጥቁር ቀለም ያላቸው እንስሳትም ሆኑ የእህል አይነቶች በማህበረሰቡ ዘንድ ለምግብነት ተመራጭ አይደሉም፡፡

11. ማህበረሰቡ ነውር ለሚላቸው ድርጊቶች የሚያቀርባቸው ምክንያቶች በዋናነት የሚታመኑ እንጅ ተጨባጭ የሆነ ማስረጃ የሚቀርብባቸው አይደሉም፡፡

በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ስለምግብና ተያያዥ ነውሮች ያለው እውቀት ምን እንደሚመስል ከዚህ በላይ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ከዚህ በሚከተለው ምዕራፍ ደግሞ ከማህበረሰቡ በተሰበሰቡ የሞት ነውሮች ላይ የመረጃ ትንተናና የውጤት ማጠቃለያ ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## የሞት ነውሮች የመረጃ አቅርቦት፣ ትንተናና ውጤት ፦

ይህ ምዕራፍ ተጠኝው ማህበረሰብ ስለሞትና ከሞት ጋር ስለተያያዙ ነውሮች ያለውን ባህላዊ አስተሳሰብ በሚመለከት የተሰበሰቡ መረጃዎች ቀርበው የተተነተኑበትና በመጨረሻም በትንተናው የተገኙ የጥናቱ ዋና ዋና ውጤቶች ተጠቃለው የቀረቡበት ነው፡፡

## 6.1 የመረጃ አቅርቦትና ትንተና

ሞት የሰው ልጆችን በህይወት ከመኖር ወዳለመኖር የሚቀይር፤ ከሚወዱት ቤተሰብ፣ ጓደኛ፣ አካባቢ ወዘተ. የሚነጥል ክስተት በመሆኑ በተጠኝው ማህበረሰብ ዘንድ እንደእሱ የሚፈራ ነገር የለም፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ የሟች መንፈስ ልዩ የሆነ የማዳን ሃይል ያለው ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ይሁን እንጅ የማዳን ሃይል ያለው የሞተ ሰው ሁሉ አይደለም፡፡ ይህን በሚመለከት መረጃ ከሰጡ ሰዎች መካከል አባ ፍቅረማሪያም (ቃመ፣ ሚያዚያ 3/ 2008) እንዲህ ይላሉ፡፡

> የሟች መንፈስ የማዳን፣ ከፈጣሪ የማገናኘት ሃይል ተሰጥቶታል፡፡ ይሁን እንጅ ይህ አይነት ሃይል የተሰጣቸው ከመሞታቸው በፊት በአኗኗር ህይወታቸው ለሌሎች አርአያ የሆነ ግላዊ ህይዎትን የመሩ፤ ሃይማኖታቸውን የጠበቁ፣ ረዘም ያለ እድሜን የኖሩና በኖሩበት ዘመንም ለአካባቢው መልካም የሚባል ተግባር የፈፀሙና መልካም ባህሪ ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ሞትና የሙት መንፈስ የሚከበሩና የሚፈሩም ናቸው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ከሞትና የሙት መንፈስ ጋር በተያያዘ ሊፈፀሙ የሚገባቸውና የማይገባቸው ለሚላቸው ድርጊቶች ድንጋጌ ያወጣል፡፡ በድንጋጌዎቹ ውስጥም ሊፈፀሙ አይገባቸውም በሚል የደነገጋቸውን ድርጊቶች መፈጸም በማን ላይ ምን ሊያስከትል እንደሚችል አካባቢያዊ እውቀቱንና በተደጋጋሚ ሙከራ የዳበራቸውን ልምዶቹን ተጠቅሞ የራሱን ማብራሪያ ያቀርባል - እንዳይጣሱም ይከላከላል፡፡

ማህበረሰቡ ስለሞትና ከሞት ጋር ስለተያያዙ ድርጊቶች ያለውን እውቀት፣ ልምድና ትግበራ ሊያሳዩ የሚችሉ 35 የሚሆኑ ነውሮች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት ሁሉም ነውሮችም ነውር የተባሉ ድርጊቶችንና ድርጊቶቹ ነውር የሆኑበትን ምክንያት በሚገልጽ መልኩ በአባሪ - ሁለት ውስጥ ከተራ ቁጥር 1 - 35 ቀርበዋል፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡትና በአባሪው ውስጥ ለሰፈሩት ነውር የተባሉ ድርጊቶች ማህበረሰቡ የሚሰጣቸው ምክንያቶች ካላቸው የጋራ ባህሪ አኳያ ሲታዩ በ5 ጭብጦች ስር ተከፋፍለው ሊታዩ ይችላሉ፡፡ በዚሁ መሰረትም የነውሮቹ ምክንያቶች ነውሮቹ በአባሪ ውስጥ የሚገኙበትን ተራ ቁጥርና በየምድቡ ውስጥ የሰፈሩ ነውሮችን ብዛት በሚያሳይ መልኩ በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡

**ሰንጠረዥ - 1 የነውሩ ምክንያት፦**

| ተ/ቁ | የነውሩ ምክንያት | ነውሩ በአባሪው ውስጥ የሚገኝበት ተራ ቁጥር<br>ከ --- እስከ --- | የነውር ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ሞትና የሙት መንፈስን ከማክበርና ከመፍራት | 1 - 17 | 17 |
| 2 | መካንነትን ለመከላከል | 18 — 22 | 5 |
| 3 | ንፅህናን ላለማጣት | 23 - 27 | 5 |
| 4 | ከድርቅና ድህነት ለመጠበቅ | 28 - 32 | 5 |
| 5 | ሃዘንን ለመርሳት | 33 - 35 | 3 |

በዚሁ መሰረትም ከመስክ ከተሰበሰቡትና በሰንጠረዡ ላይ በ5 በጭብጥ ተከፋፍለው ከቀረቡት 35 መረጃዎች መካከል ሌሎችን ይወክላሉ የተባሉ 18 ነውሮችና ነውር ለመሆናቸው የተሰጡ ምክንያቶች በማሳያነት ቀርበው ከዚህ በታች አጭር የመረጃ ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡

### 6.1.1 ሞትን የሚጠሩና የሙት መንፈስን የሚያስቀይሙ ድርጊቶች

በአካባቢው ማህበረሰብ እምነት ሰዎች የሚሞቱት በሚያጋጥማቸው የጤና ችግር ወይም ድንገተኛ አደጋ ብቻ አይደለም፡፡ ከሞትና ከሙት መንፈስ ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ አንዳንድ ድርጊቶችም ሞት ከሞቱ ሰዎች ወዳልሞቱ ሰዎች እንዲተላለፍ ያደርጋሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ሞትና የሙት መንፈስ በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ የሚፈሩና የሚከበሩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የሚፈሩና የሚከበሩ በመሆናቸውም ማህበረሰቡ ለሞት ያጋልጣሉ፣ የሙት መንፈስን ያስቀይማሉ ከሚላቸው ድርጊቶች ለመራቅም ይሞክራል፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚያሳዩት ማህበረሰቡ ሞትን ይጠራሉ፣ የሙት መንፈስንም ያስቀይማሉ በሚል ነውር የሚላቸው የተለያዩ ድርጊቶች ያሉ ሲሆን፤ አብዛኞቹ ድርጊቶችም ከአስከሬን አቀማመጥ፣ ከቀብር ቦታ አቆፋፈር፣ ከአስከሬን ወደ ቀብር ቦታ አወሳሰድ፣ ከሃዘን አደራረስ፣ የሰውን መሞት ለሌሎች ከማርዳት፣ የሟችን ቤት ለሌሎች ከማሳየት፣ ከአቀባበር ስርዓት፣ ከቀብር መልስ ከሚፈፀሙና መሰል ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ድርጊቶች ይጠቀሳሉ፡፡

## አስከሬንን በጀርባው ማስተኛት

ማህበረሰቡ በአካባቢው ሰው ሲሞት የሟችን አስከሬን እስኪቀበር ድረስ የሚያቆይበት ደንብ አለው፡፡ በአካባቢው የሞተ ሰው ከመቀበሩ በፊትም ሆነ ሲቀበር የአስከሬኑ አቀማመጥ በጀርባው ተንጋሎ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ ይሁን እንጅ አንዳንዴ አንድ ሰው በድንገት በሚሞትበት ጊዜ የሟች የቅርብም ሆነ የሩቅ ዘመድ እስኪሰባሰብ ድረስ አስከሬኑ ሳይቀበር መዋል ማደር ሊኖርበት ይችላል፡፡

ሆኖም እንዲህ አይነት ድንገተኛ ሞት ካጋጠመና ዘመድ እስኪሰባሰብ ድረስ የሟች አስከሬን ሳይቀበር መዋል ማደር ካለበት በጀርባው ተንጋሎ ሳይሆን በሆዱ ተደፍቶ ከላዩ ላይ ድንጋይ መጫን አለበት፡፡ ሟች ህይወቱ ሲያልፍ አይኑን እንዳፈጠጠ ከነበረም በሆዱ እንዲተኛ ከመደረጉ በፊት አይኑ እንዲጨፈን ይደረጋል፡፡ ይህ የሚደረግበት ምክንያት በጀርባው ተኝቶ ከዋለ ካደረ ድርጊቱ የሟችን መንፈስ ሊወስድ የመጣውን መላዕክ ሞት ስለሚያስቆጣና ሌላ ሰው ስለሚጠራ፤ አይኑን እንዳፈጠጠ ከተቀበረም ሌላ ተጨማሪ ሞት ስለሚያስከትል ነው (አቶ ቢሆነኝ አጠቃ፣ ቃመ፣ ሚያዚያ 3/2008፤ አቶ ስለሽ መኮንን፣ ቃመ፣ ሚያዚያ 15/ 2008)፡፡ ስለዚህ ዘመድ እስኪሰባሰብ ድረስ አስከሬኑ በሆዱ ተደፍቶ ይቆይና የተጠበቀው ዘመድ መምጣቱ ሲረጋገጥና ለቀብር ለማዘጋጀት ሲፈለግ ተገልብጦ በጀርባው እንዲተኛ ይደረጋል - አይኑን መጨፈኑም ይረጋገጣል፡፡

## ለቀብር  የተቆፈረ ጉድጓድን ክፍት መተው

አንድ ሰው ሞቷል ተብሎ የሟች የቅርብም ሆነ የሩቅ ዘመድ ከተሰበሰበና ለቀብር የሚሆነው ጉድጓድም ከተቆፈረ በኋላ ሞተ የተባለው ሰው በድንገት ነቅቶ (ነፍስ ዘርቶበት) ይገኛል፡፡ ይህ አይነት ሁኔታ በአካባቢው ብዙ ጊዜ ይከሰታል፡፡ ሆኖም ለሟች ተብሎ የተቆፈረው

ጉድጓድ ጉዳይ የአካባቢውን ማህበረሰብ ያሳስበዋል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ክፍት የሆኑ ነገሮች የመጥፎ ነገር ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም ጉድጓዱ ሳይደፈን ከቀረ ከሞት የተመለሰው ሰው ቤተሰብ ውስጥ ሌላ ሞት ይከሰታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህ ክፍት የሆነው ጉድጓድ ሌላ ሞትን እንዳያመጣበት ስለሚፈራ የአካባቢው ማህበረሰብም የተቆፈረው ጉድጓድ ተመልሶ እንዲሞላ ያደርጋል፡፡ ይሁን እንጅ ይህ ጉድጓድ የሚሞላው ተቆፍሮ በወጣው አፈር ብቻ አይደለም፡፡ በመጀመሪያ እህል የቀመሰ (እህል የተፈጨበት) መጅ ተፈልጎ ጉድጓዱ ውስጥ እንዲገባ ይደረጋል፡፡ በማስከተልም ከጉድጓዱ ውስጥ የወጣውን አፈር መጁ ላይ በመመለስ ጉድጓዱ እንዲሞላ ይደረጋል፡፡

ከሌሎች ነገሮች ሁሉ መጅ የተመረጠበት ምክንያት ባይታወቅም በአካባቢው መጅን የመቅበር ባህል አጀማመሩ አለቃ ገብረሃና ሲሞቱ ተከስቷል ከሚባል አንድ አፈ ታሪክ ጋር ይያያዛል፡፡ አለቃ ገብረሃና ትውልዳቸውም ሆነ ሞታቸው ተጠኝውን ወረዳ በደቡብ አቅጣጫ በሚያዋስነው ፎገራ ወረዳ ውስጥ ነው፡፡ እኝህ ሰው ቀልደኛ፣ ብልህና ተንኮለኛ ነበሩ እየተባሉ የሚነገሩ ብዙ አፈ ታሪኮች ያሏቸው ሰው ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ ስለእሳቸው የሚነገሩ አፈ ታሪኮችን ማቅረብ የዚህ ጥናት አላማ ባይሆንም መረጃ ሰጭዎች ከመጁ አጀማመር ጋር በተያያዘ የተናገሩትን አንድ አፈ ታሪክ ብቻ ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ አፈ ታሪኩም እንዲህ የሚል ነው፡፡

> አለቃ ገብረሃና በዚች ምድር በነበሩበት ጊዜ ከቀልደኛነታቸውም ባሻገር ተንኮለኛና የሌላ ሰው ሚስትን በማማገጥ ትልቅ ሃጢያት የሰሩ ሰው ነበሩ፡፡ በመጨረሻም በድንገት ይታመሙና ይሞታሉ፡፡ የአካባቢው ሰውም የሚቀበሩበትን ቦታ ካዘጋጀ በኋላ አስከሬናቸውን ወደቀብር ቦታ ይዞ ይሄዳል፡፡ ነገር ግን በህይወት እያሉ የፈፀሙት ሃጢያት ፈጣሪን ስላስቀየመ ሲቀበሩ ጉድጓዱ በተደጋጋሚ ወደ ላይ/ወደ ውጭ እየገፋ ይመልሳቸዋል/ይተፋቸዋል፡፡ በዚህ ግዜም ከማህበረሰቡ መካከል አንድ ሽማግሌ ሰው ተነስተው እስኪ እህል የተፈጨበትን የድንጋይ ወፍጮ አምጥተን አብረን እንቅበረው የሚል ሃሳብ ያቀርባሉ፡፡ የአካባቢው ሰውም የተባለውን የድንጋይ ወፍጮ በማምጣት ከአለቃ ጋር አብሮ እንዲቀበር ያደርጋል፡፡ በዚህ ጊዜ አለቃና የወፍጮ ድንጋዩ የተቀበሩበት ጉድጓድ ከፍተኛ የሆነ አስፈሪ ድምፅ በማሰማት ወደውስጥ ይዟቸው ይሰምጣል፡፡ የአካባቢው ሰውም የድንጋይ ወፍጮው ጉድጓዱ አለቃን ወደላይ እንዳይገፋቸው በማድረጉ ቢደሰትም ከአስፈሪ ድምፅ ጋር ወደውስጥ ይዟቸው የሰመጠው ነገር ግን በጣም ያስፈራዋል፡፡ በዚህ ጊዜም የአካባቢው ማህበረሰብ አለቃን ወደ ታች ያሰመጣቸው አብሯቸው የተቀበረው የወፍጮ ድንጋይ ሃጢያተኛን የመለያና የፈጣሪ ቁጣን የማስተላለፊያ መንገድ ስለሆነ

ነው ማለት ነው ብሎ አመነ (አቶ ገብረአብ ደሴ፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ የካቲት 7/ 2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው) ፡፡

የአካባቢው ማህበረሰብ አንድ ሰው ሲሞት መሬት ከተፋው ሰውየው ሃጢያተኛ ነው ፣ ከድንጋይ ወፍጮ ጋር ሲቀበር መሬት ወደ ውስጥ ከሳበው ደግሞ ከሃጢያቱ ብዛት በተነሳ ፈጣሪ ስለረገመው ነው ብሎ ተረዳ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ማህበረሰቡ ሃጢያት ሰርቶ እንደ አለቃ መሬት እንዳትተፋውና ከድንጋይ ወፍጮ ጋር አብሮ የመሬት ናዳ እንዳይበላው ፈርቶ (መጥፎ ነገር ከመስራት ተቆጥቦ) ይኖራል፡፡ በዚህ ምክንያትም ከአለቃ በኋላ በአካባቢው መሬት የተፋችው ሌላ ሰው የለም ይባላል፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ አንድ ሰው ሲሞት ነፍሱን ከስጋው በመለየት ወደ "ገነት" ና ወደ "ሲኦል" ለመውሰድ የሚመጡ "መላዕከ ሞት"ና "መላዕከ ፅልመት" የሚባሉ መናፍስት አሉ ይባላል፡፡ እንደ አባ ፍቅረማሪያም (ቃመ፣ ሚያዚያ 4/ 2008) ገለፃ፦

> ገነት ፃድቃን ወደ መንግስተ ሰማያት ከመግባታቸው በፊት ወይም እስከ እለት ምፅአት የሚቆዩበት ሰማያዊ ቦታ ሲሆን፤ መላዕከ ሞት ደግሞ ነፍስን ከስጋ ለመለየት የሚላክ መልአክ ነው፡፡ ሲኦል ክፉ የሰሩ ሰዎች እስከ እለተ ምፅአት የሚኖሩበት የስቃይና የመከራ ቦታ ሲሆን፤ መላዕከ ፅልመት ደግሞ የጨለማ መልአክ፣ ሰይጣን ነው፡፡

ስለሆነም የሚችን ነፍስ ከስጋው በመለየት ወደ "ሲኦል" ለመውሰድ የሚመጣው "መላዕከ ፅልመት" ከሞተ በኋላ በተነሳው ሰው ሁኔታ ተበሳጭቶ ሌላ ሞትን እንዳያስከትል ይረዳል በሚል ማህበረሰቡ እህል የቀመሰን (የተፈጨበትን) መጅ ይቀብራል፡፡ እህል የቀመሰ መጅ ሞቶ የተነሳው ሰው የበላውን፣ የጠጣውን ነገር ሁሉ ይተካል፣ ክፉ መንፈሱ መጁን ተከትሎ ይሄዳል ተብሎ ስለሚታሰብ በጉድጓዱ ውስጥ እሱን መቅበር የግድ ነው፡፡ ይሄ ሳይሟላ ከቀረ ግን ክፉ መንፈሱ ከአካባቢው ርቆ ስለማይሄድ የተፈራውን ሞት ያስከትላል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም በአካባቢው እህል የቀመሰ መጅ ቢጠፋ እንኳ አዲስ ድንጋይ ተፈልጎና የመጅ ቅርፅ እንዲኖረው ተደርጎ የተወሰነ እህል ከተፈጨበት በኋላ እንዲቀበር ይደረጋል፡፡

## አስከሬንን በዋናው በር ማውጣት

በማህበረሰቡ ውስጥ አስከሬንን ወደ ቀብር ቦታ ለመውሰድ ሬሳው ከቤት የሚወጣበት መንገድም ሞትን ለመጥራት ምክንያት ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡ ማህበረሰቡ ሰው

በሚሞትበት ጊዜ ሬሳውን ከቤት አውጥቶ ወደቀብር ቦታ ለመውሰድ የቤቱን ዋና በር አይጠቀምም፡፡ በምትኩ ቤቱ በጀርባው በኩል እንዲፈርስ ተደርጎ በሚዘጋጅ ጊዜያዊ በር ሬሳው እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

ማህበረሰቡ አስከሬንን በዋና በር ማውጣት በራስ ላይ ሞትን ይጋብዛል የሚል እምነት አለው፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ቤተሰቡ አዘውትሮ የሚጠቀምበት የፊት ለፊት በር በቤቱ ውስጥ የሞት አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ ይፈራል፡፡ የተለመደውና ነባሩ በር ሟች በህይወት ሳለ ይወጣ ይገባበት የነበረ ነው፡፡ የሟችን ነፍስ ለመውሰድ የሚመጡት መናፍስትም በዚሁ በር ስለሚገቡ በሩን ለይተው ያውቁታል፡፡ ስለሆነም የሟች መንፈስም ሆነ አብረውት ያሉት መናፍስት ባወቁትና በገቡበት በር ሲወጡ ሌላም ሰው ጨምረው መሄድ ይፈልጋሉ (ወ/ሮ አጀቡሽ አለማ፣ ቃመ፣ ሚያዚያ 8 /2008)፡፡ እንደእኚህ መረጃ ሰጭ መናፍስቱ ቀድመው ያወቁትን በር ሲያጡትና አዲስ በር ሲገጥማቸው ግን ተደናግጠው ተጨማሪ ሞትን ሳያስቡ እንግዳ በሆነው በር ወጥተው ይሄዳሉ ፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ቀድሞ የታወቀ፣ ነባር የሆነ ነገር የመጥፎ ገጠመኝ፤ በድንገት የተፈጠረ አዲስና እንግዳ ነገር ደግሞ የመልካም አጋጣሚ ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ስለሆነም ማህበረሰቡ መልካም የሚለው አጋጣሚ እንዲያልፈው ስለማይፈልግ በገጠር የሚኖረው ማህበረሰብ የቤቱ በር አንድ ስለሆነ በሞት ጊዜ የግድ ቤቱን በኋላ በኩል አፍርሶ ጊዜያዊ በር ማውጣት ይጠበቅበታል፡፡ በከተማ አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ ደግሞ የቤቱ በር እንደገጠሩ አንድ ብቻ ከሆነ ጊዜያዊ በር ይከፍታል፤ ዋና በር ፊት ለፊት ኖሮት ቤተሰቡ ብዙም የማይጠቀምበት በር በጀርባ በኩል ካለ ሬሳው በዛ በር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ ከቤቱ በስተኋላ በኩል ጊዜያዊ በር ለማውጣት የማያስችል ሁኔታ ተፈጥሮ ሬሳውን በፊት ለፊት በር ማውጣት የግድ ከሆነ እንኳ ቢያንስ ከቤቱ በስተኋላ በኩል ሂዶ ሰዎች በአጥር ላይ ተቀባብለው እንዲያወጡት ይደረጋል፡፡

## የሟች ቤተሰብን ትከሻ በግራ እጅ መንካት

በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ አንድ ሰው ሲሞት የሟች ቤተሰብን በቅርብ ተገኝቶ ማፅናናት፣ የሟች ቤተሰብን ትከሻ በመንካት "እግዚያብሄር ያፅናችሁ" ማለት የተለመደ ነው፡፡ ይሁን እንጅ "እግዚያብሄር ያፅናችሁ" ለማለት የሚመጣ ሰው የሟች ቤተሰብን የግራ ትከሻ መንካት አይችልም፡፡ በቀኝ እጁ የሟች ቤተሰብን የቀኝ ትከሻ መንካት

ይጠበቅበታል፡፡ ቀኝ የተመረጠበት ምክንያት ለሟች ቤተሰቦች የሞት ዳርቻ ይሁንላችሁ (ዳግም ሞት አያጋጥማችሁ)፣ ቀጣዩ ህይወታችሁ የተቃናና ሃዘን የማታዩበት ይሁንላችሁ ለማለት ነው (ወ/ሮ ሰርኬ ልይህ፣ ቃመ፣ ግንቦት 10/2008)፡፡ የሟች ቤተሰቦች በሌሎች ሰዎች ግራ እጅ ግራ ትከሻቸውን ቢነኩ ግን በቤተሰባቸው ውስጥ ተጨማሪ ሞት ይከሰታል ተብሎ ይታመናል፡፡

የሟች ቤተሰቦች ግን በአንፃሩ የቀኝ ትከሻቸውን በቀኝ እጁ ለነካቸው ሰው አጸፋውን የሚመልሱት በግራ እጃቸው የግራ ትከሻውን በመንካት ነው፡፡ ወ/ሮ ሰርኬ እንደገለፁት በቀኝ እጁ የቀኝ ትከሻቸውን ለነካቸው ሰው የሟች ቤተሰቦች በግራ እጃቸው የግራ ትከሻውን የሚነኩት የመከራ ዳርቻ እንዲሆንላቸው፣ ግራ ያጋባቸው መከራ ከእነሱ እንዲርቅ በመመኘት ነው፡፡ ይህን ከፈፀሙም ተጨማሪ ሞት አያሰጋቸውም ተብሎ ይታመናል፡፡

## የሰውን መሞት ለሌሎች ለማርዳት ብቻን መሄድ

በሞት የተለዩ ሰዎችን የመቅበር ጉዳይ በተወሰኑ ሰዎች ብቻ የሚከናወን አይደለም፡፡ የሟችን የቅርብም ሆነ የሩቅ ዘመድ፣ ጓደኛ፣ የአካባቢውን ማህበረሰብ መሰባሰብ የሚጠይቅ ማህበራዊ ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም አንድ ሰው በሞት በሚለይበት ጊዜ የሞቱን ዜና ለተጠቀሱት አካላት ሁሉ ማድረስን ይጠይቃል፡፡

ከአካባቢው ብዙም ለማይርቀው ማህበረሰብ የአቃብሩኝ ጩኸት የሚያሰማ፣ ከአካባቢው ርቀው ለሚኖሩ ሰዎች ደግሞ በአካል ተገኝቶ ሞትን የሚያረዳ ሰው መላክ ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጅ መላከ ሞት ከሟች አስከሬን ጋር ይኖራል ተብሎ ስለሚታሰብ የሞት ዜናን ለሌሎች ማድረስ ቀላል ጉዳይ ሳይሆን በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚከናወንና የራሱ የሆነ ደንብ ያለው ነው፡፡ ይህን በሚመለከት ከመረጃ ሰጭዎች መካከል ታጠቅ ቢሆነኝ (ቃመ፣ ሚያዚያ 3/ 2008) እንደገለፁት "አንድ ሰው ለመሞት በሚያጣጥርበት ጊዜ መላዕከ ሞት የሟችን ነፍስ ለመውሰድ ይመጣል፡፡ ነፍሱ ከስጋው ከተለየች በኋላም ሟች እኪቀበር ድረስ ከአስከሬኑ ጎን ይቀመጣል፡፡ ሟች ሲቀበር ከአስከሬኑ ተለይቶ ነፍሱን ይዞ ይሄዳል"፡፡ ስለሆነም በማህበረሰቡ ውስጥ አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ ለሌሎች ለማሰማት ወይም ለማርዳት አንድን ሰው ብቻውን መላክ ነውር ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው ብቻውን ከሄደ የሟችን ነፍስ ለመውሰድ የመጣው መላዕከ ሞት ተከትሎት ስለሚሄድ በመልዕክተኛው ሰው ላይ ሞትን ያመጣል ተብሎ ይታመናል፡፡

በማህበረሰቡ ዘንድ ሰው ሲሞት ለሌሎች ለማርዳት በአንድ ላይ የሚላኩ ሰዎች ሁለት እንዲሆኑ ይፈለጋል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ነጠላ፣ ጎደሎ ነገር የመጥፎ፤ ሙሉ ነገር የጥሩ ነገር ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው ብቻውን መሄዱ ነጠላነት፣ ጎደሎነት ስለሆነ መጥፎ ዕድል ይገጥመዋል፤ ሁለት ሰዎች ከሄዱ ግን ሙሉነት፣ መብዛት በመሆኑ መጥፎ ነገር አይገጥማቸውም፡፡ ምክንያቱም ሁለት ሆነው ከሄዱ መላዕከ ሞት ተከትሏቸው አይሄድም ተብሎ ይታመናል፡፡

ይሁን እንጅ ሰዎች ሁለት መሆናቸው ብቻም መላከ ሞት ተከትሏቸው እንዳይሄድ ለማድረግ በቂ አይደለም፡፡ ሰዎቹ በቀን ሳይሆን በጨለማ (አነጋግ አካባቢ) እንዲሄዱ ይፈለጋል፡፡ ምክንያቱም መላዕከ ሞት ጨለማ ስለሚፈራ ተከትሎ የመሄድ አጋጣሚው ትንሽ ነው፡፡ በቀን ከሄዱ ግን ተከትሏቸው ይሄዳል፡፡ "እገሌና እገሌ" በዚህ ቦታ፣ "እገሌና እገሌ" ደግሞ በዚህ ቦታ እያሉ ሁለት ሰዎችን በአንድ ላይ መርጠው የሚልኩ ሰዎችም በሚመድቡበት ጊዜ ድምፃቸው እንዲሰማ አይፈለግም፡፡ ምክንያቱም ድምፃቸው ከፍ ካለ መላዕከ ሞት ሰምቶ መልዕክተኞችን ተከትሎ ይሄዳል (አቶ ቢሆነኝ አጠቃ፣ ቃመ፣ ሚያዚያ 3/2008፤ አባይነህ ሙላት፣ ቃመ፣ ሚያዚያ 15/2008)፡፡ ስለሆነም የሰውን መሞት ለሌሎች ለማርዳት የሚሄዱ ሰዎች ምደባ የሚካሄደው በሹክሹክታ ድምፅና በአካል እንቅስቃሴ በመግባባት ነው፡፡ በማህበረሰቡ እምነት ለሌሎች ለማርዳት አንድ ሰው ብቻውን እንዲሄድ ካልተደረገ፣ ጉዞው በጨለማ ከተከናወነና ምደባውም መላዕከ ሞት ሊሰማው በማይችል አኳሃን ከተከናወነ መላዕከ ሞት ተጨማሪ ሰው የመውሰድ እድል የለውም ተብሎ ይታሰባል፡፡

## ሰው የሞተበትን ቤት ለሌሎች ማመልከት

በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ አንድ ሰው ቢሞትና ለአካባቢው እንግዳ የሆነ (የሟችን ቤት የማያውቅ) ሰው መጥቶ ለቅሶ ቤቱ የት አካባቢ ነው ብሎ ቢጠይቅ ያውልህ ብሎ በድምፅ መንገርም ሆነ በእጅ ምልክት ማሳየት የተከለከለ ድርጊት ነው፡፡ ይህ ድርጊት ክልክል የሆነበትን ምክንያት ከመረጃ ሰጭዎች መካከል አቶ ደስታው አባይነው (ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ ሚያዚያ 30/ 2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው) እንዲህ ይላሉ፡፡

> በድምፅም ሆነ በእጅ የጠቆመውን ሰው "ሞት ያየዋል - ይጠራዋል"፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብም ይህን ስለሚያውቅ መጀመሪያውንም ጠቁሞ አያሳይም፡፡ ምናልባት ተሳስቶ በእጅ ጣቱ ጠቁሞ ቢያሳይ እንኳ

> ወዲያውኑ የጠቆመበትን ጣቱን በጥርሱ መንከስ አለበት፡፡ ይህን ካደረገ በአካባቢያቸው በሞተው ሰው ቤት የሚገኘው መላዕከ ሞት አያየውም - አይጠራውም፡፡

ስለዚህ ለቅሶ ለመድረስ የመጣ ሰው የሟችን ቤት በራሱ መንገድ ፈልጎ ማግኘት ወይም ወደ ለቅሶ ቤቱ የሚሄዱ ሌሎች ሰዎች ካሉ መቃኘትና እነሱን እየተከተለ መሄድ ይጠበቅበታል፡፡

## በቡዳ መንፈስ ተበልቶ የሞተ ሰውን በጥይት ሳይመቱ መቅበር

በማህበረሰቡ ውስጥ አንድ ሰው በቡዳ መንፈስ ተበልቶ ከሞተ የበሉት ቡዳዎች ከመቃብር አውጥተው ልቡን በመስለብ ሲፈልጉ የቤት ቁሳቁስ - ሲፈልጉም ሰው ያደርጉታል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በለበቅ ወይም ልምጭ (ምን አይነት እንደሆነችና ከምን እንደምትሰራ አይታወቅም) በትንሹ መታ ሲያደርጉት የሞተው ሰው ተነስቶ ያዘዙትን ማንኛውንም የቤት ውስጥም ሆነ የውጭ ስራ ያከናውናል፡፡ የቡዳ መንፈሱ ካለባቸው ሰዎች ውጭ የሆነ ሰው ግን ሟቹን ሊያየውና ሊለየው አይችልም፡፡ ይህን በሚመለከት ከመረጃ ሰጭዎች መካከል መሪጌታ ይትባረክ (ቃመ፣ ሚያዚያ 15/ 2008) በአንድ ወቅት በአካባቢው ተከስቷል ሲባል ሰምቻለሁ ያሉትን አንድ ገጠመኝ እንዲህ በማለት ይገልፃሉ፡፡

> በአካባቢው አንድ ቡዳ የሆነና ቡዳ ያልሆነ ጎረቤታሞች ነበሩ፡፡ ቡዳ ያልሆነው ሰው ጥርሱ ሸራፋ ነበር፡፡ ቡዳ የሆነው ጎረቤቱ ይህን ጥርሰ ሸራፋ ሰው በልቶ ይገድለውና በቤቱ ውስጥ ሸራፋ ጋን አድርጎ ያስቀምጠዋል፡፡ ልቡን ሰልቦ ሲፈልግ ሰው ሲፈልግም የቤት ዕቃ ያደርገዋል፡፡ የቤት ውስጥም ሆነ የውጭ ስራ ያሰራዋል፡፡ የሞተው ሰውም የታዘዘውን ሁሉ ይፈፅማል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ከዕለታት አንድ ቀን የሟቹ አንዲት ሴት ህፃን ልጅ ሟች አባቷን ቡዳ ከሆነው ጎረቤታቸው ቤት ውስጥ ታየዋለች (ለህፃናት ይገለጥላቸዋል ይባላል)፡፡ ወደ ቤቷ በመመለስም ያየችውን ነገር ለቤተሰቦቿ ትናገራለች፡፡ የሟች ቤተሰቦችም የገደልክብንን ሰው ልቡን መልስልን ብለው ቡዳውን ይገርፉታል፡፡ በዚህ ጊዜ የሟቹ ልብ ተመልሶለት ሰው ሆነ ይባላል፡፡

ስለሆነም ቡዳዎች ከመቃብር አውጥተው አገልጋያቸው እንዳያደርጉትና በዚህም የሟቹ መንፈስ በቤተሰቡ ላይ ቅር እንዳይሰኝ በሚል በአካባቢው አንድ ሰው በቡዳ ተበልቶ መሞቱ ከተረጋገጠ በጀርባው በጥይት ሳይመታ አይቀበርም፡፡ ከመቃብር አውጥተው አገልጋያቸው የሚያደርጉትና የሚያዝዙት በልቡ አማካይነት ስለሆነ በጀርባው በጥይት ተመጥቶ ልቡና መሰል የሰውነት አካሉ እንዲጎድል፣ እንዲበላሽ ይደረጋል፡፡ በጀርባው

መምታት የተመረጠው ልብ ያለው ከፊት ስለሆነና ጥይት ደግሞ ጉዳት የሚያደርሰው በሚገባበት በኩል ሳይሆን በሚወጣበት በኩል ስለሆነ ነው፡፡

አሁን አሁን ግን በተለያዩ ምክንያቶች ጥይት መተኮስ ስለተከለከለ፣ የጥይት ዋጋም ስለጨመረ በጥይት ሳይመቱ መቅበር እየተለመደ ነው፡፡ ሆኖም የሟች ቤተሰብ ቢያንስ ለተከታታይ ሰባት ቀናት ያህል (ማታ ማታ) መቃብሩን ይጠብቃል፡፡ በማህበረሰቡ አስተሳሰብ የአንድ ሰው ልቡ የሚፈርሰው በሞተ በ7ተኛ ቀኑ ነው፡፡ ስለሆነም ቤተሰቡ እስከ 7 ቀን ድረስ ከጠበቀ የሟቹ ልብ ስለሚፈርስ፣ ልቡ ከፈረሰ ደግሞ ለቡዳዎችም ስለማይሰራላቸው አያወጡትም ተብሎ ይታሰባል፡፡

## ከቀብር መልስ ድምፅን ከፍ አድርጎ ማውራት፣ ማልቀስ፣ ሃዘን ማብዛት

በማህበረሰቡ ውስጥ የሟች መንፈስ ቤተሰቡንና አካባቢውን ለመጎብኘት ይመጣል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህን በሚመለከት መረጃ ከሰጡት መካከል ወ/ሮ ዳሳሽ እምሩ (ቃመ፣ ሚያዚያ 30/ 2008) እንዲህ ይላሉ፡፡

> ሟች ቤተሰቦቹ ስለሚናፍቁት ከተቀበረበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 7 ቀናት ውስጥ መንፈሱ ከቤተሰቦቹ፣ ጎረቤቶቹና አካባቢው አይለይም፡፡ በተቀበረ ከሰባተኛ ቀኑ ጀምሮ ግን ልቡ ስለሚፈርስና በዚህም መርሳት ስለሚጀምር ቶሎ ቶሎ እየመጣ የመጎብኘት አጋጣሚው ይቀንሳል፡፡ ሆኖም ግን በተከታታይ ከሚመጣባቸው 7 ቀናት በኋላም መንፈሱ አልፎ አልፎ ወደ ነበረበት ሰፈር እየመጣ ጉብኝት ያደርጋል፡፡

ከመረጃ ሰጭዎች መካከል አቶ ድንበሩ አባይነህ (ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ ሚያዚያ 30/2008፣ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው) ደግሞ የሙት መንፈስ ከፍተኛ የሆነ ድምፅ፣ ጫጫታና ሃዘን እንደማይወድ፣ የሟች መንፈስን ያስከፋሉ ከሚባሉ ድርጊቶች መካከል ከቀብር መልስ ድምፅን ከፍ አድርጎ ማውራት፣ ማልቀስና መሪር የሆነ ሃዘን ዋነኞቹ እንደሆኑ ይናገራሉ፡፡ ከቀብር መልስ ድምፅን ከፍ አድርጎ ማውራትም ሆነ ማልቀስ በአጠቃላይም ከተለመደው ወጣና ጎላ ያለ ድምፅ ማሰማትና ብዙ ማልቀስ ቤተሰቦቹንና አካባቢውን ለመጎብኘት የሚመጣውን የሙት መንፈስ ስለሚረብሹት ዳግም ለጉብኝት እንዳይመጣ ያደርጉታል ተብሎ ይታመናል፡፡

ስለሆነም ማህበረሰቡ እሱን የሚረብሹ የተባሉ ድርጊቶችን አይፈፅምም - ሌሎች እንዲፈፅሙም አይፈቅድም፡፡ የሟች ቤተሰብን ለማስተዛዘን የሚሰባሰቡ ሰዎችም ይሄንኑ

ስለሚያውቁ ንግግራቸው ሁሉ በቀስታና ሹክሹክታ ነው፡፡ በቀብር ላይ ያልተገኘና ነገር ግን ማልቀስ የሚኖርበት የሟች የቅርብ ዘመድም ሆነ ወዳጅ ወደ ሟች ቤተሰብ ቤት ሲመጣም የከረረና የመረረ የለቅሶ ድምፅ እንዲያሰማ፣ ለብዙ ጊዜ ቆሞ እንዲያለቅስ አይፈለግም፡፡ እንደመጣ ለደንቡ ያህል የተወሰነ የለቅሶ ድምፅ እንዳሰማ ማልቀሱን ትቶ እንዲቀመጥ በአስተናጋጆች ይጋበዛል፡፡

ባል ወይም ሚስት በሚሞቱበት ጊዜ ግን የሟችን መንፈስ ከከፍተኛ ድምፅና ሃዘን በተጨማሪ የሟች የትዳር አጋሮች ሌላ ትዳር የሚመሰርቱበት ሁኔታም ያስቀይመዋል ይባላል፡፡ በዚህም ምክንያት የሙት መንፈስን ላለማስቀየም ሲባል  ባል ወይም ሚስት የሞተባቸው ሰዎች ሟች በሞት ከተለያቸው ከአንድ አመት በፊት ሌላ ጋብቻ እንዲፈፅሙ አይደገፉም፡፡ ምክንያቱም እንደመረጃ ሰጭዎች "የሟች አይን ከአንድ አመት በፊት አይፈስም" ይባላል (ወ/ሪት ፍሬዘር አድማሱ፣ ቃመ፣ ሚያዚያ 30/2008)፡፡ በዚህም ምክንያት የሟች የትዳር አጋሮችም "አይኑ/ኗ ያየኛል" ብለው ስለሚፈሩ፤ የአካባቢው ማህበረሰብም ገና "አይኑ /ኗ ሳይፈስ" በሚል ስለሚያወግዛቸው ከተጠቀሰው ጊዜ በፊት ለማግባት ብዙም አይገፋፉም፡፡ የትዳር አጋራቸውን በሞት ያጡ ሰዎች የባል ወይም ሚስት ገድ የሌላቸውና ገፌ ተደርገው ስለሚታሰቡ ከአንድ አመት በፊት ብቻ ሳይሆን በቀጣይ ዘመናቸው ሁሉ የትዳር አጋር የማግኘት እድላቸውም ጠባብ ነው፡፡

የሙት መንፈስን በሚመለከት በማህበረሰቡ ውስጥ የተለያዩ አስተያየቶች አሉ፡፡ ይህን በሚመለከት ከመረጃ ሰጭዎች መካከል አቶ ጌታየ ይታየው (ቃመ፣ ሚያዚያ 15/ 2008) የሙት መንፈስ ከፈጣሪ የተሰጠው ልዩ የሆነ ሃይል ስላለው ይታደጋል፣ ከአምላክ ጋር ያቀራርባል ይላሉ፡፡ ወ/ሮ ሙሉ ገበየሁ (ቃመ፣ ሚያዚያ 15/ 2008) ደግሞ "ሰው እንደሞተ ወደርኩስ መንፈስነት ይቀየራል፡፡ በዚህም አንድ ሰው ከሞተ በኋላ በተለመደው ስሙ አይጠራም - ከተጠራ ግና የጠሩትን ሰዎች ወደሞት ይወስዳቸዋል" ይላሉ፡፡ ስለሆነም በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የሞተ ሰውን በተለመደውና በሚታወቀው ስሙ መጥራትም የሞት መተላለፊያ አንዱ መንገድ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

ስለዚህ በማህበረሰቡ ውስጥ የሙት መንፈስ ይቀየማል በሚል ልዩ ጥበቃ ይደረግለታል፤ ይታደጋል በሚል ይከበራል፤ ከሟቹ ቀጥሎ ላለመሞት በሚልም ይፈራል፡፡ ይሁን እንጅ ማህበረሰቡ ከሞት ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ አንዳንድ ድርጊቶችን በነውርነት የሚፈርጃቸው ድርጊቶቹ ሞትን የሚጠሩና የሙት መንፈስን የሚያስቀይሙ ናቸው ከሚል ብቻ

አይደለም፡፡ እንደ ማህበረሰቡ ከሞት ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙና የሚከናወኑ አንዳንድ ድርጊቶች ደግሞ መካንነትን የሚያስከትሉ ናቸው፡፡

## 6.1.2 መካንነትን የሚያስከትሉ

ከምግብ ጋር የተያያዙ ነውሮች በተቃኙበት ምዕራፍ 5 ውስጥ እንደተገለፀው በማህበረሰቡ እምነት መካንነት ራስ በፈፀሙት ወይም የቀደመ ቤተሰብ በፈፀመው የፈጣሪንና የአያት ቅድመ አያቶችን ህግ መተላለፍ ምክንያት የሚመጣ ቅጣት ወይም ርግማን ነው፡፡ ቅጣቱም ህጉን የተላለፉትን ወይም የእነሱ የሆኑ ሰዎችን የማህፀን በራቸውን በመዝጋት መውለድ እንዳይችሉ፣ ክፉ አይንም እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም መካንነት በማህበረሰቡ ውስጥ ይፈራል፡፡ በመሆኑም በማህበረሰቡ ውስጥ "እኔ መካን ነኝ" ብሎ ለመናገር - መካን መሆን አለመሆንንም ለማረጋገጥ ያስቸግራል፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ወንዶች መካን ይሆናሉ ተብሎ አይገመትም፡፡ ምናልባት መካን ነው እንዳይባል ቢፈራ እንኳ የአካባቢው ባህል የሰጠውን መብት ተጠቅሞ ሌላ ቦታ የወለዳቸው ልጆች እንዳሉት ያስወራል - የአካባቢው ማህበረሰብም ወንድ መካን ይሆናል የሚል እምነት ስለሌለው ይቀበለዋል፡፡ አንድ ባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ ለረጅም ጊዜ ልጅ መውለድ ባይችሉ ችግሩ ያለው ሴቷ ላይ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በማህበረሰቡ ውስጥ በአንድ ወቅት ተፈፅሟል የሚባል አንድ አፈ ታሪክ ይነገራል፡፡

> በአካባቢው ለረጅም ጊዜ መውለድ ያልቻሉ አንድ ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ እኒህ ባልና ሚስት ልጅ ለማግኘት የነበራቸው ጉጉት ከፍተኛ ስለነበር ሚስትዮዋ በየቀኑ ቤተ ክርስቲያን እየሄደች ትሳላለች ፣ ፀበል ትጠጣለች፣ ያውቃሉ ከሚባሉ ሰዎች ሁሉ ደጅ ትጠናች፡፡ ሆኖም ግን ማርገዝ አልቻለችም፡፡ በአንድ አጋጣሚ ግን ከአንድ ጎረቤቷ ጋር አልጋ ትጋፈፍና ታረግዛለች፡፡ የአካባቢው ሰውም ማርገዟን በማየቱ ለባሏ "እንኳን ደስ አለህ መካኗ ሚስትህ አረገዘችልህ" ይለዋል፡፡ ባልም እንኳን አብሮ ደስ አለን "በፀበል ሃይል"፣ "በአዋቂ ሃይል" እያለ ይመልሳል፡፡ ለጠየቀው ሰው ሁሉ ይሄን ሲል የሰማው ጎረቤቱም (ሚስቱን ያስረገዛት ጎረቤቱ ማለት ነው) "እኔ እኮ ነኝ ሚስትህን ያስረገዝኳት" ይለዋል፡፡ ባል ሚስቱ ከጎረቤቷ ማርገዟን በሰማ በሚቀጥለው ቀን ማርገዟን ዘግይተው የሰሙ ሌሎች ሰዎች ይመጡና "እንኳን ደስ አለህ ሚስትህ አረገዘችልህ" ይሉታል፡፡ ባልም ሚስቱ ከጎረቤቷ ማርገዟ ብዙም ሳያሳስበውና ሳያስደነግጠው እንኳን አብሮ ደስ አለን "በጎረቤት ሃይል አረገዘችልኝ" ብሎ መለሰ ይባላል (አቶ ማንችሎ ደርቤ፣ ቃመ፣ ሚያዚያ 30፣ 2008)፡፡

ከዚህ አፈ ታሪክ መረዳት እንደሚቻለው በአካባቢው ማህበረሰብ ውስጥ መካን መባል የሚያስከፍለው ዋጋ ትልቅ ነው፡፡ ምክንያቱም በአካባቢው በትዳር ላይ የሚፈፀም የዝሙት ተግባር ህይወት እስከ መጠፋፋት የሚያደርስ ነው፡፡ መካን ላለመባል ግን ልማድ እስከ መጣስ፣ የሰሙትን እንዳልሰሙ እስከ መሆንና የራስ ያልሆነን ልጅ አምኖ እስከ መቀበል ይኬዳል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ የመካንነት ዋነኛ መንስኤ ተደርጎ የሚታሰበው የፈጣሪንና የአያት ቅድመ አያቶችን ህግ አለማክበር ሲሆን፤ ሌሎች ከሞት ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ አንዳንድ ድርጊቶችም መንስኤ ይሆናሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህም ምክንያት መካንነት በተጠኝው አካባቢ የሚፈራ ጉዳይ በመሆኑ ማህበረሰቡ ለመካንነት ያጋልጣሉ የሚላቸውን ድርጊቶች ከመፈፀም ይቆጠባል፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚያሳዩት ማህበረሰቡ መካንነትን ያስከትላሉ በሚል ነውር ከሚላቸው ድርጊቶች መካከል አብዛኞቹ ከመካን ሰዎች አቀባበር፣ በቀብር ቦታ ከመገኘትና መሰል ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ድርጊቶች ይጠቀሳሉ፡፡ ከተጠቀሱት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ በማህበረሰቡ ውስጥ ነውር የተባሉ የተወሰኑ ድርጊቶችን ቀጥለን እንመልከት ፡፡

## መካን ሴትን በጀርባዋ አንጋሎ መቅበር

በአካባቢው መካን ሴቶች በሚሞቱበት ጊዜ የሚቀበሩት በልባቸው ተደፍተው ነው፡፡ እንደ መረጃ ሰጭዎች መካን ሴት ሃጢያተኛ ስለሆነች በጀርባዋ ተንጋላ ከተቀበረች ፈጣሪ የአካባቢውን ማህበረሰብ ፍሬ አልባ/መካን ያደርገዋል ይባላል (ወ/ሮ አዘነግ ገበየሁ፣ ቃመ፣ ግንቦት 6/ 2008፤ እማሆይ ድንቄ ካሳና ወ/ሮ አጀቡሽ አለማ፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ ግንቦት 8/2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው)፡፡

በአካባቢው ልማድ መሰረት መካን የሆነች መነኩሴ ሴት በምትሞትበት ጊዜም በጀርባዋ ተንጋላ እንድትቀበር አይፈለግም፡፡ ምክንያቱም እሷም የተረገመች ስለሆነች በጀርባዋ ተንጋላ ከተቀበረች የአካባቢው ሰው ሁሉ መካን ይሆናል ይባላል፡፡ ነገር ግን መካን የሆነች መነኩሴ ስትሞት መነኩሴ እንዳልሆነችው መካን ሴት በልቧ ተደፍታ አትቀበርም፡፡ ምክንያቱም በመመንኮሷ ቢያንስ የተወሰነ ሃጢያቷን የቀነሰች ስለሆነች በልቧ ተደፍታ ከተቀበረች ፈጣሪ በአካባቢው ላይ አንዳች መቅሰፍት ያመጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለዚህ መካን የሆነች መነኩሴ ስትሞት የምትቀበረው በግራ ጎኗ ሆና ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ ከመረጃ ሰጭዎች መካከል ወ/ሮ አይናለም ግርማ (ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ ግንቦት 8/

2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው) የተባሉ ሰው እንዲህ ይላሉ፡፡ “መካን መነኩሴ በግራ ጎኗ የምትቀበረው ካልመነኮሰችዋ በተወሰነ ደረጃ የተሻለች (ወደ ሃይማኖቷ የቀረበች) መሆኗን፤ ነገር ግን በሃጢያቷ ብዛት መካን በመሆኗ መረገሟን ለማመልከት ነው”፡፡ ሁለቱም ግን የተረገሙ ስለሆኑ ጉዟቸው ወደ ብርሃንና ፅድቅ ሳይሆን ወደ ጨለማና ኩነኔ ነው ተብሎ በማህበረሰቡ ዘንድ ይታመናል፡፡

## ዛር ያለባቸው ሰዎች በለቅሶ ላይ መገኘት

በማህበረሰቡ ዘንድ የዛር መንፈስ ሳቅና ደስታን እንጅ ሃዘን፣ ትካዜና ጫጫታ አይወድም፤ የፀዳና ነጭ ነገር እንጅ የቆሸሸና የጠቆረ ነገርም አይወድም ይባላል፡፡ በዚህም ምክንያት በአካባቢው የዛር መንፈስ ያለባቸው ሰዎች ለቅሶ ቤት እንዲሄዱ አይፈለግም፡፡ ምክንያቱም በለቅሶ ቤት ሃዘን፣ ትካዜ፣ ጥቁር ልብስ ወዘተ. ስለማይጠፉ የዛር መንፈስ ያለባቸው ሰዎች እነዚህን ነገሮች ሲያዩ ላያቸው ላይ ያለው መንፈስ ተቆጥቶ ይጥላቸዋል - ልጆቻቸው ዘር እንዳይኖራቸው ወይም መካን እንዲሆኑም ያደርጋቸዋል ይባላል፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን እንዲህ አይነት መንፈስ ያለባቸው ሰዎች አስከሬን አካባቢ በመቅረብ የሚችን ገላ ከነኩም የላይኛው ተመሳሳይ ችግር ይከሰታል ተብሎ ይታመናል፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ይሄ አስተሳሰብ እንዲጎለብት ምክንያት ሊሆን የሚችል አንድ አፈ ታሪክ ያለ ሲሆን፤ አፈ ታሪኩም እንዲህ የሚል ነው፡፡

> በአካባቢው በሚገኝ ብርኩቴ በሚባል ቀበሌ በድሮ ጊዜ አንዲት የታወቀች መልኮ በየነ የምትባል ባለዛር ነበረች፡፡ ይች ሴት “ሻንቂት”ና “አባ ስበር ጋንጌ” የሚባሉ ዛሮች ነበሩባት፡፡ ታዲያ አንድ ቀን በአካባቢው ትልቅ ሰው ሞቶ ለቅሶ ሄደች፡፡ ዛሩ ለቅሶና ጫጫታ ስለማይወድ ከዚያው አስንጉሮ ጣላት፡፡ ሰዎችም አንስተው ወደ ቤቷ ወሰዷት፡፡ ዛሩም ወርዶ ከዚህ በኋላ ለቅሶ ብትሄጅ ትሞቻለሽ፡፡ ለዛሬው ግን ልጆችሽ ዘር እንዳይኖራቸውና ትዳር እንዳይዙ በማድረግ ምሬሻለሁ አላት፡፡ ከዚያ በኋላ ልጆቿም ትዳር ሳይዙና ዘርም ሳይኖራቸው ሴትየዋም ደስታ ሳይኖራት ሞተች፡፡ ከዚያን ግዜ ጀምሮ ባለዛሮች ለቅሶ ቤት አይሄዱም (ወ/ሮ ዳሳሽ እምሩ፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ ግንቦት 8/ 2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው)፡፡

ስለዚህ ባለዛር የሆኑ ሰዎች ለቅሶ ቤት መሄዳቸው የዛር መንፈሱ ቁጣ ከባለዛሮቹ አልፎ ልጆቻቸውንም መካን ያደርጋል ተብሎ ይፈራል፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ የዛር መንፈስ በወንዶችም በሴቶችም ላይ ይከሰታል፡፡ ሆኖም የዛር መንፈስ በብዛት የሚያድርባቸውን ሰዎች ማንነት በሚመለከት በማህበረሰቡ ዘንድ በብዛት የሚታሰበው ሴቶች እንደሆኑ ነው፡፡ ይህን በሚመለከት ከመረጃ ሰጭዎች መካከል አባ ፍቅረማሪያም (ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ ሚያዚያ 30/2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው) እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፡፡

> ዛር የእርኩስ መንፈስ ጥንውት ነው፡፡ በአካባቢያችን ብዙውን ግዜ በዛር የሚለከፉት ሴት እህቶቻችን ናቸው፡፡ ምክንያቱም ሴቶችን ብዙውን ግዜ ክፉ መንፈስና አጋንንት ይፈታተናቸዋል፡፡ በተለይ ለአቅመ ሂዋን ደርሰው ጋብቻ ሲፈፅሙ፣ የወር አበባ ላይ ሲሆኑ፣ ውሃ ሲቀዱ፣ ከወንድ ተነጥለው ብቻቸውን መንገድ ሲጓዙ ሁሉ ተንኮለኛው አጋንንት አይለያቸውም፡፡ እነሱም በጣም ደንጋጣዎች ስለሆኑ በዚህ መንፈስ ይጠቃሉ፡፡

ወ/ሮ አጀቡሽ አለማና እማሆይ ድንቄ ካሳም (ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ ግንቦት 8/ 2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው) "ምክንያቱ ምን እንደሆን ባይታወቅም ብዙውንም ባለዛሮች ሴቶች ናቸው" በማለት የላይኛውን የሚያጠናክር ሃሳብ ይገልፃሉ፡፡

ከዚህ በላይ በጥቂቱ ለማንሳት እንደተሞከረው በማህበረሰቡ ውስጥ መካንነት ፍሬ የሚያሳጣ፣ በህይወት ሲኖሩም ከማህበረሰቡ የሚያስገልል፣ በሞት ጊዜም ከተለመደው የአቀባበር ስርዓት ውጭ የሚያደርግ በመሆኑ ተፈሪ ነው፡፡ ስለዚህ ወላጆች ብዙ ፈቃደኞች ባይሆኑም ለመውለድ ያልቻሉ ሴቶች ማህፀኔ እንዲለመልምና መውለድ እንድችል በሚል የሌሎችን ልጆች ይስማሉ፣ አዝለው ከላያቸው ላይ እንዲሸኑባቸውም ያደርጋሉ፡፡

ይሁን እንጅ ማህበረሰቡ ከሞት ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ አንዳንድ ድርጊቶችን በነውርነት የሚፈርጃቸው ድርጊቶቹ መካንነትን የሚያመጡ ናቸው ከሚል ብቻ አይደለም፡፡ እንደ ማህበረሰቡ ከሞት ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙና የሚከናወኑ አንዳንድ ድርጊቶች ደግሞ ንፅህናን የሚያሳጡ ናቸው፡፡

## 6.1.3 ንፅህናን የሚያሳጡ ድርጊቶች

ንፅህና፡- በማህበረሰቡ አረዳድ ንፁህ ሆኖ መገኘት፤ ከወንጀል፣ ከተንኮል፣ ከምቀኝነት፣ ከሃጢያት ወዘተ. ነፃ መሆንን የሚገልፅ ነው፡፡ [እ]ርክሰት፡- ደግሞ ንፁህ፤ ቅዱስ አለመሆንን፤ ነውረኛነትን፣ በሃጢያት መቆሸሽን፤ አስፀያፊ ድርጊት መፈፀምን ወዘተ.

የሚገልፅ ነው፡፡ በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ ከተለመደው ወጣ ያለ ወይም ከማህበራዊ ልማዶች ያፈነገጠና ለማህበረሰቡ ስርዓት ያልተገዛ ድርጊት ሁሉ ከመርከስ፣ ከመቆሸሸ ይቆጠራል፡፡ በዚህም ምክንያት በማህበረሰቡ ውስጥ ከሞት ጋር የተያያዙ አንዳንድ ድርጊቶች የድርጊቱን ፈፃሚም ሆነ የአካባቢውን ማህበረሰብ በጠቅላላ ንፅህና በማሳጣት ለ[እ]ርክሰት ወይም ለክፉ መንፈስ የሚያጋልጡ፣ የሚያስቀስፉ ናቸው ተብሎ ይታሰባል፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚያሳዩት ማህበረሰቡ ንፅህናን ያሳጣሉ በሚል ነውር ከሚላቸው መካከል ለሞት ከሚደረግ ቅድመ ዝግጅት፣ ከሚቀበሩ ሰዎች ማንነትና መሰል ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ድርጊቶች ይጠቀሳሉ፡፡ ከተጠቀሱት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ በማህበረሰቡ ውስጥ ነውር የተባሉ የተወሰኑ ድርጊቶችን ቀጥሎ እንመልከት፡፡

## የቁም ተስካር የሚያወጣ ሰው በራሱም ሆነ በሌሎች ድግስ ላይ መሳተፍ

ተስካር (አንዳንዶቹ ተዝካርም ይሉታል) በኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በሙታን ስም የሚዘጋጅ የመታሰቢያ ድግስ ነው፡፡ አንድ ሰው ከሞተ በኋላ የሟች ቤተሰቦች በሚመቻቸውና አቅማቸው በፈቀደላቸው ጊዜ ምግብና መጠጥ አዘጋጅተው ሰዎችን በመጋበዝ ሟችን ማሰብ የተለመደ ሲሆን፤ የመታሰቢያ ድግሱ መጠሪያም "ተስካር" ይባላል፡፡ የሟች ቤተሰብ በሟች ስም ተስካር አዘጋጅቶ የሟችን ስም ማስታወስ፣ ነፍስ ይማር ማስባል ይጠበቅበታል፡፡ ይሄን ያላደረገ የሟች ቤተሰብ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ይናቃል፣ ምክንያት እየተፈለገ ይሰደባል፡፡ ይህን በሚመለከት አቶ ትግስቱ በላይ (ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ የካቲት 7/ 2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው) የተባሉ መረጃ ሰጭ የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> የሟች ቤተሰቡን ተዝካር ያላወጣ ሰው በሌላ ሰው ተዝካር ላይ ሲገኝ ክብር የለውም፡፡ በተጋበዘበት የተዝካር ምግብና መጠጥ ላይ ሲገኝ አስተናጋጆቹ ለሌላው እንጀራና ወጥ እየሰጡ ይመጡና ከእሱ ዘንድ ሲደርሱ ደረቅ እንጀራ ብቻ ሰጥተውት ያልፋሉ፡፡ ወጥ እንዲጨምሩለት ሲጠይቃቸው "አውጥተህ ብላ" በማለት ወጥ አውጥቶ እንዲበላ ለመንገር በማስመሰል የሌሎችን ተዝካር ለመብላት መጀመሪያ የራስህን ተዝካር አውጣ በማለት ያዋርዱታል - ይሰድቡታል፡፡

ተስካር በዋናነት አንድ ሰው ከሞተ በኋላ እሱን ለማሰብ የሚዘጋጅ ቢሆንም ከመሞቱ በፊትም እራሱ ምግብና መጠጥ አዘጋጅቶ ሰዎችን በመጋበዝ እንዲያስቡት የሚያደርግበት አጋጣሚም ይኖራል፡፡ ከመሞት በፊት በራስ የሚዘጋጅ የመታሰቢያ ድግስ "የቁም ተስካር"

ይባላል፡፡ "የቁም ተስካር" መባሉም ሰውየው በህይወት እያለ እራሱ የሚያዘጋጀው ስለሆነ ነው፡፡ ሞት አይቀሬ ክስተት በመሆኑ በተለይም ዕድሜ እየገፋ በመጣ ጊዜ ያሳሳቢነቱ ደረጃ እየጨመረ ይመጣል፡፡ በዚህም ምክንያት ብዙ ጊዜ እድሜያቸው የገፉና ወደሞት እያመራሁ ነው ብለው የሚያስቡ ሰዎች የቁም ተስካር ያዘጋጃሉ፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ሰዎች የቁም ተስካር ለማውጣት የሚያስቡት በዋነኛነት በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛው ምክንያታቸው የቁም ተስካር "ያፀድቃል" ስለሚባል ሲሆን፤ ሌላኛው ምክንያታቸው ደግሞ ከሞትኩ በኋላ ተስካሬን የሚያወጣ ቤተሰብ የለኝም ብለው ሲያስቡ ነው፡፡

በዚህ መንገድ ሰዎች በህይዎት እያሉ የቁም ተስካር በማዘጋጀት ከሞቱ በኋላ ሊዘጋጅላቸው በሚችለው የተስካር ስነስርዓት ላይ የሚፈፀሙ ስርዓቶች እንዲከናወኑላቸው ያደርጋሉ፡፡ በስነስርዓቱ ላይ የተገኘው ሰው በሃይማኖት አባቶች መሪነት "የነፍስ ይማርልን ጸሎት" ያደርጋል፡፡ የተጠራው ሰው በልቶና ጠጥቶ ለመሄድ ሲነሳም "ነፍስ ይማር" እያለ ይሄዳል፡፡

በህይወት እያሉ የራሳቸውን የቁም ተስካር ያዘጋጁት ሰዎች ግን በስርዓቱ ላይ በሰው መካከል አይገኙም፡፡ ለብቻቸው ወገባቸው ላይ በገመድ ታስረው ቤት ውስጥ ይቀመጣሉ፡፡ ለእነሱ ተብሎ የተዘጋጀውን ምግብና መጠጥም አይቀምሱም፡፡ የቁም ተስካር ካበሉበት ቀን ጀምሮም ሌሎች ሰዎች በሚያዘጋጁት የቁም ተስካር ላይ አይሳተፉም፡፡ ደስታን ከሚፈጥሩ አካባቢዎች፣ ሰውነትን ከሚገነቡ ምግቦች በአጠቃላይም ከዛ በፊት ያደርጓቸው ከነበሩ ብዙ ነገሮች ይታቀባሉ፡፡ ምክንያቱም ተስካር የሚወጣላቸው ለሞቱ ሰዎች ስለሆነና የቁም ተስካርም ያን በማሰብ የሚፈፀም ስለሆነ የቁም ተስካር ያወጡ ሰዎች የሞቱ ማለት ናቸው፡፡፡ ስለሆነም በህይወት ያለ ሰው በሚያከናውናቸውና በሚሳተፍባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ አይሳተፉም (አባ ፍቅረማሪያም፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ ሚያዚያ 30/2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው)፡፡ እንደኒህ መረጃ ሰጭ የቁም ተስካር ካበሉ በኋላ ከእነሱ የሚጠበቀው ከነሃጢያታቸው ላለመሞት የሚያስችላቸውን መንገድ መጥረግ፣ ህይወት ስላላቸው ብቻ ለነፍስ ማቆያ የሚሆን የተወሰነ ምግብና መጠጥ ብቻ እየወሰዱ እራሳቸውን ማድከም ነው፡፡ ይሄን ማድረግ ካልቻሉ ግን በቁም ተስካራቸው ላይ የተፈጸመላቸው "የነፍስ ይማርልን ጸሎት" ዋጋ አይኖረውም፡፡ የሚጠብቃቸውም የጽድቅ ህይዎት ሳይሆን የመከራ፣ የኩነኔና በአጠቃላይም ንፅህናን የማጣት ህይዎት ነው፡፡

## ክርስትና ያልተነሳ ህፃንን በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ውስጥ መቅበር

በኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ወንድ ልጅን በተወለደ በአርባ ቀኑ፣ ሴት ልጅን በተወለደች በሰማንያ ቀኗ ክርስትና ማስነሳት የተለመደ ነው፡፡ ለጥናቱ የተመረጡት የማህበረሰቡ አባላትም የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች ስለሆኑ ይሄኑ ስርዓት ይፈፅማሉ፡፡ አንድ ህፃን የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነትን ተቀላቅሏል/ላለች የሚባለው በተጠቀሱት ቀናት ላይ እምነቱ በሚፈቅደው መሰረት ከሚደረግለት/ላት የመጠመቅ ስርዓት በኋላ ነው፡፡

ከዚያ በፊት ያለው ጊዜ ለእነሱ ካለመንፃት፣ ከመቆሸሽ የሚቆጠር ነው፡፡ ማህበረሰቡ ስለሙት መንፈስ ያለው እሳቤ በተነሳበት ቀደም ባለው ክፍል እንደተገለፀውም ይሄ ጊዜ ለእነሱ ነፍሳቸው የሚማርበት ስላልሆነ የሚሞተው ስጋቸውም ነፍሳቸውም ነው፡፡ በዚህም ምክንያት እነዚህ ህፃናት ከሞት በኋላ ሌላ ህይወት የላቸውም ይባላል፡፡ ከመጠመቃቸው በፊት የሚሞቱ ህፃናት በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ውስጥ እንዲቀበሩ አይፈቀድም፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ህፃናት ሃይማኖቱ በሚፈቅደው ህግ መሰረት ያልነፁ ስለሆኑ እነሱን በቤተ ክርስቲያን ቅጥር አካባቢ መቅበር ሃይማኖታዊ ተቋማቱን ከማርከስ ይቆጠራል፡፡ እንደ መረጃ ሰጭዎች ሃይማኖታዊ ተቋማቱን ማርከስ ደግሞ የፈጣሪ ቁጣን ስለሚያስከትል ቀብሩን የፈፀሙት ሰዎችም ሆኑ ድርጊቱን እያየ ዝም ያለው የአካባቢው ማህበረሰብም በሃጢያት የቆሸሸና ንፅህውን የተገፈፈ ነውረኛ ይሆናል (ቄስ ዋሌ ዘሪሁን፣ ቃመ፣ ግንቦት 9/ 2008)፡፡

ሃይማኖቱ በሚፈቅደው ህግ መሰረት ያልነፁ ህፃናትን በቤተ ክርስቲያን ቅጥር አካባቢ መቅበር በሃጢያት መቆሸሽን ብቻም ሳይሆን የህፃኑ/ኗ እናት እንድትመክን፣ በአካባቢውም ድርቅ እንዲከሰት ምክንያት ይሆናል (ወ/ሮ በለጡ ካሴ፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ ግንቦት 8/2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው)፡፡ ስለሆነም የአካባቢው ማህበረሰብ እነዚህን ነገሮች ስለሚፈራና ስለሚያከብር ክርስትና ከመነሳታቸው በፊት የሞቱ ልጆቹን በቤተ ክርስቲያን አካባቢ አይቀብርም - ሌሎች እንዲቀብሩም አይፈቅድም፡፡ በመሆኑም በአካባቢው የተጠቀሱት አይነት ህፃናት በሚሞቱበት ጊዜ ማህበረሰቡ ልጆቹን የሚቀብረው በመኖሪያ ቤቱ አቅራቢያ ነው፡፡ ይህን ያላደረገ የሟች ቤተሰብ ግን ወደ ቤተክርስቲያን እንዳይገባ በአካባቢው ማህበረሰብ እገዳ ይጣልበታል፡፡

ይሁን እንጅ ማህበረሰቡ ከሞት ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ አንዳንድ ድርጊቶችን በነውርነት የሚፈርጃቸው ድርጊቶቹ ንፅህናን የሚያሳጡ ናቸው ከሚል ብቻ አይደለም፡፡ እንደ ማህበረሰቡ ከሞት ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙና የሚከናወኑ አንዳንድ ድርጊቶች ደግሞ ለድርቅና ድህነት የሚያጋልጡ ናቸው፡፡

### 6.1.4 *ለድርቅና ድህነት የሚያጋልጡ*

በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ ከሞት ጋር የተያያዙ አንዳንድ ሁኔታዎች በአካባቢው ላይ ያልተጠበቀ ድርቅና ድህነትን ያስከትላሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ማህበረሰቡ ድርቅና ድህነትን ያስከትላሉ በሚል ነውር ከሚላቸው ድርጊቶች መካከል ከቀብር በፊትና በኋላ ከሚከናወኑ ተግባራት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ይጠቀሳሉ፡፡ ቀጥሎ የቀረቡት ምሳሌዎችም ይህን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

### ከቀብር በፊት በአካባቢው ሌላ ስራ ማከናወን

በአካባቢው አንድ ሰው መሞቱ ከተሰማበት ጊዜ ጀምሮ መቀበሩ እስከሚታወጅበት ጊዜ ድረስ የአካባቢው ማህበረሰብ ማንኛውንም የግብርና ስራ እንዲያከናውን አይፈቀድም፡፡ ምክንያቱም የሟችን መንፈስ ለማጀብ ቅዱሳን መላዕክት ወደ አካባቢው ስለሚመጡ የሞተን ሰው አፈር ሳያለብሱ ሌላ ስራ ማከናወን እግዜርን መፈታተን ስለሆነ አካባቢው በበረድ ይመታል፣ በድርቅ ይጠቃል (አቶ አለበል ደሴ፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ የካቲት 7/ 2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው)፡፡ ወ/ሮ ስፍራሽ መኮንን (ቃመ፣ ግንቦት 10/2008)ም የአቶ አለበልን ሃሳብ በመጋራት "በአካባቢው የሞተ ሰው ሳይቀበር ሌላ ስራ የሰራ ሰው ግን የእሱ ቤተሰብ ሲሞትበት የአካባቢው ማህበረሰብ አልቅሶ እንዳያቃብረው ይደረጋል" ይላሉ፡፡ ስለሆነም የአካባቢ ማህበረሰብ ስራውን ትቶ ሟችን አልቅሶ ይቀብራል፡፡ ከዛ በኋላ ወደ ስራው ይመለሳል፡፡ የሟች የቅርብ ቤተሰቦች ግን ለሳምንት ያህል የግብርና ስራ አይሰሩም፡፡

### ከቀብር በፊት ሰላምታ መለዋወጥ

በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ ሞት ከፍተኛ ሃዘንን የሚፈጥር ክስተት ነው፡፡ በመሆኑም በአካባቢው ሰው ሲሞት ሟች ከመቀበሩ በፊት መሳሳም፣ እጅ ለእጅ በመጨባበጥ ሰላምታ መለዋወጥ የተከለከለ ተግባር ነው፡፡ ምክንያቱም የሟች ቤተሰቦች በመሪር ሃዘን ውስጥ

ባሉበት፣ መላዕከ ሞትም የሟችን መንፈስ ለመውሰድ በተገኘበት ቦታ ላይ ሆኖ ዋዛ ፈዛዛ፣ ደስታ የመሳሰሉትን ድርጊቶች መፈጸም መላዕከ ሞትንና የሙት መንፈስን የሚያስቀይም ተግባር ስለሆነ አካባቢው በበረድ እንዲመታ በማድረግ ለድርቅ ያጋልጣል (አቶ ሙሉቀን ዘውዱ፣ ቃመ፣ ግንቦት 25/ 2008)፡፡

ስለሆነም የአካባቢው ሰዎች ምንም ያህል የሚያውቁትን፣ ለረጅም ጊዜ በአካል ሳያገኙት የቆዩትን ዘመድ፣ ጓደኛ የስራ ባልደረባ ወዘተ. በቀብር ቦታ ላይ ቢያገኙ እንኳ ከአንገታቸው ጎንበስ በማለት ሰላምታቸውን በምልክት ይገልፃሉ እንጅ ሟች አፈር ከመልበሱ በፊት እጅ ለእጅ በመጨባበጥ የሰላምታ ልውውጥ አያደርጉም - አይሳሳሙምም፡፡

## ከመቃብር ላይ ዛፍ ወይም ቅጠል ሳይተክሉ መመለስ

በአካባቢው ሰው ሲሞት መቃብሩ ባዶውን አይተውም፡፡ ከላዩ ላይ ልምላሜን፣ እርጥበትን የሚያሳዩና በቀላሉ ሊፀድቁ የሚችሉ እንደ ቁልቋል፣ ቅንጭብ፣ ባንቡላ የመሳሰሉ የዛፍ ዘሮች ይተከላሉ፡፡ እነዚህ ነገሮች ካልተተከሉ ግን ባዶ መቃብር የመድረቅ፣ የመጠውለግ ምልክት ስለሆነ በአካባቢው ላይ ዝናብ ይጠፋል፣ በዚህም አካባቢው ለድርቅ ተጋላጭ ይሆናል (ወ/ሮ ስፍራሽ መኮንን፣ ቃመ፣ ግንቦት 10/2008)፡፡ የተጠቀሱትን የዛፍ ዘሮች (እነሱ የመመረጣቸው ምክንያት በአካባቢው የሚገኙና በቀላሉ የሚጸድቁ እነሱ በመሆናቸው ነው) መቃብሩ ላይ ሳይተክሉ መመለስ በሟች ቤተሰቦች ላይ “በድርቅ ልታስመቱን ነው” የሚል ወቀሳን ከአካባቢው ማህበረሰብ ያስከትላል፡፡ በአካባቢው አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ የመቃብር አፈር እንደተመለሰ የተጠቀሱትን የዛፍ ዘሮች መትከል የተለመደና የማይቀር ነው፡፡

በሟች መቃብር ላይ የሚተከሉ የዛፍ ዘሮች ግን በማህበረሰቡ ውስጥ አካባቢውን ከድርቅ መጠበቂያ ብቻም አይደሉም፡፡ የሟቹ የመፅደቅና የመኮነን ሁኔታም የሚተነበይባቸው ናቸው፡፡ የተተከሉት ዛፎች ከጸደቁ ሟችም ፀድቋል፤ ዛፎቹ ከደረቁ ደግሞ ሟች ተኮንኗል ተብሎ ይተረጎማል፡፡

## የሞተ ሰውን ሳያጥቡ መቅበር

ሰው በሚሞትበት ጊዜ ወደ ቀብር ቦታ ከመወሰዱ በፊት አስከሬኑን ማጠብ የተለመደ ነው፡፡ በመሆኑም በማህበረሰቡ ውስጥ አስከሬኑ “ለንቋጣ” በሚባል የእፅዋት አይነት በልጡና ቅጠሉ

እንዲታጠብ ይደረጋል፡፡ በለንቋጣ ማጠቡም ይህ የእፅዋት አይነት ቅጠሉም ሆነ ልጡ ማላጋ (አንድን ነገር አጣብቆ የሚይዝ)፣ ቆሻሻን በቀላሉ የሚያስለቅቅ ስለሆነ ሟች ከሃጢያቱ እንዲፀዳ ያደርጋል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ የሞተ ሰው ሊሸት ይችላል ተብሎ ስለሚታሰብ አስከሬኑን የማጠብ ስራ በአብዛኛው ገመና ይጠብቃሉ ተብለው በሚገመቱ የሟች የቅርብ ቤተሰቦች ወይም የሟች የቅርብ ጓደኞች አማካኝነት ይከናወናል፡፡ ሆኖም በማህበረሰቡ ውስጥ አስከሬን የተከበረ ስለሆነ ቢሸትም እንኳ መትፋት ነውር ነው፡፡ የዚህ አንደኛው ምክንያት የሰው ልጅ በህይወት ሲኖር ሃጢያተኛ፣ የቆሸሸ ስለሆነ የነበረበትን የሃጢያት ቆሻሻ አንፅቶ ለመሸኘት ከማሰብ ነው፡፡ አስከሬን የሚታጠብበት ሌላኛው ምክንያት ደግሞ ሳይታጠብ ከተቀበረ የቤተሰቡን ሃብት ንብረት፣ ዕድሜ፣ ጤና ይዞ ስለሚሄድ በማጠብ ሟች ይዞ ሊሄድ የሚችለውን ሃብት ንብረት አጥቦ ለማስቀረት ከሚል ነው፡፡ ስለዚህ በአካባቢው የሞተ ሰውን ሳያጥቡ መቅበር የተለመደም- የሚታሰብም አይደለም፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ አንድ ሰው ሲሞት እጁን እንደጨበጠ ከተቀበረም ሳይታጠብ የሚቀበር ሬሳ እንደሚያደርገው ሁሉ የቤቱን ሃብት ንብረት በጭብጡ ውስጥ ይዞት ስለሚሄድ ቤተሰቡን ለድህነት እንዲጋለጥ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው ሲሞት እጁን ጨብጦ ከነበረ በሚከፈንበት ጊዜ እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡ ስለዚህ የሟችን ገላ ማጠብ፣ ሟች ህይወቱ ሲያልፍ እጁን ጨብጦ ከነበረ እንዲዘረጋ አድርጎ መቅበርና የመሳሰሉ ጉዳዮችን ማህበረሰቡ ሟች የቀሪውን ቤተሰብ ሃብት ንብረት በመውሰድ ቤተሰቡን ለድህነት እንዳያጋልጥ ያደርጋሉ በሚል ይተገብራቸዋል፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት የማህበረሰቡ ከሞት ጋር የተያያዙ አንዳንድ ድርጊቶች ደግሞ የሃዘን ስሜትን የሚያባብሱ ናቸው በሚል በነውርነት የተፈረጁ ናቸው፡፡

### 6.1.5 የሃዘን ስሜትን የሚያባብሱ ተግባራት

ሞት ቤተሰብን የሚነጥል በመሆኑ በቀሪው የሟች ቤተሰብ ላይ የሚፈጥረው የሃዘን ስሜት ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም የአካባቢው ማህበረሰብ የሟች ቤተሰቦችን ከጎናቸው ሆኖ ያፅናናል፣ በሂደትም ሃዘናቸውን በመርሳት ወደ ተለመደውና ወደ ቀድሞ አኗኗራቸው ተመልሰው ህይወታቸውን መምራት እንዲጀምሩ ይመክራል - ያበረታታል፡፡ ሆኖም ከሟች

ጋር እንደነበራቸው ቅርበትና ርቀት ሊወሰን የሚችል ቢሆንም የሟች ቤተሰቦች በቀላሉ ከሃዘናቸው ለመላቀቅ ይቸገራሉ፡፡

የአካባቢው ማህበረሰብም በሟች ቤተሰቦች ላይ የሚስተዋለው ሃዘንን መርሳት ያለመቻል ችግር እሱንም ያሳስበዋል፡፡ በዚህ መነሻነትም ለዘመናት ካከማቻቸው ልምዶቹ በመነሳት ሃዘንን በቀላሉ ለመርሳት የሚያስችሉና የማያስችሉ የሚላቸውን ድርጊቶች ይለያል፡፡ የሃዘን ስሜትን በቀላሉ ለመርሳት የሚያስችሉ የሚላቸውን ድርጊቶች ይተገብራል፡፡ አንዳንድ ድርጊቶችን ደግሞ የሃዘን ስሜትን የሚያባብሱ ናቸው በሚል እንዳይፈጸሙ ያደርጋል፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ማህበረሰቡ የሃዘን ስሜትን የሚያባብሱ ናቸው በሚል ነውር ከሚላቸው ድርጊቶች መካከል የቀብር ቦታን ከመቆፈር፣ አፈር ከማልበስ፣ ወደቀብር ቦታ ከመቅረብና መሰል ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ድርጊቶች ይጠቀሳሉ፡፡ ከተጠቀሱት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ በማህበረሰቡ ውስጥ ነውር የተባሉ የተወሰኑ ድርጊቶች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

## የሟች ቤተሰብ ጉድጓድ መቆፈር፣ አፈር ማልበስ

በማህበረሰቡ ውስጥ አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ ለቀብር የሚሆን ጉድጓድ የመቆፈር፣ አስከሬኑን ወደተዘጋጀለት ጉድጓድ ውስጥ የማስገባትና አፈር የመመለስ ስራ የሟች ቅርብ ቤተሰብ (ለምሳሌ፡- እናት፣ አባት፣ ሚስት፣ ልጅ፣ ወንድም፣ እህት …) ባልሆኑ ሰዎች የሚከናወን ነው፡፡ የሟች ቤተሰቦች የተጠቀሱትን ተግባራት የማይፈጽሙበትን ምክንያት አቶ ደስታው አባይነው (ቃመ፣ ግንቦት 12/2008) "… በተጠቀሱት ስራዎች ላይ ከተሳተፉ፣ ሌሎች ሲያከናውኑም ከተመለከቱ ሟች ቤተሰባቸውን ለመርሳት ይቸገራሉ፣ ሃዘናቸው ይበረታል" በማለት ይገልፃሉ፡፡ ስለሆነም የሟች የቅርብ ቤተሰቦች በተጠቀሱት ስራዎች ላይ እንዲሳተፉም ሆነ የተጠቀሱት ተግባራት በሌሎች ሰዎች ሲከናወኑ እንዲመለከቱ የአካባቢው ማህበረሰብ አይፈቅድላቸውም፡፡

የቀብር ስነስርዓቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ የሟች ቤተሰቦች ለእነሱ ቅርብ በሆኑ ዘመዶች፣ ጓደኞች ወዘተ. አማካይነት ከቀብር ቦታው ራቅ ብለው እንዲቆዩ ይደረጋል፡፡ እነሱም ይሄን ስለሚያውቁ ወደ ቀብር ቦታው ካልቀረብን ብለው ብዙ አያስቸግሩም፡፡ ሟች ከተቀበረና

የተዘጋጀው ጉድጓድ በአፈር ከተሞላ በኋላ ግን ወደ ቀብር ቦታው ቀርበው ከመቃብሩ ላይ “አፈር የመርጨት ስርዓት” ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡

በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ አንድ ሰው ሞቶ ከተቀበረ በኋላ በዕለቱ የሟች የቅርብ ቤተሰቦች መቃብሩ ላይ አፈር መርጨት የተለመደ ነው፡፡ አፈር የሚረጨት እንደዚህ አፈር ተበታትነህ ጠፍተሃልና ከዚህ በኋላ አንገናኝም በሚል መፅናናትና መርሳት እንዳለባቸው ለራሳቸው ለመንገር ነው፡፡ ከመረጃ ሰጭዎች መካከል አቶ ደስታው አባይነው (ቃመ፣ ግንቦት 12/2008) የሟች የቅርብ ቤተሰቦች አፈር የመርጨቱን ስርዓት ከፈፀሙ “በሃዘኑ ስሜታቸው ብዙም ሳይጎዳ ሟችን በቀላሉ ይረሳሉ፤ አፈር ካልረጩ ግን ሟች ሁል ጊዜ በውናቸውም ሆነ በህልማቸው ስለሚታያቸው ለመርሳት ይቸገራሉ” ይላሉ፡፡ ስለሆነም ከአካባቢው ርቀው የሚኖሩ የሟች ቤተሰቦችም የግድ በቀብር ቀን ይገኛሉ፡፡

## ሴት ልጅ ወደቀብር ቦታ መቅረብ

በማህበረሰቡ ውስጥ ሴት ልጅ በተፈጥሮዋ አንጀቷ ስስና ሩህሩህ፣ በቀላሉ የምትደሰትና በቀላሉም የምትከፋ፣ ሃዘንን በቀላሉ ለመርሳት የምትቸገር ተደርጋ ትታሰባለች፡፡ በዚህ ባህሪዋ መነሻነትም ሴት ልጅ በቀብር ጊዜ ያየችውን ሟች በቀላሉ ስለማትረሳ በአዕምሮዋ እየታወሳት የአዕምሮ በሽተኛ ልትሆን ትችላለች ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ ምክንያትም በተለይም ቅርብ ቤተሰብ የሞተባት ሴት የቀብር ስነስርዓቱ ተጠናቆ አፈር የመርጨት ጊዜው ከመድረሱ በፊት ወደ ቀብር ስፍራው እንድትቀርብ በፍፁም አይፈቀድም፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ሴት ልጅ ወደቀብር ስፍራ እንዳትቀርብ ጥብቅ የሆነ ክልከላ የሚደረግበትን ምክንያት አስመልክቶ የሚነገር አንድ አፈ ታሪክ አለ፡፡ አፈ ታሪኩም የሚከተለው ነው፡፡

> በድሮ ጊዜ አንዲት ሴት በጣም የምትወደው አንድ ልጇ ይሞትባታል፡፡ ከዚያም ወደቀብር ቦታ ትሄድና ልጇ ሲቀበር ትመለከታለች፡፡ በአየችው ነገርም በጣም ከማዘኗ የተነሳ ራሷን ስታ በሰዎች ድጋፍ ወደቤቷ ትመለሳለች፡፡ ሆኖም ግን ሲቀበር ያየችው ነገር ራሷን ለመቆጣጠር ስላላስቻላት በነጋታው ሌሊት ተነስታ ወደልጇ የቀብር ቦታ በመሄድ አውጥታ ወደቤቷ ይዛው ተመለሰች (ወ/ሮ ወይንሸት ገበየሁ፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ የካቲት 10/2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው)፡፡

እንደ አፈ ታሪኩ ከሆነ በማህበረሰቡ ውስጥ ሴት ልጅ ሰው ሲቀበር እንዳታይ የተከለከለችው ዘመኑ ባይታወቅም የልጁ እናት ፈፀመች ተብሎ ከተነገረው አፈ ታሪክ በኋላ ነው ብሎ መገመት ይቻላል፡፡

## 6.2 በመረጃ ትንተናው የተገኙ የጥናቱ አበይት ውጤቶች

ማህበረሰቡ ከሞት ጋር በተያያዘ ነውር የሚላቸውን ጉዳዮች በሚመለከት ተሰብስበው በተተነተኑት መረጃዎች ውስጥ የተገኙ የጥናቱ ዋና ዋና ውጤቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. በአካባቢው ሰው ሲሞት የሟች ቤተሰቦች ቢያንስ ለተከታታይ 7 ቀናት ያህል ማንኛውንም ስራ ከማከናወን ይታቀባሉ፡፡
2. በማህበረሰቡ ውስጥ መካን ሴቶች በፈጣሪ የተረገሙ ናቸው ተብሎ ስለሚታመን ሲሞቱ በአካባቢው የአቀባበር ወግ ልማድ መሰረት የመቀበር ዕድል የላቸውም፡፡
3. ማህበረሰቡ ከሞት ጋር በተያያዘ ክልክል ለሚላቸው ጉዳዮች የሚሰጣቸው ምክንያቶች በዋናነት ሞትንና የሙት መንፈስን ከመፍራት የሚመነጩ ናቸው ፡፡
4. በማህበረሰቡ ውስጥ ሞት ከሰው ወደ ሰው ተላላፊ በሽታ ተደርጎ ይታሰባል፡፡
5. በማህበረሰቡ ውስጥ ከሞት በኋላ ህይወት አለ ተብሎ ይታመናል፡፡
6. በማህበረሰቡ ውስጥ የሟች መንፈስ ቤተሰቦቹን ለመጎብኘት የሚመጣና በህይዎት ያሉ ሰዎች ላይ ያሉ ስሜቶች ሁሉ በእሱም ላይ የሚታዩ ተደርጎ ይታሰባል፡፡
7. *የትዳር አጋራቸውን በሞት ያጡ ሰዎች በማህበረሰቡ ውስጥ የጥሩ ነገር ምሳሌ ተደርገው አይወሰዱም፡፡*
8. *አንድ ሰው ነፍሱ ከወጣባት (ከሞተባት) እስከ ተቀበረባት ድረስ ያለችው ጊዜ በማህበረሰቡ ዘንድ የተቀደሰች ጊዜ ተደርጋ ትወሰዳለች፡፡*
9. ሰው ሲሞት መቃብሩ ላይ አፈር መርጨት በማህበረሰቡ ዘንድ ሟችን የመርሻ ስልት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
10. ማህበረሰቡ የሞት ነውሮችን ለሚከተለው ሃይማኖት ማጠናከሪያነት ይጠቀምባቸዋል፡፡
11. በማህበረሰቡ ውስጥ የዛር መንፈስ የሚያርፍባቸው በዋናነት ሴቶች ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡

12. በማህበረሰቡ ዘንድ ወንድ ልጅ መሃን ይሆናል ተብሎ አይታሰብም፡፡

በአጠቃላይ ተጠኝው ማህበረሰብ ስለሞትና ተያያዥ ነውሮች ያለው እውቀት፣ ልምድና ትግበራ ምን እንደሚመስል ከዚህ በላይ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ከዚህ በሚከተለው ምዕራፍ ደግሞ ከማህበረሰቡ በተሰበሰቡ ከግብርና ስራ ጋር የተያያዙ ነውሮች ላይ የመረጃ ትንተናና የውጤት ማጠቃለያ ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

## የግብርና ስራ ነውሮች የመረጃ አቅርቦት፣ ትንተናና ውጤት ፦

ይህ ምዕራፍ ተጠኝው ማህበረሰብ ስለግብርና ስራና ከእሱ ጋር ስለተያያዙ ነውሮች ያለውን ባህላዊ አስተሳሰብ በሚመለከት የተሰበሰቡ መረጃዎች ቀርበው የተተነተኑበትና በመጨረሻም በትንተናው የተገኙ የጥናቱ ዋና ዋና ውጤቶች ተጠቃለው የቀረቡበት ነው፡፡

## 7.1 የመረጃ አቅርቦትና ትንተና

ስራ ሲባል በመንግስትም ሆነ በግል ተቋማት ውስጥ የሚከናወኑ ስራዎችንና ስራዎችን የሚያከናውኑ ሰራተኞችን፣ በግል የሚከናወኑ ስራዎችን (ከከፍተኛ እስከአነስተኛ የንግድ ስራዎች)፣ ከግብርና ጋር የተያያዙ ተግባራትንና መሰል ስራዎችን ሁሉ ሊያጠቃልል የሚችል ሰፊ ጽንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ከፍ ሲል የተቀሱትን አይነት ተግባራት ሁሉ በስራ ውስጥ አጠቃሎ የጥናቱ አካል ማድረግ ያስቸግራል፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት ውስጥ ስራ ሲባል በተጠኝው አካባቢ የሚከናወኑ የግብርና ስራዎችን (farming activities) መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ከስራ ጋር የተያያዙ ነውሮች ሲባልም ማህበረሰቡ ባህሉን መሰረት በማድረግ በነውርነት የሚፈርጃቸውን ከስራ ጋር የተያያዙ ድርጊቶች የሚመለከት ነው፡፡

የሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ ለህይወቴ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን የተለያዩ ስራዎች ያከናውናል፡፡ ማህበረሰቡ ከሚያከናውናቸው ስራዎች መካከልም እርሻ፣ ጉልጓሎ፣ አረም፣ አጨዳ፣ እህል መከመር፣ ውቂያ፣ ማትከል፣ ቤት መስራትና ማፅዳት የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡

ይሁን እንጅ እንደ ማህበረሰቡ አስተሳሰብ በአንዳንድ የስራ ክንውኖች ወቅት የሚፈፀሙ ድርጊቶችና የስራ አይነቶች በማህበረሰቡ ህይወት ውስጥ አሉታዊ ሚና ያላቸው ናቸው፡፡

ስለሆነም ከፍ ሲል የተጠቀሱትና መሰል ስራዎች በተጠኝው ማህበረሰብ ዘንድ በዘፈቀደ የሚከናወኑ ሳይሆኑ የአካባቢውን ባህላዊ አስተሳሰብ መሰረት አድርገው የሚፈፀሙ ናቸው፡፡ ማህበረሰቡ ያለውን አካባቢያዊ እውቀትና የረጅም ጊዜ ልምዱን ተጠቅሞ በስራ ክንውኖች

ወቅት የሚፈፀሙ ድርጊቶችንና የስራ አይነቶችን ተገቢ የሆኑና ያልሆኑ በሚል ይከፍላቸዋል፡፡

ከስራ ጋር በተያያዘ ከማህበረሰቡ የተሰበሰቡትና ከዚህ በታች ገለፃ የቀረበባቸው ነውሮችም ማህበረሰቡ ስለስራ ያለው እውቀትና ልምድ ምን እንደሚመስል ከፍ ሲል በመንደርደሪያነት የቀረበውን ሃሳብ የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡

ማህበረሰቡ ስለስራ ያለውን እውቀትና ልምድ ለመረዳት የሚያስችሉ ከእርሻና ከእርሻ መሳሪያዎች፣ ከጉልጓሎ፣ ከአረም፣ ከአጨዳ፣ ከመከመር፣ ከውቂያ፣ እህል ከመስፈር፣ ከማትከል፣ ቤት ከመስራትና ከማፅዳት፣ ባልተፈቀደ ጊዜ ስራ ከማከናወን፣ ያልተፈቀዱ የስራ አይነቶችን ከመስራት ወዘተ. ጋር የተያያዙ ድርጊቶችን የሚመለከቱ 34 የሚሆኑ ነውሮች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት ነውሮችም ነውር የተባሉ ድርጊቶችንና ነውር የሆኑበትን ምክንያት በሚያሳይ መልኩ በአባሪ - ሶስት ውስጥ ከተራ ቁጥር 1 - 34 ቀርበዋል፡፡

ይህ ጥናት አይነታዊ እንደመሆኑ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት የተሰበሰቡት መረጃዎች በጭብጥ እየተከፋፈሉ የመላሾች ምክንያት ተጨምቆ ሊቀርብ ይገባል፡፡ በዚሁ መሰረትም ከመስክ ለተሰበሰቡትና በአባሪው ውስጥ ለሰፈሩት ከስራ ጋር የተያያዙ ነውሮች ማህበረሰቡ የሰጣቸው ምክንያቶች ባላቸው የጋራ ባህሪ ሲደራጁ በ4 ጭብጦች ስር ተከፋፍለው ሊታዩ ይችላሉ፡፡ የነውሮቹ ምክንያቶች ነውሮቹ በአባሪ ውስጥ የሚገኙበትን ተራ ቁጥርና በየምድቡ ውስጥ የሰፈሩ ነውሮችን ብዛት በሚያሳይ መልኩ በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡

**ሰንጠረዥ - 1 የነውሩ ምክንያት፡-**

| ተ/ቁ | የነውሩ ምክንያት | ነውሩ በአባሪው ውስጥ የሚገኝበት ተራ ቁጥር ከ --- እስከ --- | የነውር ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | በረከት ላለማጣት | ነውር 1 - 15 | 15 |
| 2 | ፍሬ አልባ ላለመሆን | ነውር 16 — 23 | 8 |
| 3 | ለድህነት ላለመጋለጥ | ነውር 24 - 30 | 7 |
| 4 | ስራን ለማሳለጥ | ነውር 31 - 34 | 4 |

ከመስክ ከተሰበሰቡትና በሰንጠረዡ ላይ በ4 ጭብጥ ተከፋፍለው ከቀረቡት 34 መረጃዎች መካከል ሌሎችን ይወክላሉ የተባሉ 18 ነውሮችና ነውር ለመሆናቸው የተሰጡ ምክንያቶች በማሳያነት ቀርበው ከዚህ በታች አጭር የመረጃ ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡

### 7.1.1 በረከትን የሚያሳጡ ድርጊቶች

ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ማህበረሰቡ በረከትን ያሳጣሉ በሚል ነውር ከሚላቸው ድርጊቶች መካከል እህል ከማጨድ፣ ከመከመር፣ ከመውቃትና ከመስፈር ስራ ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ ድርጊቶች ይጠቀሳሉ፡፡ በዚሁ መሰረትም ከመስክ ከተሰበሰቡ መረጃዎች መካከል ማህበረሰቡ በረከትን ያሳጣሉ በሚል ነውር የሚላቸው የተወሰኑት ድርጊቶች ቀርበው ከዚህ በታች የመረጃ ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡

#### ከሌላ ድንበርተኛ ጥግ ያለን እህል ጨርሶ ማጨድ

ከሌላ ድንበርተኛ ጥግ ያለን እህል ጨርሶ ማጨድ በማህበረሰቡ ዘንድ የተከለከለ ተግባር ነው፡፡ ምክንያቱም ድንበርተኛ የሆኑ ሰዎች ዘር በሚዘሩበት ወቅት በነፋስ አማካኝነት የአንደኛው ዘር ወደሌላኛው ሰው መሬት ላይ ሊያርፍ ይችላል፡፡ ስለሆነም ድንበርተኞች እህላቸውን በሚያጭዱበት ጊዜ የራሳቸው ያልሆነ ዘርን ከራሳቸው ዘር ጋር መቀላቀል ስለማይፈልጉ በሚያዋስናቸው በኩል ያለውን እህል ዳር ዳሩን አያጭዱትም፡፡ በማህበረሰቡ አስተሳሰብ የራስ ያልሆነ ዘርን ጨምሮ ማጨድ እህሉ ተሰብስቦ በሚወቃበት ጊዜ በረከት እንዳይኖረው ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ሁለቱም ድንበርተኞች የሰበሰቡትን እህል በሚወቁበት ጊዜ አውድማ ላይ የሚመጣ ለማኝ ሳያጭዱ የተውትን እህል አጭዶ እንዲወስድ ይሰጡታል (አቶ ያዛቸው ጀንበር፣ ቃመ፣ ግንቦት 10/2008)፡፡ ለማኝ እህል በሚወቃበት ቦታ ተገኝቶ እህል መጠየቅ በአካባቢው የተለመደ ባህል ነው፡፡

#### እህልን ሳይሞሉ መከመር

በማህበረሰቡ ዘንድ የምርት መቀነስን ወይም በረከት ማጣትን ያስከትላሉ ተብሎ ከሚታመንባቸው ጉዳዮች መካከል ሊጠቀስ የሚችለው ሌላኛው ጉዳይ የእህል አከማመር ሁኔታ ነው፡፡ የታጨደ እህልን ከአንድ ቦታ ላይ ሰብስቦ መከመር በአካባቢው የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ይሁን እንጅ በማህበረሰቡ ዘንድ የእህል አከማመር የራሱ የሆነ ደንብ አለው፡፡ እህል በሚከመርበት ጊዜ ክምሩን ሳይሞሉ ወይም ሳይቋጩ መተው በማህበረሰቡ

ዘንድ የጥሩ ነገር ተምሳሌት ተደርጎ አይወሰድም፡፡ ምክንያቱም ሳይሞላ በጅምር የቀረ ክምር እህሉ በሚወቃበት ጊዜ በረከት አይኖረውም (አቶ ድንበሩ አባይነህ፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ ሚያዚያ 30/2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው) ፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ለመከመር በሚሄድበት ጊዜ ሰዎች ጥሩ አድርገህ ሞልተህ ከምረው ብለው ነው የሚሸኙት፡፡

## የማይመለከታቸው ሰዎች አውድማ ውስጥ መግባት

በተጠኚው ማህበረሰብ ዘንድ ለምርት መቀነስ ምክንያት ይሆናሉ ተብሎ ከሚታመንባቸው ጉዳዮች መካከል ሊጠቀስ የሚችለው ሌላኛው ጉዳይ እህል ከመውቃት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ እህል ከታጨደና ከአንድ ላይ ከተሰበሰበ ወይም ከተከመረ በኋላ የሚቀጥለው ሂደት የተሰበሰበውን ወይም የተከመረውን እህል አውድማ (አንዳንዶቹ ውድማ ይሉታል) ላይ ዘርግፎ በመውቃት ወይም በማበራየት ፍሬውን ከገለባው መለየትና ምርቱን ወደ ቤት ማስገባት ነው፡፡

አውድማ ማህበረሰቡ ትልቅ ቦታና ክብር የሚሰጠውና ከዚህም ተነስቶ [እ]ርኩስ መንፈስ የማይለየው አድርጎ የሚወስደው የስራ አይነት ነው፡፡ በዚህም መልካም ነገርን የማይሻ፣ የምርት መትረፍረፍ የማያስደስተው መጥፎ መንፈስ አውድማ ላይ ያለውን እህል ረድኤት እንዳያስርቀው ወይም በረከት እንዳያሳጣው ይሰጋል፡፡ ከዚህ ስጋቱ በመነሳትም ማህበረሰቡ አውድማ አካባቢ ሊፈፀሙ አይገባቸውም የሚላቸውን ደንቦች ያስቀምጣል፡፡ እነዚህ ደንቦች ከተከበሩም አውድማ ባለበት አካባቢ የማይጠፋው [እ]ርኩስ መንፈስ የምርታችን ስጋት ሊሆን አይችልም ብሎ ያምናል፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ለሴት ልጅ አውድማ ውስጥ መግባት፣ ማንኛውም ሰው ጫማ ለብሶና የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፅሞ (ጥላ ሆኖ ) አውድማ ውስጥ መግባት በማህበረሰቡ እምነት አውድማ ላይ ያለውን ምርት በረከት ያሳጣል፡፡ ምክንያቱም እንደማህበረሰቡ እምነት ሴት ልጅ የወር አበባ ስለምታይ ንፁህ አይደለችም፡፡ ጫማ ለብሶ አውድማ ውስጥ መግባትም በጫማ የታፈነ እግር ንፁህ ስላልሆነ ለአውድማው ክብር ካለመስጠት ይቆጠራል፡፡ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፅሞ ወደ አውድማ መግባትም ከመርከስ ወይም ንፁህ ካለመሆን የሚቆጠር ተግባር ነው፡፡

በመሆኑም የተጠቀሱት አይነት ሰዎች አውድማ ውስጥ ከገቡ በአካባቢው ያለው ክፉ መንፈስ ከእነሱ ጋር ወደ አውድማው በመግባት ምርቱን በረከት ያሳጣዋል ወይም ይሰልበዋል (ወ/ሪት ፍሬዘር አድማሱ፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ ግንቦት 8/2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው) ፡፡ በመሆኑም የተጠቀሱት አይነት ሰዎች አውድማ ውስጥ እንዲገቡ አይፈቀድም - እንዲገቡ አለመፈቀድ ብቻም ሳይሆን በአካባቢው እንዲገኙም አይፈለግም፡፡ ከተጠቀሱት አይነት ሰዎች መካከል ጫማ ለብሶ ወደ አውድማ የሄደ ሰው ግን ለአውድማው ክብር ሲባል ጫማውን ከአውድማው ራቅ ብሎ በማውለቅ ሊገባ ይችላል፡፡ ይሁን እንጅ በማህበረሰቡ እምነት አውድማ ላይ ላለ ምርት በረከት ማግኘት የተጠቀሱትን አይነት ሰዎች ከአውድማ ማራቅ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ማህበረሰቡ የበረከት መፍጠሪያዎች ናቸው የሚላቸውን ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትንም የሚያከናውን ሲሆን፤ አውድማን ፌጦ መርጨትና በአካባቢው የሚያልፉ ሰዎችን ለአውድማ ከተዘጋጀው እህል ውሃ ማቅመስ ይጠቀሳሉ፡፡

ከመረጃ ሰጭዎች መካከል አቶ ደምለው አንማው (ቃመ፣ ግንቦት 12/2008) እንደገለፁት አውድማ ባለበት አካባቢ ተገኝቶ ምርትን የሚሰልበው ሰይጣን በባህሪው "ፌጦ" ይፈራል፡፡ ስለሆነም እህሉ ተሰብስቦ አውድማ ውስጥ እንደገባ የአውድማው ዙሪያ ፌጦ ይረጫል፡፡ ይህ ከሆነ ሰይጣን የፌጦውን ሽታ በመፍራት አካባቢውን ለቆ ስለሚሄድ ምርቱ ይበረክታል፡፡ ስለሆነም አውድማን ፌጦ መርጨትና በአካባቢው የሚያልፉ ሰዎችን ለአውድማው ከተዘጋጀው እህል ውሃ ማቅመስ ማህበረሰቡ ሰይጣንን ከአውድማ አካባቢ በማባረር የእህል በረከትን ይጨምራሉ ብሎ የሚያምንባቸውና የሚተገብራቸው ናቸው፡፡

## በበራይ ላይ ያሉ እንስሳትን እበት በየቦታው መጣል

በማህበረሰቡ ውስጥ ታጭዶ አውድማ ላይ የተሰበሰበን እህል በቀንድ ከብቶች አማካኝነት ማበራየት (እንዲደቅና እህሉ ከገለባው እንዲለይ ማድረግ) የተለመደ ነው፡፡ ከብቶች አውድማው ውስጥ ገብተው እህሉ እንዲደቅ ለማድረግ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ እበት (እዳሪም ይሉታል) ሊጥሉ ይችላሉ፡፡ ከብቶቹ አውድማውን እንዲዞሩ የሚያደርጉት ሰዎችም እበቱ እህሉን እንዳያበላሸው ከከብቶቹ ስር ስር እየተከተሉ "አግማስ መጣ" በማለት (አግማስ የሚለው ቃል በረከት፣ ረድኤት ማለት ነው) እበታቸውን በእጃቸው ወይም በቅጠል አማካኝነት ይቀበላሉ፡፡

ሆኖም የከብቶቹ እበት እንደተገኘ በየቦታው አይጣልም - አይበታተንም፡፡ ከመረጃ ሰጭዎች መካከል አቶ ሙሉቀን ዘውዱ (ቃመ፣ ግንቦት 25/ 2008) እንደገለፁት ከብቶቹ የሚጥሉት እበት ሁሉ በጥንቃቄ አንድ ቦታ ላይ እንዲሰበሰብ ይደረጋል፡፡ ምክንያቱም በየቦታው ከተበታተነ አውድማ ላይ ያለው እህልም ምርቱ ይበታተናል - አይበረክትም፡፡

በማህበረሰቡ እምነት ለእህል በረከት መታጣት መንስኤ የሚሆነው የከብቶቹ እበት በየቦታው መጣሉ ብቻም አይደለም፡፡ ከብቶቹ አውድማውን እንዲዞሩና ከአውድማው እንዲወጡ የሚደረግበት አቅጣጫም የራሱ የሆነ ሚና አለው ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም በማህበረሰቡ ውስጥ ከብቶቹ አውድማውን እንዲዞሩ የሚደረገው ከግራ ወደቀኝ ሲሆን፤ ከአውድማው እንዲወጡ የሚደረገውም በስተምስራቅ አቅጣጫ ነው፡፡ ምክንያቱም በማህበረሰቡ ዘንድ ቀኝ የበረከት፣ ምስራቅ የብርሃን ተምሳሌቶች ስለሆኑ ሁለቱም የሚፈለጉ አቅጣጫዎች ናቸው፡፡ በዚህ መንገድ የተከናወነ የአውድማ ስራ እህሉ እንዲበረክት ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡

## በአውድማ ስራ ላይ እጅን መታጠብ

አውድማ ላይ ያለ እህል ታፍሶ ወደቤት ከመግባቱ በፊት እጅን መታጠብም ማህበረሰቡ ምርትን ይቀንሳሉ ከሚላቸው ድርጊቶች የሚጠቀስ ነው፡፡ አውድማ የጣለ አንድ አባውራ እህሉ በአውድማ ላይ ሆኖ መወቃት ወይም መበራየት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እህሉ ታፍሶ ወደቤት እስኪገባ ድረስ እጁን አይታጠብም፡፡ ምክንያቱም አባውራው እጁን ከታጠበ የእህሉ በረከት አብሮ ይታጠባል (ወ/ሮ ሰርኬ ልይህ፣ ቃመ፣ ግንቦት 10/2008፤ ወ/ሮ የምስራች ወርቁ፣ ቃመ፣ ግንቦት 21 /2008)፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ወንድ ገዳም (የሰፈረው የሚበረክትለት) ነው ተብሎ ስለሚታመን አውድማ ላይ ያለን ምርት ወደ ቤት ለመውሰድ ወደሚያስችል ስልቻ የመስፈር ወይም የመጨመር ተግባርም የእሱ ብቻ ነው፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ አውድማ ላይ ያለ ምርት ከመታፈሱ በፊት ለፈጣሪ ፀሎት ማቅረብ ምርቱ የሞላ፣ ከተገመተው በላይ የበዛና የተትረፈረፈ እንዲሆን ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም አውድማ ላይ ያለውን ምርት እያፈሰ ወደ ስልቻ የሚጨምረው ሰው ለፈጣሪው የሚያቀርባቸው ልመናዎች አሉት፡፡ አንድ ሰው ከአውድማ ላይ ያለን እህል የሚያፍሰው የቤተሰቡን ስም እየጠራ “የከሴን ሆድ ታውቀዋለህና ስጠን”፣ “ለስራ ያልደረሱ ለምግብ ያላነሱ ልጆች አሉኝና ስጠን” እያለ ነው (አቶ ደለለ ሞላልኝ፣ ቃመ፣ ግንቦት 21

/2008)፡፡ ይሁን እንጅ ይህ አይነት ልመና አውድማ ላይ ላሉ ሁሉም የእህል አይነቶች ይደረጋል ማለት አይደለም፡፡ ልመና ከማይወድላቸው የእህል አይነቶች መካከል ኑግ ተጠቃሽ ነው፡፡

ማህበረሰቡ ስለምግብ አይነት ምርጫ ያለው አስተሳሰብ በተቃኘበት ምዕራፍ አምስት ውስጥ እንደተገለፀው ጥቁር የቆዳ ቀለም ያላቸው እንሰሳት በማህበረሰቡ የመጥፎ መንፈስ ማደሪያ ተደርገው የሚታሰቡ ናቸው፡፡ እንደዚሁ ሁሉ ኑግም ጥቁር ቀለም ያለው በመሆኑ ማህበረሰቡ ለኑግም ጥሩ ግምት የለውም፡፡ ማህበረሰቡ ጥቁር ቀለምን የክፉ መንፈስ ወይም ሰይጣን ተምሳሌት አድርገ ስለሚረዳው ኑግንም ከዚሁ አኳያ ይመለከተዋል፡፡ ስለሆነም ሌሎች የእህል አይነቶች ከአውድማ ላይ ሲታፈሱ ለፈጣሪ የሚያቀርበውንና ከፍ ሲል የተጠቀሰውን አይነት የበርክትልን ልመና ኑግ ከአውድማ ላይ ተወቅቶ በሚታፈስበት ጊዜ ማቅረብ በማህበረሰቡ ዘንድ አይፈቀድም፡፡ ምክንያቱም በማህበረሰቡ ውስጥ ኑግ መጥፎ መንፈስ ያለበት የእህል ዘር ተደርጎ ስለሚታሰብ ፈጣሪ እሱን እንዲያበረክተው መጠየቅ ማለት ፈጣሪ [እ]ርኩስ መንፈስን እንዲያፀድቀው እንደመለመን ይቆጠራል፡፡ በመሆኑም አውድማ ላይ ያለውን የኑግ ምርት እንዲያበዛው ለፈጣሪ ልመና ቢደረግ ምርቱ በመጨመር፣ በመብዛት ፋንታ ከታሰበውና ሊሆንም ከሚችለው በታች ይቀንሳል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለሆነም በማህበረሰቡ ውስጥ አንድ ሰው የኑግ ምርትን ከአውድማ ላይ የሚያፍሰው ፈጣሪው ምርቱን እንዲያበዛለት እየለመነና ምርቱንም እያመሰገነ ሳይሆን "ማን በርክት ብሎሃል" እያለ እየሰደበ ነው (አቶ መንግስቱ ደምሌ፣ ቃመ፣ ግንቦት 21 /2008)፡፡ ኑግ በዚህ መንገድ ከታፈሰ ምርቱ ከተጠበቀውም በላይ ይበረክታል ተብሎ ይታመናል፡፡

## እህልን በማይፈለግ ወቅት መውቃት

በተጠኝው አካባቢ ታህሳስና ጥር ጤፍ ለውቂያ የሚደርስባቸው ወሮች ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ እነዚህ ወሮች ማህበረሰቡ ጤፍን ለመውቃት የሚፈልጋቸው ወቅቶች አይደሉም፡፡ በአካባቢው በሚኖረው የክርስትና እምነት ተከታይ ማህበረሰብ ዘንድ ታህሳስ ገብርኤል (ታህሳስ 19 ቀን የሚከበረው) እሱን የማያከብሩ (በእሱ በዓል ዕለት ስራ የሚሰሩ፣ ለሌላቸው የማይዘክሩ…) ሰዎችን ምርት ወስዶ እሱን ከሚያከብሩ ሰዎች ምርት ጋር በመቀላቀል ያላከበሩትን ሰዎች ምርት ባዶ ያስቀራል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም የአካባቢው ማህበረሰብ ምርቴ በረከት አይኖረውም ብሎ ስለሚያምን ጤፉን የሚወቃው ከታህሳስ ወር

በፊት ወይም በኋላ ነው፡፡ የግድ በታህሳስ ወር ላይ ለመውቃት የሚያስገድድ ሁኔታ ቢፈጠር እንኳ የሚወቃው ቢያንስ ከታህሳስ 20 በኋላ ነው (አቶ ሙጨ ገበየሁ፣ ቃመ፣ ግንቦት 21 /2008)፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ እንደ ታህሳስ ሁሉ ጥርም ጤፍን ለመውቃት የሚፈራ ወር ነው፡፡ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ "ጥምቀት" ክርስቶስ የተጠመቀበትን ቀን በማሰብ ጥር 11 ቀን የሚከበርበት በአል ነው፡፡ ተጠኝው ማህበረሰብ ጤፍ መወቃት ያለበት ታቦት ከቤተ ክርስቲያን ወጥቶ ጥምቀተ ባህር ከመባረኩ (የጥምቀት በአል ከመከበሩ) በፊት ነው ብሎ ያምናል፡፡ ምክንያቱም ባህረ መስቀል ከተባረከ በኋላ የሚወቃ ጤፍ ባህር ይወስደዋል - እብቅ ይሆናል (ቄስ አስማማው ዋሌ፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ ሚያዚያ 30/2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው)፡፡ በመሆኑም የአካባቢው ማህበረሰብ ጤፍ የሚወቃው ከጥር 11 ቀን በፊት ነው፡፡

## የማይፈቀድላቸው ሰዎች እህል መስፈር

ማህበረሰቡ በረከትን ያሳጣሉ በሚል ነውር ከሚላቸው ድርጊቶች መካከል ከእህል ማጭድ፣ መከመርና መውቃት ጋር የተያያዙ የተወሰኑ ጉዳዮችን ከዚህ በላይ በጥቂቱም ቢሆን ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ ይሁን እንጅ በማህበረሰቡ አስተሳሰብ አንድ እህል ታጭዶ፣ ተከምሮና ተወቅቶ ወደቤት ከገባ በኋላ እህሉ ረድኤት እንዳይኖረው የሚያደርጉ ጉዳዮችም ያሉ ሲሆን፤ ከጎተራ እህል የሚያወጡ ሰዎች ማንነት አንደኛው ተጠቃሽ ነው፡፡

በማህበረሰቡ ዘንድ ምርት መስፈር (ከአውድማም ሆነ ከጎታ፣ ጎተራ) የሚችሉት ወንዶች ናቸው፡፡ አውድማ ውስጥ እንዲገቡ ከማይፈቀድላቸው ሰዎች መካከል ሴቶች ተጠቃሽ እንደሆኑ ቀደም ሲል ተነስቷል፡፡ ይሁን እንጅ በማህበረሰቡ ውስጥ ሴቶች አውድማ ውስጥ መግባት ብቻ ሳይሆን ከአውድማ ወደቤታቸው የገባ ምርትንም ከጎተራም ሆነ ጎታ ማውጣት አይችሉም፡፡ ለዚህም ማህበረሰቡ ሴቶች በተፈጥሯቸው ረድኤት በረከት ስለሌላቸው ነው የሚል ምክንያት ያቀርባል፡፡ ለምክንያቱ ማጠናከሪያነትም ከክርስትና ሃይማኖት ጋር የተያያዘ አንድ ታሪክን ዋቢ የሚያደርግ ሲሆን፤ ታሪኩም የሚከተለው ነው፡፡

> እናታችን ሄዋን አባታችንን አዳምን ባሳተችው ጊዜ እግዚያብሄር
> የነካሽው፣ ያየዝሽው አይባረክልሽ በማለት ረግሟታል፡፡ በዚህም

ፀጋዋ በሙሉ ተገፏል፡፡ በዚህ ምክንያትም ሴቶች ረድኤት በረከት

የላቸውም፣ የያዙት የጨበጡት ነገር ሁሉ ጎደሎ ነው (ወ/ሮ ወይንሸት ገበየሁ፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ ግንቦት 8/2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው)፡፡

በመሆኑም ማህበረሰቡ ይሄን ታሪክ መነሻ በማድረግ ሴቶች ምርት ከሰፈሩ ምርቱ ረድኤት በረከት አይኖረውም፣ በጎተራውና ጎታው ውስጥ ያለው እህል ማገልገል ከሚገባው ጊዜ በፊት በድንገት ባዶ ሆኖ ይገኛል ብሎ ያምናል፡፡ ስለሆነም በማህበረሰቡ ውስጥ ሴቶች ምርት እንዲሰፍሩ አይፈቀድላቸውም፤ ሴቶችም ይሄን ስለሚያውቁ እህል ለማስፈጨት፣ ገበያ አውጥቶ ለመሸጥ ቢፈልጉ እንኳ ከጎተራና ጎታ እህል አያወጡም - እህሉን እንዲያወጣላቸው የቤቱን አባውራ ወይም ሌላ ወንድ ይጠቀማሉ፡፡

በአጠቃላይ ማህበረሰቡ በረከትን ያሳጣሉ በሚል ነውር የሚላቸውን የተወሰኑ ጉዳዮች በማንሳት ማህበረሰቡ ስለስራና ተያያዥ ነውሮች ያለው አስተሳሰብ፣ እውቀትና ልምድ ምን እንደሚመስል ከዚህ በላይ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ ይሁን እንጅ ማህበረሰቡ ከስራ ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ አንዳንድ ድርጊቶችን በነውርነት የሚፈርጃቸው ድርጊቶቹ በረከትን ያሳጣሉ ከሚል ብቻ አይደለም፡፡ በማህበረሰቡ አስተሳሰብ ከስራ ጋር የተያያዙ አንዳንድ ድርጊቶች ምርትን መቀነስ ወይም በረከትን ማሳጣት ብቻም ሳይሆን ከነአካቴው ፍሬ መስጠት አለመቻልንም የሚያስከትሉ ናቸው፡፡

## 7.1.2 ፍሬ አልባነትን የሚያስከትሉ ድርጊቶች

በማህበረሰቡ ዘንድ “ፍሬ አልባነት” ከመድረቅ፣ ካለማፍራት፣ ከፍሬ መጨናገፍ፣ ከመምከን ወዘተ. ጋር ተያይዞ የሚተረጎም ነው፡፡ በማህበረሰቡ አስተሳሰብ በአንዳንድ የስራ ክንውኖች ወቅት የሚፈፀሙ አንዳንድ ድርጊቶች መሬቱ እንዲደርቅ ወይም እህል እንዳያበቅል፣ የተተከለው ወይም የተዘራው ፍሬ እንዳይዝ፣ ያፈራው እንዲረግፍ፣ ድርጊቱን የፈፀመው ሰው ዘር እንዳይኖረው ወይም እንዲመክን፣ የተሰራው ስራ ውጤታማ እንዳይሆን ምክንያት የሚሆኑ ናቸው፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ማህበረሰቡ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን አይነት የፍሬ አልባነት ችግሮች ያስከትላሉ በሚል ነውር ከሚላቸው መካከል ከእርሻ፣ አረም፣ ጉልጓሎ፣ ማትከል፣ ቤት ማፅዳት፣ ወዘተ. ጋር የተያያዙ ድርጊቶች ይጠቀሳሉ፡፡ በዚሁ መሰረትም ከመስክ ከተሰበሰቡ መረጃዎች መካከል ማህበረሰቡ ፍሬ አልባነትን ያስከትላሉ

በሚል ነውር የሚላቸው የተወሰኑት ድርጊቶች ቀርበው ከዚህ በታች የመረጃ ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡

## በአረምና ጉልጓሎ ስራ ላይ እጅን መታጠብ

የአረምና ጉልጓሎ ስራ በማከናወን ላይ እያሉ ምግብ ከመብላት በፊትም ሆነ በኋላ እጅን መታጠብ በማህበረሰቡ ዘንድ የተለመደና የሚፈቀድ ተግባር አይደለም፡፡ ምክንያቱም በእርሻ መሬቶች ላይ እጅን መታጠብ የጥሩ ነገር ተምሳሌት አይደለም፡፡ በማህበረሰቡ እምነት የእርሻ መሬት እህል የማብቀያ ብቻ ሳይሆን የሚዘራውን እህልም ሆነ አካባቢውን ከተለያዩ አደጋዎች የሚጠብቁ ቆሌዎች የሚኖሩበትም ነው፡፡ ስለሆነም ማህበረሰቡ ለእርሻ ቦታ ትልቅ ክብር ይሰጣል - ከክብሩ ስፋት በተነሳም እሱን ማቆሸሽ ልምዱ አይደለም፡፡ እንደ ማህበረሰቡ እምነት የሰው ልጅ በተለያዩ ነገሮች የቆሸሸ፣ ያደፈ፣ ሃጢያት የበዛበት ነው፡፡ እነዚህን ነገሮች የሚሰራውም በዋነኛነት በእጁ አማካኝነት ነው፡፡ በማህበረሰቡ አስተሳሰብ ከሰው ልጅ የአካል ክፍሎች ሁሉ በዋናነት የሚቆሸሸው እጅ ነው፡፡

በመሆኑም ማህበረሰቡ በእጁ አማካኝነት ለሚያከናውናቸው ድርጊቶች ሁሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋል፡፡ ከሚያደርጋቸው ጥንቃቄዎች መካከልም ክብር በሚሰጣቸው የስራ ቦታዎች ላይ ሆኖ እጅን አለመታጠብ አንዱ ነው፡፡ ከሁሉም የሰው ልጅ የአካል ክፍሎች በተለየ ሁኔታ በተለያየ አጋጣሚ የቆሸሸ እጅን እህል አብቅሎ በሚያበላና የአካባቢው ጠባቂ የሆኑ መናፍስት በሚኖሩበት ቦታ ላይ መታጠብ ትልቅ ቅጣትን የሚያስከትል ነው፡፡ በተለይም በአረምና ጉልጓሎ ስራ ላይ ሆኖ እጅን መታጠብ ለፍሬ ያልደረሰውን (በመዘራትና በመታረም ላይ ያለውን) እህል የያዘው መሬትና ዘር እንዲደርቅ፣ ባይደርቅም እንኳ ዘሩ ፍሬ እንዳይዝ ያደርጋል (አቶ ሙሉቀን ዘውዱ፣ ቃመ፣ ግንቦት 25/ 2008)፡፡ ስለሆነም ማህበረሰቡ በአረምና ጉልጓሎ ስራ ላይ እያለ ምግብ ለመብላት ሲፈልግ እጁን በመታጠብ ፋንታ አንዱን እጁን ከሌላኛው ጋር በማፋተግ ወይም በማሻሸት ይቀርባል፣ በልቶ ሲጨርስም ከመመገቡ በፊት ያደረገውን በመድገም ስራውን ይቀጥላል፡፡

## ዱባን አንድ ሰው ብቻ ሆኖ መትከል

በማህበረሰቡ አስተሳሰብ አንዳንድ የስራ አይነቶች በግል ሳይሆን በቡድን መከናወንን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በማህበረሰቡ ውስጥ የዱባ ፍሬን አንድ ሰው ብቻውን ሆኖ አይተክልም፡፡ ምክንያቱም በአንድ ሰው ብቻ የሚተከል

የዱባ ፍሬ የመብቀል እድሉ ዝቅተኛ ይሆናል - ቢበቅል እንኳ የማያፈራ፣ መሃን ወይም ፍሬ የማይሰጥ ይሆናል፡፡ በማህበረሰቡ እምነት "ነጠላነት" የመድረቅ፣ የመጠውለግ፣ ያለማፍራት፣ ያለመተካትና ያለመብዛት ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ "ሁለትነት" ደግሞ የመባዛት፣ ዘርን የመተካት፣ የመዋለድ፣ ፍሬ የመስጠትና የመልማት ተምሳሌት ነው፡፡ በመሆኑም በማህበረሰቡ ዘንድ ዱባን የመትከል ስራ  በሁለት ሰዎች የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ የመትከል ተግባሩ የሚከናወነውም ዱባውን የሚተክለው ሰው አብሮት ያለውን ሌላ ሰው በመሸከም "ዱባ ዱብ ዱብ ከሌን የሚያክል ጣል" እያለ ነው (ወ/ሮ ብርቱካን ሙላቱ፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ ሚያዚያ 30/2008፤ ሃሳቡ የቡድኑ አባላትም የተጋሩት ነው) ከሌን የሚያክል ጣል የሚለው የተሸከመውን ሰው የሚያክል ዱባ አፍራ ወይም ያዝ ለማለት ሲሆን፤ ሰው ተሸክሞ የሚተክለውም እኔ እንደተሸከምኩ ወይም ሁለት እንደሆንኩ ሁሉ አንተም ራስህን ተካ፣ አፍራ፣ ሁለት ሁን ለማለት ነው፡፡ ስለሆነም ስራው በዚህ መንገድ ከተከናወነ ዱባው የለመለመ፣ ፍሬ የሚሰጥ ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡

## ቤትን በማይፈለግ አኳሃን ማፅዳት

በቤት ውስጥ ያለን የሸረሪት ድር መጥረግ በማህበረሰቡ ዘንድ ለፍሬ አልባነት እንደአንድ ምክንያት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በመሆኑም በቤት ውስጥ ያለን የሸረሪት ድር መጥረግ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚደገፍ ተግባር አይደለም፡፡ ምክንያቱም የሸረሪት ድርን መጥረግ በጠረጉት ሰዎች ላይ የመካንነት (መውለድ ያለመቻል) ችግርን ያስከትላል (ወ/ሮ ገነት ደመላሽና ሙጭቴ ካሳ፣ ቃመ፣ ግንቦት 30/ 2008)፡፡

## ባልተፈቀዱ ቀናት ስራ ማከናወን

በማህበረሰቡ አስተሳሰብ በበኣላት ቀናት ስራ ማከናወንም ፍሬ አልባነትን የሚያስከትል ሌላኛው ጉዳይ ነው፡፡ ተጠኝው ማህበረሰብ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ነው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ሃይማኖታዊ ስርዓቱን መነሻ ባደረጉ ቀናት በዋናነትም በሚካኤል (ወር በገባ በ12ኛው ቀን)፣ በማሪያም (ወር በገባ በ21ኛው ቀን)፣ በባለእግዚያብሄር (ወር በገባ በ29ኛው ቀን)፣ እንዲሁም በቅዳሜና እሁድ በዋነኛነት የማረስ፣ የመዝራት፣ የማጨድ፣ የማረም፣ ዛፍ የመቁረጥ፣ ቤት የመስራት፣ የመፍጨት፣ የመውቀጥ (መሸክሸክ) ስራዎችን አያከናውንም፡፡ ይሄ ሲባል ግን ማህበረሰቡ በትልቅ በአልነት የሚወስዳቸውን ለመጥቀስ

ያህል እንጅ ማህበረሰቡ ከየግላዊና አካባቢያዊ ጉዳዩ በመነሳት ስራ የማያከናውንባቸው ተጨማሪ ቀናትም አሉት፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ በበአል ቀን መሰራት የሌለባቸውን የስራ አይነቶች ማከናወን ፈጣሪን የሚያስቆጣ ድርጊት ስለሆነ ስራውን በሚያከናወኑት ግለሰቦችም ሆነ በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ አንዳች መጥፎ ውጤትን ያስከትላል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከመረጃ ሰጭዎች መካከል ቄስ አስማማው ዋሌ (ቃመ፣ ግንቦት 25/ 2008) "ፈጣሪ ቁጣውን በበረድ አማካይነት በመላክ በአካባቢው የሚገኝ የአፈራም ይሁን ገና በማፍራት ላይ ያለ አዝመራ እንዲወድም፣ ፍሬው እንዲረግፍ ያደርጋል" ይላሉ፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ በበአል ቀን መከናወን የሌለባቸውን ስራዎች ከማከናወን የተቆጠበ ነው፡፡

በማህበረሰቡ አስተሳሰብ በአንድ ግለሰብም ሆነ በተወሰነ ቡድን የሚፈፀም ስህተት ሁሉንም የአካባቢውን ማህበረሰብ አደጋ ላይ የሚጥል ስለሆነ ማህበረሰቡ በበአል ቀን ከመስራት እራሱን ማቀብ ብቻ ሳይሆን ሌሎች እንዳይሰሩም አጥብቆ ይከለክላል፡፡ ማህበረሰቡ በአልን መሻር የሚያስከፍለው ዋጋ ትልቅ ነው ብሎ ከማመኑ በተነሳም በአካባቢው በሚገኙ የጥበበ ዕድ ባለሙያዎች ስራ ላይም ጣልቃ ይገባል፡፡ በአካባቢው ከሚገኙ የጥበበ ዕድ ባለሙያዎች መካከል በሸክላ ስራ የሚተዳደሩት ወ/ሮ ወይንሸት ገበየሁ (ቃመ፣ ግንቦት 30/ 2008) "ለሸክላ ስራ የሚሆነንን አፈር በበአላት ቀን ስንቆፍር የአካባቢው ማህበረሰብም ሆነ የሃይማኖት አባቶች በበአል እየሰራችሁ በረድ ልታስመቱን - ልታስቀስፉን ነው በሚል ይከለክሉናል" ይላሉ፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ የሰሪዎቹ ማንነት ሁኔታም በስራ ውጤታማና ፍሬያማ ላለመሆን ምክንያት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ለምሳሌ ያህል፡- የአካባቢው ቄሶች ቀድሰው ከወጡ በኋላ ለተወሰኑ ሰዓቶች ማንኛውንም ስራ ማከናወን አይችሉም፡፡ ምክንያቱም አንድ ቄስ ቀድሶ ሲወጣ ቅዱሳን መላዕክት አብረውት ወደ ቤቱ ይሄዳሉ ይባላል፡፡ ከመረጃ ሰጭዎች መካከል እማሆይ ድንቄ ካሳ (ቃመ፣ ግንቦት 25/ 2008) እንደተናገሩት አንድ ቄስ ቀድሶ ከቤተ መቅደስ ከወጣ ጀምሮ ቢያንስ ለ24 ሰዓት ያህል ቅዱሳን መላዕክት ከእሱ አጠገብ አይርቁም፡፡ በመሆኑም በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ስራ ከሰራ ድርጊቱ አጠገቡ ያሉትን ቅዱሳን መላዕክት ስለሚያስቆጣ መላዕክቱ የሚይዘውን፣ የሚጨብጠውንና የሚያከናውነውን ስራ ሁሉ ውጤት የሌለው ባዶ ድካም ያደርጉበታል፡፡ ቄስ ዋሌ ዘሪሁን (ቃመ፣ ግንቦት 25/ 2008) እንደተናገሩት ደግሞ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ስራ ያከናወነን ቄስ ቅዱሳን መላዕክቱ

ለ[እ]ርኩስ መንፈስ አሳልፈው ስለሚሰጡት ሰውየው የሰይጣን ስራን (ክፉነትን፣ መጥፎ ባህሪን …) ይወርሳል፤ በዚህም ዳግመኛ ወደ ቅዳሴ እንዳይገባ ስለሚደረግ ደብተራ (መፅሃፍ ገላጭ፣ ኮከብ ቆጣሪ ...) ይሆናል፡፡ ስለሆነም ከቅዳሴ የወጡ ቄሶች የነበራቸውን ሃይማኖታዊም ሆነ ማህበረሰባዊ ቦታ ማጣት ስለማይፈልጉ ደንቡን ጥሰው በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ማንኛውንም አይነት ስራ አያከናውኑም፡፡ ስራ ማከናወን ብቻም ሳይሆን የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም፣ ከአካባቢው ርቆ መሄድ፣ ከሰዎች ጋር መነጋገር ሁሉ አይችሉም፡፡ በዚህ ጊዜ የሚፈቀድላቸው ነገር ቢኖር ምግብና መጠጥ ብቻ ነው፡፡

በማህበረሰቡ አስተሳሰብ ቄሶች ሃብት ንብረት እንዲያፈሩ አይፈለግም፡፡ ቄሶች ሃብት ካገኙ ፈጣሪያቸውን ስለሚፈታተኑ፣ የሚሰጡትን ሃይማኖታዊ አገልግሎትም ስለሚቀንሱ ፈጣሪ ድሃ እንዲሆኑ ረግሟቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ለዚህም ማህበረሰቡ "የቄስ ሃብታም የለውም" የሚል አባባል አለው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ቄሶች ትኩረታቸው ሌላ ስራ ፍለጋና ሃብት ማከማቸት ላይ ሳይሆን ሃይማኖታዊ አገልግሎታቸው ላይ እንዲሆን፤ የምግብ፣ መጠጥና መሰል ጉዳያቸውም የአካባቢው ማህበረሰብ በሚያዘጋጃቸው የተለያዩ ስርዓተ ክንውኖች ላይ ተገኝተው በሚሰጡት ሃይማኖታዊ አገልግሎት እንዲሸፈን ይፈለጋል፡፡ በዚህም ምክንያት ማህበረሰቡ ሃይማኖታዊ እምነትን በመንተራስ በሚያዘጋጃቸው አንዳንድ ድግሶች ላይ የሚዘጋጅ ምግብና መጠጥ ከተበላ ከተጠጣ በኋላ ሌላው ሰው የተመገበው የተረፈ ነገር ይሰበሰባል ወይም ይመለሳል፡፡ ለቄስ ተብሎ የተዘጋጀው ምግብና መጠጥ ግን አይመለስም ወይም አይሰበሰብም "የታቦተ ጽዮን ነው" ተብሎ ይቀመጣል፡፡ ቄሶችም "የታቦተ ጽዮን ነው" ተብሎ የተቀመጠውን ምግብና መጠጥ እያረፉ በፈለጉት መጠን ይጠቀማሉ - እንዳስፈላጊነቱም ወደ ቤታቸው ይዘው ይሄዳሉ፡፡

ከመረጃ ሰጭዎች መካከል አቶ ገብረአብ ደሴ (ቃመ፣ መጋቢት 9/ 2008) እንደገለፁት

> ቀደም ባሉት ዘመናት (ጊዜው በትክክል አይታወቅም) የአካባቢው ማህበረሰብ ለተዝካር፣ ግብረሰላምና መሰል ጉዳዮች የሚያቀርባቸው በግ፣ ፍየልና በሬ ስጋቸው በአካባቢው ማህበረሰብና በቄሶች ከተበላ በኋላ ቆዳ የሚፈቀደው ለቄሶች ነበር፡፡ ቄሶችም ቆዳውን ለተለያየ አገልግሎት (ለመጫኛ፣ ለጀንዲ፣ ለስልቻ … ) ይጠቀሙበታል፡፡ አሁን አሁን ግን ቄሶች ቆዳ እንዳይወስዱ ቤተ ክርስቲያን ከልክላለች፡፡

ስለሆነም በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ቄስ በሚሰጠው ሃይማኖታዊ አገልግሎት ከሚያገኘው እህል ውሃ ያለፈ ሃብት እንዲፈጥር አይፈለግም፤ ቄሶቹም ሃብት ማፍራትን በሚመለከት ከሌላው ማህበረሰብ የተለየ አስተሳሰብ የላቸውም፡፡

## የተከበሩ ስፍራዎችን ለእርሻ አገልግሎት መጠቀም

ማህበረሰቡ በስራ ውጤታማና ፍሬያማ ላለመሆን ምክንያት አድርጎ የሚወስደው ሌላኛው ጉዳይ አካባቢውን የሚጠብቁ መናፍስት የሚኖሩባቸውን ስፍራዎች ለእርሻ አገልግሎት መጠቀም ነው፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብ ቤተሰባችን፣ ጎረቤታችንና በአጠቃላይም አካባቢያችን ከክፉ ነገር የሚጠብቁ መናፍስት መኖሪያ ናቸው የሚላቸውና በዚህም ወደ ባህላዊ ቦታነት በመለወጥ የተለያዩ ባህላዊ ስርዓተ ክንውኖችን የሚፈፅምባቸው ተፈጥሯዊ ስፍራዎች/ቦታዎች አሉት፡፡ ከእነዚህ ቦታዎች መካከልም ወንዞች፣ ተራሮች፣ ዛፎች፣ ጫካዎች ወዘተ. ይጠቀሳሉ፡፡ ለእነዚህ ቦታዎች የአካባቢው ማህበረሰብ ትልቅ ክብር ይሰጣል፡፡ በመሆኑም በእንደነዚህ አይነት ቦታዎች ዙሪያ ስራ ሲያከናውን ከፍተኛ ጥንቃቄን ያደርጋል - በአካባቢው አሉ ብሎ የሚያምንባቸውን መናፍስት እንዳይዳፈርም ይሰጋል፡፡

ማህበረሰቡ ባህላዊ እምነቱን የሚገልፅባቸውን ወንዞች፣ ጫካዎች፣ ትልልቅ ዛፎች፣ ዋሻዎች ተጠግቶ አያርስም፡፡ ምክንያቱም እነዚህን ቦታዎች ተጠግቶ ማረስ የአካባቢውን ጠባቂ መንፈሶች ከመድፈር ስለሚቆጠር የሚዘራው እህል አያፈራም፣ ተጠግቶ ያረሰው ግለሰብም ይቀሰፋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከእነዚህ አይነት ቦታዎች መካከል አንዱን ብቻ እዚህ ቦታ ላይ በምሳሌነት አንስተን እንመልከት፡፡ በአካባቢው “ጥቁር ባህር” የሚባል ወንዝ አለ፡፡ ይሄ ውሃ በተለይም በበጋ ወቅት ቀለሙ ጥቁር ሲሆን፤ ብዙ የአሳ ክምችትም አለበት ይባላል፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብ ይሄን ወንዝ ከመነሻ እስከ መድረሻው ድረስ የሚቆጣጠር አንድ መንፈስ አለ ብሎ ስለሚያምን መንፈሱ ከአደጋ እንዲጠብቀው፣ መልካም ጤንነትን እንዲሰጠው፣ አካባቢውን ሰላም እንዲያደርገው ይፈልጋል፡፡ ከዚህ ፍላጎቱ በመነሳትም በየአመቱ ወደ ወንዙ እየሄደ ቡና ቆልቶ፣ ዶሮም ሆነ በግ አርዶ እርስበርሱ ተገባብዞ ወንዙንም አቅምሶ (ከሚበላውና ከሚጠጣው ነገር ወደ ወንዙ ውስጥ ጨምሮ)፣ ለቀጣዩ አመት በሰላም እንዲያደርሰውም በውሃው ውስጥ አለ ለሚለው መንፈስ ልመና አድርሶ ይመለሳል፡፡ አንዳንዱም ዶሮ ከነነፍሱ አስቀምጦ ይሄዳል፡፡

ይህ ወንዝ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የሚከበርና የሚፈራ ስለሆነ ወንዙን ተጠግቶ ማረስ መንፈሱን ስለሚያስቆጣው የሚያርሰውን ሰው ወደ ውሃው ውስጥ ስቦ ያስቀረዋል ይባላል፡፡ ይህን አስመልክቶ ከመረጃ ሰጭዎች መካከል አቶ ደስታው አባይነው (ቃመ፣ ግንቦት 29/2008) እንደገለፁት፡-

> የአካባቢው ማህበረሰብ ይሄን ወንዝ ተጠግቶ ማረስ ብቻ ሳይሆን አንድ ሰው ብቻውን ለመሻገር፣ ውሃው በሚነጣበት በክረምት ወቅት እንኳ ከዚህ ውሃ ውስጥ አሳ ለማስገር አያስብም፡፡ ስለሆነም የአካባቢው ማህበረሰብ እንዲህ አይነት ስፍራዎችን መዳፈር የአያት ቅድመ አያቶችን መንፈስ ቅር ስለሚያሰኝ በማህበረሰቡ ዘንድ መቅሰፍት ያስከትላል ብሎ ስለሚያምን እንደነዚህ አይነት ቦታዎችን ይንከባከባቸዋል፡፡

ይሁን እንጅ እንደኝህ መረጃ ሰጭ የአካባቢው ማህበረሰብ ቁጥሩ እየበዛና መሬት እየጠበበው በመምጣቱ አሁን አሁን አንዳንድ ሰዎች እነዚህን የተከበሩ ቦታዎች ተጠግተው ማረስ የጀመሩ ሲሆን፤ አብዛኛው ሰው ግን አሁንም ቦታዎቹን ያከብራቸዋል - ተጠግተው የሚያርሱትንም ያወግዛል፡፡

በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ፍሬ አልባነትን ያስከትላሉ በሚል ነውር ከሚላቸው ድርጊቶች መካከል የተወሰኑትን በማንሳት ማህበረሰቡ ስለስራና ተያያዥ ነውሮች ያለው አስተሳሰብ፣ እውቀትና ልምድ ምን እንደሚመስል ከዚህ በላይ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ ይሁን እንጅ ማህበረሰቡ ከስራ ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ አንዳንድ ድርጊቶችን ነውር የሚላቸው ድርጊቶቹ ለፍሬ አልባነት መንስኤዎች ናቸው ከሚል ብቻ አይደለም፡፡ እንደማህበረሰቡ ከስራ ጋር የተያያዙ አንዳንድ ድርጊቶች የፍሬ አልባነት ብቻ ሳይሆኑ የእሱ ውጤት ለሆነው ድህነትም የሚያጋልጡ ናቸው፡፡

## 7.1.3 የድህነት መንስኤ የሚሆኑ ተግባራት

ድሃ ብዙ ጊዜ ችግረኛ ለሆኑ፣ በቂ መተዳደሪያ ለሌላቸው ሰዎች የሚሰጥ ቅጽል ስም ነው፡፡ ድህነት የሚከሰትባቸው በርካታ ምክንያቶች ያሉ ቢሆንም በተጠኝው ማህበረሰብ አስተሳሰብ በአንዳንድ የስራ ክንውኖች ወቅት የሚፈፀሙ አንዳንድ ድርጊቶችም የድህነት ምንጭ ይሆናሉ፡፡ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ማህበረሰቡ ድህነትን ያስከትላሉ በሚል በነውርነት ከሚፈርጃቸው መካከል ቤት ከመስራት፣ ከስራ ምርጫ፣ ከመስሪያ ቁስ አያያዝ ወዘተ. ጋር የተያያዙ ድርጊቶች ይጠቀሳሉ፡፡ በዚሁ መሰረትም ማህበረሰቡ ድህነትን

ያስከትላሉ በሚል ነውር የሚላቸው የተወሰኑት ድርጊቶች ቀርበው ከዚህ በታች የመረጃ ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡

## አዲስ ቤት ሲሰራ ጣሪያውን ሳይደፍኑ ማሳደር

በማህበረሰቡ ዘንድ ቤት በሚሰራበት ጊዜ የቤቱ ጣሪያ በዕለቱ ተገጥሞ ወይም ተደምድሞ ማደር አለበት፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ የቤቱ ጣሪያ ሳይደፈን ካደረ የቤቱ ባለቤቶች የነበራቸው ሃብት ንብረት ሁሉ ይጠፋል፣ ይሰለባል፣ ቀጣይ ህይወታቸው በድህነት የተሞላ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በማህበረሰቡ እምነት ከአናቱ ያልተደፈነና ክፍት የሆነ ነገር መከላከያ የሌለው፣ ለአደጋ የተጋለጠ፣ ባዶና ረድኤት የሌለው ነው፡፡

በመሆኑም የአካባቢው ማህበረሰብ ቤት በሚሰራበት ጊዜ በአንድ ቀን ጣሪያውን እስከመድፈን የሚያደርሰውን የሰው ብዛት ይጠቀማል፡፡ ጣሪያውን መድፈን ዋነኛው ነገር ሆኖ ማህበረሰቡ ቤት በሚሰራበት ጊዜ ቤቱ ገዳም እንዲሆን (የቤቱ ባለቤቶች ቀጣዩ ህይወታቸው የተቃና እንዲሆን) ለማድረግ በሚል ሌሎች ተግባራትንም ያከናውናል፡፡ ቤቱ የሚሰራበት ቦታ ከተወሰነ በኋላ በአካባቢው ከሚኖሩ ሰዎች መካከል በእድሜ ገፋ ያለ አንድ ሰው ተፈልጎ የቁፋሮ ስራውን እንዲያስጀምር ይደረጋል፡፡ ይህ ሰው መጀመሪያ የሚቆፈረውን መሬት በመቆፈሪያ አንድ ጊዜ መታ ያደርግና መቆፈሪያውን መሬት ላይ ይጥለዋል፡፡ በማስከተልም መሬት ላይ የጣለውን መቆፈሪያ አንስቶ ቤቱን ለሚሰራው አባውራ ይሰጠውና ስራው በዚህ መንገድ ይጀመራል (አቶ ሙሉቀን ዘውዱ፣ ቃመ፣ ግንቦት 25/2008)፡፡ የሚቆፈረው መሬት አንድ ጊዜ መታ ተድርጎ መቆፈሪያው መሬት ላይ እንዲጣል የሚደረገው አፈር የክፉ መንፈስ ማርከሻ ስለሆነ ለቤት መስሪያነት በተመረጠው ቦታ ላይ ያለ ክፉ መንፈስ ከአካባቢው እንዲርቅ ለማድረግ ነው ይባላል፡፡ ይህ ስርዓት ከተከናወነም አዲሱ ቦታ ለቤቱ ባለቤቶች የሚስማማና ሃብት የሚያፈሩበት ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡

## ከራስ ዘር ውጭ በሆነ የስራ አይነት ላይ መሰማራት

ከራስ ዘር ውጭ ያለን የስራ አይነት ማከናወንም ማህበረሰቡ ለድህነት አጋላጭ ክስተት አድርጎ የሚመለከተው ሌላኛው ጉዳይ ነው፡፡ የማህበረሰቡ የስራ አደረጃጀትና የስራ ምርጫ ሁኔታ በዋናነት የዘር ሃረግን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በመሆኑም በማህበረሰቡ ውስጥ የገበሬ

ልጅ ገበሬ፣ የቄስ ልጅ ቄስ፣ የጥበበ ዕድ ባለሙያ ልጅ የጥበበ ዕድ ባለሙያ ወዘተ. እንዲሆን ይጠበቃል፡፡

በማህበረሰቡ አስተሳሰብ ከቀደምቶች ከተወረሱ የስራ አይነቶች ውጭ በሆኑ ስራዎች ላይ (በሙሉም ሆነ በከፊል) መሳተፍ ስራውን ለመረጠው ግለሰብም ሆነ ለቤተሰቡ መልካም ነገር ይገጥመዋል ተብሎ አይታመንም፡፡ ምክንያቱም ድርጊቱ የአያት ቅድመ አያቶችን መንፈስ ቅር የሚያሰኝ በመሆኑ በአካባቢው ላይ አንዳች መቅሰፍትን ያመጣል፡፡ በተለይም ያልተለመደውንና የማይፈቀደውን የስራ አይነት በመምረጥ የቀደምቶቹን ደንብ በጣሰው ግለሰብ ላይ የሚደርሰው መቅሰፍት ከባድ ነው፡፡ ይህን በሚመለከት መረጃ ከሰጡ ሰዎች መካከል አቶ ስለሽ መኮንን (ቃመ፣ ግንቦት 30/ 2008) እንዲህ ይላሉ፡፡

> የማህበረሰቡን ቀደምት ትውልዶች ደንብ የጣሰ በአካባቢው ማህበረሰብ ይወገዛል፡፡ በአባቶችህ ደንብ ስር ለመኖር ስላልፈቀድክ የያዝከው የነካኸው ሁሉ አይባረክ ተብሎ ይረገማል፡፡ የቀደምቶቹን ደንብ የተላለፈ ግለሰብም ሆነ እሱ ያከናወነው ስራ የተወገዘ፣ የተረገመ በመሆኑም ሰውየው የሰራው ስራ ውጤት የማይታይበት፣ ሰውየውም ሁሌም የማይሞላለትና ሙሉ ህይወቱን በድህነት የሚገፋ ይሆናል፡፡ ይህ ሰው ከአካባቢው ማህበረሰብ ባህል ያፈነገጠ ስለሆነ ከተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶችም ይገለላል፡፡ እሱም ሆነ ቤተሰቦቹ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ጋብቻ የመፈፀም መብታቸውን ያጣሉ፡፡

ስለሆነም በአካባቢው ቀደምቶቹ በግብርና ስራ የሚተዳደሩ የነበሩና እሱም በዚሁ ስራ የሚታወቅ ሰው በድንገት ተነስቶ የጥበበ ዕድ ባለሙያ (ሸክላ፣ ብረት፣ ቆዳ፣ ሸማ ሰሪ) ሊሆን አይችልም፡፡ ቀደምቶቹ የጥበበ ዕድ ባለሙያ የነበሩና እሱም በዚሁ ስራው ይታወቅ የነበረ አንድ ሰውም ከምንም ተነስቶ አርሶ አደር አይሆንም፡፡

አንዳንድ መረጃ ሰጭዎች ግን ከራስ ዘር ውጭ ያለን የስራ አይነት ማከናወን ለድህነት ያጋልጣል የሚል እምነት የላቸውም፡፡ ይህን በሚመለከት መረጃ ከሰጡ መካከል አቶ ሙጨ ገበየሁ (ቃመ፣ ግንቦት 30/ 2008) "... ወላጆቹ ጨዋ ገበሬዎች ስለነበሩ እኔም ካለማረስ የማውቀው ነገር የለኝም፡፡ እና እንደኔ ሰው ስለሚፈራ ነው እንጅ እስካበላ ድረስ ማነኛውንም ሞያ መልመድ ችግር የለውም፡፡ አያደኸጊም" ይላሉ፡፡

## ምጣድን ክፍት መተው

ምጣድ ተጠኝው ማህበረሰብ በህይወት ለመኖር የሚያገለግሉትን እንደ እንጀራ፣ ዳቦ፣ ቂጣና መሰል ምግቦች የሚጋግርበት ወይም የሚያበስልበት የቤት ዕቃ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ አንድ ምጣድ ለምግብነት የሚፈለጉ ምግቦች ከተጋገሩበት በኋላ ክፍቱንና እንደተጣደ እንዲያድር አይፈለግም፡፡ በማህበረሰቡ እምነት ጨለማ የሰይጣን ጊዜ ነው፤ ያልተከደነ ነገርም ለብክነት የተጋለጠ ወይም ባዶ ነው፡፡ በመሆኑም ክፍቱን ያደረ ምጣድ ሰይጣን ስለሚያርፍበት በሚቀጥለው ጊዜ በምጣዱ ላይ የሚጋገረው ምግብ ሁሉ ረድኤት በረከት አይኖረውም፡፡ በዚህ የተነሳም የምጣዱ ባለቤቶች ለድህነት ይዳረጋሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለሆነም አንድ ምጣድ የሚጠበቅበትን የዕለት ተግባር ከፈጸመ በኋላ በአግባቡ እንዲከደን፣ ተጥዶ ከነበረበት ቦታ ላይም እንዲነሳ ወይም እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ለድህነት ያጋልጣሉ በሚል ነውር ከሚላቸው ድርጊቶች መካከል የተወሰኑትን በማንሳት ማህበረሰቡ ስለስራና ተያያዥ ነውሮች ያለውን አስተሳሰብ ከዚህ በላይ በአጭሩ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ ይሁን እንጅ ማህበረሰቡ ከስራ ጋር በተያያዘ አንዳንድ ድርጊቶችን ነውር የሚላቸው ድርጊቶቹ የድህነት መንስኤ ይሆናሉ ከሚል ብቻ አይደለም፡፡ እንደ ማህበረሰቡ ከስራ ጋር የተያያዙ አንዳንድ ድርጊቶች ደግሞ የሚከናወነው ስራ እንዳይሰልጥ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

## 7.1.4 የስራ አለመስለጥን የሚያስከትሉ ተግባራት

በማህበረሰቡ ውስጥ በአንዳንድ የስራ ክንውኖች ወቅት የሚፈፀሙ ድርጊቶች የሚከናወነው ስራ እንዳይሰልጥ (በፍጥነትና በቅልጥፍና እንዳይከናወን፣ ስራው እንዳይቀና) ምክንያት ይሆናሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ማህበረሰቡ የስራ አለመስለጥን ያስከትላሉ በሚል ነውር ከሚላቸው መካከል ከእርሻ፣ አጨዳና አረም ጋር የተያያዙ ድርጊቶች የሚጠቀሱ ሲሆን የተወሰኑት ድርጊቶች ቀርበው ከዚህ በታች የመረጃ ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡

## በእርሻ ቦታ ላይ ዱላ መትከል/ ማቆም

በማህበረሰቡ ውስጥ አንድ ሰው እያረሰ እያለ የሚታረሰው የእርሻ ቦታ ውስጥ እራሱም ሆነ ሌላ ሰው ዱላ መትከል ወይም ማቆም አራሹ ብዙ እንዳያርስ፣ ስራው እንዳይቀናው፣

አራሹም ሆነ የሚታረሱት በሬዎች እንዲደክሙ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡ የአካባቢው አርሶ አደሮችም በዚህ ስለሚያምኑ በእርሻ ስራ ላይ እያሉ ሌላ ሰው ባይመጣባቸው ይመርጣሉ፡፡ ሌላ ሰው ከመጣም ቢያንስ ግን የመጣው ሰው ዱላውን የሚታረሰው መሬት ላይ እንዳያቆም ጥንቃቄ ያደርጋሉ፡፡ አንድ አርሶ አደር እያረሰ እያለ ሌላ ሰው መጥቶ ስለሁኔታው ካለማወቅም ሆነ በመርሳት ዱላውን ከሚታረሰው መሬት ላይ ተክሎ ቢቆም የሚያርሰው ሰው "ይሄን ከፊቴ አቁመህ ገትረኸኝ ልትውል ነው... እንኳን አቁመኸው እንዲያውም ቀሞብኛል (እርሻው አልገፋ ብሎኛል ለማለት ነው)" ይለዋል (ቄስ አስማማው ዋሴ፣ ቃመ፣ ግንቦት 27/ 2008)፡፡ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ዱላ ያቆመው ሰውም ለአራሹ ይቅርታ ይጠይቃል - ያቆመውን ዱላም ነቅሎ መሬት ላይ ያጋድማል ወይም በትከሻው ይይዛል፡፡ ስለሆነም በማህበረሰቡ እምነት ዱላን የእርሻ ቦታ ላይ መትከል የእርሻ ስራው ቀና እንዳይሆን፣ አራሹም ሆነ የእርሻ በሬዎቹ የድካም ስሜት እንዲሰማቸው የሚያደርግ ድርጊት ነው፡፡

## በስራ ላይ ባሉ ሰዎች ፊት መቆም

በእርሻ ቦታ ላይ ዱላን እንደማቆም ሁሉ የአጨዳና አረም ስራ በማከናወን ላይ ባሉ ሰዎች ፊት መቆምም በማህበረሰቡ ውስጥ ስራው እንዳይቀና የሚያደርግ ድርጊት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ሰዎች በአረምና አጨዳ ስራ ላይ እያሉ የሆነ ሰው መጥቶ ከፊት ለፊታቸው ከቆመ በስራው ላይ ያሉት ሰዎች የድካም ስሜት ይጫናቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያትም መስራት የሚገባቸውንና ቀድመው ይሄን ሰርተን እንውላለን ብለው ያቀዱትን ስራ ሳይጨርሱት መሽቶ ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ፡፡ ስለሆነም ሰዎች በአጨዳና አረም ስራ ላይ ተሰማርተው እያለ የሆነ ሰው መጥቶ ከፊታቸው ከቆመ "ከፊታችን ገለል በልልን (ከፊታችን አትቁም) ቶሎ ቶሎ እንስራበት" ይሉታል (አቶ ሙጨ ገበየሁ፣ ቃመ፣ ግንቦት 21 /2008)፡፡ ይህን የተባለው ሰውም የአካባቢውን ልማድ የሚያውቅ ከሆነ ለምን "ገለል በልልን" አሉኝ ብሎ ቅር ሳይሰኝ ይቅርታ ጠይቆ ወደ ስራው ይቀላቀላል አለያም ቦታውን ለቆ ይሄዳል፡፡ የአካባቢውን ልማድ የማያውቅ ሰው ከሆነም ለምን እንደዛ እንደተባለ ጠይቆ ከተረዳ በኋላ ይቅርታ በመጠየቅ እሱም ወደ ስራው ይቀላቀላል አለያም የመጣበትን ሁኔታ በፍጥነት ገልፆ ወደሚፈልገው ቦታ ይሄዳል፡፡

## እየታጨደ ያለ እህልን ከስር ከስር መሰብሰብ

ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በማህበረሰቡ ውስጥ በአረምና አጨዳ ስራ በተሰለፉ ሰዎች ፊት እንደመቆም ሁሉ እየታጨደ ያለን እህል ከስር ከስር መሰብሰብም ስራው እንዳይቀና ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብ እህል የሚያጭደው ብዙ ጊዜ በህብረትና በሳቅ ጨዋታ ታጅቦ ነው፡፡ አጫጆችም እያጨዱ ከኋላቸው የሚያስቀምጡትን የእህል ነዶ ዞር እያሉ ሲያዩት ይበልጥ ለስራ ይበረታታሉ፣ ብዙ እንደሰሩም ያምናሉ፡፡ በአንፃሩ ግን እያጨዱ የሚያስቀምጡት ነዶ ከስር ከስራቸው ከተነሳ ዞር ብለው ሲመለከቱ ቦታው ባዶ ሆኖ ስለሚያዩት ብዙ ያልሰሩ፣ የእለቱ የስራ ገድ ያልቀናቸው ያህል ይሰማቸዋል፤ የነበራቸውን የደስታ ስሜትም ይነጥቃቸዋል፡፡ ይህ አይነት ስሜትም የድካም መንፈስን በውስጣቸው ይዘራባቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያትም በድካምና ተስፋ መቁረጥ ስሜት ተሸንፈው በውኋቸው እናከናውነዋለን ብለው ያሰቡትን ያህል ሳይፈፅሙ ይመለሳሉ (አቶ ስለሽ መኮንን፣ ቃመ፣ ግንቦት 30/ 2008)፡፡ በመሆኑም በማህበረሰቡ እምነት መሰረት እህል በቡድንም ይሁን በግል ሲታጨድ የታጨደው እህል ከፊት ከፊት አይሰበሰብም፡፡

## 7.2 በመረጃ ትንትናው የተገኙ የጥናቱ አበይት ውጤቶች

ማህበረሰቡ ከስራ ጋር በተያያዘ ነውር የሚላቸውን ጉዳዮች በሚመለከት ተሰብስበው በተተነተኑት መረጃዎች ውስጥ የተገኙ የጥናቱ ዋና ዋና ውጤቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. በማህበረሰቡ ውስጥ ከስራ ጋር በተያያዘ ነውር የሚባሉ ድርጊቶች ነውር የሚባሉበት ዋነኛው ምክንያት ድርጊቶቹ በረከትን የሚያሳጡ ናቸው ከሚል መነሻ ነው፡፡
2. እንደ ጉልጓሎ፣ አረምና ውቂያ ያሉ የስራ አይነቶች በማህበረሰቡ ውስጥ በሚሰሩበት ጊዜ ምግብ ከመብላት በፊትም ሆነ በኋላ እጅን መታጠብን የሚከለክሉ ናቸው፡፡
3. ከራስ ዘር ውጭ የሆኑ ሰዎችን ሙያ መልመድም ሆነ መስራት በማህበረሰቡ ዘንድ የተነወረ ተግባር ነው፡፡
4. በማህበረሰቡ ውስጥ ሴቶች ንፁህ አይደሉም ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህም ምክንያት እነሱ እንዲያከናውኗቸው የማይፈቀዱ የስራ አይነቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ፦ አውድማ ውስጥ መግባትና በስራው ላይ መሳተፍ፡፡
5. በማህበረሰቡ ውስጥ ሴቶች በረከት ወይም ረድኤት የለሽ ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ ምክንያትም እነሱ እንዲያከናውኗቸው የማይፈቀዱ የስራ አይነቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ ፦ ከጎታም ሆነ ጎተራ እህል ማውጣት ወይም መስፈር፡፡
6. ሳይደፈንና ሳይሞላ በጅምር የቀረ ነገር ሁሉ በማህበረሰቡ ዘንድ የመጥፎ ገጠመኝ ተምሳሌት ነው፡፡
7. ስራ በማከናወን ላይ ባሉ ሰዎች ፊት መቆም በማህበረሰቡ ዘንድ የተነወረ ድርጊት ነው፡፡
8. ወንዞች፣ ሃይቆች፣ ጫካዎች፣ ትልልቅ ዛፎችና ዋሻዎች በማህበረሰቡ ዘንድ የሚፈሩና የሚከበሩ ናቸው፡፡
9. በማህበረሰቡ እምነት ክፉ መንፈስ ይፈታተናቸዋል ተብሎ ከሚታመንባቸው የስራ አይነቶች መካከል የአውድማ ስራ ቀዳሚ ነው፡፡
10. ታህሳስና ጥር ማህበረሰቡ እህል ለመውቃት የማይመርጣቸው ወሮች ናቸው፡፡

11. የጥናቱ ትኩረት የሆነው የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ማህበረሰብ በወር ውስጥ ቢያንስ ለ11 ቀናት ያህል እንዲያከናውናቸው የማይፈቀዱ የስራ አይነቶች አሉት፡፡

በአጠቃላይ ተጠኝው ማህበረሰብ ስለግብርና ስራና ተያያዥ ነውሮች ያለው እውቀት፣ ልምድና ትግበራ ምን እንደሚመስል ከዚህ በላይ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ከዚህ በሚከተለው ምዕራፍ ደግሞ የጥናቱን የውጤት ትንተናና ትርጎማ የሚመለከቱ ጉዳዮች ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ ስምንት

## የውጤት ትንተናና ትርጎማ፦

ይህ ጥናት በነውሮች አማካይነት የሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብን የህይወት ፍልስፍና ለመግለፅ ታስቦ የተካሄደ ነው፡፡ ስለሆነም ባለፉት የመረጃ ትንተና ምዕራፎች ውስጥ የተገኙ ውጤቶችን ለሌሎች ለመግለፅና የማህበረሰቡ የህይወት ፍልስፍና ምን እንደሚመስል ለማሳየት በመረጃ ትንተናው በተገኙት የጥናቱ ውጤቶች ላይ የውጤት ትንተናና ትርጎማ ማቅረብ አስፈላጊነት አለው፡፡

በመሆኑም በዚህ ክፍል በመረጃ ስብሰባና ትንተና ወቅት በተገኙ የተወሰኑ የጥናቱ ውጤቶች ላይ የጥናቱን ርዕስ፣ ዓላማና ጥናቱ የሚመልሳቸውን ጥያቄዎች መሰረት ያደረገ የውጤት ትንተናና ትርጎማ ለመስጠት ተሞክሯል፡፡ የውጤት ትንተናና ትርጎማ ስራው በዋናነት አምስት ርዕሰ ጉዳዮችን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ በዚሁ መነሻነትም በመጀመሪያ ማህበረሰቡ ስለነውር ያለውን እሳቤና የሚሰጠውን ማህበራዊ ፍች የተመለከተ አጭር የውጤት ትንተናና ትርጎማ ቀርቧል፡፡ በሁለተኛ፣ ሶስተኛና አራተኛ ቀርበው የውጤት ትንተናና ትርጎማ የተካሄደባቸው በቅደም ተከተል የማህበረሰቡን የምግብ፣ ሞትና ስራ እሳቤ፤ እንዲሁም ከነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ማህበረሰቡ ነውር የሚላቸውን ጉዳዮችና ነውር ለማለትም የሚሰጣቸውን ምክንያቶች የተመለከቱ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመጨረሻ የቀረበው ርዕሰ ጉዳይ ደግሞ የማህበረሰቡ ነውሮች ያላቸውን አዎንታዊና አሉታዊ ሚና የተመለከተ ነው፡፡ በዚሁ መሰረትም በተጠቀሱት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረገው የውጤት ትንተናና ትርጎማ ርዕሰ ጉዳዮቹ እንደተጠቀሱበት ቅደምተከተል ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

### 8.1 የነውር እሳቤ

የሰው ልጅ የሚኖርበትን አካባቢና የዓለምን ምንነት የሚተረጉምበት፣ የክስተቶችን አመጣጥና ምክንያት የሚረዳበት ከልምድና ድግግሞሽ የሚያገኘው ኢ- መደበኛና የግለሰብ ወይም የአንድ ቡድን የሆነ ህሊናዊ እውቀት (subjective knowledge) አለው (Pehkonen እና Anu, 2003: 3)፡፡ እንደዚሁ ሁሉ የሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብም በአካባቢው ያሉ ነገሮችን የሚረዳበትና ፍች የሚሰጥበት፤ ምን መስራት እንዳለበትና እንደሌለበት፣ እንዴት መኖር እንዳለበትና እንደሌለበት የሚመራበት በአጠቃላይም የቆየ ባህሉን የሚያስቀጥልበት

አካባቢያዊ የሆነ እውቀት አለው፡፡ ማህበረሰቡ ካለው እውቀት መካከልም ነውር አንዱ ነው፡፡ በጥናቱ ከተገኘው ውጤት በመነሳት ተጠኝው ማህበረሰብ ባለበት መቆየትን የሚወድ፣ ካወቀውና ከለመደው ውጭ አዲስ ነገር ተፈጥሮ እንዲነቅለው የማይፈልግ፤ በአጠቃላይም በቆየ ልማድ የመጽናት ሁኔታ የሚታይበትና ለዚህም ነውርን በመሳሪያነት የሚጠቀም ነው ማለት ይቻላል፡፡

በተጠኝው ማህበረሰብ ዘንድ ነውር የሚለው እሳቤ እራስን፣ ቤተሰብንና የአካባቢውን ማህበረሰብ ከጉዳት ለመጠበቅ ሲባል በሰዎች ላይ የሚጣል ክልከላ ነው የሚል ፍች የያዘ ነው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ አካባቢያዊ ልማዱን መነሻ አድርጎ በአካባቢው የሚገኙትን ነገሮች ሁሉ ነውር የሆኑና ያልሆኑ በሚል በሁለት እንደሚፈርጃቸው ጥናቱ ያሳያል፡፡ ማህበረሰቡ ነውር የሚላቸውን ነገሮች ከእርክሰት (Danger)፣ ነውር ያልሆኑ የሚላቸውን ደግሞ ከንፅህና (purity) ጋር አያይዞ ይተረጉማቸዋል፡፡ [እ]ርክሰት ተጠኝው ማህበረሰብ ነገሮችን በማደራጀትና ስርዓት አልባውን ህገኛ አድርጎ በማስተካከል የፀናው ስርዓት እንዳይፈርስና እሳቤውን ይዞ እንዲቀጥል ለማድረግ፤ ንፅህናን (purity) ደግሞ ደንብና ስርዓት ማምጫ ሰበብ አድርጎ የተጠቀመበት ነው፡፡ ይህ በሌሎች ሃገራት በተካሄዱ የጥናት ውጤቶች ውስጥም በተደጋጋሚነት የተጠቀሰ ነው፡፡

በማህበረሰቡ ዘንድ ከተለመደው ወጣ ያለ ወይም ከማህበራዊ ልማዶች ያፈነገጠና ለማህበረሰቡ ስርዓት ያልተገዛ ድርጊት ሁሉ ከመርከስ፣ ከመቆሸሽ እንደሚቆጠር የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ይህም Chigidi (2009:175) በዚምባብዌ በሚገኙ የሾና ጎሳዎች ላይ ባደረጉት ጥናት ካገኙት የምርምር ውጤት ጋር ተደጋጋፊነት ያሳያል፡፡ በአንፃሩ ግን ከተለመደው ያፈነገጠ ሃሳብና ድርጊት ሁሉ ያረክሳል፣ ያቆሽሻል ማለት አይቻልም ከሚለው የDouglas (1966:161- 162) ሃሳብ ጋር ይቃረናል፡፡

በመረጃ ስብሰባ ወቅት እንደታየው ማህበረሰቡ ነውር በሚል ለሚፈጥራቸው ድርጊቶች የራሱን ምክንያት ያቀርባል - የሚያቀርባቸውን ምክንያቶችም ትክክለኛ ናቸው ብሎ ያምናል፡፡ ሆኖም ማህበረሰቡ ነውር ለሚላቸው ድርጊቶች የሚያቀርባቸው ምክንያቶች በዋናነት የሚታመኑ እንጅ ተጨባጭ የሆነ ማስረጃ ሊቀርብባቸው የሚችሉ እንዳልሆኑ በትንተናው ከተገኘው ውጤት ለመረዳት ተችሏል፡፡ እስኪ ጉዳዩን ከማህበረሰቡ የተሰበሰቡ የተወሰኑ ነውሮችንና ነውር ለመሆናቸው የሚሰጡ ምክንያቶችን በማንሳት እንመልከተው፡፡ ለምሳሌ ፦ በማህበረሰቡ ውስጥ በእርጎ በልቶ እጅን መታጠብ የእርጎው ምንጭ የሆነችው

ላም እንድትደርቅ (በቀጣይ መውለድም ሆነ ወተትና እርጎ መስጠት እንዳትችል) ያደርጋል፤ የሞተን ሰው ስም መጥራት በጠሩት ላይ ሞት ያመጣል፤ መካን ሴትን በጀርባዋ አንጋሎ መቅበር የአካባቢው ሴቶች ሁሉ መካን እንዲሆኑ ያደርጋል፤ ከራስ ዘር ውጭ በሆነ ስራ ላይ መሰማራት ድሃ ያደርጋል፤ በአረምና ጉልጓሎ ስራ ላይ እያሉ ምግብ ከመብላት በፊትም ሆነ በኃላ እጅን መታጠብ የታጠቡበት መሬት እህል እንዳያበቅል ያደርጋል፤ እህል በመወቃት ላይ እያለ የስራው ባለቤት እጁን ከታጠበ እህሉ አይበረክትም፤ በቤት ውስጥ ያለን የሸረሪት ድር መጥረግ መካን ያደርጋል ወዘተ. ተብሎ ይታመናል፡፡

ነገር ግን ለተጠቀሱት ነውሮች ማህበረሰቡ የሰጣቸው ምክንያቶች ትክክለኛ ናቸው፣ የተጠቀሱት ነውሮች ቢጣሱ የተባሉት ችግሮች በትክክል ይደርሳሉ ብሎ ለማረጋገጥ ያስቸግራል፡፡ በአፍሪካውያን ነውሮች ላይ በተካሄዱ አንዳንድ ጥናቶች የተገኙት ውጤቶችም ለምሳሌ፦ የMasaka እና Munamato (2011፡145) የOsei (2006፡ 52) አማኞቹ ስለነውሮች ያሏቸው እምነቶችና የሚያቀርቧቸው እምነታዊ ገለፃዎች እውነተኛነታቸው ብዙ ጊዜ በዘመናዊ ሳይንስ ሊረጋገጡ የሚችሉ እንዳልሆኑ የሚገልፁ ናቸው፡፡ ይሄ ማለት ግን የዚህ ጥናት ትኩረት ከሆነው ማህበረሰብ የተሰበሰቡት ነውሮች የማህበረሰቡ ማንነትና ማህበራዊ ደረጃ በአጠቃላይም አካባቢያዊ እውቀት፣ እምነትና ፍልስፍና የሚገለፅባቸው ስለሆኑ የእምነቱ በሳይንስ መረጋገጥም ሆነ አለመረጋገጥ፣ እውነት መሆን አለመሆን ነውሮች ዋጋ የሌላቸው ናቸው ወደሚል እሳቤ ሊወስድ የሚችል አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ግን የሚፈጠሩ ሁሉንም ነውሮችና ለነውርነታቸውም የሚሰጡ ምክንያቶችን ሁሉም የማህበረሰቡ አባል ትክክለኛ ናቸው ብሎ የተቀበላቸው ናቸው ለማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም አንዳንድ የነውር አይነቶችና ለነውርነታቸውም የሚሰጡ ምክንያቶች ተገቢና ትክክለኛ ያልሆኑ ናቸው የሚል መረጃ የሰጡ የተወሰኑ ሰዎችም ነበሩ፡፡ ለምሳሌ ያህልም፦ ነገዴዎች ያዘጋጁትን ምግብ ከመመገብ፤ ከራስ ዘር ውጭ የሆነ ሙያን ከመልመድ ጋር የተያያዙ ነውሮች የአካባቢውን ማህበረሰብ ጫና በመፍራት የሚከበሩ እንጅ ሁሉም ፈቅዶ የተቀበላቸው እንዳልሆኑ የገለፁ መረጃ ሰጭዎች አጋጥመዋል፡፡ ስለዚህ ሁሉንም ነውሮች ማህበረሰቡ በጋራ ተስማምቶ የፈጠራቸው፣ ፈቅዶና ወዶ የተቀበላቸው ናቸው ማለት እንደማይቻል፤ በሌሎች ጫና ብቻ የተፈጠሩና ተከብረውም የሚኖሩ ነውሮችም በማህበረሰቡ ውስጥ እንዳሉ መናገር ይቻላል፡፡

በጥናቱ እንደታው ማህበረሰቡ ነውሮቹን የሚያስከብርባቸውና የሚያስቀጥልባቸው የተለያዩ ስልቶች (ስነቃሎች፣ ቅጣቶች ...) አሉት፡፡ ለምሳሌ ያህል፡- "ነውሩን የበላ ጥርሱ ይሰበራል - በቁምጥና በሽታ ይያዛል" የሚለውን አባባል ብንመለከት ማህበረሰቡ በነውርነት የሚፈርጃቸውን የምግብ አይነቶች አባላቱ ከመጠቀም እንዲቆጠቡ (የተጠቀሱት አይነት ችግሮች ይደርሱብኛል ብሎ በመፍራት) የሚያደርግበት አንዱ መንገድ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የጥናቱ ውጤቶች እንደሚያሳዩት የሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ አብዛኞቹ ነውሮች ምግብ፣ ሞትና ስራን ርዕሰ ጉዳያቸው ያደረጉ ናቸው፡፡ እነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች (በተለይም ምግብና ሞት) በሌሎች የአፍሪካ ሃገራት ባህሎች ውስጥም ነውሮች እንደሚዘወተሩባቸው አንዳንድ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ማህበረሰቡ ስለምግብና ተያያዥ ነውሮች ያለው እሳቤ ምን እንደሚመስል በጥቂቱ እንመልከት፡፡

## 8.2 የምግብና ተያያዥ ነውሮች እሳቤ

ማህበረሰቡ ሁሉም የምግብ አይነቶች ጠቀሜታ አላቸው ብሎ እንደማያምንና በዚህም ያለውን አካባቢያዊ እውቀትና የረጅም ጊዜ ልምዱን ተጠቅሞ በአካባቢው የሚገኙ የእህል አይነቶችን የሚበሉና የማይበሉ በሚል እንደሚከፍላቸው ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ማህበረሰቡ የማይበሉ የሚባሉ የምግብ አይነቶችን መጠቀም በተጠቃሚው ግለሰብ ላይም ሆነ በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ አንዳች መጥፎ አጋጣሚን ያስከትላል ብሎ ያምናል፡፡ በጥናቱ የተገኙ ውጤቶች እንደሚያሳዩት በማህበረሰቡ ውስጥ ለምሳሌ፡- እንደ ተልባ፣ ባቄላ፣ ሙዝ፣ እንቁላል፣ የስጋ ዘሮች ወዘተ. የሚፈሩና በዚህም የተለያየ እገዳ የሚጣልባቸው ናቸው፡፡ በጥናቱ ከተገኙ ውጤቶች ማህበረሰቡ የተጠቀሱትንና መሰል የምግብ አይነቶችን በነውርነት ለመፈረጅ ምክንያት የሚያደርገው በዋናነት የጤና መታወክን ያስከትላሉ፣ የትዳር አጋር ያሳጣሉ፣ ድርቅና ረሃብን ያመጣሉ፣ ውግዘትን ያስከትላሉ የሚል እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ማህበረሰቡ ነውር ናቸው ለማለት ከሚሰጣቸው ምክንያቶች መካከል የተጠቀሱት የምግብ አይነቶች ለተለያዩ የጤና ችግሮች መንስኤ ይሆናሉ የሚለው ከፍተኛውን ቁጥር (ለጥናቱ ከተመረጡት ጠቅላላ 57 ነውሮች ውስጥ ለ31ዱ የተሰጠ ምክንያት ነው) ይዞ ይገኛል፡፡ በሌሎች አጥኚዎች ለምሳሌ፡- በDawit *et al.* (2005፡32)፣ *Kuzma et al.* *(2013፡1)፣ Omobola (2013፡224) የተገኙ የጥናት ውጤችም ከሞላ ጎደል ለምግብ ነውሮች*

በዋና ምክንያትነት የሚጠቀሰው ጤናን የሚመለከት እንደሆነ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ እዚህ ላይ ግን ማህበረሰቡ ነውር ለሚላቸው የምግብ አይነቶች የሚሰጣቸው ምክንያቶች ለምን ጤና ላይ ትኩረት ሊያደርጉ እንደቻሉ ማህበረሰቡ ስለምግብ ካለው እሳቤ ጋር በማናበብ የተወሰነ ማብራሪያ መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡ እስኪ ነገሩን "ፍርሃት" ና "የበላይነት አስተሳሰብ" ከሚሉ ሁለት ጽንሰ ሃሳቦች አኳያ በአጭሩ እንመልከተው፡፡

የሰው ልጅ ቢደላውም ባይደላውም በህይዎት መቆየትን፣ ረጅም ዕድሜን፣ ሃብትና ንብረትን ወዘተ. የመመኘት ባህሪ ያለው ፍጡር ነው፡፡ ይህን ምኞቱን ለማሳካት ደግሞ ጤናው የተጠበቀ ሊሆን ይገባል፡፡ በመሆኑም ከበሽታ የራቀና ሙሉ ጤናማ የሆነ አካል በማንኛውም አገር የሚኖር የማህበረሰብ ክፍል ሁሉ አጥብቆ የሚሻው የሰው ልጆች የጋራ መገለጫ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የሊቦ ከምከም ማህበረሰብም አንዳንድ የምግብ አይነቶችን ነውር የሚላቸው ጤነኛ ለመሆን ካለው ጉጉትና የተጠቀሱት የምግብ አይነቶች በትክክልም የጤና ጠንቅ ናቸው ከሚል ፍርሃት በተነሳ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በጥናቱ በዋናነት ጎልቶ የወጣው ጉዳይም ይሄን ሃሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን የምግብ ነውሮች ዋነኛ ምክንያት ጤና ለምን ሆነ ሲባል ጤናን ሽፋን ያደረጉ (ሰዎች ለጤናቸው የሚሰጡትን ከፍተኛ የሆነ ቦታ እንደመደበቂያ የሚጠቀሙ) ሌሎች ጉዳዮችም ከኋላ ሊኖሩ እንደሚችሉ ፍንጭ ሰጭ የሆኑ ክስተቶች በጥናቱ ታይተዋል፡፡ ለዚህም በአብዛኞቹ መረጃ ሰጭዎች የተደገፈ ሃሳብ ባይሆንም አንዳንድ ወንዶች በጤና አሳበው በሴቶች ላይ የበላይነትን ለማሳየት የሚፈጥሯቸው ነውሮችም በማህበረሰቡ ውስጥ ሊኖሩ እንደሚችሉ (ለምሳሌ፦ የአድባር መሰዋዕት የሚሆን ምግብን ሴቶች እንዲያዘጋጁ የማይፈቀድ መሆኑን በመጥቀስ) መረጃ የሰጡ ሰዎች መኖራቸው እንደማሳያ ሊወሰድ ይችላል፡፡

የጥናቱ ግኝቶች እንደሚያሳዩት ለጥናቱ ከተመረጡትና ቁጥራቸው 57 ከሚሆኑት የማህበረሰቡ የምግብ ነውሮች መካከል 35 ነውሮች ሁሉንም የማህበረሰቡ አባላት፣ 15 ነውሮች ሴቶችን፣ 5 ነውሮች ወንዶችን፣ 2 ነውሮች ደግሞ ህፃናትን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ከተጠቀሱት የማህበረሰቡ አባላት መካከል የነውሮቹ ዋነኛ ትኩረቶች የትኞቹ ናቸው? የሚለውን ስንመለከት ደግሞ በጥናቱ ግኝት መሰረት የነውሮቹ ዋነኛ ትኩረቶች ሴቶች (በተለይም በእርግዝና ላይ ያሉ) ናቸው፡፡ ምክንያቱም ከተጠቀሱት ነውሮች መካከል 15ቱ ሴቶችን ብቻ የሚመለከቱ ሲሆኑ፣ ሁሉንም የማህበረሰቡ አባላት የሚመለከቱት 35 ነውሮች ደግሞ ሴቶችንም ስለሚያካትቱ የማህበረሰቡ ነውሮች ዋነኛ ትኩረት ሴቶች እንደሆኑ

*መገንዘብ ይቻላል፡፡* እዚህ ላይ ግን የማህበረሰቡ የምግብ ነውሮች ለምን ሴቶች (በተለይም በእርግዝርና ላይ የሆኑ) ላይ ትኩረት ሊያደርጉ እንደቻሉ የተወሰነ ሃሳብ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡

*የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው ቀደም ሲል የተጠቀሱትና መሰል የምግብ አይነቶች በማህበረሰቡ ውስጥ በእርግዝና ላይ ያሉ እናቶች እንዲመገቧቸው አይፈለግም፡፡ በጥናቱ ግኝት መሰረት በማህበረሰቡ ውስጥ በእርግዝና ላይ ላሉ ሴቶች የሚከለከሉት የምግብ አይነቶች አብዛኞቹ በፕሮቲን የበለፀጉ ናቸው፡፡ የዚህ ጥናት ግኝት ከሌሎች አጥኚዎች የጥናት ግኝቶች ለምሳሌ፦ ከነ* Kuzma (*2013፡7*) *ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ እዚህ ላይ ግን በማህበረሰቡ ዘንድ በፕሮቲን የበለፀጉ ምግቦች በተለየ ሁኔታ ለምን ተከለከሉ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ሆኖም የዚህ ጥያቄ መልስ የተጠቀሱት የምግብ አይነቶች ፅንሱ ከመጠን በላይ እንዲፋፋ በማድረግ በወሊድ ጊዜ የምጥ መጥበቅንና ከፍተኛ የሆነ የደም መፍሰስን ያስከትላሉ ከሚለው የማህበረሰቡ እምነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በአጭሩ በፕሮቲን የበለፀጉ ምግቦች* በእርግዝርና ላይ ላሉ ሴቶች የመከልከላቸው ምክንያት ማህበረሰቡ ካለው የምግብና ጤና እሳቤ የሚመነጭ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ይሄ ማለት ግን በማህበረሰቡ ውስጥ የጤና ጠንቅ ናቸው ተብለው የሚታሰቡት የምግብ አይነቶች ብቻ ናቸው ማለት አይደለም፡፡ ከመስክ የተሰበሰቡትና የተተነተኑት መረጃዎች እንደሚያሳዩት ምግቦቹን የሚያዘጋጇቸው አንዳንድ ሰዎችም (ለምሳሌ፦ መካን ሴቶች) በማህበረሰቡ ዘንድ ለጤና መታወክ እንደመንስኤ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ በትንተናው በተገኙ ውጤቶች መሰረት በማህበረሰቡ ውስጥ መካንነት ለፈጣሪ ካለመገዛት፣ የአያት ቅድመ አያቶችን ደንብ ከመጣስ የሚመጣ ቅጣት ወይም እርግማን ነው፡፡ በማህበረሰቡ አስተሳሰብ መካንነት ከሴትነት ጋር የተያያዘ ሲሆን፤ የዚህ አስተሳሰብ መነሻም (እርግማኑ ለምን የተወሰኑት ሴቶች ላይ ብቻ ሊሰራ ይችላል የሚል ጥያቄ ሊያጭር የሚችል ቢሆንም) ሔዋን አዳምን በማሳቷ ፈጣሪ ረግሟታል ወደሚል ሃይማኖታዊ አስተምህሮ የሚያመራ ነው፡፡ በዚህም መነሻነት መካን ሴቶች የተረገሙ ስለሆኑ ሰውን የሚጎዳ ክፉ አይን ያደረባቸው ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህም በማህበረሰቡ ውስጥ መካኖች በአንዳንድ ማህበራዊ ግንኙነቶች ላይ ከተቀረው የአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በእኩልነት እንዲሳተፉ አይደረጉም፡፡ ለምሳሌ ያህልም፦ በአራስ እህል ዝግጅት ላይ እንዲሳተፉ አይፈቀድላቸውም፡፡ ይህ የሚሆንበት ዋናው ምክንያትም በማህበረሰቡ ዘንድ አራሶችና

አዲስ የተወለዱ ጨቅላ ህፃናት ለክፉ መንፈስ ተጋላጭ ናቸው የሚል አስተሳሰብ ስላለና መካኖች ካዩዋቸው የተጠቀሱት ሰዎች ይታመማሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

*በአጠቃላይ ግን ማህበረሰቡ የሚሰጣቸው ምክንያቶች ምንም ይሁኑ ምን የማህበረሰቡ የምግብ ነውሮች ዋነኛው መንስኤ ማህበረሰቡ* እያንዳንዳቸው የምግብ አይነቶች በምግብነት ወደ ሰዎች አካል ውስጥ ገብተው ሊሰጡ ስለሚችሉት ጠቀሜታና እነሱን አለማግኘትም ሊኖረው ስለሚችል ጉዳት ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ስለሰው ልጅ ህይወትና የአፈጣጠር ሁኔታ ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑም ሌላኛው መንስኤ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የKuzma et al. (*2013፡1*) እና Nejimu *(2015፡414) የጥናት ውጤቶችም የጥናታቸው ትኩረት የሆኑት የማህበረሰብ ክፍሎች ስለምግብና ተያያዥ ነውሮች ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ ሆኖ እንዳገኙት የሚገልፁ ናቸው፡፡* ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ማህበረሰቡ ስለሞትና ተያያዥ ነውሮች ያለው እሳቤ ምን እንደሚመስል በጥቂቱ እንመልከት፡፡

## 8.3 የሞትና ተያያዥ ነውሮች እሳቤ

ማህበረሰቡ ከሞት ጋር በተያያዘ ነውር የሚላቸውን ድርጊቶች ለምን በነውርነት ፈረጃቸው ብለን ስንጠይቅ ማህበረሰቡ ከሚሰጣቸው ምክንያቶች መካከል ድርጊቶቹ ሞትን የሚጠሩና የሙት መንፈስን የሚያስቀይሙ፣ መካንነትን የሚያስከትሉ፣ ንፅህናን የሚያሳጡ፣ ለድርቅ የሚያጋልጡ፣ የሃዘን ስሜትን የሚያባብሱ ናቸው የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ማህበረሰቡ ከሚሰጣቸው ምክንያቶች መካከል ከፍተኛውን ቁጥር ይዞ የሚገኘው ግን ድርጊቶቹ ሞትን የሚጠሩና የሙት መንፈስን የሚያስቀይሙ ናቸው (ለጥናቱ ከተመረጡት ጠቅላላ 35 ነውሮች ውስጥ ለ17ቱ የተሰጠ ምክንያት ነው) የሚለው ነው፡፡ ይህ በማህበረሰቡ ውስጥ ሞትና የሙት መንፈስ ከምንምና ከማንም በላይ የሚፈሩና የሚከበሩ ክስተቶች እንደሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ለሞት ተስማሚ የሚላቸውን ነውሮች እየፈጠረ ከሚያስፈራው ከዚህ አይቀሬ የሆነ ተፈጥሯዊ ክስተት ጋር ራሱን አላምዶና አስማምቶ ይኖራል፡፡ ይሄ ማለት ግን ሞት በሌላው ዓለም ተፈሪ አይደለም ማለት አይደለም፡፡ ደረጃው ሊለያይ ካልቻለ በስተቀር በማንኛውም ሃገርና ህዝብ ውስጥ ሞትን የማይፈራ ሰብአዊ ፍጡር ይኖራል ለማለት ይከብዳል፡፡ ስለሆነም እዚህ ላይ ለማንሳት የተሞከረው ማህበረሰቡ ስለሞት ያለው እሳቤ ምን እንደሚመስል ለመጠቆም ያህል እንጅ ማህበረሰቡ ሞትን የመፍራቱ ጉዳይ የዚህ ጥናት አዲስ ግኝት ስለሆነ አይደለም፡፡

ከጥናቱ በተገኘው ውጤት መሰረት በማህበረሰቡ ውስጥ ሞት ከሰው ወደ ሰው ተላላፊ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ለምሳሌ፦ የሟችን አስከሬን ወደ ቀብር ቦታ ለመውሰድ በቤቱ ዋና በር ማስወጣት፣ የሃዘን እህልን ወደ ቤት መመለስና የመሳሰሉት ድርጊቶች ሞት ከሟች በህይወት ወዳሉ ሌሎች ሰዎች እንዲተላለፍ ያደርጋሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህም ምክንያት ማህበረሰቡ ሟችን ላለመከተል (ከሟች ቀጥሎ ላለመሞት) በማሰብ የተጠቀሱትንና መሰል ድርጊቶችን ከማድረግ የተቆጠበ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ሞት ከአንዱ ወደ ሌላው እንዲተላለፍ ያደርጋሉ ተብለው የሚፈሩት ግን ከፍ ሲል የተጠቀሱት ድርጊቶች ብቻም አይደሉም፡፡

የሞተ ሰውን በተለመደውና በሚታወቀው ስሙ መጥራትም የሞት መተላለፊያ አንዱ መንገድ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በተጠኝው ማህበረሰብ እምነት አንድ ሰው እንደሞተ ወደ[እ]ርኩስ መንፈስነት ይቀየራል፡፡ ስለሆነም ሟችን በተለመደው ስሙ መጥራት [እ]ርኩስ መንፈስን እንደመጥራት ስለሆነ የጠሩትን ሰዎች ወደሞት ይጠራል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህ መነሻነትም በአካባቢው አንድ ሰው ህይወቱ ካለፈባት ቅፅበት ጀምሮ በቤተሰቡ ሳይቀር ይፈራል፡፡ ከቤተሰቡ መካከል ተጨማሪ ሰው እንዳያስከትል ይሰጋል፡፡ ስለሆነም በማህበረሰቡ ውስጥ አንድ ሰው እንደሞተ ይጠራበት የነበረ ስሙን እንዲያጣ ይደረጋል - በምትኩ “ ሟቹ” “ሟቿ” የሚል አዲስ ስም ይሰጠዋል፡፡ የሟች ስም ከተቀየረ ግን ሟች አዲሱን ስሙን ስለማያውቀው ሞትን ወደ ሌሎች ሰዎች አያስተላልፍም (ወደ ሞት አይወስድም) ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ ከMhaka (2014፡381) የጥናት ውጤት ጋር ተመሳሳይነት ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ግን የዚህ ጥናት ውጤት የሞተ ሰውን አስከሬን ሳያጥቡ መቅበር ሞት ሳያጥቡ ወደ ቀበሩት ሰዎች እንዲተላለፍ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል ከሚለው የMhaka የጥናት ውጤት ጋር ይቃረናል፡፡ ምክንያቱም የዚህ ጥናት ውጤት የሚያሳየው በሊቦ ከምከም ማህበረሰብ ዘንድም የሞተ ሰውን አስከሬን ሳያጥቡ መቅበር ነውር ቢሆንም የነውርቱ መንስኤ ተደርጎ የሚወሰደው ግን ሳይታጠብ ከተቀበረ የቤተሰቡን ሃብት ንብረት፣ ዕድሜ፣ ጤና ይዞ ይሄዳል የሚል ነው፡፡

ተጠኝው ማህበረሰብ ስለሞትና ተያያዥ ነውሮች ያለውን እሳቤ በሚመለከት በትንተናው የተገኘው ሌላኛው ውጤት በማህበረሰቡ ውስጥ ከሞት በኋላ ህይወት አለ ተብሎ የሚታመን መሆኑ ነው፡፡ በማህበረሰቡ እምነት ሞት የህይወት መጨረሻ አይደለም - ከሞት በኋላ የሚኖርበት ሌላ አለም አለ፡፡ በዚህም በአካባቢው አንድ ሰው ሲሞት የሟች መንፈስ ወደ

አያት ቅድመ አያቶቹ (ከእሱ ቀድመው ወደ ሞቱት) የሚቀላቀልበትና ከሞት በኋላ ወዳለው አዲስ ህይወት የሚሸጋገርበት እንደሆነ ይታመናል፡፡ ሟች ከቤተሰቡ በስጋ ቢለይም መንፈሱ ግን አብሮ እንደሚኖርና በየጊዜው እየመጣም አካባቢውንና ቤተሰቡን እንደሚጎበኝ፣ በህይወት ባሉ ሰዎች ላይ የሚታዩ ስሜቶች ሁሉ በእሱም ላይ የሚገለፁ (የሚያይ፣ የሚሰማና የተለያዩ ፍላጎቶች ያሉት) ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ይህም የአፍሪካውያን የሞት እሳቤ ከሞት በኋላ ህይወት አለ የሚል ነው ከሚለው የMhaka (2014፡379) የጥናት ውጤት ጋር ተመሳሳይነት ያሳያል፡፡ ሆኖም ግን ይህ እሳቤ አለማቀፋዊነት ያለው ነው ለማለት አይቻልም፡፡ እንደ Baloyi (ዓ.ም የለውም፣ ገፅ 236) በአውሮፓ አሜሪካውያን ዘንድ ያለው አስተሳሰብ ከሞት በኃላ ህይወት የለም (የሰው ልጅ የህይወት ዑደት በፅንሰት ይጀመራል - በሞት ይቋጫል) የሚል ነው፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ከሞት በኋላ ህይወት አለ ብቻ ሳይሆን ሰው ከሞተ በኃላ መንፈሱ ለጉብኝት የሚመጣ ተደርጎም ይታሰባል፡፡ አንድ ሰው ከሞተ በኃላ በተለይም ከተቀበረበት ቀን ጀምሮ ባሉ የተወሰኑ የመጀመሪያ ተከታታይ ቀናት ውስጥ መንፈሱ በተደጋጋሚነት ወደ ቤቱ እየተመላለሰ፣ በሂደትም አልፎ አልፎ ብቅ እያለ ቤተሰቦቹንና አካባቢውን እንደሚጎበኝ ይታመናል፡፡ ይሁን እንጅ ከቀብር መልስ ድምፅን ከፍ አድርጎ ማልቀስ - ማውራትና ሃዘን ማብዛት የመሳሰሉት ድርጊቶች የሟች መንፈስን የሚረብሹትና የሚያደርገውን ጉብኝትም እንዲያቋርጥ የሚያደርጉ ናቸው ተብሎ እንደሚታሰብ በጥናቱ ታይቷል፡፡

የማህበረሰቡ የሙት መንፈስ እሳቤ ሁለት መልክ ያለው ነው፡፡ አንደኛው እሳቤ የሙት መንፈስ ከፈጣሪ የተሰጠው ልዩ የሆነ ሃይል ስላለው ይታደጋል፣ ከአምላክ ጋር ያቀራርባል ብሎ ከማመን የሚመነጭ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ማህበረሰቡ ከፈጣሪ አንዳች ሃይል ተሰጥቶታል ብሎ በሚያምንበት የሙት መንፈስ ለመጠቀምና በእሱ ለመጠበቅ በሚል ያከብረዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ ሰው እንደሞተ ወደርኩስ መንፈስነት ይቀየራል ብሎ በማመን ይፈራዋል፡፡

በጥናቱ ውጤት መሰረት በማህበረሰቡ ውስጥ አንድ ሰው ህይወቱ ካለፈበት እስከተቀበረበት ድረስ ያለችው ጊዜ የተቀደሰች ተደርጋ ትታሰባለች፡፡ ምክንያቱም በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የሞተ ሰው በፈጣሪ እጅ ያለ ስለሆነ አንድ ሰው ሊሞት ሲያጣጥር ጀምሮ ቅዱሳን መላዕክት ወደ እሱ ይመጣሉ፣ በአካባቢው ሁሉ ይሰራጫሉ፣ ከሞተ በኋላም እስኪቀበር ድረስ

አብረውት ይቆያሉ፣ እንደተቀበረም ነፍሱን ይዘው ይሄዳሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለሆነም በአካባቢው አንድ ሰው መሞቱ ከተሰማበት ጊዜ ጀምሮ መቀበሩ እስከሚታወጅበት ጊዜ ድረስ የአካባቢው ማህበረሰብ ማንኛውንም የግብርና ስራ እንዲያከናውን አይፈቀድም፡፡ ምክንያቱም ያች ጊዜ ቅዱሳን መላዕክት በአካባቢው የተገኙባትና አካባቢውን የሚባርኩባት የተቀደሰች ጊዜ ስለሆነች በዚች ሰዓት ሌላ ስራ ማከናወን ቅዱሳን መላዕክትን መፈታተን ስለሆነ አካባቢው በበረድ ይመታል፣ በድርቅ ይጠቃል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ሰው የሞተበት አካባቢ ማህበረሰብ ከግል ስራው ይልቅ የተቀደሰች ለተባለችው ቀን ቅድሚያ በመስጠት በሟች ቤት በመገኘት ያስተዛዝናል፡፡ የሟችን አስከሬን ወደ ቀብር ቦታ ወስዶ ይቀብራል፡፡ ከዛ በኋላ ወደ ግላዊ ስራው ይመለሳል፡፡

በትንተናው ከተገኘው ውጤት በማህረሰቡ ዘንድ አንድ ሰው ከሞተባት (ህይወቱ ካለፈባት) ደቂቃና ዕለት ጀምሮ የሟች የቅርብ ቤተሰቦች ቢያንስ ለአንድ ሳምንት ያህል ከእርሻ ስራቸው ራሳቸውን እንደሚያቅቡ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህም ከOsei (2006፡54) እና ከAdewara (2012:134) የጥናት ግኝቶች ጋር ተደጋጋፊነት ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ግን የስራ እቀባ ቀናቱን ቁጥር በሚመለከት በዚህና በእነሱ የጥናት ውጤቶች መካከል ልዩነት ይስተዋላል፡፡ ለምሳሌ፡- በOsei የጥናት ግኝት ለብዙ ቀናት የሚል እንጅ የቀናቱ ትክክለኛ ቁጥር አልተገለፀም፡፡ የAdewara የጥናት ግኝት ደግሞ ለሁለት ሳምንት ያህል በሚል የቀረበ ነው፡፡

ማህበረሰቡ ለመፈራታቸው የሚሰጠው ምክንያት ይለያይ እንጅ በማህበረሰቡ ውስጥ እንደሞት ሁሉ መካንነትም ተፈሪ ነው፡፡ ቀደም ሲል የማህበረሰቡን የምግብና ተያያዥ ነውሮች እሳቤ ለማብራራት ሲሞከር በማህበረሰቡ ውስጥ መካኖች የተረገሙና ሰውን የሚጎዳ ክፉ አይን ያላቸው ስለሆኑ የጤና መቃወስን ያስከትላሉ ተብለው እንደሚፈሩ ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡ ጉዳዩን ከማህበረሰቡ የሞትና ተያያዥ ነውሮች እሳቤ አኳያ ስንመለከተው ደግሞ መካኖች መውለድ፣ ማፍራት፣ ፍሬ መስጠት ካለመቻል ጋር በተያያዘ ይፈራሉ፡፡ ከመስክ የተሰበሰቡትና በትንተናው የተገኙት ውጤቶች እንደሚያሳዩት በማህበረሰቡ ውስጥ መካኖች በህይወት ሲኖሩ ብቻ ሳይሆን ሲሞቱም ይፈራሉ፡፡

የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ በሆነው ተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ የተለመደው የአቀባበር ስርዓት (የሴትም ሆነ የወንድ) የሟች አስከሬንን ጀርባውን ወደታች ፊቱን ደግሞ ወደ ላይ በማድረግ (በጀርባው በማስተኛት) የሚከናወን ነው፡፡ በጀርባው እንዲተኛ

መደረጉም ሟች ፊቱ ወዳላይ ሆኖ መንፈሱ ከፈጣሪው ጋር እንዲተያይ፣ ወደ ብርሃን እንዲመለከት ያደርጋል ከሚል ነው፡፡ በአጠቃላይም በማህበረሰቡ ውስጥ ሟችን በጀርባው እንዲተኛ አድርጎ መቅበር ሟችን ወደ ፅድቅ መንገድ ይመራዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

መካን ሴቶች ግን በፈጣሪ የተረገሙ ስለሆኑ በሚሞቱበት ጊዜ በአካባቢው የተለመደውን የአቀባበር ልማድ (በጀርባ አስተኝቶ መቅበር) መከተል ድርጊቱ የፈጣሪንና የቅድመ አያቶችን ህግ ከመጣስ ይቆጠራል፡፡ ከዚህ እምነት በተነሳም መካኖች በሚሞቱ ጊዜ ማህበረሰቡ የሚቀብራቸው በልባቸው በመድፋት (ፊታቸውን ወደ ታች በማድረግ) ነው፡፡ ማህበረሰቡ በመካኖች ላይ ከአካባቢው የተለየ የአቀባበር ስርዓትን ለምን ተከተለ? ብለን ስንመረምር ምክንያቱ በሁለት ተደጋጋፊ ሃሳቦች አማካይነት ሊገለፅ ይችላል፡፡ አንደኛው ምክንያት በእነሱ ላይ በአካባቢው የተለመደውን አይነት የአቀባበር መንገድ መከተል ድርጊቱ የፈጣሪንና የቅድመ አያቶችን ህግ መጣስ ስለሆነ የጥሰቱ ውጤት የአካባቢው ሴቶች ሁሉ መካን እንዲሆኑ ያደርጋል ከሚል እምነት የሚመነጭ ነው፡፡ ሌላኛው ምክንያት ደግሞ መካኖች የተረገሙ ስለሆኑ ወደ ብርሃን እንዳያዩ፣ ወደ ፈጣሪ እንዳይመለከቱ በልባቸው ደፍቶ መቅበር ይገባል የሚል እምነትን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በማህበረሰቡ እምነት ሟችን  በልብ ደፍቶ መቅበር ሟችን ወደ ጨለማ፣ ወደ ሲኦል መላክ ተደርጎ ይታመናል፡፡

የማህበረሰቡ የሞት እሳቤ ምን እንደሚመስል ለመግለጽ በተሞከረበት ከዚህ ከፍ ባለው ክፍል ከሞት በኋላ ህይዎት አለ፣ የሞቱ ሰዎች የማዳን ሃይል አላቸው ተብሎ እንደሚታመን ተነስቷል፡፡ መካኖችን በሚመለከት የተሰበሰቡትና የተተነተኑት መረጃዎች እንደሚያሳዩት ግን በማህበረሰቡ ውስጥ መካን ሴቶች የተረገሙ፣ የረከሱ ስለሆኑ ከሞት በኋላ ሌላ ህይዎትም ሆነ የማዳን ሃይል በአጠቃላይም የሙት መንፈስ የሚባል ነገር የላቸውም ተብሎ ይታመናል፡፡ በሌላ አገላለጽ መካኖች ሲሞቱ የሚሞተው ስጋቸው ብቻ ሳይሆን ነፍሳቸውም ጭምር ነው እንደማለት ነው፡፡

*በአጠቃላይ የማህበረሰቡ* ከሞት ጋር የተያያዙ ነውሮች ማህበረሰቡ ስለሞት ያለው ግንዛቤና የሞት ፍርሃት፤ እንዲሁም ስለመካንነት ያለው እሳቤ ምን እንደሚመስል ጠቋሚ እንደሆኑ ከዚህ በላይ በጥቂቱ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ማህበረሰቡ ስለስራና ተያያዥ ነውሮች ያለው እሳቤ ምን እንደሚመስል እንመልከት፡፡

## 8.4 የስራና ተያያዥ ነውሮች እሳቤ

ማህበረሰቡ አንድ ስራ በሚከናወንበት ወይም በሚሰራበት ጊዜና ቦታ ላይ የሚፈፀሙ አንዳንድ ድርጊቶች ድርጊቱን በፈፀመው ግለሰብ ላይም ሆነ በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ አንዳች መጥፎ አጋጣሚን የሚያስከትሉ ናቸው ብሎ እንደሚያምን፤ ከዚህ እምነቱ በመነሳትም ተገቢ ያልሆኑ ለሚላቸው ድርጊቶች ገዥ የሆኑ ነውሮችን ፈጥሮ በእነሱ እንደሚገለገል በትንተናው ከተገኘው ውጤት ለመረዳት ተችሏል፡፡

ማህበረሰቡ ከስራ ጋር በተያያዘ ነውር የሚላቸውን ድርጊቶች ለምን በነውርነት እንደሚፈርጃቸው የራሱን ምክንያት ይሰጣል፡፡ በጥናቱ ግኝት መሰረት ማህበረሰቡ ከስራ ጋር በተያያዘ ነውር ለሚላቸው ድርጊቶች የሚሰጣቸው ምክንያቶች ድርጊቶቹ በረከትን የሚያሳጡ፣ ፍሬ አልባነትን የሚያስከትሉ፣ ድህነትን የሚጠሩ፣ የሚሰራው ስራ እንዳይሰልጥ (እንዳይቀና) የሚያደርጉ ናቸው የሚሉ ናቸው፡፡ ማህበረሰቡ ከሚሰጣቸው ምክንያቶች መካከል ከፍተኛውን ቁጥር ይዞ የሚገኘው (ለጥናቱ ከተመረጡት ጠቅላላ 34 ነውሮች ውስጥ ለ15ቱ የተሰጠ ምክንያት ነው) ድርጊቶቹ በረከትን ያሳጣሉ የሚለው ነው፡፡ ማህበረሰቡ በረከትን ያሳጣሉ በሚል ነውር የሚላቸው ድርጊቶች በዋናነት እህል ከማጨድ፣ ከመከመር፣ ከመውቃት (ከአውድማ ስራ)፣ ከመስፈር ስራ ጋር የተያያዙ ሲሆኑ፤ ከተጠቀሱት የስራ አይነቶች መካከል ነውር የተባሉ ድርጊቶች በስፋት የሚስተዋሉት በአውድማ ስራ (ከ15ቱ ነውሮች ውስጥ 11ዱ) ላይ እንደሆነ የጥናቱ ግኝት ያሳያል፡፡ በመሆኑም ከስራ ጋር በተያያዘ ለሚፈጠሩ ነውሮች ማህበረሰቡ የሚሰጠው ምክንያት ለምን በረከት ላይ እንዳተኮረና ለምንስ ከአውድማ ስራ ጋር የተያያዙ ነውሮች እንደበዙ እዚህ ቦታ ላይ የተወሰነ ማብራሪያ ላቅርብ፡፡

በማህበረሰቡ ዘንድ "በረከት" የሚለው ቃል የበዛ፣ መጠኑ የጨመረ፣ የተትረፈረፈ የሚል ትርጉም የያዘ ነው፡፡ በእርሻ ስራ የሚተዳደር አንድ አርሶ አደር የስራው ውጤታማነት የሚለካው መሬቱን አርሶና አለስልሶ፣ ዘርቶ፣ አርሞ፣ እንዲሁም አጭዶና ሰብስቦ በመውቃቱ ሳይሆን ይሄ ሁሉ ስራ በቅደም ተከተል ከተከናወነ በኋላ መጨረሻ ላይ ምን ያህል ምርት አስገባ በሚለው ነው፡፡ በመሆኑም ብዙ የደከመበት እህል የመጨረሻ ውጤቱ የበረከተ፣ ሙሉ ቤተሰቡን የሚያጠግብና ከተቻለም ከቤተሰቡ ተርፎ ለገበያ የሚውል ከሆነ ለአርሶ አደሩ ከዚህ የበለጠ ደስታ የለውም፡፡ በዚህ ምክንያትም ማህበረሰቡ እህልን ከማጨድ እስከ

መውቃትና መስፈር ድረስ የሚፈፀሙ አንዳንድ ድርጊቶች የሚመረተውና ወደ ቤት የሚገባው እህል በረከት ረድኤት እንዳይኖረው ምክንያት ይሆናሉ የሚል እምነት አለው፡፡ ስለሆነም እንደነዚህ አይነት ድርጊቶችን ላለመፈፀም፣ ሌሎችም እንዳይፈፅሟቸው ለማድረግ ጥረት ያደርጋል፡፡ የማህበረሰቡን የበረከት እሳቤ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ እስኪ ማህበረሰቡ ለ "ሙሉነት"፣ "ንፅህና"ና "ግብግ" የሚሰጠውን ትርጉም በአጭሩ እንመልከት፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ሙሉ የሆነ ነገር ሁሉ የመትረፍረፍና የመጨመር ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በአንፃሩ ከጅምሩ ሳይሞላ ወይም ሳይቋጭ የቀረ፣ ያልተደፈነና ከመነሻው የጎደለ ነገር ሁሉ የመጨረሻ ውጤቱም የጎደለ፣ ያነሰ፣ ረድኤት ያጣ ነው፡፡ ከዚህ ተነስቶም ማህበረሰቡ እንዲሞላ ተደርጎ ያልተከመረ እህል ከላዩ ላይ ክፉ መንፈስ ስለሚያድርበት በሚወቃበት ጊዜ እህሉ በረከት አይኖረውም ብሎ ስለሚያምን የታጨደ እህሉን በሚከምርበት ጊዜ እንዲሞላ አድርጎ በጥንቃቄ ይከምራል፡፡

ይሁን እንጅ ማህበረሰቡ ለበረከት ማጣት መንስኤ የሚያደርገው እህልን ሳይሞሉ መከመር ብቻ አይደለም፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ለእህል በረከት ማጣት ከሁሉም በላይ ትልቅ መንስኤ ተደርጎ የሚወሰደው ከአውድማ ስራ ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ ድርጊቶች ናቸው፡፡ አውድማ ማህበረሰቡ አንድን ምርት ለማግኘት ያወጣውን የጊዜ፣ የጉልበትና የገንዘብ ውጭ የሚያወራርድበት ቦታ ስለሆነ ከሁሉም የስራ አይነቶቹ በተለየ ሁኔታ ትልቅ ቦታና ክብር ይሰጠዋል፡፡ ለእሱ ከሚሰጠው ትልቅ ቦታ በመነሳትም ማህበረሰቡ ክፉ መንፈስ ይፈታተናቸዋል ብሎ ከሚያምንባቸውና ልዩ ጥበቃ ከሚያደርግላቸው የስራ አይነቶች መካከል የአውድማ ስራ ቀዳሚው ነው፡፡ ይሄን ጉዳይ እስኪ ማህበረሰቡ ለንፅህና ከሚሰጠው ትርጉም አኳያ እንመልከተው፡፡

በማህበረሰቡ አስተሳሰብ ለእህል በረከት ማግኘትም ሆነ ማጣት ወደ አውድማ ውስጥ የሚገቡ ሰዎች የንፅህና ሁኔታ የሚወስን ሲሆን፣ ንፁህ ያልሆኑ ነገሮች ደግሞ የመጥፎ መንፈስ ማደሪያዎች ናቸው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ማህበረሰቡ ንፁህ አይደሉም በሚል ወደ አውድማ እንዳይገቡ ከሚከለክላቸው ሰዎች መካከል ጫማ የለበሱ፣ የግብረ ስጋ ግንኙነት የፈፀሙ (በማህበረሰቡ አባባል ጥላ የሆኑ) እና ሴቶች ይጠቀሳሉ፡፡ ማህበረሰቡ ለንፅህና የሚሰጠውን ትርጉም ለምሳሌ ያህል ከሴቶች አኳያ እንመልከተው፡፡ ሴት ልጅ በተፈጥሮዋ ንፁህ ያልሆነችና በረከትም የሌላት ተደርጋ ትሳላለች፡፡ ማህበረሰቡ ለንፅህና ተፈጥሯዊ የሆነውን የሴቶች ፀጋ (የወር አበባን) እንደ ምክንያት ያነሳል፡፡ በረከት ማጣትን ደግሞ

ሔዋን አዳምን ባሳተችው ጊዜ ያየሸው፣ የነካሽው ሁሉ አይባረክልሽ - ተብላ ተረግማለች ከሚል ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ጋር ያያይዘዋል፡፡ በመሆኑም የተጠቀሱት አይነት ሰዎች አውድማ ውስጥ እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም - ባጋጣሚ ከገቡም አውድማ ላይ ያለው ምርት በረከት እንዲያጣ ያደርጋሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

በመረጃ ትንተናው የተገኙ የጥናቱ ውጤቶች እንደሚያሳዩት በማህበረሰቡ ውስጥ አውድማ ላይ የሚደረገው የግብዣ ስርዓትም የምርትን የመበርከትም ሆነ ያለመበርከት ሁኔታ ይወስናል፡፡ ለአውድማ ተብሎ የተዘጋጀ እህል ውሃን የስራው ተሳታፊዎች ያልሆኑና በአካባቢው የሚያልፉ ሰዎች ሁሉ እንዲቀምሱ ይፈለጋል፡፡ ምክንያቱም ለአውድማው የተዘጋጀው እህል ውሃ በአካባቢው የሚያልፉ ሰዎችን ስለሚሸታቸው ከእሱ ሳይቀምሱ ከሄዱ የምርቱን በረከት ይዘውት ይሄዳሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህም ምክንያት አውድማ የጣለ (ያዘጋጀ) ሰው በአካባቢው የሚያልፉ ሰዎችን ሁሉ (ጠላቶቹም ቢሆኑ) እየጠራ ከተዘጋጀው እህል ውሃ እንዲቀምሱ ያደርጋል፡፡ በአካባቢው የሚያልፉ ሰዎችም ባለአውድማውን የማይወዱትም ቢሆኑ የሰው በረከት ይዛችሁ ሄዳችሁ ስለሚባሉ ግብዣውን እንደማይቃወሙ በጥናቱ ማየት ተችሏል፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ለበረከት ማጣት መንስኤ ተደርጎ የሚታሰበው ሌላኛው ጉዳይ ከበኣላት ቀናትና ወራት እሳቤ ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው፡፡ በኣል በዋናነት የሚከበር፣ ስራ የማይሰራበትና ታርፎ የሚዋልበት ቀን የሚል ትርጎም የያዘ ነው፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳው ተጠኝው ማህበረሰብ በወር ውስጥ ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ ቢያንስ 11 አካባቢ የሚሆኑ የበኣላት ቀናት አሉት፡፡ ይህ ወደ ዓመት ሲቀየር ማህበረሰቡ 132 አካባቢ የሚሆኑ የበኣላት ቀናት አሉት፡፡ ይህ የአብክመ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ (2001፡26) ባሳተመው መጽሃፍ ከተገለፀው የበኣላት ቁጥር ጋርም ተመሳሳይነት አለው፡፡ ማህበረሰቡ በእነዚህ የበኣላት ቀናት የሚከናወን ስራ ድርጊቱ ፈጣሪን የሚያስቀይም ስለሆነ አካባቢውን በረድ ያስመታል፣ ድርቅ ያስከትላል በአጠቃላይም የተሰራውን ስራ ፍሬ አልባ ያደርጋል የሚሉ ለዘመናት ሰርፀው የኖሩ እምነት መራሽ ልማዶች አሉት፡፡ በማህበረሰቡ እምነት እንኳን በበኣል ቀን የተሰራ ስራ ይቅርና በበኣል ቀን (በተለይም በሰንበት) የተፀነሰ ልጅ እንኳ ሽፍታ፣ ገዳይ፣ ባህሪው ከሰው የማይገጥም ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለዚህ በማህበረሰቡ ውስጥ በበኣል ቀን ስራ መስራት ብቻ ሳይሆን የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም

እንኳ ይከለከላል፡፡ ማህበረሰቡ "ያም ሽሮ የፀደቀ - በአል ሽሮ የከበረ የለም" የሚል የተለመደ አባባሉን በመጠቀምም በበኣል ቀን የሚከናወን ስራን አጥብቆ ያወግዛል፡፡

ከዚህ ተነስቶም ማህበረሰቡ በኣላት በሚላቸው ቀናት የማያከናውናቸውና ሌሎችም እንዲያከናውኗቸው የማይፈቅዳቸው የስራ አይነቶች ያሉት ሲሆን፤ ከስራ አይነቶቹ መካከልም ማረስ፣ መዝራት፣ ማጨድ፣ ማረም፣ ዛፍ መቁረጥ፣ ቤት መስራት፣ መፍጨትና መውቀጥ (መሸክሸክ) ዋነኞቹ እንደሆኑ ከትንተናው ከተገኘው ውጤት ለመረዳት ተችሏል፡፡ እዚህ ላይ ግን በተለይም ሃይማኖታዊ መሰረት ያላቸውን በኣላት አስመልክቶ በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚነሳ አንድ ጉዳይን በአጭሩ ማንሳት ይገባል፡፡

ለምሳሌ ያህል፡- የአብክመ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የአማራ ህዝብን ባህልና ቋንቋ አስመልክቶ ያሳተመውን መጽሃፍ (2001፡26) ብንመለከት በተለይም የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖትን መሰረት ያደረጉ የበኣላት ቀናት ቁጥራቸው የበዛ እንደሆነና ይህም በእምነቱ ተከታዮች የስራ ባህልና ምርታማነት ላይ ትልቅ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ እንደሆነ የሚገልፅ ነው፡፡ ይህ ሃሳብ በሌሎች አንዳንድ ጸሃፍትም የሚደገፍ ሃሳብ ነው፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ ጥናት የታየው ተጠኝው ማህበረሰብ በኣላት በሚላቸው ቀናት ፈፅሞ ስራ አያከናውንም ማለት እንደማይቻል ነው፡፡

በጥናቱ እንደታየው ማህበረሰቡ በአላት በሚላቸው ቀናት እንስሳትን የመንከባከብ፣ አጥር የማጠር፣ አዝመራ የመጠበቅ፣ አረሞ የማውጣት፣ ቦይ የማፋሰስ (ጎርፍ የመከላከል)፣ የታጨደ እህልን የመሰብሰብ፣ የመከመር፣ አውድማ የማዘጋጀትና ለመወቃት የደረሰ አዝመራን ወደ አውድማ በሸክም የማጓጓዝ፣ በሽተኛ የመጠየቅ፣ ገበያ ወጥቶ ለቤት የሚያስፈልግ ነገር የመግዛት፣ ዘመድ የመጠየቅ፣ ለእስረኛ ስንቅ የማቀበልና የመሳሰሉ ስራዎችን ያከናውናል፡፡ ከዚህም በላይ እናቶች በስራ ቀን ከሚሰሩት የበለጠ ታላላቅ ስራዎችን የሚሰሩት (ለምሳሌ፡- የተለያየ የምግብና የጠላ ዝግጅት) በበኣላት ቀናት ነው፡፡ ስለዚህ ገበሬው በበኣላት ቀናትም አርፎ አይውልም፤ በበኣላት ቀናት የሚሰራቸው ከፍ ሲል የተጠቀሱት ስራዎችም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከምርትና ምርታማነት ጋር የተገናኙ ናቸው፡፡ በመሆኑም የበኣላት ቁጥር መብዛትን እንደ ጎጅ ባህል የማየትና የድህነታችንም ብቸኛ መንስኤ አድርጎ የመመልከት አስተሳሰብ የአርሶ አደሩን የበኣል አከባበር በቅጡ ካለመገንዘብ የሚነሳ ይመስለኛል፡፡ በመሆኑም እንደ እኔ የበኣላትን ቁጥር መብዛት ከመኮነን ይልቅ አከባበራቸውን በማስተማር ማስተካከል የተሻለ የሚሆን ይመስለኛል፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ እህል እንዳይበረክት ምክንያት ይሆናል ተብሎ የሚታመንበት ሌላኛው ጉዳይ ማህበረሰቡ ስለወራት ካለው እሳቤ የሚመነጭ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ሁሉም ወራቶች ለስራ ተመራጭ አይደሉም፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በተለይም ታህሳስና ጥር ወሮች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚወቃው እህል ውጤቱ የማያምር፣ በመብዛት ፋንታ መቀነስን የሚያሳይ እንዲሆን ያደርጋሉ ተብለው ይታሰባሉ፡፡ ከሌሎች ወሮች በተለየ ለምን እነዚህ ወሮች እንዲህ አይነት ግምት ተሰጣቸው? ስንል የጥናቱ ውጤቶች የሚያሳዩት የግምቱ መነሻ ሃይማኖታዊ አንድምታ ያለው መሆኑን ነው፡፡ እነዚህ ወሮች በኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ሁለት አበይት ክብረ በአላት (በየአመቱ ታህሳስ 19 የሚከበረው የታህሳስ ገብርኤል ክብረ በኣል እና በየአመቱ ጥር 11 የሚከበረው የጥምቀት ክብረ በአል) የሚከበሩባቸው ናቸው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ገብርኤል እሱን የማያከብሩ ሰዎችን ምርት ወስዶ እሱን ከሚያከብሩ ሰዎች ምርት ጋር ይቀላቅላል፤ ጥምቀት ከተከበረ (ባህረ መስቀል ከተባረከ) በኋላ የሚወቃ እህልም ባህር ይወስደዋል - እብቅ ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ ጉዳይ የማህበረሰቡን የሃይማኖት እሳቤም በተወሰነ መልኩ ሊያሳይ የሚችል ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የተጠቀሱት ወሮች በማህበረሰቡ ዘንድ በተለይም ለአውድማ ስራ የሚመረጡ አይደሉም፡፡ ይህም አንዳንድ ወሮች ስራ የማይሰራባቸው እንደሆኑ ካሳዩት ከእነ Stifel et al. (2011፡2) ጥናት ውጤት ጋር የተወሰነ የመቀራረብ ሁኔታ ያሳያል፡፡ ስራ ለማይሰራባቸው ወሮች ከሚሰጡ ምክንያቶች አኳያ ግን የሁለቱ የጥናት ግኝቶች የተለያዩ ናቸው፡፡

በመረጃ ትንተናው የተገኙ ውጤቶች እንደሚያሳዩት የማህበረሰቡ የመካንነት እሳቤ ከምግብና ሞት ጋር ብቻ ሳይሆን ከስራ ጋርም ይያያዛል፡፡ የማህበረሰቡ የምግብና የሞት እሳቤ በተነሳበት ከፍ ባለው ክፍል እንደተገለጸው በማህበረሰቡ ውስጥ ሰዎች መካን የሚሆኑት የተረገሙ ስለሆኑ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይሁን እንጅ በማህበረሰቡ ውስጥ አንዳንድ የስራ አይነቶችም መካን ለመሆን እንደ መንስኤ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በቤት ውስጥ ያለን የሸረሪት ድር መጥረግ ጠራጊዎቹ መካን እንዲሆኑ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም የሸረሪት ድሩ መጠረግ ካለበት እንኳ ወልደው ያበቁ ወይም በፊቱንም መካን የሆኑ ሰዎች ተፈልገው እንዲጠርጉት ይደረጋል እንጅ ገና ያልወለዱና ወልደው ያልጨረሱ ሰዎች እንዲጠርጉት አይፈለግም፡፡

ተጠኝው የሊቦ ከምከም ማህበረሰብ ስለነውር ያለውን ግንዛቤና የሚሰጠውን ፍች፤ እንዲሁም ስለምግብ፣ ሞት፣ ስራና ተያያዥ ነውሮች ያለውን እሳቤና ነውር ለሚላቸው ጉዳዮች የሚሰጣቸውን ምክንያቶች በሚመለከት ከዚህ በላይ አጭር የውጤት ትንተናና ትርጎማ ለመስጠት ተሞክሯል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የማህበረሰቡን ነውሮች ሚና የሚመለከት አጭር የውጤት ትንተናና ትርጎማ ቀርቧል፡፡

## 8.5 የነውሮች ሚና

ነውሮች ተጠኝው ማህበረሰብ የአባላቱን እምነትና ባህሪ የሚቀርፅባቸው፤ ስጋዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶቹን ለማርካት የሚያስችለውን እውቀትና ክሂል የሚያስታጥቅባቸው፤ የአባላቱን አስተሳሰብ፣ ስሜትና ባህርይ የሚገዛባቸው ወይም የሚወስንባቸውና በአጠቃላይም ለአኗኗሩ መርህ፣ ለግንኙነቱ ደንብና ህግ አድርጎ የሚገለገልባቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ነውሮችን ያለ አንዳች ምክንያት አይፈጥራቸውም - ከዚህ ተነስቶም አዎንታዊ እንጅ አሉታዊ ገፅታ ይኖራቸዋል የሚል እምነትም የለውም፡፡ ማህበረሰቡ ነውሮችን ያላንዳች ምክንያት አይፈጥራቸውም - አሉታዊ ገፅታ ይኖራቸዋል ብሎም አያምንም ሲባል ግን ሁሉም ነውሮች አዎንታዊ ሚና ብቻ ያላቸው ናቸው ለማለት አይቻልም፡፡ በትንተናው የተገኙ የጥናቱ ውጤቶች እንደሚያሳዩት የማህበረሰቡ ነውሮች አዎንታዊም አሉታዊም ሚና ያላቸው ናቸው፡፡

በመሆኑም በዚህ ክፍል ከማህበረሰቡ የተሰበሰቡና የተተነተኑ የተወሰኑ ነውሮችን ዋቢ በማድረግ በነውሮች አዎንታዊና አሉታዊ ሚና ዙሪያ የውጤት ትንተናና ትርጎማ ለማካሄድ ተሞክሯል፡፡ ይሄ ሲባል ግን የማህበረሰቡ ነውሮች ያላቸው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ሚና ከዚህ በታች የቀረበው ብቻ ነው፤ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ሚና ያላቸው የማህበረሰቡ ነውሮችም ከዚህ በታች የቀረቡት ብቻ ናቸው ማለት አይደለም፡፡ በትንተናው በተገኘው ውጤት መሰረት ብዙዎቹ የማህበረሰቡ ነውሮች መንታ (በአንድ በኩል አዎንታዊ በሌላ በኩል ደግሞ አሉታዊ) ሚና ያላቸው ናቸው፡፡ ይህም በዘርፉ ዙሪያ ከተደረጉ አንዳንድ የጥናት ግኝቶች ለምሳሌ፦ ከFershtman et al (2011: 140) የጥናት ግኝት ጋር ይደጋገፋል፡፡

ስለሆነም በዚህ ክፍል ውስጥ ከዚህ በታች ለማድረግ የተሞከረው የተወሰኑትን ነውሮች በመውሰድና ጎልቶ ከሚታይ አንድ ሚናቸው አኳያ በመዳሰስ ነውሮች ሊኖራቸው

የሚችለውን የተወሰነ አወንታዊና አሉታዊ ሚና ማሳየት ነው፡፡ በዚሁ መሰረትም ከዚህ ቀጥሎ የነውሮችን አዎንታዊ ሚና ያስቀደመና አሉታዊ ሚናቸውን ያስከተለ አጭር የውጤት ትንተናና ትርጎማ ቀርቧል፡፡

ማህበረሰቡ ነውሮችን የሚፈጥራቸው በዋናነት ከጤና መታወክ፣ ከድርቅ፣ ከውግዘት፣ ከሞት፣ ከመካንነት፣ ከንፅህና ጉድለት፣ ከሃዘን ስሜት፣ ከበረከት ማጣትና ከፍሬ አልባነት ወዘተ. ይታደጉኛል በሚል እንደሆነ ቀደም ሲል በተለያዩ የጥናቱ ክፍሎች ውስጥ ተነስቷል፡፡ ይሁን እንጅ ማህበረሰቡ እነሱን በመፍጠሬ አገኛቸዋለሁ ከሚላቸውና ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ጉዳዮች በሻገር ያለው የማህበረሰቡ ነውሮች ሚና ሲመረመር በርካታ አዎንታዊ ሚና ያላቸው ናቸው፡፡ የተወሰኑትን ለምሳሌ ያህል ቀጥሎ እንመልከት፡፡ የማህበረሰቡ ነውሮች ለፈጥራቸውም ሆነ እነሱን ተቀብሎና አክብሮ ለሚኖረው የአካባቢው ማህበረሰብ ራስን ከአደጋና በሽታ የመከላከል፣ መልካም ምግባርን የመቅረፅ፣ ሃይማኖታዊ ዶግማን የማስከበርና የማስቀጠል፣ መተሳሰብና መቻቻልን የማጎልበት፣ የአካባቢ መራቆትን የመከላከል፣ ውስጣዊ ሰላምን የመፍጠር፣ ባህልን የመጠበቅ ወዘተ. አዎንታዊ ሚና ያላቸው ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ እስኪ የነውር አዎንታዊ ሚናዎች ናቸው ያልናቸውን እነዚህን ጉዳዮች በተወሰኑ ምሳሌዎች እያስደገፍን ከዚህ ቀጥሎ በአጭር በአጭሩ እንመልከታቸው፡፡

## ራስን ከአደጋና በሽታ የመከላከል ሚና

የማህበረሰቡን አንዳንድ ነውሮች ስንመለከት ለምሳሌ፡- እየበሉ ማውራትና መሳቅ፤ አብዝቶና ቶሎ ቶሎ መጉረስ፤ ከቀብር መልስ እጅን ሳይታጠቡ ማንኛውንም ነገር ማከናወንና ሌላ ሰውን መንካት የመሳሰሉት የተነወሩ ድርጊቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም የመጀመሪያዎቹን ሁለት ነውሮች ስንመለከት ተመጋቢዎቹ ከሚከተሉት የአመጋገብ ስርዓት ጋር በተያያዘ ሊደርስባቸው ከሚችል የመታነቅ (ሲበሉ ትን የማለት)፣ የበሉት ምግብ አልስማማ የማለትና መሰል ችግሮች ራሳቸውን እንዲከላከሉ የሚያግዙ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ሶስተኛውን ነውር ስንመለከትም ሰዎች የግል ንፅህናቸውን በመጠበቅ ራሳቸውንና ሌሎችን እጅን ካለመታጠብ ሊመጣ ከሚችል በሽታ እንዲጠብቁ የማድረግ ሚና ያለው ነው፡፡

## መልካም ምግባርን የመቅረፅ ሚና

የማህበረሰቡ አንዳንድ ነውሮች ደግሞ ህፃናትን በማህበረሰቡ ወግ ልማድ መሰረት ኮትኩቶ ለማሳደግ አጋዥነት ያላቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ፦ ለህፃናት ከአዋቂዎች ጋር በአንድ ሞሰብ መብላት፣ ከአዋቂዎች በላይ ተቀምጦ መብላት የተነወሩ ድርጊቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም እነዚህ አይነት ነውሮች በልጆች የአስተዳደግ ነፃነት ላይ የተወሰነ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖራቸው የሚችል ቢሆንም ልጆች ታላላቆቻቸውንና ወላጆቻቸውን የሚያከብሩ፣ በመልካም ምግባር የታነፁ እንዲሆኑ በማስቻል ደረጃ የራሳቸው አዎንታዊ ሚና ይኖራቸዋል ማለት ይቻላል፡፡

## ሃይማኖታዊ ዶግማን የማስከበርና የማስቀጠል ሚና

የማህበረሰቡ አንዳንድ ነውሮች ደግሞ ራስን ከአደጋና በሽታ በመከላከል፣ ህፃናትን በመልካም ምግባር በመቅረፅ ረገድ ብቻ ሳይሆን ማህበረሰቡ የሚከተለውን የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት በማስከበርና በማስቀጠል ረገድም አዎንታዊ ሚና የሚጫወቱ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፦ በማህበረሰቡ ውስጥ ተባርከው ያልታረዱ የቤት እንስሳትን መመገብ፣ ለማህበር የተዘጋጀ ምግብን ቄስ ሳይባርከው መመገብ፣ ክርስትና ያልተነሳ ህፃንን በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ውስጥ መቅበር የተነወሩ ድርጊቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም እነዚህ ነውሮች የአካባቢው ማህበረሰብ የሚከተለውን የሃይማኖት ዶግማ ተከትሎና የቀደምቶቹን ወግ ልማድም አክብሮ እንዲቀጥል በማድረግ ረገድ አዎንታዊ ሚና ያላቸው ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

## መተሳሰብና መቻቻልን የማጎልበት ሚና

የማህበረሰቡ አንዳንድ ነውሮች የማህበረሰቡ እርስበርሳዊ ግንኙነት የተጠናከረና የጎለበተ እንዲሆን ለማድረግ ጉልህ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ ናቸው፡፡ ይህን ከመስክ በተሰበሰቡት ነውሮች አማካኝነት ብንመለከተው ለምሳሌ ፦ የሞተ ሰው ሳይቀበር መሳሳም፣ የእጅ ሰላምታ መሰጣጠት በማህበረሰቡ ውስጥ የተነወረ ድርጊት ነው፡፡ ይህ መሆኑም የአካበቢው ማህበረሰብ ለሟች ቤተሰቦች ያለውን ድጋፍ የሚገልፅበት፣ ሃዘናችሁ የእኔም ስለሆነ በእናንተ ለቅሶ ላይ እኔ ልደሰት አልችልም የሚል መልዕክት የሚያስተላልፍበት ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ነውር የአካባቢውን ማህበረሰብ የመተሳሰብና የመተዛዘን ባህል ያጎለብታል፡፡ በማህበረሰቡ

ውስጥ ከሌላ ድንበርተኛ ጥግ ያለን እህል ጨርሶ ማጨድም የተከለከለ ተግባር ነው፡፡ ይህ መሆኑም በማህበረሰቡ መካከል ድንበሬን ገፋህ፣ እህሌን ጨምረህ አጨድክ በሚል ሊፈጠር ከሚችል አለመግባባት በመታደግ በመጋጨት ፋንታ መፋቀርን በማስፋት የማህበረሰቡን የመደጋገፍና የመቻቻል ባህል ይበልጥ ሊያጠናክር ይችላል፡፡

ለአውድማ ስራ ተብሎ ከቤት ወደ አውድማ የሄደን እህል ውሃ በአካባቢው ለሚያልፍ ሰው (የተጣሉት ሰውም ቢሆን) ሳያቀምሱ ዝም ብሎ ማሳለፍም በማህበረሰቡ ዘንድ ነውር ነው፡፡ ይህ ነውር በማህበረሰቡ ውስጥ የመቻቻል መንፈስን በመዝራት በአንድ አጋጣሚ ተጣልተውና ለአስታራቂም አስቸግረው የነበሩ ሰዎችን ሊያቀራርብና ይቅር ባይነትንም ለሌሎች ሊያስተምር የሚችል ነው፡፡ ስለዚህ ነውሮች የማህበረሰቡ መልካም የሚባሉ ነባር ምግባራዊ ደምቦች እንዲከበሩ የማድረግ፣ የአካባቢውን ሰላም የመጠበቅ ቁልፍ ሚና አላቸው፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩትም ወንጀልን በመከላከልና ሰላምን በማስፈን ረገድ ሃገራት ከሚመድቡት የፀጥታ ሃይል የላቀ ነውሮች ሚና አላቸው፡፡ ለምሳሌ፡- Omobola (2013: 223) ጥናት ባካሄዱበት የናይጀሪያዎቹ የዩርባ ጎሳዎች ውስጥ ነውሮች ሞራላዊ እሴቶችንና ሰላምን የማስጠበቅ ቁልፍ ሚና ስላላቸው - በዛ ማህበረሰብ ዘንድ ፖሊስና የፖሊስ አገልግሎት እንደሌለ ይገልፃሉ፡፡

## የአካባቢ መራቆትን የመከላከል ሚና

አንድ ሰው ሞቶ ከተቀበረ በኋላ ከመቃብሩ ላይ ዛፍ ወይም ቅጠል ሳይተክሉ መመለስ በማህበረሰቡ ልማድ መሰረት የተከለከለ ነው፡፡ ይህ ክልከላ ቢያንስ የቀብር ስፍራዎች በደን እንዲሸፈኑ የሚያደርግ ስለሆነ የአካባቢውን ስነ ምህዳር በመጠበቅ ረገድ የራሱ የሆነ የጎላ ሚና ይኖረዋል፡፡ በአካባቢው የጎላ ተፈጥሯዊ ገፅታ ያላቸውን ቦታዎች (ለምሳሌ፡- ትልልቅ ወንዞች፣ ሃይቆች፣ ጫካዎች፣ ዋሻዎች) ተጠግቶ ማረስ፣ ለተለየ ግላዊ አገልግሎት ማዋል በነውርነት የተፈረጀ ተግባር ነው፡፡ በአካባቢው ለረጅም ዘመናት የኖሩ እንደ ዋርካ ያሉ ትልልቅ ዛፎችን መቁረጥም ነውር ነው፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ *የአካባቢው ተፈጥሯዊ ገፅታ እንዲከበርና ጥንተ መልኩን ሳይለውጥ እንዲቀጥል የሚያደርግ ስለሆነ በተወሰነ መልኩም ቢሆን አካባቢውን ከመራቆትና ከበረሃማነት ሊታደግ የሚችል ነው፡፡ ሃገር በቀልና ነባር የሆኑ የእፅዋት ዝርያዎች እንዲጠበቁ በማድረግ ረገድም የራሱ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ የ*

Yeshambel (2013፡12) *የጥናት ግኝትም ነውሮች የአካባቢ ተፈጥሮን በመንከባከብ ረገድ ከፍተኛ የሆነ ሚና እንዳላቸው የሚገልፅ ነው፡፡*

## ውስጣዊ ሰላምን የመፍጠር ሚና

የማህበረሰቡ አንዳንድ ነውሮች ደግሞ ለሚፈጥራቸውም ሆነ እነሱን ተቀብሎና አክብሮ ለሚኖረው የአካባቢው ማህበረሰብ ውስጣዊ ሰላም የመስጠት አዎንታዊ የሆነ ሚናም አላቸው፡፡ ለዚህም ማህበረሰቡ ነውሮችን የሚፈጥርባቸውን ምክንያቶች በማሳየት እንመልከት፡፡ ማህበረሰቡ ነውሮችን የሚፈጥራቸውና የሚያከብራቸው በዋናነት በህይወቴ ላይ የጤና መታወክን ያስከትሉብኛል፣ ሞትን ወደ እኔ ይጠሩብኛል፣ በብዙ ድካም ያከናወንኩት ስራ ውጤታማ እንዳይሆን ያደርጉብኛል የሚላቸውን ድርጊቶች ለመከላከል ነው፡፡ ስለሆነም ማህበረሰቡ አይበጁኝም ለሚላቸው ድርጊቶች ነውሮችን መደንገጉና እነሱንም ማክበሩ የተጠቀሱት አይነት ችግሮች የእኔም ሆነ የአካባቢዬ ስጋቶች አይሆኑም የሚል መንፈሳዊ ድልንና ስነልቡናዊ መረጋጋትን ይፈጥርለታል፡፡

በጥናቱ እንደታየው በማህበረሰቡ ውስጥ የሟች የቅርብ ቤተሰቦች በመቃብሩ ላይ አፈር ሳይረጩ ወደ ቤታቸው አይመለሱም፤ ከቀብር መልስ ከፍተኛ የሆነ የለቅሶ ድምፅና የመረረ ሃዘንም አይፈቀድም፡፡ እነዚህ ነውሮች በራሳቸው ለአካባቢው ማህበረሰብ ውስጣዊ ሰላምን የመስጠት ሚና አላቸው፡፡ ምክንያቱም የሟች የቅርብ ቤተሰቦች በመቃብሩ ላይ አፈር የሚረጩት አፈር መርጨት ሟችን በቀላሉ ለመርሳት ያስችላል ከሚል እምነት ተነስተው ነው፡፡ ስለሆነም የሟች ቤተሰቦች በቀብር ላይ ተገኝተን አፈር መርጨታችን ሟችን በቀላሉ እንድንረሳ ይረዳናል የሚል ተስፋን በውስጣቸው ስለሚያሳድሩ የደረሰባቸውን ሃዘን በቀላሉ ለመርሳትና ተረጋግተው ወደ ተለመደው ዘወትራዊ የኑሮ ሂደታቸው ለመመለስ ይሄ ነውር ሊያግዛቸው ይችላል፡፡ በአካባቢው ከቀብር መልስ ከፍተኛ የሆነ የለቅሶ ድምፅና የመረረ ሃዘን የማይፈቀደውም በማህበረሰቡ ዘንድ ሟች ከተቀበረ በኋላ ቤተሰቦቹን ለመጎብኘት ሲመጣ (ከሞት በኋላ ህይዎት ስላለ) የተጠቀሱትን ነገሮች ካየ ዳግም አይመጣም የሚል እምነት ስላለ ነው፡፡ ስለሆነም ይሄ ነውር ለአካባቢው ማህበረሰብ ቢያንስ ሁለት ጠቀሜታዎች ሊኖሩት ይችላል፡፡ አንደኛው ጠቀሜታ ከቀብር መልስ የመረረ ሃዘን የተከለከለ መሆኑ የሟች የቅርብ ቤተሰቦች ብዙም ሳይጎዱ ሟችን በቀላሉ ለመርሳት ሊያግዛቸው ይችላል፡፡ ሁለተኛው ጠቀሜታ ደግሞ ከሞት በኋላ ህይዎት አለ ተብሎ

መታመኑ ሟችን በአካል ባያዩትም በመንፈስ ግን ሁሌም እንደሚጎበኛቸውና ካጠገባቸውም እንዳለ እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህም ሞት ተስፋ እንዳያስቆርጣቸው የሚያደርግ ውስጣዊ የመንፈስ ጥንካሬን ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

**ባህልን የመጠበቅ ሚና**

በጥናቱ እንደታየው ተጠኚው ማህበረሰብ ከለመደውና ከሚያውቀው ውጭ ሆኖ የተፈጠረ ወይም ያጋጠመ ነገር ውጤቱ መልካም አይሆንም ብሎ ያምናል፡፡ ስለሆነም ወቅታዊ የሆኑ አዳዲስ ባህሎችንና የአኗኗር ዘይቤዎችን ለመቀበል ይጠላል፡፡ በአንፃሩ ግን ለዘመናት በአካባቢው የቆዩ ልማዶችን የማስቀጠል ከፍተኛ ፍላጎት ያለው ሲሆን፤ ለቆዩ ልማዶቹ ማስቀጠያም አመች የሚላቸውን ነውሮች እየፈጠረ በእነሱ አማካይነት ወጣቱን ትውልድ ያስተምራል፡፡ በዚህም መልካም የሚላቸው ነባር ምግባራዊ ደምቦች እንዲከበሩ ይጥራል፡፡

በመሆኑም የባህል ተለዋዋጭነት የሚጠበቅና አይቀሬ ቢሆንም ማህበረሰቡ የሚፈጥራቸው ነውሮች ባህልን በመጠበቅ፣ በማስቀጠልና ልቅ የሆነ የባህል ወረራን በመከላከል ረገድ በጎ ሚና ይኖራቸዋል ማለት ይችላል፡፡ Patrick, A (2015: 1)ም ነውሮች ነባር የሆኑ ወይም የቆዩ ልማዶችን የመጠበቂያ መሳሪያ በመሆን እንደሚያገለግሉ ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ የማህበረሰቡ ነውሮች ሊኖሯቸው ከሚችሉ አዎንታዊ ሚናዎች መካከል የተወሰኑትን ከዚህ በላይ በአጭሩ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ ከዚህ በማስከተል ደግሞ የማህበረሰቡ ነውሮች ሊኖሯቸው ከሚችሉ አሉታዊ ሚናዎች መካከል የተወሰኑት በማሳያነት ቀርበዋል፡፡

ተጠኚው ማህበረሰብ ነውሮችን የሚፈጥራቸው አብሮነቴን አጠናክርባቸዋለሁ፣ ሰላሜን አስጠብቅባቸዋለሁ፣ ሊደርስብኝ ከሚችል አንዳች ችግር ራሴንና አካባቢዬን እከላከልባቸዋለሁ የሚል ግንዛቤን በመያዝ ነው፡፡ በመሆኑም የምፈጥራቸው ነውሮች ይጠቅሙኛል እንጅ የጎንዮሽ ጉዳትም ሊያስከትሉብኝ ይችላሉ የሚል ጥርጣሬም፣ እምነትም እንደሌለው በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ውስጥ በተለያየ አጋጣሚ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጅ ማህበረሰቡ እነሱን በመፍጠሬ አገኛቸዋለሁ ከሚላቸው ጠቀሜታዎች በሻገር ያለው የነውሮች ሚና ሲመረመር ግን የማህበረሰቡ አንዳንድ ነውሮች አሉታዊ ሚናም ያላቸው ናቸው፡፡ ከአሉታዊ ሚናዎቻቸው መካከል የተወሰኑትን ለምሳሌ ያህል እንመልከት፡፡ የማህበረሰቡ ነውሮች በፈጠራቸውም ሆነ እነሱን ተቀብሎና አክብሮ በሚኖረው የአካባቢው

ማህበረሰብ ላይ የጤና፣ የስነልቡና፣ የኢኮኖሚ ወዘተ. ችግሮችን ሊያስከትሉ የሚችሉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ እስኪ የማህበረሰቡ ነውሮች ሊያስከትሏቸው የሚችሉ ችግሮች (የነውሮቹ አሉታዊ ሚናዎች) ናቸው ያልናቸውን እነዚህን ጉዳዮች በተወሰኑ ምሳሌዎች እያስደገፍን ከዚህ ቀጥሎ በአጭር በአጭሩ እንመልከታቸው፡፡

## ከጤና አኳያ

ከትንተናው የተገኙ የጥናቱ ውጤቶች እንደሚያሳዩት በማህበረሰቡ ውስጥ ለሴቶች (በተለይም በእርግዝና ላይ ላሉ እናቶች) ነውር የሆኑት አብዛኞቹ የምግብ  አይነቶች በፕሮቲን የበለፀጉ ናቸው፡፡ ፕሮቲን እንደ እንቁላልና ስጋ ባሉ የምግብ አይነቶች ውስጥ የሚገኝና ለሰውነት ግንባታና ለጤንነት በጣም አስፈላጊ የሆነ አልሚ ምግብ ነው፡፡ ይሁን እንጅ በማህበረሰቡ ውስጥ እንደ እንቁላልና ስጋ ያሉ የምግብ አይነቶች ፅንሱ እንዲፋፋ ስለሚያደርጉ በወሊድ ጊዜ በእናቲቱ ላይ የምጥ መጥበቅን ያስከትላሉ ተብሎ ስለሚታመን በእርግዝና ላይ ላሉ እናቶች የማይፈቀዱ የምግብ አይነቶች ናቸው፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ በእርግዝና ላይ ያሉ እናቶችን ለተመጣጠነ የምግብ እጥረት የሚያጋልጥና በተለያዩ በሽታዎች እንዲጠቁ የሚያደርግ፤ በዚህ መንገድ የሚወለዱትን ልጆችም ለፕሮቲን እጥረት በማጋለጥ በሽታን የመከላከል ሃይል የሌላቸው፣ አካላዊ ገጽታቸው ያልተስተካከለና የማሰብ ችሎታቸውም ዝቅተኛ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው፡፡  እነዚህ የጥናቱ ውጤቶች በሌሎች ሃገራት ነውሮች ላይ ጥናት ካካሄዱ ምሁራን ግኝቶች ጋርም ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ፦ Kuzma, et al (2013:7) በአብዛኛው ዓለም በፕሮቲን የበለጸጉ ምግቦች ፅንስ እንዲፋፋና ኪሎው ከፍተኛ እንዲሆን በማድረግ በወሊድ ወቅት በእናትየዋ ላይ ችግር እንዲፈጠር የሚያደርጉ ናቸው ተብሎ እንደሚታመንና በዚህም በእርግዝና ላይ ላሉ እናቶች እንደሚከለከሉ ይገልፃሉ፡፡ ነገር ግን እንደነKuzma በፕሮቲን የበለፀጉ ምግቦች እናትና ልጁ የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙና ከበሽታ የተጠበቁ እንዲሆኑ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ በፕሮቲን የበለፀጉ የምግብ አይነቶች የፅንሱ ክብደት ከመጠን በላይ እንዲሆን ያደርጋሉ የሚለው ሃሳብም ትክክል አይደለም፡፡

በትንተናው የተገኙ ውጤቶች እንደሚያሳዩት የማህበረሰቡ አንዳንድ ስራዎች ደግሞ እጅ መታጠብን የሚከለክሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፦ በማህበረሰቡ ውስጥ በአረምና ጉልጓሎ ስራ ላይ እያሉ ምግብ ከመብላት በፊትም ሆነ በኋላ እጅን መታጠብ፤ በአውድማ ላይ ያለ ምርት ታፍሶ ወደ ቤት ከመግባቱ በፊት ባለአውድማው እጁን መታጠብ የተከለከሉ ተግባራት

ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ እነዚህ አይነት ነውሮች በግል ንፅህና አጠባበቅ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በማሳደር ማህበረሰቡን እጅን ባለመታጠብ ሊመጡ ለሚችሉ የተለያዩ በሽታዎች ሊያጋልጡ የሚችሉ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ከሰው ልጅ የአካል ክፍሎች መካከል ብዙ እንቅስቃሴ የሚያደርገውና የተለያዩ ነገሮችን በተደጋጋሚነት የሚነካው እጅ በመሆኑ በአግባቡ ንፅህናው ካልተጠበቀ ለጤና ችግር ማጋለጡ አይቀርም፡፡

## ከስነልቡና አኳያ

የማህበረሰቡ አንዳንድ ነውሮች ፆታን፣ የአመጋገብ ልማድን፣ የስራ ባህሪንና መሰል ጉዳዮችን መሰረት አድርገው የተወሰኑ የማህበረሰቡ ክፍሎችን የሚያገሉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ የማህበረሰቡን ነውሮች ከፆታ አኳያ ስንመለከታቸው ሴቶችን ዝቅ የሚያደርጉ (ንፁህ ያልሆኑ፣ በፈጣሪ የተረገሙና በረከት የሌላቸው አድርገው የሚስሉ) ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ያህልም፦ ያለወንዶች አንዳች እገዛ  በዕለት ተለት የምግብ ዝግጅት ስራ ላይ የምትጠመደው ሴት ልጅ ማህበረሰቡ የአካባቢውን ጠባቂ መንፈስ ለማክበር በሚል የሚያዘጋጀውን የአድባር መሰዋት ምግብ ግን ንፁህ ስላልሆንሽ (በተለይም ከወር አበባ ጋር በተያያዘ) አንች አታዘጋጅም - ይሄ ወንዶችን የሚመለከት ነው ትባላለች፡፡ አንች ያየሽው የነካሽው ሁሉ ረድኤት በረከት የሌለው ይሁን ተብለሽ በፈጣሪ ስለተረገምሽ አውድማ ውስጥ እንዳትገቢ፣ ከጎታም ሆነ ጎተራ እህል እንዳትሰፍሪ (እንዳትቆነጥሪ) ትባላለች፡፡

በማህበረሰቡ እምነት መካንነትም ሴቶች በፈጣሪ በመረገማቸው ለእነሱ ብቻ የተሰጠ የቅጣት ዋጋ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት መካን ሴቶች በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ በህይወት ሲኖሩ ክፉ አይን አላቸው በሚል ይፈራሉ፤ ሲሞቱም መካንነትን በአካባቢው ላይ ዘርተው ይሄዳሉ ተብለው ይፈራሉ - ይገፋሉ፡፡ በዚህ የተነሳም መካኖች በአራስ እህል ዝግጅት ላይ እንዲሳተፉ አይፈለጉም፣ ሲሞቱም በአካባቢው ማህበረሰብ የአቀባበር ወግ ልማድ መሰረት እንዲቀበሩ አይፈቀድላቸውም፡፡ በመሆኑም የማህበረሰቡ አንዳንድ ነውሮች ሴቶችን ይጫናሉ - ያገላሉ፤ ከወንዶች ጋር ያላቸውን የእኩልነት መብትም አጥብቀው ይጋፋሉ፡፡ ይህ ግኝት Kikelomo (2005፡1) በናይጀሪያዎቹ ኢሳን (Esan) ጎሳዎች ላይ ባደረጉት ጥናት ካገኙት ውጤት ጋርም ይመሳሰላል፡፡ ስለሆነም እንደነዚህ አይነቶቹ የማህበረሰቡ ነውሮች ሴቶችን የሚያገሉ፣ የሚጫኑ፣ ድምፅ አልባ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የማህበረሰቡ አብዛኞቹ ነውሮች ሴቶች ራሳቸውን የወንዶች የበታች አድርገው እንዲቆጥሩ፤ በዚህም የአስተሳሰብ፣ የስሜት፣ የባህሪና የአመለካከት መዛነፍ (መጎዳት) እንዲደርስባቸው ሊያደርጉ የሚችሉ ናቸው፡፡

የማህበረሰቡ አንዳንድ ነውሮች ደግሞ የአመጋገብ ልማድንና የስራ ባህሪን መሰረት በማድረግ የተወሰኑ የማህበረሰቡ አባላትን ለማግለል በሚል የተፈጠሩ ይመስላሉ፡፡ ነገሩን እስኪ በሁለት ነውሮች ማሳያነት እንመልከተው፡፡ በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ የነገዴ ማህበረሰብ አባላት በአካባቢው ከተለመደው ወጣ ያለ የአመጋገብ ልማድ አላቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ መነሻነትም እነሱ ያዘጋጁትን ምግብ መመገብ በተጠኘው የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ ማህበረሰብ ዘንድ ከመርከስ የሚቆጠርና በዚህም ሃይማኖታዊም ሆነ ባህላዊ ውግዘትን የሚያስከትል ነውር ነው፡፡ ይህ ነውር ግን ነገዴዎች ያዘጋጁትን ምግብ አለመብላትን ብቻ ሳይሆን እነሱ ገብተውበታል ተብሎ በታመነ ቤት ውስጥ በሌሎች ሰዎች የተዘጋጀ ምግብን መመገብንም ይጨምራል፡፡ የሙያቸው ባህሪ ከቆዳ ስራ ጋር የተያያዘ የማህበረሰቡ አባላት ያዘጋጁትን ምግብ መመገብም - ያረክሳል ተብሎ የሚታመንበትና ትልቅ ክልከላ የሚጣልበት አንዱ ጉዳይ ነው፡፡ ከማህበረሰቡ ከተሰበሰቡትና ከዚህ በላይ ለማሳያ ያህል ከቀረቡት ውስን ነውሮች በመነሳት አንዳንዶቹ የማህበረሰቡ ነውሮች ሰዎችን የተለየ የአመጋገብ ልማድና የስራ ባህሪ ስላላቸው ብቻ የሚያገሉ ናቸው፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ የተገለሉት የማህበረሰቡ አባላት ለምን ተገለልን በሚል ከፍተኛ የሆነ ስነልቡናዊ ጫና እንዲያድርባቸው ሊያደርጉ የሚችሉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

በመረጃ ትንተናው ከተገኙ የጥናቱ ውጤቶች መረዳት እንደተቻለው ነውሮችን መጣስ ለፈጣሪና ለአያት ቅድመ አያቶች ህግ ካለመገዛት ይቆጠራል፡፡ በመሆኑም ነውሮች እንዳይጣሱና ለመጣስም እንዳይታሰቡ ማህበረሰቡ የተለያዩ የመጠበቂያ ስልቶችን ይጠቀማል፡፡ ከስልቶቹ መካከልም ነውሮችን መጣስ በጥሰት ፈፃሚው ላይ አንዳች የጤና እክል እንደሚያስከትል ጥሰት ከመፈፀሙ በፊት አስቀድሞ ማስጠንቀቅ (ማስፈራራትም ሊባል ይችላል) አንዱ ነው፡፡ "ነውሩን የበላ ጥርሱ ይሰበራል - በቁምጥና በሽታ ይያዛል" የሚለው አባባል የዚህ አንዱ ማሳያ ሊሆን ይችላል፡፡ ሌላኛው ስልት ጥሰት በፈፀሙ ግለሰቦች፣ ቡድኖችና ቤተሰቦቻቸው ላይ ቅጣት መጣል ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል፦ ነገዴዎች ያዘጋጁትን ምግብ የበላ ሰው ወደ ሃይማኖታዊ ተቋማት እንዳይሄድ ቅጣት ይጣልበታል፡፡ ሰው ሞቶ ከቀብሩ በፊት የግል ስራ ሲያከናውኑ የተገኙ ሰዎች ቢኖሩ ቤተሰብ ሲሞትባቸውም ሆነ

ራሳቸው ሲሞቱ የአካባቢው ማህበረሰብ በቀብራቸው ላይ እንዳይገኝ የሚያደርግ ቅጣት ይጣልባቸዋል፡፡ ሌሎችም በቀጣይ ይሄን ተግባር እንዳይፈፅሙ ይሄው ተመሳሳይ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው አስቀድሞ ይነገራቸዋል፡፡ ከራስ ዘር ውጭ በሆነ ስራ ላይ ለመሰማራት ለሚያስቡ ሰዎችም ድርጊቱን ከፈጸሙ እራሳቸውም ሆነ ቤተሰቦቻቸው ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች እንዳይሳተፉና ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋርም ጋብቻ እንዳይፈፅሙ እንደሚደረጉ አስቀድሞ ይነገራቸዋል፡፡ ድርጊቱን በተግባር ፈፅመው ሲገኙም የተጠቀሰው ቅጣት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

ስለሆነም የተጠቀሱት አይነት ማስጠንቀቂያዎችና ቅጣቶች መኖራቸው ማስጠንቀቂያውና ቅጣቱ በሚያርፍባቸው ሰዎች ላይ የፍርሃትና ጥፋተኝነት ስሜትን በመፍጠር ስነልቡናዊ ጫናን ያስከትላሉ፡፡ በዚህ ዙሪያ ከተካሄዱ ጥናቶች መካከል ለምሳሌ፡- የFershtman et al (2011፡143-145) የጥናት ግኝትም ነውሮች እንዲህ አይነት አሉታዊ ሚናም እንደሚኖራቸው የሚገልጽ ነው፡፡

## ከኢኮኖሚ አኳያ

የማህበረሰቡ አንዳንድ ነውሮች ደግሞ በማህበረሰቡ ሰርቶ የመለወጥ ፍላጎትና ኢኮኖሚያዊ አቅም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳርፉ የሚችሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- በአካባቢው ሰው በሚሞትበት ጊዜ የአካባቢው ሰው ከቀብር በፊት ሌላ ስራ ማከናወን ነውር ነው - የሟች ቤተሰብ ደግሞ ቢያንስ ለአንድ ሳምንት ያህል ከእለት ተለት ስራው መራቅ ይጠበቅበታል፡፡ እንዲህ አይነት ነውሮች ደግሞ የስራ ሰዓትን በመሻማት የአካባቢውን ማህበረሰብ ለድህነት ሊያጋልጡ ይችላሉ፡፡ ይህም በሌሎች አጥኝዎች ለምሳሌ፡- በOsei (2006፡ 54)ና Adewara (2012:134) ከተገኙ ውጤቶች ጋር ተቀራራቢነት የሚታይበት ነው፡፡

ከራስ ዘር ውጭ ያለን የስራ አይነት መልመድም ሆነ ማከናወን በማህበረሰቡ ውስጥ የተነወረ ተግባር ነው፡፡ ስለዚህም እነዚህ አይነት ነውሮች የማህበረሰቡ ልጆች ከተቀረው የአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ተቀራርበውና በመረጡት የስራ ዘርፍ ላይ ተሰማርተው የተሻለ ህይወትን እንዲመሩ የማያግዙ ናቸው፡፡ በአንፃሩ ግን ልጆች ከቤተሰቦቻቸው በሚረከቧት ውስን መሬት ላይ ተወስነውና እሷኑ ብቻ አርሰው ህይወታቸውን በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ሆነው እንዲመሩ የሚያስገድዱ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ክልከላ “ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሃገሪቱ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራት፣ እንዲሁም

መተዳደሪያውን፣ ስራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው" የሚለውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 41 ድንጋጌም የሚጥስ ነው፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተጠኝው ማህበረሰብ ስለነውር ያለውን እሳቤና የሚሰጠውን ፍች፤ ስለምግብ፣ ሞት፣ ስራና ተያያዥ ነውሮች ያለውን እሳቤና ነውር ለሚላቸው ጉዳዮች የሚሰጣቸውን ምክንያቶች፤ እንዲሁም የነውሮችን ሚና የሚመለከት የውጤት ትንተናና ትርጎማ ቀርቧል፡፡ በዚህም ማህበረሰቡ ያለው ሁለንተናዊ ባህሪ፣ አስተሳሰብና ፍልስፍና ምን እንደሚመስል በነውሮች አማካኝነት ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ከዚህ በሚከተለውና የጥናቱ መቋጫ በሆነው ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ የጥናቱ ማጠቃለያና ይሁንታ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## የጥናቱ ማጠቃለያና ይሁንታ ፦

ይህ ምዕራፍ ጥናቱ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያለፈባቸው አበይት ሂደቶች፣ የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶችና ጠቃሚ ሃሳቦች ተመርጠው የቀረቡበት እና በመጨረሻም ጥናቱ የደረሰበት ነገር ተጠቃሎ የቀረበበት ነው፡፡ በማስከተልም ይሁንታ ሃሳቦች ተጠቁመዋል፡፡

### 9.1 ማጠቃለያ

ጥናቱ የነውር እሳቤ በሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ እምነት የሚል ርዕስ ያለው ነው፡፡ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናት ለማድረግ ካነሳሱኝ ጉዳዮች መካከል ለጥናቱ በተመረጠው አካባቢ በአንድ ወቅት ሃገር በቀል በሆነው የልጆች አስተዳደግ ዙሪያ ጥናት ሳካሂድ የነውሮች ሚና የጎላ ሆኖ ማግኘቴ አንዱና ዋነኛው አነሳሽ ምክንያት ነበር፡፡ ሌላኛው አነሳሽ ጉዳይ ደግሞ ባካሄድኩት የቤተ መፃህፍት ንባብ በተለይም የአፍሪካውያን ነውሮች ጎጅ ባህልና ያልተማሩ ህዝቦች ቅርስ ተደርገው እንደሚታሰቡና በዚህም የአፍሪካውያንም ሆኑ የሃገራችን ነውሮች የአጥኝዎችን ትኩረት እንዳላገኙ መገንዘቤ ነው፡፡ በእነዚህ አነሳሽ ምክንያቶች በመመስረትም የሃገራችንን ነውሮች በማጥናት በዘርፉ ዙሪያ ያለውን ያለመጠናት ክፍተት በተወሰነ መጠንም ቢሆን ለመሙላት እና ነውሮች ጎጅ ልማዶች ናቸው የሚለውን አገላለጽም ለመፈተሽ ተገፋፋሁ፡፡

የጥናቱ ዋና ዓላማ የሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብን ነውሮች በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን በነውሮቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን የህይዎት ፍልስፍና መመርመርና የነውሮችን ሚና መግለጽ ነበር፡፡ የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስም በዋናነት ማህበረሰቡ ስለነውር ያለውን እሳቤ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ተዘውታሪ የሆኑ የነውር አይነቶችንና ነውር ለመሆናቸው የሚሰጡ ምክንያቶችን፣ እንዲሁም ነውሮች ያላቸውን ሚና የሚመለከቱ የምርምር ጥያቄዎች አስቀድሞ ተዘጋጅተው ነበር፡፡ እነዚህን የምርምር ጥያቄዎች ለመመለስና የጥናቱን አላማ ለማሳካትም ከመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መካከል የቤተ መዛግብት ምርመራ፣ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና ተተኳሪ የቡድን ውይይት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ያስቻለው የመረጃ ሰጭዎች ናሙና አመራረጥም

በአላማ ተኮር (Purposive sampling) እና ጠቋሚ ናሙና ስልት (Network or snowball sampling) አማካይነት የተከናወነ ሲሆን፤ በመረጃ ሰጭነትም እድሜያቸው ከ18 - 80 አመት የሆኑ 30 ወንድና 20 ሴት በድምሩ 50 ሰዎች ተሳትፈዋል፡፡

ከፍ ሲል የተጠቀሱትን የመረጃ መሰብሰቢያና የናሙና መምረጫ ዘዴዎች በመጠቀም መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን፤ ከተሰበሰቡት ነውሮች መካከልም አብዛኞቹ ምግብን፣ ሞትንና የግብርና ስራን ርዕሰ ጉዳያቸው ያደረጉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በዚሁ መሰረትም ከተሰበሰቡት በርካታ ነውሮች መካከል ምግብን፣ ሞትንና ስራን ርዕሰ ጉዳያቸው ያደረጉ እንደቅደም ተከተላቸው 57፣ 35ና 34 በድምሩ 126 የሚሆኑ ነውሮች ባላቸው የጋራ ጭብጥ ተደራጅተው የጥናቱ አካል ተደርገዋል፡፡ ከእነዚህ ነውሮች መካከልም ከምግብ 26 (45.6 %)፣ ከሞት 18 (51.4 %) እና ከስራ 18 (53 %) በድምሩ 62 (49.2 %) ያህል ነውሮች በማሳያነት ተወስደው ጭብጥን መሰረት ያደረገ የመረጃ ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡ በመረጃ ትንተናው ከተገኙ የጥናቱ ውጤቶች መካከልም በተወሰኑት ላይ ጥናቱ የሚመልሳቸውን ጥያቄዎች መነሻ ያደረገ የውጤት ትንተናና ትርጉማ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

በተካሄደው የመረጃ ትንተና ውስጥ በርካታ ውጤቶች የተገኙ ሲሆን፤ ከተገኙት የጥናቱ ውጤቶች መካከል ዋና ዋና የሚባሉት ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡ ነውር የሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ በአካባቢው ያሉ ነገሮችን የሚረዳበትና ፍች የሚሰጥበት፤ ምን መስራት እንዳለበትና እንደሌለበት፣ እንዴት ባለ መንገድ መኖር እንዳለበትና እንደሌለበት ወዘተ. የሚመራበት አካባቢያዊ የሆነ እውቀትና ባህል ነው፡፡ የጥናቱ ውጤቶች እንደሚያሳዩት ነውሮች ማህበረሰቡ የአባላቱን አጠቃላይ ባህሪና የልጆቹን ሰብዕና የሚቀርፅባቸው፤ ስጋዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶቹን ለማርካት የሚያስችለውን እውቀትና ክሂል የሚያስታጥቅባቸው፤ የአባላቱን አስተሳስብና ስሜት የሚገዛባቸው ወይም የሚቆጣጠርባቸው፤ በአጠቃላይም ለአኗኗሩ መርህ፣ ለግንኙነቱ ደንብና ህግ አድርጎ የሚገለገልባቸው ናቸው፡፡

ማህበረሰቡ ነውሮችን የሚፈጥራቸውና የሚያከብራቸው ንጽህናን ለማጎልበትና [እ]ርክሰትን ለማስወገድ በሚል ነው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ነውርን ለአብሮነቱ፣ ለሰላሙና ለጤናው ሁነኛ አጋዥ አድርጎ የሚመለከተው ሲሆን፤ ከዚህ ተነስቶም ነውር ለሚላቸው ድርጊቶች ትክክለኛ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን ምክንያቶች በማቅረብ ነውሮቹን ያስቀጥላል፡፡ ሆኖም ማህበረሰቡ ነውር ለሚላቸው ነገሮች የሚያቀርባቸው ምክንያቶች በዋናነት በእምነት

የሚገለፁ እንጅ ተጨባጭ የሆኑና ትክክለኛነታቸው ሊረጋገጥ የሚችሉ እንዳልሆኑ ጥናቱ ያሳያል፡፡

በጥናቱ ከተገኙ ውጤቶች በአንድ በኩል ማህበረሰቡ ነውሮች እንዳይጣሱ ጥብቅ ጥበቃ እንደሚያደርግላቸው፤ በሌላ በኩል ግን አንዳንዶቹ ነውሮች በተለይም አሁን አሁን ችላ እየተባሉ (እየተጣሱ) እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለምሳሌ፦ በፊት ምግብ እየበሉ ማውራት፣ ልጆች ከአዋቂዎች ጋር ሞሰብ መጋራት ክልክል እንደነበረና አሁን አሁን ግን እነዚህ ደንቦች እየተጣሱ እንደሆነ፤ ቀደም ሲል በቡዳ መንፈስ ተበልቶ የሞተን ሰው በጥይት ሳይመቱ መቅበር ነውር እንደነበረና አሁን አሁን ግን ይሄ እየቀረ እንደሆነ፤ ቀደም ሲል ባህላዊ ስፍራዎችን ተጠግቶ ማረስ ክልክል እንደነበረና አሁን አሁን ግን ይሄ ክልከላ እየተጣሰ መሆኑ በጥናቱ ታይቷል፡፡ ሆኖም ግን ነውሮች ዛሬ ላይም በማህበረሰቡ ውስጥ የቀጠሉና የባህሉ ዋነኛ አካል የሆኑ እምነት መራሽ ልማዶች ናቸው፡፡

የሊቦ ከምከም አካባቢ ነውሮች ማህበረሰቡ ተስማምቶ፣ ወዶና ፈቅዶ የተቀበላቸው ናቸው፡፡ ይሄ ሲባል ግን ሁሉም የአካባቢው ማህበረሰብ ያለማንም ጣልቃ ገብነት የራሱ አድርጓቸዋል ማለት አይደለም፡፡ በመረጃ ትንተናው የተገኘው የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳው አንዳንዶቹ ነውሮች ሰዎች ሳያምኑባቸው በሌሎች ጫና ተገደው ብቻ የሚቀበሏቸው ናቸው፡፡

በጥናቱ እንደታየው ማህበረሰቡ አንዳንድ የምግብ አይነቶችን በጎጅነት የሚፈርጃቸውና -ከዚህ ተነስቶም ነውር የሚላቸው ሲሆን፤ ነውር ለማለቱ የሚያቀርበው ምክንያትም በዋናነት ለጤና ጠንቅ ናቸው ከሚል እምነት የሚመነጭ ነው፡፡ የማህበረሰቡ የምግብ አይነት ምርጫ ነውሮች በዋናነት በሴቶች ላይ (በተለይም በእርግዝና ላይ ባሉ) ያተኮሩ ሲሆኑ፤ በዋናነትም በፕሮቲን የበለፀጉ የምግብ አይነቶች ይጠቀሳሉ፡፡ በጥናቱ ግኝት መሰረት ለምግብ አይነት ነውሮች መኖር ዋናው ምክንያት *ማህበረሰቡ ስለእያንዳንዳቸው የምግብ አይነቶች* ጠቀሜታም ሆነ ስለምግብ ነውሮች ጉዳት ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆን ነው፡፡

ሞት ማህበረሰቡ በከፍተኛ ደረጃ የሚፈራውና የሚያከብረው ክስተት ሲሆን፤ ከዚህ ተነስቶም እንደ ምግብ ሁሉ ከሞት ጋር ለተያያዙ አንዳንድ ድርጊቶችም ነውሮችን ይደነግጋል፡፡ በጥናቱ እንደታየው ማህበረሰቡ ከሞት ጋር በተያያዘ ነውር ለሚላቸው ድርጊቶች የሚያቀርበው ምክንያት በዋናነት ድርጊቶቹ ወደ ሞት ያመራሉ ከሚል እምነት የመነጨ ነው፡፡ በመረጃ ትንተናው ከተገኘው የጥናቱ ውጤት በማህበረሰቡ ውስጥ ከሞት በኋላ

ህይወት አለ፣ የሟች መንፈስ ቤተሰቡን እየተመላለሰ ይጎበኛል፣ እንደተላላፊ በሽታዎች ሁሉ ሞትም ከሰው ወደ ሰው ይተላለፋል ተብሎ እንደሚታመን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ አንድ ሰው ህይወቱ ካለፈባት እስከተቀበረባት ድረስ ያለችው ጊዜ የተቀደሰች ተደርጋ እንደምትታሰብና በዚህም የአካባቢው ማህበረሰብ ከቀብር በፊት ሌላ ስራ እንደማያከናውን ጥናቱ ያሳያል፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ከግብርና ስራ ጋር የተያያዙ አንዳንድ ድርጊቶችን መፈጸምም ድርጊቶቹን በፈፀመው ግለሰብም ሆነ በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ አንዳች መጥፎ አጋጣሚን የሚያስከትል ተደርጎ ይታመናል፡፡ ከዚህ እምነት በመነሳትም ማህበረሰቡ ተገቢ ያልሆኑ ለሚላቸው ድርጊቶች ገዥ የሆኑ ነውሮችን ፈጥሮ በእነሱ ይገለገላል፡፡ ማህበረሰቡ ከስራ ጋር በተያያዘ ነውር የሚላቸውን ድርጊቶች በነውርነት የሚፈርጃቸው በዋናነት ድርጊቶቹ የተሰራው ስራ በረከት እንዳይኖረው ያደርጋሉ በሚል እንደሆነ ከጥናቱ መረዳት ተችሏል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ በረከትን ያሳጣሉ በሚል ነውር የሚባሉ ድርጊቶች በስፋት የሚስተዋሉበት የስራ አይነት አውድማ ነው፡፡ የአውድማ ስራ አንድን ምርት ለማግኘት መሬትን ከማረስና እህል ከመዝራት ጀምሮ እስከማጨድና መከመር ድረስ ብዙ የተደከመበት እህል ፍሬው የሚለካበት ስለሆነ ማህበረሰቡ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው የስራ አይነት ነው፡፡ ማህበረሰቡ ሰዎች በደከሙት መጠን እንዲጠቀሙ የማይፈልገው ክፉ መንፈስ  አውድማን ይፈታተነዋል የሚል አካባቢያዊ እምነትም አለው፡፡ ከዚህ ተነስቶም ማህበረሰቡ ከሌሎች የስራ አይነቶች በተለየ አኳሃን በአውድማ ስራ ላይ ልዩ ጥንቃቄ ያደርጋል፡፡

በጥናቱ ግኝት መሰረት በማህበረሰቡ ውስጥ ንፁህ ያልሆኑ የሚባሉ ሰዎች (ሴቶች፣ የግብረ ስጋ ግንኙነት የፈፀሙ፣ ጫማ የለበሱ ...) ወደ አውድማ ውስጥ እንዲገቡ መፍቀድ፤ ለአውድማ ተብሎ የተዘጋጀን ምግብ በአካባቢው ለሚያልፍ ሰው ሳያቀምሱ መላክ እህሉ እንዳይበረክት ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በበዓላት ቀናት መስራትም በማህበረሰቡ ውስጥ ለእህል በረከት ማጣት እንደ አንድ መንስኤ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በዚህም ምክንያት የአካባቢው ሰው ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ በወር ውስጥ ቢያንስ በዓላት የሚላቸው 11 ቀናት ያሉት ሲሆን፤ ስራዎችንም በበዓላት ቀናት የማይሰሩና የሚሰሩ በሚል በሁለት እንደሚከፍላቸው በጥናቱ ታይቷል፡፡ ማህበረሰቡ በዓላት በሚላቸው ቀናት ውስጥ ከማያከናውናቸው የስራ አይነቶች መካከል ማረስ፣ መዝራት፣ ማጨድ፣ ማረም፣ ዛፍ

መቁረጥ፣ ቤት መስራት፣ መፍጨትና መውቀጥ (መሸክሸክ) ዋነኞቹ ናቸው፡፡ በበአላት ቀናት ከሚያከናውናቸው የስራ አይነቶች መካከል ደግሞ የእንስሳት መኖ ማዘጋጀት፣ አጥር ማጠር፣ አረሞ ማውጣት፣ መከመር፣ አውድማ ማዘጋጀት፣ በሽተኛ መጠየቅ፣ ገበያ ወጥቶ ለቤት የሚያስፈልግ ነገር መግዛት፣ ዘመድ መጠየቅ፣ ለእስረኛ ስንቅ ማቀበልና የመሳሰሉ ስራዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የጥናቱ የውጤት ትንተናና ትርጎማ እንደሚያሳው ማህበረሰቡ ነውሮቹ ይጠቅሙኛል እንጅ የጎንዮሽ ጉዳትም ሊያስከትሉብኝ ይችላሉ የሚል እምነት የለውም፡፡ ይሁን እንጅ የማህበረሰቡ ነውሮች በጥልቀት ሲመረመሩ አዎንታዊም አሉታዊም ሚና ያላቸው ናቸው፡፡

ማህበረሰቡ እነሱን በመፍጠሬ አገኛቸዋለሁ ከሚላቸው ጠቀሜታዎች በሻገር ያለው የነውሮች ሚና ሲመረመር የማህበረሰቡ ነውሮች ለፈጥራቸውም ሆነ እነሱን ተቀብሎና አክብሮ ለሚኖረው የአካባቢው ማህበረሰብ የሚያበረክቱት አዎንታዊ ሚና አላቸው፡፡ ለምሳሌ ያህልም፦ ራስን ከአደጋና በሽታ የመከላከል፣ ምግባርን የማስተማርና ባህሪን የመቅረፅ፣ ሃይማኖታዊ ዶግማን የማስከበርና የማስቀጠል፣ መተሳሰብና መቻቻልን የማጎልበት፣ የአካባቢ መራቆትን የመከላከል፣ ውስጣዊ ሰላምን የመፍጠር፣ የባህል ወረራን የመከላከል ወዘተ. አዎንታዊ ሚና ሊኖራቸው እንደሚችል በጥናቱ ታይቷል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንዶቹ ነውሮች በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያላቸው ናቸው፡፡ በማሳያነትም አንዳንዶቹ ነውሮች በተቀባዮቻቸው (ነውሮቹ በሚመለከቷቸው የማህበረሰቡ አባላት) የጤና ሁኔታ፣ ስነልቡናና ኢኮኖሚ ላይ የተለያዩ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ሊያሳድሩ የሚችሉ እንደሆኑ በጥናቱ ታይቷል፡፡

በመረጃ ትንተናው መሰረት ነውሮች የሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብን እውቀት ለመረዳት አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ ምክንያቱም የማህበረሰቡ ነውሮች የማህበረሰቡን ጥንተ ማንነት (ማህበራዊ፣ ርዕየተ ዓለማዊና ሃይማኖታዊ ማንነት) የማሳየት አቅም እንዳላቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ የጥናቱ ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፍ በቀረበበት ምዕራፍ ሁለት ውስጥ እንደተነሳው እውቀት ተፈጥሯዊ ሳይሆን ማሕበራዊ ስሪት የሆነ፤ የሰው ልጅ የሚኖርበትን አካባቢና የዓለምን ምንነት፣ የክስተቶችን አመጣጥና ምክንያት ከልምዱ ተነስቶ የሚረዳበት ዘዴና ችሎታ ነው፡፡ ስለዚህም ነውሮች የሰው ልጆች ያላቸውን ፍልስፍና ለመረዳት አማራጭ የመረጃ ምንጮች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በሊቦ ከምከም ወረዳ ውስጥ የሚገኙ ነውሮች የማህበረሰቡ ባህል፣ ደንብ፣ አስተሳሰብ፣ በአጠቃላይም የህይወት ፍልስፍና ምን እንደሚመስል ለመረዳት የሚያስችሉ ናቸው፡፡ አብዛኞቹ ነውሮች ለፈጥራቸውም ሆነ እነሱን ተቀብሎና አክብሮ ለሚኖረው የአካባቢው ማህበረሰብ አዎንታዊ ሚና ያላቸው፤ አንዳንዶቹ ደግሞ አሉታዊ ሚና ያላቸውና መፍትሄም ሊፈለግላቸው የሚገቡ ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ ነውሮችን ሁሉ በደምሳሳው ኃላ ቀርና ጎጅ ባህሎች አድርጎ ከመውሰድ ይልቅ አዎንታዊ ሚና ያላቸውን በማክበርና በማስፋፋት በተለይም ጠቀሜታ ላላቸው ባህሎች ማጠናከሪያና ለልጆች የመልካም ምግባር ማስተማሪያ፣ ለዘላቂ ልማት መሳሪያ ማድረግ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ አሉታዊ ሚና ያላቸውም በሂደት ሊቀሩ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ይሆናል፡፡

## 9.2 ይሁንታ

ይህ ጥናት የሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ በነውር ላይ ያለውን እሳቤ መርምሮ በያዛቸው ዓላማዎቹ መሰረትም ግኝቶቹን አስፍሯል፡፡ አንድ ማህበረሰብ ለአዎንታዊ ለውጥ እንዲነሳሳ ለማድረግ ሲፈለግ በመጀመሪያ የዛ ማህበረሰብ አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና፣ እምነት፣ ፍላጎት መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ የጥናት ውጤት መገንዘብ እንደሚቻለው ደግሞ ነውሮች የአንድን ማህበረሰብ አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና፣ እምነት፣ ፍላጎት ወዘተ. የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በመሆኑም ነውሮች ኋላ ቀር የሆኑ ጎጅ ባህሎች ናቸው በሚል ወደ ጎን ሊተው የሚገባቸው አይደሉም፡፡ ይሄ ሲባል ደግሞ የነውሮች አዎንታዊና አሉታዊ ገፅታዎች መጤን አለባቸው፡፡ በመሆኑም በጥናቱ በታዩ ጉዳዮች መነሻነት የይሁንታ ሃሳቦችንና ለወደፊት ሌሎች ተመራማሪዎች ቢያተኩሩባቸው ያልኳቸውን የተወሰኑ የምርምር ነጥቦች ከዚህ በታች ለመጠቆም ሞክሬያለሁ፡፡

- በዚህ ጥናት ውስጥ እንደታየው የተጠኝው ማህበረሰብ ነውሮች ስለግለሰብ፣ ቡድንና ማህበረሰብ እርስ በርሳዊ ግንኙነት፣ ስለማህበረሰብ እውቀት፣ እምነት ወዘተ. መረጃ ይሰጣሉ፡፡ ነውሮች በሰዎች መካከል መተሳሰብና መቻቻልን የሚያጎለብቱ፣ ልጆችን ስለመልካም ምግባር የማስተማር ሚናም ያላቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም ነውሮች የየአካባቢያቸውን የማህበረሰብ ፍልስፍና የሚረዱና ነገ ሃገራችንን የሚረከቡ መልካም ዜጎችን ለማፍራት አጋዥ ሊሆኑ ስለሚችሉ የሚመለከታቸው የትምህርት ተቋማት ነውሮችን በተለይም የስነ ዜጋና ስነ ምግባር ስርዓተ ትምህርት አካል ቢያደርጓቸው፡፡

- የማህበረሰቡ ነውሮች ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉት በዋናነት በቃል አማካይነት ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ጠቀሜታ ያላቸው የማህበረሰቡ አንዳንድ ነውሮች በመጥፋትና በመለወጥ ላይ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ነውሮች ደግሞ በመጣስ/ችላ በመባል ላይ ያሉና በዚህም የቀጣይ እጣ ፋንታቸው አደጋ ላይ የወደቁ ናቸው፡፡ በጥናቱ እንደታየው ስለሰው አክባሪነትና በጎ ምግባር ሊያስተምሩ የሚችሉ ነውሮች (ለምሳሌ፦ እየበሉ ከማውራት፣ ለህፃናት ከትልልቆች በላይ ተቀምጦ ከመመገብም ሆነ አንድ ሞሰብ ከመጋራት ወዘተ. ጋር የተያያዙ) አሁን አሁን ችላ እየተባሉ ናቸው፡፡ አካባቢን ከመራቆት ሊጠብቁ የሚችሉ ነውሮችም (ለምሳሌ፦ ባህላዊና የተቀደሱ የሚባሉ ስፍራዎችን ለእርሻ አገልግሎት ከመጠቀም ጋር የተያያዙ) አሁን አሁን እየተጣሱ ናቸው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ የሚመለከታቸው በየደረጃው ያሉ የባህልና ቱሪዝም ተቋማት፤ በባህል ዘርፍ ጥናትና ምርምር የሚያደርጉ ተመራማሪዎች ነውሮችን በመሰብሰብ፣ በመተንተንና በመሰነድ አዎንታዊና አሉታዊ ሚና ያላቸውን የመለየት፤ አዎንታዊ ሚና ያላቸው የሚጠናከሩበትንና ለዘላቂ ልማት አጋዥ የሚሆኑበትን፤ አሉታዊ ሚና ያላቸው ደግሞ ቀስ በቀስ እየተዳከሙ በሌሎች ጠቃሚ ነውሮች የሚተኩበትን ሁኔታ ቢያመቻቹ ፡፡

- በጥናቱ እንደታየው ለአካባቢው ባህል እንግዳ የሆኑ ጎብኝዎች ማህበረሰቡ ነውር የሚላቸውን ድርጊቶች የሚጥሱ ሲሆን፤ የዚህም ዋናው ምክንያት ጎብኝዎቹ በማህበረሰቡ ውስጥ የተከለከሉና የተፈቀዱ የሚባሉ ነገሮችን የሚገልፅ መረጃ ስለሌላቸው ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ቅሬታ እየፈጠረ ያለና ወደ ግጭትም ሊያመራ የሚችል ሃገራዊ ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ የሚመለከተው የባህልና ቱሪዝም ሴክተር በጉዳዩ ላይ ሰፊ ጥናት በማድረግ ለጎብኝዎች የሚያገለግል የአድርግ (DOs) አታድርግ (DONTs) መረጃዎችን መሰብሰብና በተለያዩ ቋንቋዎች እያዘጋጀ ማሰራጨት ቢችል ጎብኝዎች እነሱን በመለየትና በማክበር ከሚጎበኙት አካባቢ ማህበረሰብ ጋር መልካም ተግባቦትን እንዲፈጥሩ የሚያደርግና የቱሪዝም ገቢያችንም የሚያሳድግ ይመስለኛል፡፡

- በጥናቱ እንደታየው አንዳንዶቹ ነውሮች (በተለይም ከምግብ ጋር የተያያዙት) ሰዎችን የተመጣጠነ ምግብ በማሳጣት ለተለያዩ የጤና ችግሮች የሚዳርጉ ናቸው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ የሚመለከታቸው በየደረጃው ያሉ የጤና ተቋማት ለማህበረሰቡ

ስለእያንዳንዱ የምግብ አይነቶች ጥቅምና የጤና ጠንቅ ስለሚያስከትሉ ከምግብ ጋር የተያያዙ ነውሮች ተከታታይነት ያለውና በጥናት ላይ የተመሰረተ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ቢሰሩ፡፡

- አንዳንዶቹ የማህበረሰቡ ነውሮች ሃይማኖትን መነሻ በማድረግ አንዳንድ የማህበረሰቡ ክፍሎችን የሚያገሉ፤ የስራ ሰዓትን የሚሻሙ፣ የማህበረሰቡን የጋራ እውቅናም ሳያገኙ በተወሰኑ የማህበረሰቡ አባላት ግፊት ብቻ እየተተገበሩና እየቀጠሉ ያሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህ አይነት ነውሮች አሉታዊ ሚናቸው የሚያመዝኑና ናቸው፡፡ ስለሆነም የማህበረሰቡ ነውሮች ካለፈው ትውልድ እየተላለፉ የመጡና የአሁኑ ትውልድም የአድርግ አታድርግ ህግ አድርጎ የሚገለገልባቸው ስለሆኑ እነሱን በአንድ ጊዜ ማስቀረት አስቸጋሪ ነው፡፡ ነገር ግን የተጠቀሱት አይነት ነውሮች ቀስ በቀስም ቢሆን ሊቀየሩ ወይም ሊቀሩ የሚገባቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም የአካባቢው የሃይማኖት አባቶችና የሃገር ሽማግሌዎች ማህበረሰቡን በማወያየት፣ በማስተማርና የነውሮቹን አሉታዊ ሚና በማሳየት እንደነዚህ አይነት ነውሮች በሂደት የሚቀሩበትን ሁኔታ ቢፈልጉ፡፡

- በጥናቱ እንደታየው በማህበረሰቡ ውስጥ ነውርን ርዕሰ ጉዳይ ያደረገ ግልጽና ነፃ ውይይት ወይም ንግግር ማድረግ በራሱ እንደነውር ይቆጠራል፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ነውሮች በማህበራዊና መንፈሳዊ ህይዎቱ ላይ ሊያስከትሉ ስለሚችሉት ተፅዕኖ በግልፅ የመናገርና የመወያየት ልምዱ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ስለሆነም አዎንታዊ ሚና ያላቸው ነውሮችን ለማስቀጠልና አሉታዊ ሚና ያላቸውን ደግሞ ለማስወገድ ይቻል ዘንድ ማህበረሰቡ ስለነውሮች ሚና በግልፅ የመወያየት ባህልን ቢያዳብር፡፡

- የማህበረሰቡ ነውሮች የማህበረሰቡን እርስ በርሳዊ ግንኙነት በማጠናከር ወንጀል የማይከሰትበትና ሰላማዊ እንቅስቃሴ ያለበት አካባቢን የመፍጠር ሚናቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ስለሆነም ህግን ማስከበርና ፍትህን ማረጋገጥ/ማስፈን የእለት ተዕለት ተግባራቸው ያደረጉ የፀጥታና የፍትህ ተቋማት ነውሮችን የስራዎቻቸው አጋዥ አድርገው ቢጠቀሙባቸው፡፡

በጥናቱ እንደታው የተጠኘው ማህበረሰብ ህይወት በነውሮች የተሞላ ነው፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ ጥናት የተዳሰሱት ከተወሰኑ ርዕሰ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ጥቂት ነውሮች ብቻ

ናቸው፡፡ የጥናቱ መረጃዎች የተሰበሰቡትም በወረዳው ውስጥ ከሚገኙ የተወሰኑ ቀበሌዎችና መረጃ ሰጭዎች ነው፡፡ ስለሆነም ጥናቱ የወረዳውን ማህበረሰብ አጠቃላይ ገፅታ ሙሉ በሙሉ ያሳየ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ሆኖም ግን ከነውስንነቶቹም ቢሆን ጥናቱ በነውሮች ዙሪያ በተጠኘው አካባቢ (በአጠቃይ በአማራ ክልልም ሊባል ይችላል) የተካሄደ የመጀመሪያ ስራ ስለሆነ ሌሎች ሰዎች በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ በቀጣይ ሰፊ ምርምር እንዲያደርጉ ያነሳሳል የሚል ትልቅ ተስፋ አለኝ፡፡

በመሆኑም ይሄን ጥናት ለማካሄድ ካነበብኳቸው፣ በመስክ መረጃ ስብሰባ ወቅት ከተገነዘብኳቸውና ትምህርትም ካገኘሁባቸው የጥናቱ ውጤቶች በመነሳት በዚህ ጥናት ከተዳሰሰው አካባቢ ውጭ ባሉ አካባቢዎችና የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ነውሮች በስፋትና በጥልቀት ቢጠኑ ጠቀሜታቸው የጎላ ነው የሚል እምነት ይዣለሁ፡፡ ከዚህ እምነቴና ከጥናቱ ውስንነት በመነሳትም ከርዕሰ ጉዳዩ አኳያ ለወደፊት በሌሎች አጥኝዎች ቢተኮርባቸው የምላቸውን የተወሰኑ የምርምር ነጥቦች ከዚህ ቀጥዬ እጠቁማለሁ፡፡

- በነውሮች ጥንተ አመጣጥና ተስተላልፎ ዙሪያ የተደረገ ሰፊ ጥናት የለም፡፡ ስለሆነም ይሄ አንድ የምርምር ነጥብ ሊሆን ይችላል፡፡
- የነውሮች ለውጥና ቀጣይነት ሁኔታ ራሱን የቻለ አንድ ሰፊ የምርምር ርዕሰ መሆን ይችላል፡፡
- የአንድን አካባቢ ማህበረሰብ ነውሮች ከሌላ አካባቢ ማህበረሰብ ነውሮች ጋር ማወዳደርና ማነፃፀር ጥሩ የምርምር ስራ ሊወጣው ይችላል፡፡
- ነውሮች በዋናነት ስርዓተ ጾታ ተኮር ናቸው፡፡ ስለሆነም ይሄ ጉዳይ አንድ የምርምር ነጥብ መሆን ይችላል፡፡
- ነውሮች ማንነትን (Identity) የመግለፅ ሚናቸው የጎላ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ አንድ የምርምር ነጥብ መሆን ይችላል፡፡

# የተጠቀሱ ምንጮች

ሰሎሞን ተሾመ ባዬ ፡፡ ፎክሎር፡ ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ፡፡ አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ማተሚያ ድርጅት፣ 2007፡፡

ነጋሪት ጋዜጣ፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት፡፡ 1987፡፡

ኪዳነወልድ ክፍሌ፡፡ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፡፡ አዲስ አበባ፤ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948፡፡

ዋልተንጉስ መኮንን፡፡ "ተፈጥሮን መናቅ፣ ሥጋን ማክበር፤ለክፉ ዐይን አጋላጭ ክስተት፤ በምስራቅ ጎጃም በሚገኘው የጎዛምን ማህበረሰብ እምነት"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለፎክሎር ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ 2007፡፡

የሊቦ ከምከም ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት፡፡ "የሊቦ ከምከም ወረዳ ህዝብ ቅድመ ታሪክና አሁን ያለበት የታሪክ ሁኔታ"፡፡ (ያልታተመ ጥራዝ)፣ ጥቅምት 2000፡፡

የሊቦ ከምከም ወረዳ ማስታወቂያ ጽህፈት ቤት፡፡ "ሊቦ ከምከም የህዳሴው ልማት ምድር ንግድና ኤክስፖ ሳምንት መጽሄት"፡፡ ሊቦ ከምከም፣ (ያልታተመ ጥራዝ)፣ 2001፡፡

የሊቦ ከምከም ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት፡፡ "የ2002 በጀት ዓመት ዓመታዊ ስታትስቲካዊ መጽሔት"፡፡ ሊቦ ከምከም፣ (ያልታተመ ጥራዝ)፣ 2003፡፡

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡ የአማራ ህዝብ ባህልና ቋንቋ፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 2001፡፡

የራስ ወርቅ አድማሴ፡፡ "ባህልና ልማት፦ ምንነታቸውና ትስስራቸው"፡፡ ሺፈራው በቀለ (አርታኢ)፣ ባህልና ልማት በኢትዮጵያ፡፡ የራስ ወርቅ አድማሴ፣ "ባህልና ልማት፦ ምንነታቸውና ትስስራቸው"፡፡ አዲስ አበባ፣ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ፣ 2004፣ 1-25 ፡፡

*ያለው እንዳወቀ፡፡ የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር ፡፡ አዲስ አበባ ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2004 ፡፡*

*ያዴሳ ቶሎሳ ወዬሳ፡፡ አጠቃላይ የትምህርት እና የሥራ ላይ ምርምር ዘዴዎችና አተገባበር፡፡ አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ. የተ. የግ. ማህበር፣ 2008፡፡*

ደስታ ተክለወለድ፡፡ *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት* ፡፡ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣1962፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ *የስነ ቃል መምሪያ*፡፡ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣ 1991 ፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡ *አማርኛ መዝገበ ቃላት* ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1993፡፡

Abelson, Robert P. "Differences between belief and knowledge systems."*Cognitive science* 3.4 (1979): 355-366.

Adebileje, Adebola. "Socio-Cultural and Attitudinal Study of Selected Yoruba Taboos in South West Nigeria." *Studies in Literature and Language* 4.1 (2012): 94.

Adewara, M. "Scientific explanations & educational implications of superstitious beliefs held by Ijaraisin people of Kwara state, Nigeria". In partial fulfilment of the reqiurements for M.A Degree in Science education, Ilorin, Nigeria, march 2012.

Baloyi, Lesiba. "The African Conception of Death: A Cultural Implication." University of South Africa, South Africa. (No Year).

Bascom, William R. "Four Functions of Folklore." *The Journal of American Folklore* 67.266 (1954): 333-349.

Belay Tefera and Abdinasir Ahmed. Research Methods. Addis Ababa, Mega printing Press, 2015.

Bloor, Michael. *Focus groups in Social Research*. Sage, 2001.

Calhoun, Craig (ed). Dictionary of the social sciences. NewYork, Oxford University press, 2002.

Central Statistical Agency. "The 2007 Population and Housing Census of Ethiopia Result for Amhara Region." Statistical Result on Population size and characteristics (part 1). Addis Ababa. August, 2010.

Chemhuru, M. and Dennis, M. "Taboos as sources of Shona people's environmental ethics." *Journal of Sustainable Development in Africa* 12.7 (2010): 121-133.

Chigidi, William Lungisani. "Shona taboos: The language of manufacturing fears for sustainable development." *The Journal of Pan African Studies* 3.1 (2009): 174-188.

Crotty, Michael. *The Foundations of Social Research: Meaning and Perspective in the research process*. Sage, 1998.

Dawit Assefa , et al. "Harmful Traditional Practices in Ethiopia." Ethiopian Public Health, Training Initiative, Training Module, 2005.

Dawson, Catherine. *Introduction to Research Methods: A practical guide for anyone undertaking a research project*. Hachette UK, 2007.

Denzin, K. and Yvonna, S. "The discipline and practice of qualitative research." *Handbook of qualitative research* 2 (2000): 1-28.

Dorson, Richard Mercer. *Folklore and folklife: An introduction*. University of Chicago Press, 1972.

Douglas, Mary. Purity and Danger. London: Routledge and Kegan, 1966.

Evans, J. & Myers, R. « Child Rearing Practice». Creating Programs Where Traditions & Modern Practices Meet. 1994.

Fershtman, C., Uri, G. and Moshe, H. "Taboos and identity: Considering the unthinkable." *American Economic Journal: Microeconomics* 3.2 (2011): 139-164.

Gadegbeku, Cynthia, et al. "Food taboos among residents at Ashongman Accra, Ghana." Department of Family & Consumer Sciences, College of Agric. & Consumer Sciences, University of Ghana, (Online) Vol.15, 2013.

Given, Lisa M. (ed). *The Sage Encyclopedia of qualitative research methods*. Sage Publications, 2008.

Goldstein, Kenneth S. *A guide for field workers in folklore*. Vol. 52. Gale/Cengage Learning, 1964.

Green, Thomas A. (ed). *Folklore: an encyclopedia of beliefs, customs, tales, music, and art*. Vol. 1. Abc-clio, 1997.

*Hurreiz, S. H. Studies In African Applied Folklore. Khartoum:The Occation of the African Universities Congress,2006.*

Isiguzo, A. I. "African culture and symbolism: A rediscovery of the seam of a fragmented identity." 2008.

Jimmy-Gama, Dixon. *An assessment of the capacity of faculty-based youth friendly reproductive health services to promote sexual and reproductive health among unmarried adolescents: evidence from rural Malawi*. Diss. Queen Margaret University, 2009.

Julia, R. F. *Ethnography Research*. Lapan,2008.

Jupp, Victor. *The Sage dictionary of social research methods*. Sage, 2006.

Kikelomo, Dibua. "Gender, Discourse and Cultural Taboos in a Rural African Society: The Esan People of Nigeria". Ogun state University, 2005.

Kilonzo, S., Kurgat, G. and Omare, G. "The Role of Taboos in the Management of Natural Resources and Peacebuilding: A Case Study of the Kakamega Forest in Western Kenya." *Africa Peace and Conflict Journal* 2.1 (2009): 39-54.

Kothari, Chakravanti. *Research Methodology: methods and techniques*. New Age International, 2004.

Kuzma, Jerzy, et al. "Food taboos and traditional customs among pregnant women in Papua New Guinea: Missed opportunity for education in antenatal clinics." *Contemporary PNG Studies* 19 (2013): 1.

Marvasti, Amir. *Qualitative Research in Sociology*. Sage, 2003.

Masaka, Dennis, and Munamato, Chemhuru. "Moral dimensions of some Shona taboos (Zviera)." *Journal of Sustainable Development in Africa* 13.3 (2011): 132-148.

Mbaya, Maweja. "Linguistic taboo in African marriage context: A study of the Oromo Laguu." *Nordic Journal of African Studies* 11.2 (2002): 224-235.

Mhaka, Edison. "Rituals and Taboos Related To Death As Repositories of Traditional African Philosophical Ideas: Evidence From The Karanga of Zimbabwe." *Academic Research International* 1.5 (2014): 370-384.

Mossa Endris. "Socio cultural & Economic status of rural female – headed households: The case of Libo kemkem Woreda of South Gondar Zone in Amhara Region." Unpublished, In partial fulfillment of the requirements for M.A Degree in Sociology. Addis Ababaa University, December 2006.

Motz, Marilyn. "The practice of belief." *Journal of American Folklore* (1998): 339-355.

Mouton, Johann and Hendrik, Christoffel. *Basic Concepts in the Methodology of the Social Sciences*. HSRC Press, 1988.

Muhammad, Aminu, et al. "Taboo Across Cultures: A Reading of Selected Nigerian/African Literary Texts." *Journal of Humanities and Social Science 20.9 (2015) : 01 - 03.*

Nejimu, B. Z. "Food Taboos and Misconceptions among Pregnant Women of Shashemene District, Ethiopia." *Science Journal of Public Health* 3.3 (2015): 410-416.

Ogunyemi, Olatunji. "The implications of taboos among African diasporas for the African press in the United Kingdom." *Journal of Black Studies* (2007).

Omobola, Odejobi. "An overview of taboo and superstition among the Yoruba of Southwest of Nigeria." *Mediterranean Journal of Social Sciences* 4.2 (2013): 221.

O'reilly, Karen. *Ethnographic Methods*. Routledge, 2012.

Osei, Joseph. "The value of African taboos for biodiversity and sustainabledevelopment." *Journal of Sustainable Development in Africa* 8.3 (2006): 42-61.

Patrick, Ayumu. “Africa’s sex taboos: Superstition, or common sence?” 2015.

Patrick B. Mullen. Listening to old voices: *Folklore, life stories, and the elderly*. University of Illinois Press, 1992.

Pehkonen, E and Anu, P. "On relationships between beliefs and knowledge in mathematics education." *Proceedings of the CERME-3 (Bellaria) meeting*. 2003.

Rugg, Gordon. *A Gentle Guide to Research Methods*. McGraw-Hill Education (UK), 2006.

Schoemaker, George (ed). *The emergence of folklore in everyday life: A fieldguide and sourcebook*. Trickster Press, 1990.

Selvi, K and Ramachandran, S. "Socio-cultural Taboos concerning Menstruation: A Micro Level Study in the Cuddalore District of Tamil Nadu, India." *International Journal of Scientific and Research Publications* 2.8 (2012): 1-7.

Sims, Martha and Stephens, Martine. *Living folklore: An introduction to the study of people and their traditions*. The Ohio State University,UTAH,2005.

Sorcar, Piya . "*Teaching taboo topics without talking about them: an epistemic study of a new approach to HIV/AIDS prevention education in India*". ProQuest, 2009.

Stifel, D. Marcel, F. and Bart, M. "Taboos, Agriculture and Poverty." *Journal of Development Studies* 47.10 (2011): 1455-1481.

Takoyoh, Eyong, et al. “Literature & Culture — The sustainability connection from an African perspective.” *Journal* of Area studies, Vol. 2, No year.

Toelken, Barre. *Dynamics of Folklore*. University Press of Colorado, 1996.

Vaismoradi, M., Hannele, T. and Terese, B. "Content analysis and thematic analysis: Implications for conducting a qualitative descriptive study." *Nursing & health sciences* 15.3 (2013): 398-405.

Vanderstoep, S and Deirdre D. "Research methods for everyday life." *John Willey,* 2009.

Yeshambel Mulat. "The Role Of Cultural Practices In Trees Management Practices Among The Qemant Community Chilga Woreda (District) Ethiopia". International Journal of Innovative Research and & Development. July*, 2013* Vol 2 Issue 7.

# አባሪዎች

## አባሪ  አንድ - የምግብ አይነት፣ የአዘገጃጀትና የአመጋገብ ነውሮች ስብስብ

### ሀ. ነውር የሆኑ የምግብ አይነቶችንና ነውር የመሆናቸውን ምክንያት የሚያሳይ

ሰንጠረዥ ፦

| ተ/ቁ | ነውር የሆነው የምግብ አይነት | ነውር የመሆኑ ምክንያት |
|---|---|---|
| 1 | ተልባ | ድግምትን ይሽራል፣ ህመምን ይቀሰቅሳል፣ በሽታንና ድጋምን ይደብቃል |
| 2 | ባቄላ | ለዳፍንት (የአይን በሽታ)፣ ለሆድ ቁርጠት  ያጋልጣል |
| 3 | የሰንበት ቂጣ (ፃዲቅ) | ህመም ያመጣል |
| 4 | ኳያ | አካልን ይሰብራል |
| 5 | ጥቁር ቀለም ያላቸው እንስሳት ስጋ | አይነስውርነትን ያስከትላል |
| 6 | እንገር | የልጆችን ጉሮሮ ያቆስላል |
| 7 | እንቁላል | ፅንሱ ስለሚፋፋ የምጥ መጥበቅን ያስከትላል፣ የሚወለዱት ልጆች ሌባ እንዲሆኑ ያደርጋል |
| 8 | አሳ | የአተነፋፈስ ችግርን ያስከትላል |
| 9 | ጠላ | ሆድን በመንፋት ለህመም ይዳርጋል |
| 10 | ሙዝ | ውርጃን፣ የምጥ መጥበቅን ያስከትላል |
| 11 | ጨው | የሚወለዱ ልጆች በቀላሉ ለበሽታ የሚጋለጡ እንዲሆኑ ያደርጋል |
| 12 | ሩዝ | የሚወለዱት ልጆች የቆዳ ቁስለት ያጋጥማቸዋል |
| 13 | ፓፓያ | ውርጃን፣ የምጥ መጥበቅን ያስከትላል |
| 14 | አናናስ | በወሊድ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ የደም መፍሰስን ያስከትላል፣ |

| | | |
|---|---|---|
| 15 | ቂጣ | የትዳር አጋር ያሳጣል፣ ከትዳር ያፋታል |
| 16 | የዶሮ ፈረሰኛ | የትዳር አጋር ያሳጣል፣ ከትዳር ያፋታል |
| 17 | የበግ ወይም የፍየል ቆለጥ | የትዳር አጋር ያሳጣል፣ ከትዳር ያፋታል |
| 18 | የዶሮ መቋደሻ | ለትዳር ታማኝ አለመሆንን፣ ፍችን ያስከትላል |
| 19 | ራስ ምላስ | ለፍላፊ/ምላሳም ያደርጋል |
| 20 | ቅልጥም | ለትዳር አጋር ታዛዥ አለመሆንን ያመጣል |
| 21 | ካሲናን (ጭላሃ) | ድህነት ያመጣል |
| 22 | የላም ስጋ | ላሞችን ያደርቃል፣ ድርቅና ድህነትን ያመጣል |
| 23 | እልበት | ላሞችን ያደርቃል፣ ድህነት ያመጣል |
| 24 | የዶሮ ክንፍ | ከቦታ ቦታ ዘዋሪ ወይም ከርታታ ያደርጋል |
| 25 | ነጠላ ዶሮ | ከርታታ፣ ረድኤት የለሽ፣ ቀልበቢስ ያደርጋል |

ለ. ከምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ጋር በተያያዘ ነውር የሆኑ ድርጊቶችንና ነውር የመሆናቸውን ምክንያት የሚያሳይ ሰንጠረዥ ፦

| ተ/ቀ | ነውር የሆነው ድርጊት | ድርጊቱ ነውር የሆነበት ምክንያት |
|---|---|---|
| 26 | በእርጎ ምግብ በልቶ እጅን መታጠብ | ላሟ ትሞታለች፣ ትደርቃለች |
| 27 | ወተትን እሳት ላይ መድፋት | ላሟ ትሞታለች፣ ትደርቃለች |
| 28 | እንጀራን ቆርሶ (በቁርጥ መልክ ) ማቅረብ | ድሃ ያደርጋል |
| 29 | መሶብ ሳይነሳ ቀድሞ መነሳት | ድሃ ያደርጋል |
| 30 | ለህፃናት ከአዋቂዎች ጋር መብላት፣ ከአዋቂዎች በላይ ተቀምጦ መመገብ | ድሃ ያደርጋል |
| 31 | እየበሉ ማውራት፣ መሳቅ… | ድሃ ያደርጋል |
| 32 | ለሴት ልጅ ምግብን መባረክ ወይም ከወንድ ቀድማ ምግብ መቁረስ | ሴት የቆረሰው አይበረክትም |
| 33 | በግራ እጅ መመገብ | አያጠግብም፣ ምግቡ ረድኤት አይኖረውም |
| 34 | በግራ እጅ ምግብ ለሌሎች መስጠት | ለተቀበለው ሰው ምግቡ አይስማማውም ፣ አያጠግበውም |
| 35 | ለማህበር / ሰንበቴ የተዘጋጀ ምግብን ቄስ ሳይባርከው መመገብ | ምግቡ ረድኤት አይኖረውም፣ በማህበርተኞቹ መካከል ጠብ ይፈጠራል |
| 36 | ለሴት ልጅ ግብር ውሃ ሳትወጣ ምግብ ማቅረብ | የቤቱ እህል አይበረክትም፣ የቤቱን እህል አይጥ ይበላዋል |
| 37 | አብዝቶና ቶሎ ቶሎ መጉረስ | ስስታም ያደርጋል፣ አያጠግብም |
| 38 | ቆሞ፣ ተጋድሞ መመገብ | አያጠግብም |
| 39 | ነገዴዎች ያዘጋጁትን ምግብ መመገብ | ያረክሳል፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ውግዘትን ያስከትላል |
| 40 | ቆዳ ሰሪዎች ያዘጋጁትን ምግብ መመገብ | ያረክሳል፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ውግዘትን ያስከትላል |
| 41 | ለሴት ልጅ የአድባር መስዋዕት ምግብ | የአካባቢው አድባር/ቆሌ ስለሚቆጣ |

| | | |
|---|---|---|
| | ማዘጋጀት | ለህመም ይዳርጋል |
| 42 | ለ“ደጁ” ስርዓት ከበራ የተዘጋጀ ምግብን ቤተሰብ ያልሆነ ሰው መመገብ | ቆሌው ስለሚቆጣ ቤተሰብ ያልሆኑት ሰዎች ይታመማሉ |
| 43 | ለወንድ ልጅ የቤተሰብን ጤና ለመጠበቅ በአመት አንዴ በቤት ውስጥ ለሚከናወን ስርዓት ከበራ የተዘጋጀ ምግብን መብላት | ቆሌው ስለሚቆጣ ተመጋቢው ይታመማል |
| 44 | ለአደባባይ ስርዓት ከበራዎች የቀረቡ ምግቦችንም ሆነ የመስሪያ እቃዎችን ወደቤት መመለስ | የተሸኘው በሽታ ወደቤት አብሮ ይመለሳል፣ ለአድባሩ የቀረበው ልመና ይረክሳል |
| 45 | ቡና እየተጠጣ እያለ አቋርጦ መሄድ | አቋርጦ በሄደው/ችው ላይ አንዳች ህመምን ያስከትላል |
| 46 | ቡናን ያለቁርስ ማቅረብ | ቆሌው /አድባሩ ስለሚቆጣ ለህመም ያጋልጣል |
| 47 | እንግዳ ሰውን ምግብ ሳያበሉ መላክ | እንግዳው በጥነን (ጆሮ ደግፍ፣ አንገት የሚያጣምም) በሽታ ይታመማል |
| 48 | መሶብ ላይ የቀረበ ምግብን ጨርሶ መመገብ | የአካባቢው ቆሌ ስለሚቆጣ ለበሽታ ይዳርጋል |
| 49 | በጨለማ ውስጥ ሆኖ መመገብ | ለህመም ይዳርጋል |
| 50 | በሌሊት (ሰዓት እላፊ) መሶብ መክፈት፣ መብላት፣ መጠጣት | ለህመም ይዳርጋል |
| 51 | የባለዛር የተባሉ ነገሮችን መመገብ | የበሉት ሰዎች ይታመማሉ፣ የዛር መንፈሱ ወደበሉት ሰዎች ይሸጋገራል |
| 52 | ጠላን እንደተቀበሉ መጠጣት | ለእርኩስ መንፈስ ይዳርጋል፣ በቀላሉ ያሰክራል፣ |
| 53 | ለመካን ሴት በአራስ እህል ዝግጅት ላይ መሳተፍ | በአራሷም ሆነ በተወለዱት/በሚወለዱት ህፃናት ላይ ህመም ያመጣል |

| | | |
|---|---|---|
| 54 | ልጆች ከመወለዳቸው በፊት ለእነሱ የሚሆን ምግብ አስቀድሞ ማዘጋጀት | የሚወለዱት ልጆች በሽተኛ ይሆናሉ |
| 55 | ለቁስ ተብሎ የተዘጋጀ ምግብን መመገብ | ተመጋቢዎቹ ይታመማሉ |
| 56 | ተባርከው ያልታረዱ ወይም በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች የሞቱ የቤት እንሰሳትን መመገብ | የተመገቡት ይሞታሉ |
| 57 | ባል ለሚስቱ ቀድሞ ሳያጎርስ መመገብ | ፍቅርን ይቀንሳል፣ በባል ላይ ሞትን ያመጣል |

## አባሪ ሁለት - ከሞት ጋር የተያያዙ ነውሮች ስብስብ

**ከሞት ጋር በተያያዘ ነውር የሆኑ ድርጊቶችንና ነውር የመሆናቸውን ምክንያት የሚያሳይ ሰንጠረዥ ፡**

| ተ/ቁ | ነውር የሆነው ድርጊት | ድርጊቱ ነውር የሆነበት ምክንያት |
|---|---|---|
| 1 | ሰው ሳይሞት ለሴት ልጅ ነጠላ ማዘቅዘቅ፣ ለወንድ ልጅ ቀኝ እጅን ማውጣት | ሞትን ይጠራል |
| 2 | ሬሳን በዋናው በር ማስወጣት | ተጨማሪ ሞትን ያስከትላል |
| 3 | ሟች ነፍስ ከዘራ ለእሱ መቃብር የተቆፈረውን ጉድጓድ ክፍት መተው | በቤተሰቡ ላይ ሞት ያመጣል |
| 4 | ሰው የሞተበትን ቤት በድምፅም ሆነ በአካል እንቅስቃሴ ለሌላ ሰው ማመልከት | ሞት ያይዛል |
| 5 | ሳይቀበር መቆየት/ መዋል/ ማደር ያለበትን ሬሳ በሆዱ ሳይደፉ ማቆየት | በጀርባው ተንጋሎ ከተኛ ሌላ ሰው ያስከትላል |
| 6 | የሞተን ሰው አይኑን እንዳፈጠጠ፣ እጁን እንደጨበጠ መቅበር | ሟች ሌላ ሰው ይጠራል/ያስከትላል |
| 7 | ሰው ሲሞት ለሌሎች ለማርዳት (ለመንገር) አንድ ሰው ብቻውን መሄድ | መላከ ሞት አብሮ ይሄዳል |
| 8 | ሰው ሲሞት ለሌሎች ለማርዳት (ለመንገር) የሚሄዱ ሰዎችን ለመመደብ ድምፅን ከፍ አድርጎ መነጋገር | መላከ ሞት ይሰማል |
| 9 | የሃዘን እህልን ወደቤት መመለስ፣ ወደሌላ ቤት ማስገባት | ሞት ተከትሎ ይሄዳል |
| 10 | ሬሳን መዝለል/መራመድ | የዘለለው ሰው ይሞታል |
| 11 | ገድሎ አልገደልኩም ብሎ መማል | በራስ ላይ ሞት ያመጣል |
| 12 | የሟች ቤተሰብን /ሃዘንተኛን የሚደርስ ሰው የሃዘንተኛውን ትከሻ በእግራ እጁ መንካት | በሟች ቤተሰብ ላይ ተጨማሪ ሞትን ያመጣል |

| | | |
|---|---|---|
| 13 | የሞተን ሰው ስሙን መጥራት | ስሙን የጠሩትን ሰዎች ወደሞት ይጠራል |
| 14 | ከቀብር መልስ ድምፅን ከፍ አድርጎ ማውራት፣ ማልቀስ፣ ሃዘን ማብዛት | የሚች መንፈስ ይረበሻል |
| 15 | በቡዳ ተበልቶ መሞቱ የተረጋገጠን ሰው በጥይት ሳይመቱ መቅበር | ቡዳዎች አውጥተው አገልጋያቸው ያደርጉታል |
| 16 | ባል/ሚስት ለሞተባቸው ሰዎች ከአንድ አመት በፊት ሌላ ጋብቻ መፈፀም | የሚች መንፈስ ይቀየማል |
| 17 | ሬሳን ማቋረጥ | የሚች መንፈስ ይቀየማል |
| 18 | መካን ሴት ስትሞት በጀርባዋ አንጋሎ መቅበር | የአካባቢው ማህበረሰብ መካን ይሆናል |
| 19 | መካን የሆነች መነኩሴ ስትሞት በጀርባዋ አንጋሎ መቅበር፤ | የአካባቢው ማህበረሰብ መካን ይሆናል |
| 20 | ዛር ላለባቸው ሰዎች የሚችን ገላ መንካት፣ በለቅሶ ላይ መገኘት | ልጆቻቸው ዘር አይኖራቸውም |
| 21 | ለባለዛሮች (ባለአውልያዎች) ሬሳ ከወጣበት ቤትም ሆነ ለእዝን የመጣ ምግብን መመገብ | ልጆቻቸው ዘር አይኖራቸውም |
| 22 | ሴት ልጅ ሬሳ መሸከም | የማህፀኗ በር ይዘጋል/መካን ትሆናለች |
| 23 | ከቀብር ቦታ መልስ እጅን ሳይታጠቡ ማንኛውንም ነገር ማከናወን | ያረክሳል |
| 24 | ክርስትና ከመነሳቱ በፊት የሞተን ህፃን ልጅ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ መቅበር | ያረክሳል |
| 25 | የቁም ተዝካር የሚያወጣ ሰው እራሱ ያዘጋጀውንም ሆነ ሌሎች ያዘጋጁትን የቁም ተዝካር ምግብና መጠጥ መውሰድ/መመገብ፤ | የጽድቅ ህይዎትን ያሳጣል |
| 26 | በእርግዝና ላይ ያለች ሴት ለለቅሶ የተዘጋጀ ምግብን መመገብ | አካሉ ያልተስተካከለ ልጅ ይወለዳል |
| 27 | ለእርጉዝ ሴት ለቅሶ ቤት መሄድ | የተረገዙት ህፃናት በክፉ መንፈስ የተጠቁ ሆነው ይወለዳሉ፣ |
| 28 | የሞተ ሰው ሳይቀበር መሳሳም፣ የእጅ ሰላምታ | በአካባቢው ድርቅ ይከሰታል ፣በረድ |

| | | |
|---|---|---|
| | መሰጣጠት፣ | ያስመታል |
| 29 | በአካባቢው የሞተ ሰው ሳይቀበር ሌላ ስራ ማከናወን | በአካባቢው ድርቅ ይከሰታል፣ በረድ ያስመታል |
| 30 | ሚችን ከቀበሩ በኋላ ከመቃብሩ ላይ ዛፍ/ቅጠል ሳይተክሉ መመለስ | በአካባቢው ድርቅ ይከሰታል |
| 31 | የሞተ ሰውን ሳያጥቡ መቅበር | የቤቱን ሃብት ንብረት፣ዕድሜ፣ጤና ይዞ ይሄዳል |
| 32 | ሬሳ የወጣበትን ቤት ከቀብር መልስ በፊት መዝጋት | የሚች ቤተሰብ ንብረት ይጠፋል፣ ቤተሰቡ ድሃ ይሆናል |
| 33 | የሚች ቤተሰብ ጉድድ መቆፈር፣ አፈር ማልበስ | ቤተሰቡ ሃዘኑ ይበረታበታል |
| 34 | ሴት ልጅ ወደቀብር ቦታ መቅረብ | ሚችን ለመርሳት ትቸገራለች |
| 35 | ሴት ልጅ መቃብር መቆፈር | ሚችን ለመርሳት ትቸገራለች፣ ውስጧ በሃዘን ይጎዳል |

## አባሪ ሶስት - ከግብርና ስራ ጋር የተያያዙ ነውሮች ስብስብ

ከግብርና ስራ ጋር በተያያዘ ነውር የሆኑ ድርጊቶችንና ነውር የመሆናቸውን ምክንያት የሚያሳይ ሰንጠረዥ ፡-

| ተ/ቁ | ነውር የሆነው ድርጊት | ድርጊቱ ነውር የሆነበት ምክንያት |
|---|---|---|
| 1 | ለሴት ልጅ አውድማ ውስጥ መግባት | አውድማው ላይ ያለው ምርት አይበረክትም |
| 2 | ለሴት ልጅ (ምርት መስፈር) በጎተራ ውስጥ ያለ እህል መስፈር/መቆንጠር | እህሉ አይበረክትም |
| 3 | ጫማ ለብሶ ውድማ ውስጥ መግባት | ምርቱ አይበረክትም |
| 4 | እህል ሲከምሩ ሳይሞሉ /ሳይቋጩ መተው | እህሉ አይበረክትም |
| 5 | በማታ/ጨለማ ቤት መጥረግ | የቤቱን ሲሳይ ይዞ ይወጣል |
| 6 | ኑግ ተወቅቶ ከአውድማ ላይ ሲታፈስ እንዲበረክት በሚል ለፈጣሪ ፀሎት ማቅረብ | አውድማው ላይ ያለው ምርት አይበረክትም |
| 7 | እህል ተወቅቶ አውድማ ላይ ሲሰፈር ድምፅ ማሰማት | አውድማው ላይ ያለው ምርት አይበረክትም |
| 8 | በታህሳስና ጥር ወር ውስጥ እህል መውቃት | አውድማው ላይ ያለው ምርት አይበረክትም |
| 9 | በውቂያ/ በራይ ጊዜ የሚበራዩ እንሰሳትን እዳሪ/እበት በየቦታው መጣል | ምርቱ አይበረክትም |
| 10 | ከሌላ ድንበርተኛ ጥግ ያለን እህል ጨርሶ ማጨድ | እህሉ ረድኤት እንዳይኖረው ያደርጋል |
| 11 | አረቄ፣ ቅባ ኑግ እየተወጣ ብዙ ማውራት/መለፍለፍ | አረቄው፣ ቅባ ኑጉ ዲንቃ (ድፍርስ፣ ዝቃጭ፣ አተላ) ይሆናል |
| 12 | ለአውድማ የመጣ ምግብን ወደቤት መመለስ | የምርቱን በረከት ይዞ ይሄዳል |
| 13 | አውድማ የጣለ አባውራ እህሉ ወደቤት ሳይገባ እጁን መታጠብ | የእህሉ አግማስ (በረከት) አብሮ ይታጠባል |
| 14 | ለአውድማ የተዘጋጀን እህል ውሃ በአካባቢው ለሚያልፍ ሰው አለማቅመስ | አውድማ ላይ ያለው እህል አይበረክትም |

| | | |
|---|---|---|
| 15 | የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፅሞ (ጥላ ሆኖ) አውድማ ውስጥ መግባት | አውድማ ላይ ያለው እህል አይበረክትም |
| 16 | ዱባን አንድ ሰው ብቻውን ሆኖ መትከል | ዱባው የማያፈራ/መሃን ይሆናል |
| 17 | በቤት ውስጥ ያለን የሸረሪት ድር መጥረግ | መካን ያደርጋል |
| 18 | ላም እያለቡ ማውራት | ላሚቱ ትነጥፋለች፣ ወተቱን ጅን ይወስደዋል፣ |
| 19 | በበዓል ቀን መስራት | በረድ ያስመታል |
| 20 | በአረም ፣ ጉልጓሎ ስራ ላይ እያሉ ምግብ ከመብላት በፊትም ሆነ በኋላ እጅን መታጠብ | የታጠቡበት መሬት እህል አያበቅልም |
| 21 | ለቁሶች ከቀደሱ በኋላ ማንኛውንም ስራ ማከናወን | የተሰራው ስራ ውጤት አይኖረውም |
| 22 | የወር አበባ ላይ ያለች ሴት ወንዝ ወርዶ ውሃ መቅዳት፣ ልብስ ማጠብ | እንስራው ይሰበራል፣ ልብሱ ታጥቦ አይጠራም |
| 23 | ወንዞችን፣ ሃይቆችን፣ ጫካዎችን፣ ትልልቅ ዛፎችን፣ ዋሻዎችን ተጠግቶ ማረስ | የተዘራው እህል አያፈራም |
| 24 | ዘር በሚዘራበት ጊዜ ከፊት ለፊት ሆኖ በዘሩ መረጨት | የተረጨው ሰው ድሃ ይሆናል |
| 25 | ቤት ሲሰራ ሳይደመድሙ/ሳይገጥሙ ማሳደር | ባለቤቱ ድሃ ይሆናል፣የባለቤቱ ሃብት ይሰለባል |
| 26 | ከራስ ዘር ውጭ ያለን የስራ አይነት ማከናወን | ድሃ ያደርጋል፣ የአያት ቅድመ አያቶችን መንፈስ ቅር ያሰኛል |
| 27 | እንጀራ የተጋገረበትን ምጣድ ክፍቱን ማሳደር | ድሃ ያደርጋል |
| 28 | ቤት ሲሰራ ወጋግራውን ከ7፣9 ወይም 12 ውጭ ማድረግ | የባለቤቱ ሃብት ንብረት ይጠፋል |
| 29 | እርሻ ሲታረስ የዋለበትን የበሬ እቃ እንደረገጡ /እንዳሰሩ ማሳደር | ቤተሰቡ ለድህነትና ረሃብ ይጋለጣል፣በሬዎቹ ይሞታሉ |
| 30 | የበሬ ዕቃን ለማገዶነት መጠቀም | ቤተሰቡ ለድህነትና ረሃብ ይጋለጣል |
| 31 | በጋራ በሚከናዎን አጨዳም ሆነ አረም ላይ ቦታ መቀየር | የአጨዳም ሆነ አረም ስራው አይቀናም |
| 32 | የአጨዳም ሆነ የአረም ስራ በሚያከናውኑ | አጫጆቹም ሆኑ አራሚዎቹ የድካም ስሜት እንዲሰማቸውና ስራውም |

| | | |
|---|---|---|
| | ሰዎች ፊት መቆም | እንዳይቀናቸው ያደርጋል |
| 33 | አንድ ሰው እያረሰ እያለ የእርሻ ቦታው ውስጥ ዱላ/ብትርን መትከል | አራሹ ብዙ እንዳያርስ፣ስራው እንዳይቀናው ያደርጋል |
| 34 | እየታጨደ ያለ እህልን ከፊት ከፊት መሰብሰብ | የአጨዳ ስራው አይቀናም |

## አባሪ አራት - የመረጃ ሰጭዎች ግላዊ መረጃ

### 1. በቃለ መጠይቅ የተሳተፉ ሰዎች ግላዊ መረጃና የቀረቡ ጥያቄዎች ናሙና

#### ሀ. በቃለ መጠይቅ የተሳተፉ ሰዎች ግላዊ መረጃ

| ተ.ቁ | ስም | ፆታ | ዕድሜ | የት/ት ደረጃ | ስራ | መኖሪያ ቀበሌ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ደስታው አባይነው | ወ | 48 | ቢ..ኤ ዲግሪ | የታሪክ ባለሙያና አስጎብኝ | አዲስ ዘመን |
| 2 | አቶ ገብረአብ ደሴ | ወ | 35 | ዲፕሎማ | መምህር | አዲስ ዘመን |
| 3 | አባ ፍቅረ ማሪያም | ወ | 78 | 8ኛ | ሃይማኖታዊ አገልግሎት | ብራ አቦ |
| 4 | አቶ በላይ ዋለ | ወ | 62 | 3ኛ | አርሶ አደር | አግድ ቅርኛ |
| 5 | አቶ ቢሆነኝ አጠቃ | ወ | 65 | - | አሳ ማስገር | አግድ ቅርኛ |
| 6 | አቶ አባይነው ጥጋቡ | ወ | 35 | ዲፕሎማ | የጤና ባለሙያ | ብርኩቴ |
| 7 | አቶ ድንቁ በላይነህ | ወ | 80 | 4ኛ | ጡረተኛ | ብርኩቴ |
| 8 | አቶ ድንበሩ አባይነህ | ወ | 62 | - | የሃገር ሽማግሌ | ይፋግ |
| 9 | አቶ አለበል ደሴ | ወ | 65 | - | የሃገር ሽማግሌ | ይፋግ |
| 10 | ዲያቆን ብርሃኔ ያረጋል | ወ | 32 | 5ኛ | ሃይማኖታዊ አገልግሎት | ሚካኤል ደብር |
| 11 | ወ/ሮ በለጡ ካሴ | ሴ | 69 | - | የቤት እመቤት | ብራ አቦ |
| 12 | ወ/ሮ አጀቡሽ አለማ | ሴ | 61 | - | ሸክላ ሰራተኛ | ብራ አቦ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 13 | ወ/ሮ አዲሴ ያለው | ሴ | 48 | ሰርተፊኬት | መምህርት | ብርኩቴ |
| 14 | ወ/ሮ አይናለም ግርማ | ሴ | 78 | - | የቤት እመቤት | አግድ ቅርኛ |
| 15 | እማሆይ ድንቄ ካሳ | ሴ | 72 | - | የገዳም አገልግሎት | ሚካኤል ደብር |
| 16 | አቶ ስለሽ መኮንን | ወ | 42 | 8ኛ | ፖስተኛ | አዲስ ዘመን |
| 17 | ወ/ሮ ሃይማኖት አስማረ | ሴ | 38 | ሰርተፊኬት | መምህርት | አዲስ ዘመን |
| 18 | ወ/ሮ ዳሳሽ እምሩ | ሴ | 46 | ዲፕሎማ | መምህርት | ሚካኤል ደብር |
| 19 | አቶ ካሴ መንግስቱ | ወ | 67 | - | ቆዳ ሰራተኛ | ብራ አቦ |
| 20 | ወ/ሪት ፍሬዘር አድማሱ | ሴ | 25 | ሰርተፊኬት | የጤና ባለሙያ | ብርኩቴ |
| 21 | አቶ በለጠ ማስረሻ | ወ | 48 | - | አርሶ አደር | ብርኩቴ |
| 22 | አቶ ጌታየ ይታየው | ወ | 72 | - | ነጋዴ | ይፋግ |
| 23 | ወ/ሮ ሙሉ ገበየሁ | ሴ | 32 | - | ነጋዴ | ይፋግ |
| 24 | አቶ ማንችሎ ደርቤ | ወ | 65 | - | ዘበኛ | ይፋግ |
| 25 | ወ/ሪት አዘነግ ገበየሁ | ሴ | 18 | 7ኛ | ተማሪ | ሚካኤል ደብር |
| 26 | መሪጌታ ይትባረክ | ወ | 46 | 3ኛ | ሃይማኖታዊ አገልግሎት | ሚካኤል ደብር |
| 27 | ቄስ ዋሌ ዘሪሁን | ወ | 38 | 6ኛ | ሃይማኖታዊ አገልግሎት | ሚካኤል ደብር |
| 28 | ወ/ሮ ስፍራሽ መኮንን | ሴ | 76 | - | የቤት እመቤት | ሚካኤል ደብር |
| 29 | ወ/ሮ ስመኝ አዳነ | ሴ | 72 | - | የቤት እመቤት | ይፋግ |
| 30 | አቶ ሞገስ ይሁኔ | ወ | 49 | ሰርተፍኬት | የግብርና ባለሙያ | አግድ ቅርኛ |
| 31 | ወ/ሮ አያልነሽ ብርሃኑ | ሴ | 64 | - | የቤት እመቤት | ብራ አቦ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 32 | ወ/ሮ ማርታ ተሰማ | ሴ | 62 | - | የቤት እመቤት | አግድ ቅርኛ |
| 33 | ወ/ሪት ቦሰና ድሌ | ሴ | 21 | 8ኛ | ተማሪ | ብርኩቴ |
| 34 | አቶ ትግስቱ በላይ | ወ | 65 | 3ተኛ | አርሶ አደር | ብርኩቴ |
| 35 | ቄስ አስማማው ዋሌ | ወ | 68 | 4ተኛ | ሃይማኖታዊ አገልግሎት | አዲስ ዘመን |
| 36 | አቶ ሙሉቀን ዘውዱ | ወ | 60 | መሰረተ ትምህርት | ብረት ሰራተኛ | ብራ አቦ |
| 37 | ወጣት ታጠቅ ቢሆነኝ | ወ | 18 | 9ኛ | ተማሪ | አዲስ ዘመን |
| 38 | ወጣት አባይነህ ሙላት | ወ | 19 | - | አሳ ማስገር | አግድ ቅርኛ |
| 39 | አቶ ያለው ደርሶ | ወ | 71 | - | የሃገር ሽማግሌ | ይፋግ |
| 40 | አቶ በየነ ምናሉ | ወ | 69 | - | አርሶ አደር | አዲስ ዘመን |
| 41 | አቶ ያዛቸው ጀንበር | ወ | 78 | - | አርሶ አደር | አዲስ ዘመን |
| 42 | ወ/ሮ ሰርኬ ልይህ | ሴ | 61 | - | አርሶ አደር | አዲስ ዘመን |
| 43 | አቶ ደምለው አንማው | ወ | 62 | መሰረተ ትምህርት | ነጋዴ | ይፋግ |
| 44 | ወ/ሮ የምስራች ወርቁ | ሴ | 71 | - | አርሶ አደር | ይፋግ |
| 45 | አቶ ደለለ ሞላልኝ | ወ | 54 | - | አሳ ማስገር | አግድ ቅርኛ |
| 46 | አቶ መንግስቱ ደምሌ | ወ | 72 | - | ብረት ሰራተኛ | ብራ አቦ |
| 47 | አቶ ሙጪ ገበየሁ | ወ | 60 | - | ብረት ሰራተኛ | ብራ አቦ |
| 48 | ወ/ሮ ሙጭቴ ካሳ | ሴ | 63 | - | ሸክላ ሰራተኛ | ብራ አቦ |
| 49 | ወ/ሮ ወይንሸት ገበየሁ | ሴ | 64 | - | ሸክላ ሰራተኛ | ብራ አቦ |
| 50 | ወ/ሮ ገነት ደመላሽ | ሴ | 21 | 8ኛ | ተማሪ | ብርኩቴ |

❖ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት መረጃ ሰጭዎች መካከል ከተራ ቁጥር 1 — 15 ያሉት ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ናቸው፡፡

## ለ. ለቃለ መጠይቅ የቀረቡ ጥያቄዎች ናሙና

1. ነውር ማለት ለእርስዎ ምን ማለት ነው?
2. በማህበረሰቡ ዘንድ ነውር የተባሉ ተግባሮችንና ለምን ነውር እንደሆኑም ጭምር የቻሉትን ያህል ቢነግሩኝ?
3. የማህበረሰቡ ነውሮች በዋናነት በየትኞቹ የማህበረሰቡ ክፍሎች ላይ እንደሚያተኩሩና ለምን በእነሱ ላይ እንዳተኮሩ ቢነግሩኝ?
4. የነውሮችን ጥቅምና ጉዳት በምሳሌ እያስደገፉ ቢያብራሩልኝ?
5. በማህበረሰቡ ውስጥ ነውር የተባሉ ነገሮች ቢጣሱ በማን ላይ ምን ይደርሳል? ቢከበሩስ ማን ምን ያገኛል? በምሳሌ አስደግፈው ቢገልፁልኝ?
6. ነውሮችን ከመጣስም ሆነ ከማክበር ጋር በተያያዘ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚነገሩ አባባሎች ካሉ ቢነግሩኝ?

## 2. በተተኳሪ የቡዱን ውይይት የተሳተፉ አባላት

### ሀ. በነውር ምንነት፣ አይነትና የመከልከላቸው ምክንያቶች ዙሪያ

| ተ.ቁ | የአባላት ስም ዝርዝር | የቡድኑ መለያ፣ ውይይት የተካሄደበት ቀንና ዓ.ም |
| --- | --- | --- |
| 1 | አቶ ገብረአብ ደሴ | **ቡድን - አንድ** (የካቲት 7/2008 ዓ.ም) |
| 2 | አቶ በላይ ዋለ | |
| 3 | አቶ አለበል ደሴ | |
| 4 | አቶ አባይነው ጥጋቡ | |
| 5 | አቶ በየነ ምናሉ | |
| 6 | አቶ ትግስቱ በላይ | |
| 7 | ዲያቆን ብርሃኔ ያረጋል | |

## ለ. ለሴቶችና ህፃናት ነውር በሆኑ ጉዳዮችና ምክንያቶቻቸው ዙሪያ

| ተ.ቁ | የአባላት ስም ዝርዝር | የቡድኑ መለያ፣ ውይይት የተካሄደበት ቀንና ዓ.ም |
|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ በለጡ ካሴ | ቡድን - ሁለት (የካቲት 10 እና ግንቦት 8 /2008 ዓ.ም) |
| 2 | ወ/ሮ አጀቡሽ አለማ | |
| 3 | ወ/ሮ አይናለም ግርማ | |
| 4 | ወ/ሮ ዳሳሽ እምሩ | |
| 5 | እማሆይ ድንቁ ካሳ | |
| 6 | ወ/ሮ ወይንሸት ገበየሁ | |
| 7 | ወ/ሪት ፍሬዘር አድማሱ | |

ሐ. ነውሮችን መጣስ ሊያስከትል በሚችለው ቅጣት፣ ማክበር ሊያስገኝ በሚችለው ጥቅም፣ ከነውሮች ጋር በተያያዙ ልማዳዊ እምነቶችና ድርጊቶች ዙሪያ

| ተ.ቁ | የአባላት ስም ዝርዝር | የቡድኑ መለያ፣ ውይይት የተካሄደበት ቀንና ዓ.ም |
|---|---|---|
| 1 | አቶ ደስታው አባይነው | ቡድን - ሶስት (ሚያዚያ 30/2008 ዓ.ም) |
| 2 | ወ/ሮ አዲሴ ያለው | |
| 3 | ወ/ሮ ብርቱካን ሙላቱ | |
| 4 | አቶ ድንበሩ አባይነህ | |
| 5 | አባ ፍቅረማሪያም | |
| 6 | ቄስ አስማማው ዋሌ | |
| 7 | ወ/ሮ አያልነሽ ብርሃኑ | |

# ማረጋገጫ (Declaration)

"የነውር እሳቤ በሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ እምነት" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በፎክሎር ለዶክተሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሠራ፣ ለማንኛውም ተቋም ያልቀረበና የራሴ ወጥ ሥራ መሆኑን፣ የተጠቀምኩባቸው ዋቢ መረጃዎችም በትክልል በዋቢነት ያገለገሉ መሆናቸውንና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ ባለቤት መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም :- ሞላ ጀምበሬ አለምነህ

ፊርማ :- ....................

ቀን :- ......................